## መቅድም

ዜና ዘዳግም ሲል ነው፣ ይዞት እንደ መጣውስ ኦሪት ዘኑምስ ቢል በቀና ነበር ዘዳግም ያለበት ምሥጢሩ አል ታወቀም፤ አንድም ታውቋል፣ ለኦሪት ዘኍልቍ ዳግም ብሎታል፤ አንድም ሙሴ አራቱን ብሔረ ኦሪት ለአበው ጽፎ አምስተኛውን ለውሉድ የጻፈውን ዳግም ብሎታል፤ አንድም እንዳለ ይሆናል፣ በኦሪት ዘልደት በኦሪት ዘፀዓት፣ በኦሪት ዘሌዋውያን በኦሪት ዘኍልቍ ያለውን (የተናገረውን) መልሶ ያነባልና፣ (ይተረጕማልና) ስለዚህ ዘዳግም አለው፣ ይህንንም ሠለስቱ ምዕት ለመጻሕፍት ሁሉ አርእስት ሲሰጡ ሰጥተውታል፣ እርሱ ግን ነገሩን ዝንቱ ነገር ዘነገሮሙ ሙሴ ለኵሉ እስራኤል ብሎ ያመጣዋል።

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ዝንቱ ውእቱ ነገር ዘነገሮሙ ሙሴ ለኵሉ እስራኤል በማዕዶተ ዮርዳኖስ በመንገለ ዓረቢሃ በነበ ባሕረ ኤርትራ በማዕከለ ፋራን ወጦፌል ወሉባን ወአውሎን ወዘኬሪስያ ፣

በኬሪስያና በአውሎን በሉባንና በጦፌል በፋራን መካከል ባለች በኤርትራ ባሕር ዘንድ በሞዓብ በስተግራ በዮርዳኖስ ማዶ ዮርዳኖስን ሳይሻገሩ ለእስራኤል ሁሉ ሙሴ የነገራቸው ነገር ይህ ነው ፤

፪፤ በዓሡር መዋዕል እምኮሬብ በፍኖተ ደብረ ሴይር እስከ ቃዴስ በርኔ ፣

ዝንቱ ውእቱ ዘነገሮሙ ያለውን አመጣ፣ ወደ ሴይር ተራራ በሚወስደው ጎዳና አጠገብ ካለ ከኮሬብ ጀምሮ እስከ ቃዴስ በርኔ የሆነውን ነገር ዐሥር ቀን ጉባኤ አድርጎ ነገራቸው፤ አንድም ከኮሬብ ጀምሮ እስከ ቃዴስ በርኔ ድረስ ዓሥር ቀን ተጉዘው፤ አንድም ዓሥር ቀን የሆነውን ነገር ዓሥር ቀን ጉባዔ አድርጎ ነገራቸው፤

፫፤ ወኮነ አመ አርብዓ ዓም አመ ዓሡር ወአሚሩ ወርኀ አመ ሠርቀ ወርኀ ነገሮሙ ሙሴ ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል ኵሎ ዘአዘዞ እግዚ አብሔር ይንግሮሙ ፣



ሪታና ቤተሰቧ ቤተ መጻሕፍት

ከግብጽ በወጡ በአርባ ዘመን በዓሥራ አንደኛው ወር በየካቲት መባቻ ይነግራቸው ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ሙሴ ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው ፤

፬፤ እምድኅረ ቀተልዎ ለሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘይነብር ውስተ ሐሴቦን ወለዓግ ንጉሠ ባሳን ዘይነብር ውስተ አስጣሮት ወኤንድራይን በማዕዶተ ዮርዳኖስ ውስተ ምድረ ሞዓብ ፣

በሐሴቦን የሚኖር የአሞሬዎን ንጉሥ ሴዎንንና በአስጣሮትና በኤንድራይን የሚኖር የባሳን ንጉሥ ዓግን ከወጉ በኋላ በዮርዳኖስ ማዶ በሞዓብ አውራጃ ሳሉ ነገራቸው ፤

፭፤ ወአኀዘ ሙሴ ይንግር ዘንተ ሕገ ፣

ሙሴም ይህን ሕግ ይናገር ጀመር ፤

፮፤ ወይቤ እግዚአብሔር አምላክነ ነገረነ በኮሬብ ወይቤለነ አክለክሙ ኀዲሮቱ ውስተ ዝንቱ ደብር ፤

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በኮሬብ ሳለን በዚህ ተራራ መኖሩ ይበቃችኋል አለን ፤

፯፤ ተንሥኡ እንከ ወሑሩ ወባኡ ውስተ ደብረ አሞሬዎን ውስተ ኵሉ ማኅደረ ዓረባ ወውስተ ኵሉ ደብሩ ወውስተ ኵሉ ገዳሙ ፣

ተነሥታችሁ ሂዱችሁ ወደ አሞሬዎን ተራራ በምዕራቧ በኩል ወዳለው ተራራም ግቡ፤ አንድም ዓረባ ስመ ሀገር ነው፣ ዓረባ ወደሚባል ሀገር ወደ ተራራውና ወደ ምድረ በዳው ሁሉ ግቡ ፤

ወውስተ ሲባ ወውስተ ጰራልዩ ዘምድረ ከነዓን ወአንጢሊባኖስ እስከ ፈለግ ዐቢይ ፈለገ ኤፍራጥስ፣

በዓረባ ቀኝ ወዳለች መዓዝን፤ አንድም ሲባ ስመ ሀገር ነው፣ ሲባ ወደሚባል አገር በከነዓን አውራጃ ወዳለው ገጠር ጠጠር ግቡ፣ ጰራልያ ገጠር ጠጠር ማለት ነው፣ አንጢሊባኖስ ወደሚባለው አገር እስከ ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ ሂዱችሁ ግቡ አለ እግዚአብሔር ብሎ ይነግራቸው ጀመር፤ አንድም ምስለኔ ሁን፣ እንደኔ ነውና ሙሴ ተነሥታችሁ ሂዱችሁ ወደነዚህ አገሮች ግቡ አላቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፤ ናሁ ወሀብኩክሙ ይእተ ምድረ እንተ መሐልኩ ለአበዊክሙ፣ ቅድሜክሙ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ከመ አሀቦሙ ሎሙ ወለዘርኦሙ እም ድኅሬሆሙ ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ፤

ለአባቶቻችሁ ለአብርሃም ለይ ስሐቅ ለያዕቆብ ከነሱም በኋላ ለልጆቻቸው እሰጣቸው ዘንድ (አወርሳቸው ዘንድ) የማልሁ ላቸውን ተድላ ደስታ የሚገ ኝባትን በፊታችሁ የምታዩዋት ያችን አገር እነሆ ሰጠኋችሁ አለ እግዚአብሔር አላቸው፤

፱፤ ወእቤለክሙ በውእቱ መዋዕል እንዘ እብል ኢይክል ባሕቲትየ ክሂሎተክሙ ፤

ብቻዬን እናንተን መሥራት መቅጣት አይቻለኝም፤ አን ድም ከናንተ ጋር ብቻዬን መከራከር አይቻለኝም ብዬ ነገርኋችሁ፤

፲፤ እስመ አብዝኀነ እግዚአብሔር አምላክነ ወናሁ ብዙኃን አንትሙ ዮም ከመ ከዋክብተ ሰማይ፣

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በቸርነቱ አብዝቶናልና፣ እነሆ እናንተም ዛሬ እንደ ሰማይ ኮከብ እንደ ባሕር አሸዋ በዝታችኋልና ብቻዬን መሥ ራት መቅጣት አይቻለኝም ፤

፲፩፤ ወያብዝኀክሙ እግዚአብሔር አምላክሙ ለአበዊነ ምእልፊተ ወይባርክሙ በከመ ይቤለክሙ ፤

መሆኑንስ የአባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔርም አብዝኖ አበ ዝኀክሙ ወባርኮ እባርከክሙ እንዳለ የብዙ ብዙ አድርጎ ያብዛችሁ፣ ፈጽሞ ያክብራችሁ፤

፲፪፤ ወእፎ እክል ባሕቲትየ ፃማክሙ ወሥራሐክሙ ወተባህሎ ተክሙ ፤

ነገር ግን እኔ ብቻዬን ክር ክራችሁን ድካማችሁን መስ ማት እንደምን እችላለሁ?

፲፫፤ አምጽኡ ለክሙ ዕደወ ጠቢባነ ወለባውያነ ወማእምራነ እምነገድክሙ ወእሠይሞሙ ለክሙ መሳፍንተክሙ፣

ብልሆችንና አዋቂዎች ሰዎ ችን ከየነገዳችሁ መርጣችሁ አምጡና ሹማምንት አድርጌ እሾምላችኋለሁ፣ (ሐተታ) ጠቢ ባን የእጅ ጥበብ፣ ለባውያን የልብ ዕውቀት፣ ማእምራን የወል ነው፤

፲፬፤ ወአውሣእክሙኒ ወትቤሉኒ ሠናይ ዝንቱ ቃል ወትቤሉኒ ግበር ከማሁ ፤

እናንተም ይህ የተናገርኸው በጎ ነገር ነውና እንደ ተናገ ርኸው አድርግልን ብላችሁ መለሳችሁልኝ ፤

፲፭፤ ወነሣእኩ እምውስቴትክሙ ዕደወ ጠቢባነ ወማእምራነ ወለ ባውያነ ወሤምክዎሙ ላዕሌክሙ ይኩኑክሙ መላእክተ ፲፻ት ወመላእክተ ፻ት ወመላእክተ ፶ ወመላእክተ ዐሠርቱ ወጸሐፍቶሙ ለመኳንንቲክሙ ፤

ከናንተ ወገን ብልሆችን፣ አዋ ቂዎችን መርጬ የሺሕ አለቃ፣ የመቶ አለቃ፣ የአ ምሳ አለቃ፣ የዐሥር አለቃ ይሆኗችሁ ዘንድ ሾምሁላ ችሁ፣ ጸሐፍቱንም ለመኳን ንቶቻችሁ ሾምሁላቸው፤ (ሐተታ) እንዳለፈው (ኦሪት ዘፀዓት ምዕ. ፲፰ ቁ. ፳፭ ተመልከት ፤

፲፮፤ ወእቤሎሙ በውእቱ መዋዕል ስምዑ ማዕከለ አኀዊክሙ ወማዕ ከለ ግዩር ወማዕከለ ብእሲ ወእ ኁሁ ወአግብኡ ፍትሐ በጽድቅ ፤



ወንድም ከወንድሙ ጋር በተጣላ ጊዜ በወንድማችሁ በእስራኤልና በመጻተኛው መካከል ያለውን ነገር ሰምታ ችሁ በእውነት ፍረዱ፤

፲፯፤ ወኢትንሥኡ ገጸ በፍትሕ ኢለንዑስ ወኢለዓቢይ ወኩንኑ በጽ ድቅ ወኢትንሥኡ ገጸ ሰብእ እስመ ፍትሕ ዘእግዚአብሔር ውእቱ፣

በፍርድ ጊዜ ለትንሹም ለት ልቁም ፊት አይታችሁ አታ ድሉ፣ በእውነት ፍረዱ እንጂ፣ ፍርድ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነውና የሰው ፊት አይታችሁ አታድሉ ፤

ወለእመቦ ዘዓፀበክሙ ነገር ታዓ ርጉ ኀቤየ ወእሰምዖ ፤

የረቀቀባችሁ (የከበዳችሁ) ፍርድ ቢኖርም በይግባኝ ወደኔ አድር ሱትና እኔ እሰማዋለሁ ብዬ ነገርኋቸው ፤

፲፰፤ ወአዘዝኩክሙ በውእቱ መዋ ዕል ኵሎ ቃለ ዘትገብሩ ፤

የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ፣ የምትፈርዱትን ፍርድ ሁሉ በዚያ ወራት አዘዝኋችሁ ይላቸዋል፣ ለዳኞችም ለሕዝ ቡም ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፱፤ ወግዕዝነ እምኮሬብ ወሖርነ ኵሎ ገዳመ ገዳመ ዐቢየ ወግሩመ ዘርኢክሙ በፍኖተ ደብረ አሞሬዎን ዘከመ አዘዘነ እግዚአብሔር አምላክነ ወበጻሕነ እስከ ቃዴስ በርኔ ፤

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እንዳዘዘን ከኮሬብ ተጉዘን በአሞሬዎን ተራራ መንገድ ያያችሁትን ያን የሚያስፈራ ታላቅ ምድረ በዳ ሂደን እስከ ቃዴስ በርኔ ደረስን፤

፳፤ ወነገርኩክሙ በውእቱ መዋዕል ወእቤለክሙ ብጽሑ እስከ ደብረ አሞሬዎን ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ፤

በዚያ ወራት ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እስከሚያወርሳችሁ እስከ አሞሬዎን ተራራ ድረስ ሂዱ ብዬ ነገርኋችሁ፤

፳፩፤ ወናሁ ርእዩ ከመ ወሀበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ይእተ ምድረ ቅድመ ገጽክሙ ፤

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በፊታችሁ ያለችውን ያችን አገር እንደ ሰጣችሁ እንዳ ወረሳችሁ እነሆ ዕወቁ ፤

ዕርጉ እንከ ወተዋረስዋ በከመ ይቤሎሙ እግዚአብሔር አምላክሙ ለአበዊነ ኢትፍርሁ ወኢትደንግፁ ፤

የአባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ትወርሷታላችሁ እንዳ ላቸው ወጥታችሁ ውረሷት፤ አንወርስም በማለትም አት ፍሩ አትደንግጡ ፤

፳፪፤ ወእምዝ መጻእክሙ ኵልክሙ ኀቤየ ወትቤሉኒ ንፈኑ ዕደወ ቅድሜነ ይርአይዋ ለይእቲ ምድር ለነ ወይዜንዉነ ለይእቲ ፍኖት እንተ ሀለወነ ንዕርግ ውስቴታ ወለአህጉርኒ እለ ሀለወነ ንባእ ውስቴቶን ፤

ከዚህ ሁላችሁ ወደኔ መጥ ታችሁ አስቀድመን ጉበኞችን እንላክና ያችን አገር ይዩልን፤ አይተውም ወደሷ እንገባ ዘንድ ያለንን የዚያችን አገር ጎዳናና የምንወርሳቸውን አገ ሮች ወሬ ይንገሩን አላች ሁኝ፤

፳፫፤ ወአደመኒ ውእቱ ነገር ወነሣእኩ እምኔክሙ ፲ተ ወ፪ተ ዕደወ በበአሐዱ ብእሲ እምነገድ ፤

ይህም ነገራችሁ ደስ አሰኘ ቶኝ ከየነገዳችሁ አንዳንድ ሰው አወጣጥቼ ዐሥራ



ሁለት ሰው ወሰድሁ፤ (ተቀ በልሁ)፤ (ሐተታ) ከዚያ በኦ ሪት ዘኍልቍ ጌታ ሙሴን ፈኑ ዕደወ ሰብአ ዓይን አለው ይላል ፤ ከዚህ ሕዝቡ ንፈኑ ዕደወ ብለው ጠየቁት አለ፤ እንደምን ቢሉ፤ ነገር እንደ ኦሪት ዘኍልቍ ነው፤ ጌታ ፈኑ. ሰብአ ዓይን ብሎታል፤ ከዚህ ጌታ እንዳዘዘው አው ቀው እነሱም ንፈኑ ዕደወ ብለውታል፤ አንድም ጌታ ፈኑ ሰብአ ዓይን ቢለው ሂዶ ከየነገዳችሁ አንዳንድ ሰው አውጡ አላቸው፤ አወጣ ጥተው ይዘው ሂደው ንፈኑ ዕደወ ብለውታል ፤

፳፬፤ ወሖሩ ወዓርጉ ውስተ ደብር ወበጽሑ ውስተ ቈላተ ዓጽቅ ወርእይዋ ፤

ጉበኞችም ሂደው ወደ ተራራው ወጥተው የወይን ዘለላ ካለበት ቆላ ደርሰው ያችን አገር አዩዋት ፤

፳፭፤ ወነሥኡ ምስሌሆሙ እምፍሬሃ ለይእቲ ምድር ወአምጽኡ ኀቤነ ወንቤ ሠናይት ምድር ዘይሁበነ እግዚአብሔር አምላክነ ፤

ቆላተ ዓጽቅ ብሎ ነበርና ለመድረሳቸው ምልክት ሲሆ ናቸው ከስንዴው ዛላ፤ ከወ ይኑ ዘለላ ይዘውልን መጡ፤ እኛም ዐይተን ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የሚያወርሰን አገር ያማረች የተወደደች ናት አልን ፤

፳፮፤ ወአበይክሙ ዓሪገ ወክሕ ድክሙ ቃለ እግዚአብሔር አምላ ክክሙ ፤

ነገር ግን ወደሷ መውጣትን እንቢ አላችሁ፤ ትወርሷታላ ችሁ ያላችሁ የእግዚአብሔ ርን ቃል (ትእዛዝ) አንሰ ማም አላችሁ፤

፳፯፤ ወአንጐርጐርክሙ በውስተ ተዓይኒክሙ ወትቤሉ እስመ ይጸልአነ እግዚአብሔር አውፅአነ እምድረ ግብጽ ከመ ያግብአነ ውስተ እዴሆሙ ለአሞሬዎን ወከመ ይሥርወነ ፤

እግዚአብሔር ጠልቶናልና በአሞሬዎን እጅ ሊጥለንና ፈጽሞ ሊያጠፋን ከግብጽ ምድር አወጣን ብላችሁ በሰ ፈራችሁ ሁናችሁ አንጐራ ጐራችሁ ፤

አይቴ እንከ ነዓርግ ንሕነ ፤

እንግዲህ ወዴት እንወጣለን? ወዴትስ እንሄዳለን? አላችሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፰፤ ወባሕቱ አኃዊክሙ አክሐ ድዎ ስልብክሙ ወይቤሉክሙ ዐቢይ ሕዝብ ወብዙኃ ወይጸንዑ እምኔክሙ ፤

ነገር ግን በዚያ ያሉት ወገ ኖች ፈጽመው ብዙ ናቸው፣ ከእናንተም ይበረታሉ፤

ወአህጉሪሆሙኒ ዐበይት ወቦቱን ጥቅም ዘይበጽሕ እስከ ሰማይ ወር ኢነ በህየ ደቂቆሙ ለእለ ያርብህ ፤

አምባዎቻቸውም የጸኑ ናቸው፣ እስከ ሰማይ የሚደርስ ቅጽ ርም አላቸው፣ በዚያም ያርበ ኞችን ልጆች አየን ብለው ተናግረው ወንድሞቻችሁ ልቡ ናችሁን አስካዱት ፤

፳፱፤ ወእቤለክሙ ኢትፍርሁ ወኢ ትደንግፁ እምኔሆሙ ፤

ያጠፉናል ብላችሁ ከነሱ የተ ነሣ አትፍሩ፣ አትደንግጡ አልኋችሁ ፤

፴፤ እግዚአብሔር አምላክክሙ ውእቱ ይፀብዕ ለክሙ ምስሌክሙ ወውእቱ የሐውር ቅድመ ገጽክሙ በከመ ኵሉ ዘገብረ ለክሙ በምድረ ግብጽ፣

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በግብጽ አገር እንዳደረገላችሁ ሁሉ በረድኤት ከናንት ጋር ሁኖ ጠላቶቻችሁን ይወጋ ላችኋል (ያጣፋላችኋል)፣ ፊታ ውራሪም ሆኖ በፊታችሁ ይሄዳል፤

፴፩፤ ወበውስተ ገዳም ዘርኢክሙ በከመ ሴሰየክሙ እግዚ አብሔር አምላክክሙ በከመ ይሴሲ ብእሲ ውሉዶ በኵሉ ፍኖት እንተ ሖርክሙ እስከ በጻሕክሙ ውስተ ዝንቱ መካን ፤

በዚህ በአያችሁት ምድረ በዳም ወደዚህ ቦታ እስካ ደረሳችሁ ድረስ በሔዳችሁበት ጎዳና ሁሉ አባት ልጁን እን ዲመግብ ፈጣሪያችሁ እግዚ አብሔር መና ከደመና አው ርዶ፣ ውሀ ከደነጊያ አፍልቆ እንደመገባችሁ ነገርኋችሁ ፤

፴፪፤ ወኢአመንክምዎ በዝንቱ ቃል ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ዘየሐውር ቅድሜክሙ ውስተ ፍኖት ከመ ይኅሪይ ለክሙ መካነ ፤

እናንት ግን የምትኖሩባት አገር ከነዓንን ሊመርጥላችሁ በምትሄዱበት ጎዳና ሁሉ በፊታችሁ የሚሄድ ፈጣሪያ ችሁ እግዚአሔርን አላመና ችሁበትም ፤



፴፫፤ ዐይምራሕክሙ ሌሊተ በእሳት ከመ ያርኢክሙ ፍኖተ ዘተሐውሩ ባቲ መዓልተ በደመና ፤

ይምራሕክሙ ሌሊተ በእሳት ወመዓልተ በደመና ከመ ያርኢክሙ ፍኖተ ዘተሐውሩ ሲል ነው፣ የምትሄዱባትን ጎዳና ያሳያችሁ ዘንድ ቀን በዓምደ ደመና፣ ሌሊት በዓምደ እሳት ይመራችሁ ዘንድ በፊ ታችሁ የሚሄድ እሱን አላ መናችሁትም ፤

፴፬፤ ወሰምዐ እግዚአብሔር ቃለ ነገርክሙ ወተምዓ ወመሐለ ወይቤ ከመ ኢይሬእይዋ እሉ ዕደው ለይእቲ ምድር ቡርክት ዘመሐልኩ ለአበዊሆሙ ዘእንበለ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ፤

እግዚአብሔርም የተናገራች ሁትን ነገር ሰምቶ ቃለ ነጐርጓርክሙ ይላል፣ ያንጐራ ጐራችሁትን ማንጐራጐር ሰምቶ ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብ በቀር እሊህ ሰዎች ለአባቶቻ ችሁ የማልሁላቸው ያችን የከበረች አገር አይወርሷትም ብሎ ማለ፤

፴፭፤ ወውእቱ ዘይሬእያ ወሎቱ እሁባ ለይእቲ ምድር እንተ ውስቴታ ዓርገ ወለደቂቁ እስመ ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ልቡ ፤

ልቡናው በአምልኮት ከእግዚ አብሔር ጋር ነውና ያችን የሰለላትን አገር ለሱም ለልጆ ቹም እሰጣታለሁ፣ ገብቶ የሚያያትም እርሱ ነው ፤

፴፮፤ ወኪያየኒ ተምዓኒ እግዚአ ብሔር በእንቲአክሙ ወይቤለኒ አንተኒ ኢትበውእ ህየ ፤

እኔንም በናንተ ምክንያት ተቆጥቶ አንተም ወደዚያ አገር አትገባም አለኝ፤

፴፯፤ እስመ ኢያሱ ወልደ ነዌ ዘይቀውም ቅድሜከ ውእቱ ዘይበውእ ህየ ኪያሁ አጽንዖ ወውእቱ ያወርሶሙ ይእተ ምድረ ለእስራኤል ፤

በፊትህ የሚቆም ማለት በአ ንተ የሚተካ የነዌ ልጅ ኢያሱ ወደዚያ የሚገባ እሱ ነውና እሱን አጽናው፣ እሱም ያችን አገር ለእስራኤል ያወር ሳቸዋል፤

፴፰፤ ወደቂቅክሙ እለ ትቤሉ ይዔወዉ ወኵሉ ሕፃን ንዑስ ዘኢየአምር ዮም ሠናይተ ወእኪተ እሙንቱ ይበውኡ ህየ ወሎሙ እሁባ ወእሙንቱ ይወርስዋ፣

www.ethiopianorthodox.org

ይማረካሉ የምትሏቸው ልጆቻችሁ ዛሬ ክፉና በጎ ለይተው የማያውቁ ታናናሾቹ ልጆች ሁሉ እነሱ ወደዚያች አገር ይገባሉ፣ እኔም ለነሱ እሰጣታለሁ፣ እነሱም ይወርሷታል ፡፡

፴፱፡ ወአንትሙሰ ተመየጡ ወገዓዙ ውስተ ገዳም ፍኖተ ባሕረ ኤርትራ፣

እናንተ ግን ተመልሳችሁ በኤርትራ ባሕር ጎዳና ወደ ምድረ በዳው ተጓዙ አልኋችሁ ፡፡

፵፡ ወአውሣእክሙኒ ወትቤሉኒ አበስነ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ ነዓርግ ንሕነ ወንትቃተል ወንገብር ኵሎ በከመ አዘዘነ እግዚአብሔር አምላክነ ፣

በፊጣሪያችን በእግዚአብሔር ፊት በድለናልና ወጥተን እንዋጋለን ፣ እርሱ እንዳዘዘን ሁሉን እናደርጋለን ብላችሁ መለሳችሁልኝ ፡፡

፵፩፡ ወነሣእክሙ ብእሲ ብእሲ ንዋየ ሐቅልክሙ ወዓረግሙ ውስተ ደብር፣

ይህንንም ብላችሁ አልቀራችሁም ፣ አንዱም አንዱም ሰው ጋሻ ጦራችሁን ይዛችሁ ወደተራራው ወጣችሁ ፡፡

፵፪፡ ወይቤለኒ እግዚአብሔር በሎሙ ኢትዕርጉ ወኢትትቃተሉ እስመ ኢሀለውኩ ምስሌክሙ ከመ ኢትትቀጥቀጡ ቅድመ ፀርክሙ፣

እግዚአብሔርም ከናንተ ጋር በረድኤት የለሁምና በጠላቶቻችሁ ፊት እንዳትወድቁ ወጥታችሁ አትዋጉ በላቸው አለኝ፡፡

፵፫፡ ወነገርኩክሙ ወኢሰማዕክሙኒ ወተዓወርክሙ ቃለ እግዚአብሔር ወተኀየልክሙ ወዓረግሙ ውስተ ደብር፣

እኔም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ነገርኋችሁ፣ እናንተ ግን አንሰማም ብላችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ቸል ብላችሁ ተጋፍታችሁ ወደ አሞሬዎን ተራራ ወጣችሁ፡፡

፵፬፡ ወወፅአ አሞሬዎን እለ ይነብሩ ውስተ ውእቱ ደብር ወተቀበሉክሙ፣

ያን ጊዜ በዚያ ተራራ የሚኖሩ የአሞሬዎን ሰዎች ወጥተው በጦርነት ተቀበሏችሁ፡፡

ወአንትዑክሙ ወሰደዱክሙ ወነደፉክሙ ከመ ንህብ ወወግዑክሙ እምሴይር እስከ ሔርማ፣



ድል ነሥተው አባረሯችሁ፣ እንደ ቀትር ንብ ሁነው ተዋግተው ከሴይር እስከ ሔርማ ፈጅመው ወጓችሁ፡፡

፵፭፡ ወነበርክሙ ወበከይክሙ ቅድመ እግዚአብሔር ወኢሰምዓክሙ ቃለክሙ ወኢነጸረክሙ፣

ድል ከተነሣችሁ በኋላ ተቀምጣችሁ በእግዚአብሔር ፊት አለቀሳችሁ፣ ነገር ግን ከፊቃድ ወጥታችሁ አሳዝናችሁታልና ልቅሷችሁን አልሰማችሁም፣ በዓይነ ምሕረትም አልተመለከታችሁም ፡፡

፵፮፡ ወነበርክሙ ውስተ ቃዴስ ብዙኃ መዋዕለ አምጣነ ነበርክሙ ቀዲሙ፣

ቀድሞ የኖራችሁትን ያህል በቃዴስ በርኄ ብዙ ዘመን ተቀመጣችሁ ፡፡

## ምዕራፍ ፪

፩፡ ወተመየጥነ ወሖርነ ውስተ ገዳም ፍኖተ ባሕረ ኤርትራ በከመ ይቤለነ እግዚአብሔር ወዖድናሁ ለደብረ ሴይር ብዙኃ መዋዕለ፣

እግዚአብሔር እንደነገረን ከዚያ ተመልሰን ወደ ኤርትራ ባሕር በሚወስደው ወደ ምድረ በዳው ሄድን፣ የሴይርን ተራራም ብዙ ዘመን ዞርነው፡፡

፪፡ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ኮንክሙ ዓዊዶቱ ለዝንቱ ደብር ግብኡ እንከሰ ለመንገለ መስዕ፣

ከዚያ በኋላ ግን እግዚአብሔር ይህን ተራራ መዞር በቃችሁ እንግዲህ ወደ ምሥራቅ ሀገር ተመለሱ አለኝ፡፡

፫፡ ወአዝዞሙ ለሕዝብ ወበሎሙ ናሁ ተሐውሩ አንትሙ እንተ አድዋሊሆሙ ለአኃዊክሙ ደቂቀ ኤሳው እለ ይነብሩ ውስተ ምድረ ሴይር ወይፈርሁክሙ ጥቀ፣

በሴይር አገር ወደሚኖሩ ወደ ወንድሞቻችሁ ወደ ኤሳው ልጆች አውራጃዎች ሂዱ፣ እነርሱም እጅግ ይፈሯችኋል ብለህ ሕዝቡን እዘዛቸው አለኝ፡፡

፬፡ ዑቁ ኢትትቃተሉ ምስሌሆሙ እስመ ኢይሁበክሙ እምድሮሙ ርስተ ወኢምሥጋረ እግር እስመ መክፈልቶ ወሀብክዎ ለኤሳው ደብረ ሴይር፣

የሴይርን ተራራ ለኤሳው ዕፃ አድርጌ ስለሰጠሁት ከሀገ

www.ethiopianorthodox.org

ራቸው አንድ የእግር እርምጃ ስንኳ ርስት አድርጌ አልሰጣችሁምና ከነርሱ ጋር እንዳትዋጉ እወቁ፤

፮፤ ወተሣየጡ እክለ እምኀቤሆሙ በወርቅክሙ ወተሴሰዩ ወማየኒ በመስፈርት ንሥኡ እምኀቤሆሙ በወርቅክሙ ወስትዩ፣

እህሉን ከነርሱ በገንዘባችሁ ሸምታችሁ ተመገቡ፤ ውሀውንም በገንዘባችሁ ገዝታችሁ መጥናችሁ ጠጡ፤

፯፤ እስመ ባረከከሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ በኵሉ ግብረ እደዊክሙ፣

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በእጃችሁ በቃላችሁ ሥራ ሁሉ አክብሯችኋልና ተሣየጡ ላሰው፣ አእምር ማኅሻ፤ እንድም እግዚአብሔር አክብሯችኋልና፤

፯፤ እእምር እፎ የድኀሁ ለዝንቱ ገዳም ዐቢይ ዘግሩም ውእቱ ናሁ ፵ ዓመ ሀለወ ምስሌካ እግዚአብሔር አምላክከ እንዘ አልቦ ዘየኀጥአከ እምኵሉ ዘነበብከ፣

ጽኑ የሆነ ይህን ምድረ በዳ እንደምን ዞርከው የሚል ቢኖር ይህን አድርግልኝ ብለህ ከለመንከው ሁሉ ያሳጣህ ሳይኖር ፈጣሪህ እግዚአብሔር አርባ ዘመን ከአንተ ጋር በረድኤት እንደኖረ እወቅ ፤

፰፤ ወተኀደውናሆሙ ለአኀዊነ ደቂቀ ኤሳው እለ ይነብሩ ውስተ ሴይር ኀበ ፍኖተ ዐረባ እም ኤሎም ወእምጋሴዮንጋቤር ፤

ከጋሴዮንጋቤርና ከኤሎም ተነሥተን በሴይር አገር የሚኖሩ የኤሳውን ልጆች ወንድሞቻችንን አልፈናቸው ወደ ዐረባ ጐዳና ሄድን፤ አንድም በሴይር አገር የሚኖሩ የኤሳውን ልጆች ወንድሞቻችንን አልፈናቸው ከጋሴዮንጋቤርና በኤሎም አጠገብ ወዳለች ወደ ዐረባ ጎዳና ሄድን ፤

ወእምዝ ተመየጥነ ወተኀደውነ ፍኖተ ገዳም ዘሞዓብ ፤

ከዚያም በኋላ ተመልሰን በሞዓብ ምድረ በዳ ያለውን ጎዳና አልፈን ሄድን፤ አንድም በሞዓብ ምድረ በዳ ያለውን ጎዳና አልፈን ወደ ሞዓብ ከተማ ተመለስን ፤

፱፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ኢትፃረርዎሙ ለሞዓባውያን ወኢ



ትትቃተሉ ምስሌሆሙ እስመ ኢይሁበክሙ ርስተ እምድሮሙ እስመ ለደቂቀ ሎጥ ወሀብክዎሙ ርስቶሙ ፤

ፈጣሪያችን እግዚአብሔርም ሞዓብን ለሎጥ ልጆች ርስት አድርጌ ስለሰጠኋቸው ከሀገራቸው አይሰጣችሁምና የሞዓብን ሰዎች አትጣሏቸው፡ ከነርሱም ጋር አትዋጉ አለኝ፤

፲፤ ወዘሚን ቀዲሙ ነበሩ ውስቴታ ሕዝብ ዐበይት ጥቀ ወጽኑዓን ከመ እለ ውስተ አቂም ወራፋይን ፤

በአቂምና በራፋይን እንደሚኖሩ የጸኑ የታላላቅ ወገኖች የሚሆኑ አርበኞች በሞዓብ ይኖሩ ነበር ፤

፲፩፤ ካዕበ የኀድሩ እሙንቱኒ ከመ እለ ውስተ አቂም ወሞዓባውያን ዞሚን ይብልዎሙ ፤

በአቂም አርበኞች እንዲኖሩ ከኛ አስቀድመው አርበኞች ይኖሩባታል፣ የሞዓብም ሰዎች አርበኞች ሲሉ ዞሚን ይሏቸው ነበር ፤

፲፪፤ ወኮሬዎስ ውስተ ሴይር ይነብሩ ቀዲሙ ወደቂቀ ኤሳው አጥፍዕዎሙ ወተቀቀጥዎሙ እምቅድመ ገጾሙ ወነበሩ በመከኖሙ፡

ኮሬዎስ የሀገር ስም፤ አንድም አርበኞች ማለት ነው፣ እነርሱ ቀድሞ ሴይርን ወርሰዋት ይኖሩ ነበር፣ እነርሱንም የኤሳው ልጆች ከፊታቸው ፈጽመው አጥፍተዋቸው በቦታቸው ኖሩ ፤

ከማሁ ይገብርዋ እስራኤል ለምድረ ርስቶሙ ዘወሀቦሙ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር ርስት አድርጎ የሰጣቸው ከነዓንን የእስራኤል ልጆች እንደዚሁ ያደርጓት ማለት ይወርሷት፤ አንድም የኤሳው ልጆች በሴይር አስቀድመው የነበሩ የኮሬዎስን ሰዎች እልምድርግም አድርገው አጥፍተው በቦታቸው እንደኖሩ እስራኤልም ሰብአ ከነዓንን አጥፍተው እግዚአብሔር የሰጣቸው ከነዓንን ይወርሷታል፤

፲፫፤ ወይእዜኒ ተንሥኡ ወግዕዙ አንትሙ ወሑሩ ውስተ ቈላተ ዛሬድ ወተዓደውናሁ ለቈላተ ዛሬድ ፤

www.ethiopianorthodox.org

አሁንም እናንተ ተነሥታችሁ ተጕዛችሁ ወደዛሬድ ቆላ (በረሀ) ሂዱ አለኝ፣ እኛም ይህን ሰምተን የዛሬድን በረሀ አልፈነው ሄድን፤

፲፬፤ ወመዋዕሊሁ በዘቦእ ግዕዝነ እምቃዴስ በርኔ እስከ ተዓደውናሁ ለቈላተ ዛሬድ ሠላሳ ወሰመንቱ ዓመት እስከ ሞቱ ኵሎሙ ዕደው ዘይእቲ ትውልድ እለ መስተቃትላን እሙንቱ ወጠፍዑ እማዕከለ ትዕይንት በከመ መሐለ ላዕሌሆሙ እግዚአብሔር እግዚእ ፡

ፈጣሪ እግዚአብሔር አጠፋቸዋለሁ ብሎ እንደማለባቸው መጠን ከእስራኤል የተወለዱ አርበኞች ሁሉ ከወገኖቻቸው መካከል ተለይተው እስኪጠፉ ድረስ ከቃዴስ በርኔ ተነሥተን የዛሬድን በረሀ አልፈነው እስክን ሄድ ድረስ የተጓዝንበት ዘመኑ ሠላሳ ስምንት ዘመን ነው፤

፲፭፤ እስመ እደ እግዚአብሔር ሀለወት ላዕሌሆሙ ከመ ታጥፍኦሙ እማዕከለ ትዕይንት እስከ ወድቁ ፡

ፈጽመው እስኪጠፉ ድረስ ከወገኖቻቸው መካከል ለይታ ሊታጠፋቸው የእግዚአብሔር ሥልጣን በነሱ ላይ ታዛባቸዋለችና ስሳው እልፍ አጋር በምድረ በዳ እንደሻሽ ተነጥፈው እንደ ቅጠል ረግፈው ቀሩ ፤

፲፮፤ ወኮነ እምዘወድቁ ኵሎሙ ውእቶሙ ዕደው መስተቃትላን ወሞቱ እማዕከለ ሕዝብ ፡፡

እነዚያ አርበኞች ሁሉ ከወገኖቻቸው ተለይተው ከጠፉ በኋላ እንዲህ ሆነ ፤

፲፯፤ ወነበበኒ እግዚአብሔር ወይቤለኒ ናሁ ተሐውሩ ወተዓድዉ ውስተ አድዋሊሆሙ ለሞዓብ ወትበጽሑ ቅሩቦሙ ለደቂቀ አሞን ፡

የሞዓብን አውራጃ ተሻግራችሁ ትሄዳላችሁ፣ ወደ አሞንም ልጆች አቅራቢያ ትደርሳላችሁ ብሎ እግዚአብሔር ነገረኝ ፤

፲፰፤ ኢትፃረርዎሙ ወኢትትገዓዙ ቀትለ ምስሌሆሙ እስመ ኢይሁበክሙ ርስተ እምድሮሙ ለደቂቀ አሞን እስመ ለደቂቀ ሎጥ ወሀብክዎሙ መክፈልቶሙ፤

ለሎጥ ልጆች ዕፃ አድርጌ ስለሰጠኋቸው ከአሞን ልጆች



ምድረ ርስትን አልሰጣችሁምና ከነሱ ጋራ ሰልፍ አትጀምሩ አትጣሏቸውም፤ እንድም ለሎጥ ልጆች ዕፃ አድርጌ ሰጥቻቸዋለሁና ከሞአብ አገር ለናንተ ርስት አድርጌ ስለማልሰጣችሁ ሄዳችሁ አትዋጓቸው፣ ከነሱ ጋራም ሰልፍ አትጀምሩ ብሎ እግዚአብሔር ነገረኝ፤

፲፱፤ ወይእቲ ምድረ ራፋይን ትሰመይ እስመ ራፋይን ይነብሩ ውስቴታ ቀዲሙ ወአሞናውያንኒ ዘሚን ይብልዎሙ ፡

ቀድሞ አርበኞች ይኖሩባት ነበርና፣ ያችም አገር የአርበኞች አገር ትባላለች፣ የአሞንን ሰዎችም አርበኞች ይሏቸው ነበር ፤

፳፤ ሕዝብ ዐበይት ወብዙኃን ወጽኑዓን ወኃያላን ከመ እለ አቂም ዘአጥፍኦሙ እግዚአብሔር እምቅድመ ገጾሙ ወወረስዎሙ ወነበሩ ህየንቴሆሙ ፡

እግዚአብሔር ከፊታቸው እንደ አጠፋቸው ኃይለኞች ታላላቅ የበዙ የጸኑ አርበኞች ወገኖች ናቸው፣ የሎጥ ልጆችም ወርሰዋቸው በነሱ ፈንታ ኖሩ ፤

፳፩፤ ከመ ገብሩ ደቂቀ ኤሳው እለ ይነብሩ ውስተ ሴይር በከመ አሥዓሮሙ እግዚአብሔር እምቅድመ ገጾሙ ለኮራውያን ወወረስዎሙ ወነበሩ ህየንቴሆሙ እስከ ዛቲ ዕለት ፡

እግዚአብሔር ኃይለኞችን ከፊታቸው አጥፍቶላቸው በሴይር የሚኖሩ የኤሳው ልጆች እንዳደረጉ ወርሰዋቸው ስለነሱ ፈንታ እስከዚች ቀን ድረስ እንደኖሩ የሎጥም ልጆች ወርሰዋቸው ኖሩ ፤

፳፪፤ ወለሔዋውያንኒ እለ ይነብሩ ውስተ አሴሮት እስከ ጋዜስ ወቀጰዶቅያ አጥፍዕዎሙ ወነበሩ ህየንቴሆሙ ፡

እስከ ቀጰዶቅያና እስከ ጋዜስ ድረስ በአሴሮት የሚኖሩ ኃይለኞችንም አጥፍተው ስለርሳቸው ፈንታ ኖሩ፤

፳፫፤ ወይእዜኒ ተንሥኡ ወገዓዙ አንትሙ ወዕድውዎ ለቈላተ አርኖን ፡

አሁንም ተነሥታችሁ ተጕዛችሁ የአርኖንን ቈላ (ሸለቆ) ተሻግራችሁ (አልፋችሁ) ሂዱ፤

www.ethiopianorthodox.org

ናሁ አግባእክዎ ውስተ እዴከ ለሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን አሞርያዊ ወለምድሩ ወምልካ ወተዋረሳ ወአንዝዞሙ ወተቃተሎሙ ፡

**የአሞሬዎን ሰው የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎንንም በእጅህ ጭብጥ በእግርህ እርግጥ አድርጌ ሰጠሁህ፤ አገሩንም ልትገዛት ልትወርሳት ሰጠሁህ፤ ሊወጉህም ቢመጡ ተሰልፈህ ተዋጋቸው ፤**

፳፭፤ ወበዛቲ ዕለት አቀድም አምጽእ ላዕለ ኵሉ አሕዛብ እለ ሀለዉ መትሕተ ሰማይ ከመ ይፍርሁከ ወይርዓዱ እምኔከ ወይደንግፁ እምከመ ሰምዑ ስመከ ወትእኅዞሙ ፍርሃት እምቅድመ ገጽከ ፡

**ስምህን የሰሙ እንደ ሆነ ከአንተ የተነሣ ፊርተው ደንግጠው ይንቀጠቀጡ ዘንድ ከሰማይ በታች ባሉ በአሕዛብ ሁሉ በዚች ቀን አስቀድሜ ፍርሃትን አመጣለሁ፤ በፊትህም ፍርሃት ትይዛቸዋለች፤**

፳፮፤ ወፈነውኩ ተናብልተ እምነ ገዳም ዘቄድሞት ኀበ ሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን በቃለ ሰላም ፡

**ከቄድሞት ምድረ በዳ ሁነህ ወደ ሐሴቦን ንጉሥ ወደ ሴዎን በፍቅር ቃል መልእክተኞችን ላክህ ፤**

፳፯፤ እንዘ ትብል እኅልፍ እንተ ምድርከ ወፍኖተ አሐውር ወኢይትገኃሥ ኢ ለየማን ወኢ ለፀጋም፡

**ወደ ቀኝም ወደ ግራም ሁኖ ከመንገድ አልወጣም፤ ጥርጊያውን ጎዳና ሳልለቅ በሀገርህ ልለፍ ብለህ መልእክተኞችን ላክህ፤**

፳፰፤ እክለኒ በወርቅየ ትሁበኒ ወእሴሰይ ወማየኒ በወርቅየ ትሁበኒ ወእሰቲ ወዳዕሙ እኅልፍ በእግርየ ፡

**ለእግሬ መንገድ ሰጥተኸኝ አልፌ ልሂድ እንጂ እህሉን በገንዘቤ ሸምቼ እመገባለሁ፤ ውሀውንም በገንዘቤ ገዝቼ እጠጣለሁ ፤**

፳፱፤ በከመ ገብሩ ሊተ ደቂቀ ኤሳው እለ ይነብሩ ውስተ ሴይር ወሞአባውያንኒ እለ ይነብሩ ውስተ አሮኤር እስከ አዓድዎ ለዮርዳኖስ ውስተ ምድር እንተ ወሀበኒ እግዚአብሔር አምላክነ ፡

**ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የሰጠኝን ምድረ ርስት ለመውረስ ዮርዳኖስን እስከሻገር ድረስ በአሮኤር የሚ**



**ኖሩ የሞዓብ ሰዎችና በሴይር የሚኖሩ የኤሳው ልጆች እንዳደረጉልኝ መንገድ ሰጥተኸኝ አልፌ ልሂድ ብለህ በፍቅር ቃል ላክህ ፤**

፴፤ ወአበየ ሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን አኅልፎተነ እንተ ኀቤሁ እስመ አጽንዓ እግዚአብሔር አምላክነ መንፈሶ ወአእከየ ልቦ ከመ ይግባእ ውስተ እዴነ በይእቲ ዕለት ፡

**በዚያች ቀን በእጃችን ይወድቅ ዘንድ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ልቡናውን አጽንቶታልና በሱ አገር አልፈን እንሂድ ዘንድ የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎን መንገድ አልሰጥም ብሎ እንቢ አለ፤**

፴፩፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ናሁ አኀዝኩ አግብኦ ውስተ እዴከ በቅድመ ገጽከ ለሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን አሞርያዊ ወምድሮኒ ወአኀዝ ወተዋረስ ምድሮ ርስተ ፡

**እግዚአብሐርም የአሞሬዎን ሰው የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎንንና ሀገሩን በእጅህ ልሰጥህ ጀመርኩ፤ አንተም አገሩን ርስት አድርገህ ወርሰህ ኑር አለኝ፤**

፴፪፤ ወወፅአ ሴዎን ወተቀበለነ ውእቱ ወኵሉ ሕዝቡ ከመ ይትቃተለነ በኢያሳ ፡

**ሴዎንም ከሠራዊቱ ጋር ወጥቶ በኢያሳ ሊዋጋን በጦርነት ተቀበለን ፤**

፴፫፤ ወአግብኦ እግዚአብሔር አምላክነ ውስተ እዴነ ወቀተልናሁ ሎቱ ወለኵሉ ደቂቁ ወለኵሉ ሕዝቡ ፡

**ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በተራዳኢነቱ ጠላታችን ሴዎንን በእጃችን ጣለልን፤ እሱን ገደልነው፤ ልጆቹንም ወገኖቹንም ሁሉ ወጋናቸው፤**

፴፬፤ ወነሣእነ ኵሎ አህጉሪሁ በውእቱ መዋዕል ወአጥፋዕናሆን ለኵሎን አህጉሪሁ ወአንስቲያሆሙኒ ወደቂቆሙኒ ፡

**በዚያ ወራት አገሩን ሁሉ ወርሰን እጅ አደረግነው፤ ከዚያም በኋላ ሊጠፉ የሚገባቸውን አገሮች ሁሉ እየመረመርን አጠፋናቸው፤ ሚስቶቻቸውንም ልጆቻቸውንም ሁሉ አጠፋናቸው፤**

፴፭፤ ወአልቦ ዘአትረፍነ ነፋዒተ እምኔሆሙ ዘእንበለ እንስሳሆሙ ዘማሕረክነ ለነ ወበርበርነ አህጉሪሆሙ ፡

**ለኛ ይጠቅሙናል ብለን ከዘረፍናቸው ከከብቶቻቸው**

www.ethiopianorthodox.org

በቀር ከነሱ ሸሽቶ የሚያመልጥ አላስቀረንም አገራቸውንም ዘረፍነው ፤

፴፮፤ ወነሣእነ ምድሮሙ እምአሮኤር እንተ ማዕዶተ ፈለገ አርኖን ወለአህጉርኒ እለ ሀለዋ ውስተ ቆላት እስከ ደብረ ገለዓድ፣

ከአርኖን ወንዝ ማዶ ካለ ከአሮኤር ጀምሮ በቆላ ያሉ አገሮቻቸውንም እስከ ገለዓድ ተራራ ድረስ እጅ አደረግን ፤

፴፯፤ ወአልቦ ሀገር እንተ አምሠጠተነ እስመ ኵሎ አህጉረ አግብአ እግዚአብሔር አምላክነ ውስተ እዴነ ዘእንበለ ውስተ ምድረ ደቂቀ አሞን ዘኢበጻሕነ ፡

ካልደረስንበት ከአሞን ልጆች አገር በቀር ያመለጠን አገር የለም፣ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር አገሩን ሁሉ በእጃችን ጥሎልናልና፣ (ሐተታ) ዘኢበጻሕነ አለ፣ ርኅቀተ ፍና ርኅቀተ ሀገር ነው፤ አንድም ጌታ አትውጓት ብሎ አዟቸው ነው ፤

፴፰፤ ወኵሎ ዘውስተ ፈለገ ያቦቅ አህጉረኒ ዘውስተ ቴርኒ በከመ አዘዘነ እግዚአብሔር አምላክነ ፡

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እንዳዘዘን ቴርኒ በሚባል አገርና በያቦቅ ወንዝ ውስጥ ያለውን አገር ሁሉ እጅ አደረግን ፡፡

## ምዕራፍ ፫

፩፤ ወተመየጥነ ወዓረግነ ውስተ ፍኖተ ባሳን ወወፅአ ዓግ ንጉሠ ባሳን ወተቀበለነ ውእቱ ወኵሉ ሕዝቡ ውስተ ኤንድራይን ከመ ይትቃተለነ ፡

ከዚያ ተመልሰን ወደ ባሳን ጎዳና ወጣን፣ የባሳን ንጉሥ አግም ሊወጋን ወጥቶ ከሕዝቡ ጋር በኤንድራይን በጦርነት ተቀበለን፤

፪፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ኢትፍርሆ እስመ ውስተ እዴከ አገብእ ወለኵሉ ሕዝቡ ወለኵሉ ምድሩ ፡

እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፣ የባሳን ንጉሥ አግን ወገኖቹንም ሁሉ አገሩንም ሁሉ በእጅህ እጥልልሃለሁና አትፍራው አለኝ ፤

ወትገብሮ በከመ ገበርካሁ ለሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘይነብር ውስተ ሐሴቦን ፡



በሐሴቦን የሚኖር የአሞሬዎን ንጉሥ ሴዎንን እንዳደረግኸው አግንም እንደሱ ታደርገዋለህ ማለት ሴዎንን አጥፍተህ አገሩን እንደወረስህ አግንም አጥፍተህ አገሩን ትወርሳለህ ሲለው ነው፣

፫፤ ወአግብአ እግዚአብሔር አምላክነ ውስተ እዴነ ለአግ ንጉሠ ባሳን ወለኵሉ ሕዝቡ ወቀተልናሁ እስከ ኢያትረፍነ ዘርአ እምኔሁ ፡

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የባሳን ንጉሥ አግን ከሠራዊቱ ጋር በእጃችን ጣለው፣ ከሱ ወገን የሰው ዘር ሳናስቀር አጠፋነው ፤

፬፤ ወአስተጋባእነ ኵሎ አህጉሪሁ በውእቱ መዋዕል ወአልቦ ሀገር ዘኢነሣእነ እምኔሆሙ ፡

በዚያ ወራት አገሩን ሁሉ እጅ አደረግን፣ ከአገሮቹም ያልወረስነው የለም ፤

ስድሳ አህጉረ ወኵሎ ዘአድያማ ለአርጎብ ዘመንግሥቱ ለአግ በባሳን ፡

ስሳውን አገሮች በበሳን ያለ የአግ ግዛት የምትሆን የአርጎብን አውራጃ ሁሉ እጅ አደረግን፤ አንድም ከነ ዚህ ሁሉ አገሮች ያልወረስነው አገር የለም፤ (ትች) እነዚህም የወረስናቸው ስድሳ አገሮች ናቸው ፤

፭፤ ወኵሎን አህጉር እለ ቦን ጥቅም ወነዋኃት አረፋቲሆን እለ ቦን መዓፁት ወመናሥግት ዘእንበለ አህጉረ ፌርዜዎን እለ ብዙኃት እማንቱ ጥቀ ፡

እጅግ ብዙ የሆኑ የፌርዜዎን አገሮች ሳይቀሩ አጥር ቅጥር ያላቸው ቅጥሮቻቸውም ረጃጅሞች የሆኑ መዝጊያ ቍልፍ ያላቸው አገሮችን ሁሉ እጅ አደረግን፤ አንድም የወረስናቸው አገሮች ሁሉ አጥር ቅጥር ያላቸው ናቸው ፤

፮፤ ወሠረውናሆሙ በከመ ገበርነ በሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን ወአጥፋዕነ ኵሎ አህጉረ ኅቡረ አንስቲያሆሙ ወደቂቆሙኒ እስከ ኢያትረፍነ ነፋሢተ ፡

የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎንን እንዳጠፋነው አጠፋናቸው፣ ሸሽቶ የሚያመልጥ ሳናስቀር ልጆቻቸውንም ሚስቶቻቸውንም አገሮቻቸውንም ሁሉ በአንድነት አጠፋን ፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፤ ወኵሎ እንስሳሆሙ ወምሕር ካሆሙ ዘበርበርነ እምአህጉሪሆሙ፡

ከአገሮቻቸው የዘረፍነው ግን ዘባቸውንና ከብቶቻቸውን ሁሉ አጠፋን ፤

፰፤ ወነሣእነ ምድሮሙ በውእቱ መዋዕል እምእዴሆሙ ለክልኤቱ ነገሥተ አሞሬዎን እለ ሀለዉ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ፡

በዚያ ወራት በዮርዳኖስ ማዶ ካሉ ከሁለቱ የአሞሬዎን ነገሥታት እጅ አገራቸውን እጅ አደረግን ፤

፱፤ እምፈለገ አርኖን እስከ ኤርሞን ዘይብልዎ ሰብአ ፊንቂስ አኤርሞን ወሳኒዮርስ ወአሞሬዎን ይብልዎ ሳኔር ፡

ከአርኖን ወንዝ ጀምሮ የፊንቂስ ሰዎች አኤርሞን የሳኒዮርስና የአሞሬዎን ሰዎች ሳኔር እስከሚሉት እስከ ኤርሞን ድረስ አገራቸውን ሁሉ እጅ አደረግን፤

፲፤ ወኵሎ አህጉረ እለ ሚሴሶር ወኵሎ ዘገለዓድ ወኵሎ ዘባሳን እስከ ኤልክድ ወኤንድራይን ሀገረ መንግሥቱ ለዓግ በባሳን ፡

በባሳን ያለ የዓግ ግዛት የምትሆን እስከ ኤንድራይ ንና ኤልክድ ድረስ የባሳንን አገር ሁሉ የገለዓድና የሚ ሴሶርን አገሮች ሁሉ እጅ አደረግን ፤

፲፩፤ ወባሕቱ እስመ ዓግ ንጉሠ ባሳን ውእቱ ዘተርፈ እምራፋይን፡

እስመ ዋዌ ነው፤ ነገር ግን የባሳን ንጉሥ ዓግ ከአር በኞች ወገን የቀረ ነው፤ አንድም ከአርበኞች ወገን የቀረ የባሳን ንጉሥ አግ ነው፤ አንድም ባሕቲቱ ይላል ከአርበኞች ወገን የቀረ የባሳን ንጉሥ ዓግ ነው እኮን ፤

ወናሁ ዓራቱ ዓራተ ሐፂን ሀለ ወት ውስተ ጽንፎሙ ለደቂቀ አሞን ትስዕ በእመት ኑኃ ወር. ብዕ በእመት ግድማ ፡

እነሆ የብረት የምትሆን አል ጋውም በአሞን ልጆች አገር ዳርቻ ተዘርግታ ትኖር ነበር፤ ይችውም አቈልቋይዋ ዘጠኝ ክንድ ወርዷ አራት ክንድ ነበር፤

፲፪፤ ወበርበርናሃ ለይእቲ ምድር በውእቱ መዋዕል እምአሮኤር እስከ ማዕዶተ ፈለገ አርኖን ፡

ከአሮኤር እስከ አርኖን ወንዝ ማዶ በዚያ ወራት ያችን አገር ዘረፍናት ፤



ወመንፈቃ ለደብረ ገለዓድ ወአህጉሪሁኒ ወሀብክዎሙ ለሮቤል ወለጋድ ፡

የገለዓድን አገር እኩሌታ የአግን አገሮች ሁሉ ለሮ ቤልና ለጋድ ወገኖች ሰጠ ኋቸው ፤

፲፫፤ ወዘተርፈ እምገለዓድ ወኵሎ ባሳን እመንግሥቱ ለዓግ ወሀብ ክዎሙ ለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ወኵሎ ዘአድያሚሃ ለአርጎብ ፡

ከገለዓድ የቀረውንና ከአግ ግዛት የቀረውን ባሳንን ሁሉ የአርጎብን አውራጃ ሁሉ ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ሰጠኋቸው ፤

ዝንቱ ኵሉ ባሳን ዘይትኌለቍ ውስተ ምድረ ራፋይን ፡

ይህ የባሳን አገር ሁሉ አር በኞች ከሚገዙት አገር ጋር የሚቈጠር ነው ፤

፲፬፤ ወኢያእር ወልደ ምናሴ ነሥአ ኵሎ አድያሚሃ ለአርጎብ እስከ ደወለ ጌርጋሴ ወመከጢ ፡

የምናሴ ልጅ ኢያእርም እስከ ጌርጋሴና እስከ መከጢ ድረስ ያለውን የአር ጎብን አውራጃ ሁሉ እጅ አደረገ ፤

ወሰመዮ በስሙ ለባሳን አውታይ ኢያእር እስከ ዛቲ ዕለት ፡

እስከ ዛሬ ድረስ አውታይ ባሳንን በኢያእር ስም ጠራው ፤

፲፭፤ ወለማኪር ወሀብክዎ ገለዓ ድሃ ፡

ለምናሴ ልጅ ለማኪርም ገለዓድን ሰጠሁት ፤

፲፮፤ ለሮቤል ወለጋድ ወሀብ ክዎሙ ምድረ ገለዓድ እስከ ፈለገ አርኖን ዘማዕከለ ፈለገ አድባር ወእስከ ኢያቦቅ ፈለገ አድባር ዘደቂቀ አሞን ፡

ለሮቤልና ለጋድም በደጋ ወንዝ መካከል እስከ አለው እስከ አርኖን ወንዝና የአሞን ልጆች እስከ ያዙት የደጋው ውሃ እስከሚፈ ስበት እስከ ኢያቦቅ ወንዝ ድረስ የገለዓድን አገር ሁሉ ሰጠኋቸው ፤

፲፯፤ ወዓራባ ወዮርዳኖስ ወሰ ኖሙ ለመካናራ ወእስከ ዓረብ ባሕረ ኤሌቁ እምአሴይን ዘፋስጋ ጽባሒሁ ፡

ምሥራቁ ፋስጋ ከሚሆን ከአሴይን ጀምሮ ይኸውም ባሕረ ዔው ነው፤ በስተግራ

www.ethiopianorthodox.org

እስከአለው ባሕር ድረስ የመከናሩ ድንበር እስከሚ ሆን እስከ የዮርዳኖስና እስከ ዓረባ ድረስ ያለውን ሁሉ ሰጠኋቸው ፤

## ጉባኤ

፲፰፤ ወአዘዝኩክሙ በውእቱ መዋዕል ወእቤለክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወሀበክሙ ዛተ ምድረ መክፈልተክሙ ከመ ትሑሩ ምስለ ንዋየ ሐቅልክሙ ቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል አኃዊክሙ ኵሉ ደቂቀ ኃይል ዘእንበለ አንስቲያክሙ ወደቂቅክሙ ፤

ከልጆቻችሁና ከሚስቶቻችሁ በቀር ኃይል ያላችሁ ሁሉ የጦር መሣሪያችሁን ይዛችሁ በወንድሞቻችሁ በእስራኤል ልጆች ፊት ትሄዱ ዘንድ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ይችን አገር ዕፃ አድርጎ ሰጣችሁ ብዬ በዚያ ወራት አዘዝኋችሁ ፤

፲፱፤ ወአእምር ከመሂ ብዙኀ እንስሳ ብክሙ ወይንበሩ ባሕቲቶሙ ውስተ አህጉሪክሙ ዘወሀብኩክሙ እስከ አመ የዓርፎሙ እግዚአብሔር አምላክነ ለአኃዊክሙ ከማክሙ ፤

ብዙ ከብት እንደ አላችሁ አውቃለሁ፤ ነገር ግን ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ወንድሞቻችሁን እንደናንተ ምድር ሰጥቶ እስኪያሰፍራቸው ድረስ ከብቶቻችሁ በሰጠኋችሁ አገር ይኑሩ ፤

፳፤ ወይወርሱ እሙንቱሂ ምድረ እንተ ይሁቦሙ እግዚአብሔር አምላክነ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ፤

እነሱም ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በዮርዳኖስ ማዶ የሚሰጣቸውን ምድረ ርስት እስኪወርሱ ድረስ በዚያ ይኑሩ ፤

ወእምዝ ትገብኡ ኵልክሙ ውስተ ርስትክሙ ዘወሀብኩክሙ፤

ከዚያ በኋላ ግን ሁላችሁም ወደ ሰጠኋችሁ (ወደ አወረስኳችሁ) ርስታችሁ ትመለሳላችሁ አልኋቸው ፤

፳፩፤ ወአዘዝክዎ ለኢያሱኒ በውእቱ መዋዕል ወእቤሎ ርእየ አዕይንቲከ ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር በእሉ ክልኤቱ ነገሥት ከማሁ ይገብር እግዚአብሔር በኵሉ መንግሥት ኀበ ተሐውር አንተ ህየ ፤

በዚያ ወራት ኢያሱን እንዲህ ብዬ አዘዝኩት፤ እግዚአ



ብሔር በዚያ በሁለቱ ነገሥታት በዓግና በሲዖን ያደረገውን ተአምራት ዓይኖችህ አዩ፤ እንግዲህም ወዲህ አንተ በምትዘምትባቸው በከነዓን ነገሥታት የሚያደርገውን ታያለህ አልሁት ፤

፳፪፤ ወኢትፍራህ እምኔሆሙ እስመ እግዚአብሔር ይፀብእ ለክሙ ፤

እግዚአብሔር ጠላቶቻችሁን ያጠፋላችኋልና ከነሱ የተነሳ አትፍራ፤

፳፫፤ ወሰአልክዎ ለእግዚአብሔር በውእቱ መዋዕል ወእቤሎ፤

በዚያ ወራት እግዚአብሔርን እንዲህ ብዬ ለመንኩት፤

፳፬፤ እግዚኦ እግዚእየ አንተ አንገዝከ ታርእዮ ለገብርከ ዕበየከ ወኃይለከ ወጽንዓ እዴከ ወልዕልና መዝራዕትከ፤

አቤቱ ጌታዬ ገናንነትህንና ከሀሊነትህን ጽኑ ሥልጣንህንም ለኔ ለባርያህ ትገልጥ ዘንድ ጀመርህ፤ አንድም በጽኑ ሥልጣንህ በግብጽ ያደረግኸውን ዘጠኙን መቅሠፍት፤ ዐሥረኛ ሞተ በኵርን፤ ዓሥራ አንደኛ ሥጥመትን ገልጸህ አሳየኸኝ፤

ወመኑ ውእቱ አምላክ በሰማይ ወበምድር ዘይገብር በከመ ገበርከ አንተ፤

በሰማይ በምድር አንተ እንዳደረግኸው የሚያደርግ ፈጣሪ ማን ነው? የለም ሲል ነው፤

፳፭፤ አብሐኒ እዕዱ ወእርአያ ለይእቲ ምድር ቡርክት እንተ ሀለወት ማዕዶተ ዮርዳኖስ ወለውእቱ ደብር ቡሩክ ወለአንጢሊባኖን፤

ተሻግሬ በዮርዳኖስ ማዶ ያለች ያችን የከበረች አገር አያት ዘንድ ያንንም የከበረ (የኢየሩሳሌምን ተራራ) አንጢሊባኖንን አይ ዘንድ አሰናብተኝ ብዬ ለመንኩት፤አንጢሊባኖን ገጠር ጠጠር አንፃረ ሊባኖስ ማለት ነው፤

፳፮፤ ወተጸመመኒ እግዚአብሔር ወኢሰምዓኒ ወይቤለኒ እግዚአብሔር በዝንቱ አክለከ ወኢትድግም እንከ ተናግሮ ዘንተ ቃለ፤

ነገር ግን እግዚአብሔር ቸል አለኝ እንጂ አልሰማኝም፤ እንዲያውም የተናገርኸው ነገር በዛ በቃህ ይህን ነገር ዳግመኛ አትናገረው፤

፳፯፤ አላ ዕርግ ውስተ ርእሰ ዘውቅሮ ወነጽር በአዕይንቲከ መንገለ ባሕር ወመስዕ ወአዜብ ወሠ

www.ethiopianorthodox.org

ርቅ ወርኢ በአዕይንቲከ እስመ ኢተዓድዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ፤

ይህን ዮርዳኖስን አትሻገረውምና ኖራ (ግንብ) ወዳለበት ተራራ ወጥተህ በዓይኖችህ የከነዓንን ፬ቱን መዓዝን ተመልከት እንጂ ይህን ነገር ዳግመኛ አትናገረው አለኝ፤ አንድም ይህ ነገርህ በዛ (በቃህ) ዳግመኛ አትናገረው ብሎ እግዚአብሔር አልሰማኝም ቸል አለኝ፤ አንድም እግዚአብሔር ቸል አለኝ ፤ ብለምነውም አልሰ ማኝም፤

፳፰፤ ወአዝዞ ለኢያሱ ወአጽንዖሎቱ እስመ ውእቱ የዓዱ ቅድሜሁ ለዝንቱ ሕዝብ ወውእቱ ያወርሶሙ ምድረ እንተ ርኢከ ኪያሃ፤

ይልቁንስ በዚህ ወገን ፊት ዮርዳኖስን ይሻገራልና፤ አንተ ያየኻትን ያችንም አገር የሚያወርሳቸው እርሱ ነውና ኢያሱን እዘዘው፤ እርሱን አጽናው (አበርታው) አለኝ፤

፳፱፤ ወነበርነ ውስተ ወግር ኀበ ቤተ ፌጎር፤

ፌጎር የሰው ስም፤ አንድም ጣዖት ነው፤ከዚህ በኋላ ተጕዘን ሂደን ፌጎር በሚባል ሰውቤት አጠገብ ባለ ኮረብታ ተቀመጥን፡፡

ምዕራፍ ፬

፩፤ ወይእዜኒ እስራኤል ስምዑ ኵነኔሁ ወፍትሖ ለእግዚአብሔር ዘእሜህረክሙ አነ ዮም፤

እስራኤል አሁንም እኔ የማስተምራችሁን የእግዚአብሔርን አምልኮቱን ዘጠኙን ሕግጋት ስሙ ፤ አንድም ኵነኔሁ አምስት መቶ ሰባ ወነበቦ ፍትሖ ፲ቱ ቃላት ነው፤ ፍትሕ አለው፤ ከአምስት መቶ ሰባ ወነበቦ ዐሥሩ ቃላት ይበልጣሉና፤ አንድም ኵነኔሁ ዘጠኙ ቃላት፤ ፍትሖ ኢታምልክ ነው፤ ከዘጠኙ ሕግጋት እርሱ ይበልጣልና፤ አንድም የእግዚአብሔር ፍጹም ሕጉን ስሙ፤

ከመ ትግበሩ ወትሕየዉ ወትትባዝኁ ወትምልዑ ወትባኡ ወትረስዋ ለምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክሙ ለአበዊክሙ፤

ሕጉን ሠርታችሁ ከመከራችሁ ትድኑ ዘንድ ፈጽማችሁ ትበዙ ዘንድ ከዚያም ገብታችሁ የአባቶቻችሁ ፈጣሪ እግዚአብሔር የሚሰጣችሁ ምድረ



ርስትን ትወርሱ ዘንድ የእግዚአብሔርን ፍጹም ሕጉን ስሙ፤ አስተምረዋቸው የማይሠሩ አሉና ከመ ትግበሩ አለ፤

፪፤ ወኢትወስኩ ላዕለ ዝቃል ዘአኤዝዘክሙ አነ ዮም ወኢታንትጉ እምኔሁ ከመ ትዕቀቡ ኵሎ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ፤

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ሁሉ ትጠብቁ ዘንድ እኔ በማገዛችሁ (በማስተምራችሁ) በዚህ ቃል ላይ አነሰ ብላችሁ አትጨምሩ| በዛ ብላችሁ አትክፈሉ፤ (አትቀንሱ)፤

፫፤ አዕይንቲክሙ ርእያ ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር አምላክነ በብዔልፌጎር እስመ ለኵሉ ብእሲ ዘሖረ ድኅረ ብዔልፌጎር ቀጥቀጦ እግዚአብሔር አምላክክሙ እምኔክሙ፤

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ከብዔልፌጎር በኋላ የሄደውን ሰው ማለት ጣዖት ያመለከውን ሰው ሁሉ ከናንተ ለይቶ አጥፍቶታልና ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በጣዖቱ ላይ ያደረገውን ሁሉ ዓይኖቻችሁ አዩ፤

፬፤ ወአንትሙሰ እለ ገባእክሙ ኀበ እግዚአብሔር አምላክክሙ ሕያዋን ኵልክሙ ዮም፤

በሕግ በአምልኮት ወደ እግዚአብሔር የተመለሳችሁ እናንተ ግን ከጥፋት ሕያዋን ናችሁ፤

፭፤ ናሁ ርእዩ ዘአርአይኩክሙ ኵነኔ ወፍትሐ በከመ አዘዘኒ እግዚአብሔር እግበር ከማሁ ትግበሩ በምድር ዘትበውኡ ህየ አንትሙ ከመ ትትዋረስዋ፤

ይህን አደርግ ዘንድ እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ እናንተም ትወርሷት ዘንድ በምትገቡባት ምድር እንደዚሁ ታደርጉ ዘንድ ያስተማርኋችሁን ኢታምልክንና ዘጠኙን ቃላት እዩ፤ ተመልከቱ፤

፮፤ ወዕቀብዎ ወግበርዎ እስመ ውእቱ ጥበብክሙ ወአእምሮትክሙ በቅድመ ኵሉ አሕዛብ እለ ይሰምዕዎ ለዝንቱ ኵሉ፤

ይህን ሁሉ በሚሰሙት በአሕዛብ ፊት እሱ ጥበባችሁ፤ ዕውቀታችሁ ነውና ጠብቃችሁ አድርጉት፤

ወይብሉ ናሁ ዝንቱ ሕዝብ ጠቢብ ወማእምር ወሕዝብ ዐቢይ ውእቱ ዝንቱ፤

እለ ይሰምዕዎ ለዝንቱ ኵሉ ብሎ ነበርና ይህን ሁሉ የሚሰሙ አሕዛብ ይህ ወገን

www.ethiopianorthodox.org

እነሆ ብልህ ዓዋቂ ወገን ነው ይላሉ፤

፯፤ ወመኑ ውእቱ ሕዝብ ዐቢይ ዘቦቱ አምላክ ዘይቀርቦ ከመ አምላክነ እግዚአብሔር በኵሉ ዘጸዋዕናሁ፤

በለመንነው ሁሉ የሚሰማ እንደ ፈጣሪያችን እንደ እግዚአብሔር ያለ የሚቀርበው ፈጣሪ ያለው ደግ ወገን ማነው?

፰፤ ወመኑ ውእቱ ሕዝብ ዓቢይ ዘቦቱ ኵነኔ ወፍትሕ ዘጽድቅ በከመ ዝንቱ ኵሉ ሕግ ዘአነ እሁበክሙ ዮም ቅድሜክሙ፤

እኔ ዛሬ በፊታችሁ እንደ ማስተምራችሁ ሕግ እውነተኛ ሕግና ሥርዓት ያለው ደግ ወገን ማነው?

፱፤ ዐቅ ርእሰከ ወዕቀብ ነፍሰከ ጥቀ ከመ ኢትርሳዕ ኵሎ ዘንተ ነገረ ዘርእያ አዕይንቲከ ወኢይዓእ እምልብከ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትከ ወመሀሮሙ ለደቂቅከ ወለደቂቀ ደቂቅከ፤

ለራስህ ዕወቅ፤ ዓይኖችህ ያዩትን ሁሉ እንዳትዘነጋ ልቡናህን ከክሕደት ከኑፋቄ ጠብቅ፤ ባለ በዘመንህ ሁሉ ሕጉ ከልቡናህ አይራቅ፤ (አይለይ) ይህንም ለልጆችህ ለልጅ ልጆችህም አስተምራቸው፤

፲፤ ወአይድዮሙ ዘከመ ቆምክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ በኮሬብ አመ ዕለተ ተጋባእክሙ እስመ ይቤለኒ እግዚአብሔር አስተጋብኦሙ ለሕዝብ ኀቤየ፤

እግዚአብሔር ሕዝቡን እኔ ወዳለሁበት ወደ ደብረ ሲና ሰብስባቸው ብሎኛልና በኮሬብ በተሰበሰባችሁበት ቀን በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት እንደቆማችሁ ንገራቸው፤

ወይስምዑ ቃልየ ከመ ይትመሀሩ ፈሪሆትየ በኵሉ መዋዕል ዘቦቱ የሐይዉ እሙንቱ ላዕለ ምድር ወይምሀሩ ለደቂቆሙ፤

በዚህ ዓለም በሕይወት በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ አምልኮቴን ይማሩ ዘንድ፤ ልጆቻቸውም ያስተምሩ ዘንድ ቃሌን ሕጌን ሲሰሙ ሕዝቡን ወደኔ ሰብስባቸው ብሎኛልና፤

፲፩፤ ወመጻእክሙ ወቆምክሙ ታሕተ ደብር ወይነድድ ደብሩ በእሳት እስከ ሰማይ ወጽልመት ወዓውሎ ወጣቃ፤

መጥታችሁም በደብረ ሲና በተራራው በታች ቆማችሁ ተራራውም እስከ ሰማይ በእሳት ይቃጠል ነበር፤ ያን ጊዜ ጨለማ፤ ጥቅል ነፋስ ነበር፤ እስከ ሰማይ አለ፤ በገዘፉ ይታይ ነበር ሲል ነው፤

፲፪፤ ወነበበኒ እግዚአብሔር በማዕከለ እሳት ወሰማዕክሙ አንትሙ ቃሎ ወርእዮቶሰ ኢርኢክሙ ዘእንበለ ቃሉ ዘሰማዕክሙ፤

ያን ጊዜ እግዚአብሔር በእሳቱ መካከል ተነጋገረኝ፤ እናንተም ሲነጋገረኝ ቃሉን ሰማችሁ፤ ነገር ግን ቃሉን ከመስማት በቀር መልኩን አላያችሁም፤

፲፫፤ ወአይድዓክሙ ኪዳኖ ዘአዘዘክሙ ከመ ትግበሩ ዓሠሩ ቃላተ ዘጸሐፎን ውስተ ክልኤ ጽላት ዘዕብን፤

ኪዳኖ ያለውን ዓሥሩ ቃላተ ብሎ ገለጸው፤ በሁለቱ ጽላት የጻፋቸውን አሥሩን ቃላት ትሠሩት ዘንድ ያዘዛችሁን ሕጉን ነገራችሁ፤ ሕጉን ኪዳን ይለዋል፤ ብትጠብቁት ይጠብቃችኋል ብሎ ተከያይዶበታልና፤

፲፬፤ ወሊተኒ አዘዘኒ እግዚአብሔር ከመ እምሀርክሙ በውእቱ መዋዕል ኵነኔ ወፍትሐ ዘትገብሩ በምድር እንተ ውስቴታ ትበውኡ አንትሙ ትረስዋ፤



ትወርሷት ዘንድ እናንት በምትገቡባት ምድር (አገር) የምትሠሩትን አምልኮቱንና ዘጠኙን ቃላት አስተምራችሁ ዘንድ እኔንም እግዚአብሔር አዘዘኝ፤

፲፭፤ ወዕቀቡ ጥቀ ነፍሰክሙ እስመ ኢርኢክሙ ርእዮቶ በይእቲ ዕለት እንተ ባቲ ተናገረክሙ እግዚአብሔር በኮሬብ ላዕለ ደብር እማዕከለ እሳት ከመ ኢትጌግዩ፤

እንዳትበድሉ በኮሬብ ተራራ በእሳቱ መካከል እግዚአብሔር ከናንተ ጋር በተነጋገረባት በዚች ቀን ቃሉን ሰማችሁ እንጂ መልኩን አላያችሁምና ምንም ባታዩት ልቡናችሁን (ሰውነታችሁን) ከኃጢአት ከክሕደት ፈጽማችሁ ጠብቁ፤

፲፮፤ ወኢትግበሩ ለክሙ ግልፎ በአምሳለ ኵሉ ምስል ፤ በአምሳለ ተባዕት አው በአምሳለ አንስት፤

በወንድም አምሳል፤ በሴትም አምሳል ቢሆን ዓይን ጆሮ እጅ እግር የተቀረጸለት ጣዖት ይረባናል ይጠቅመናል ብላችሁ አታቁሙ፤

፲፯፤ ወበአምሳለ ኵሉ እንስሳ ዘሀለወ ላዕለ ምድር ወበአምሳለ ኵሉ ዖፍ ወኵሉ ሠራሪ ዘይሠርር በታሕተ ሰማይ፤

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ዓለም ባለ በክብት ሁሉ አምሳል ከሰማይ በታች በሚ ኖርም ወፍ ሁሉ አምሳል፤

፲፰፤ ወበአምሳለ ኵሉ ሕያው ዘይትሐወስ ላዕለ ምድር ወበአምሳለ ኵሉ ዓሣ ዘሀሎ ውስተ ማይ መትሕተ ምድር፣

በደማዊት ነፍስ ሕያው ሁኖ በዚህ ዓለም በሚንቀሳቀሰው ፍጥረት ሁሉ አምሳል ከም ድር በታች ባለ በዓሣ ሁሉ አምሳል ጣዖት አትሥሩ፤

፲፱፤ ወለእመ ነጸርከ ሰማየ ወርኢከ ፀሐየ ወወርኃ ወከዋክብተ ወኵሎ ሠርጉቲሃ ለሰማይ ዮጊ ትጌጊ፡፡

ወደ ሰማይ አቅንተህ ፀሐይ ንና ጨረቃን፣ የሰማይ ጌጥ የሚሆኑ ከዋክብትን ሁሉ ብታይ ትበድል ይሆናል (መጠ ራጠር አይደለም)፣ ትጌጊ ያለ ውን ያመጣዋል፤

ወትሰግድ ሎሙ ወታመልኮሙ ለእለ ገብረ እግዚአብሔር አምላክከ ለኵሉ አሕዛብ ዘመትሕተ ሰማይ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሰ ማይ በታች ላሉ ሰዎች ሁሉ የፈጠራቸውን እነዚህን ሁሉ ታመልካቸዋለህ፣ ትሰግድላቸ ዋለህና ትበድላለህ፤

፳፤ ወኪያክሙሰ ነሥአክሙ እግዚ አብሔር ወአውፅአክሙ እምእቶነ ሐፂን እምግብጽ ከመ ትኩንዎ መክፈልተ ሕዝቡ እስከ ዛቲ ዕለት፣

እናንተን ግን እግዚአብሔር እስከዚች ቀን ድረስ የወገኖቹ ዕድል ትሆኑ ዘንድ ጽኑ አገ ዛዝ ካለበት ከግብጽ አው ጥቶ፤ አንድም እምእቶነ እሳት ከፈርዖን አገዛዝ አድኖ ወእምነ ግብጽ፣ ከግብጽ አገር አውጥቶ ገንዘብ አደረጋችሁ፤

፳፩፤ ወተምዓኒ እግዚአብሔር በእንተ ዘትቤሉ አንትሙ ወመሐለ ከመ ኢየዓድዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ ወከመ ኢይበውእ ውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ርስተ፤

እናንት ስለተናገራችሁት ነገር እግዚአብሔር እስመ ኢቀደስ ክሙኒ በኀበ ማየ ቅስት ብሎ እግዚአብሔር እኔን ተቈጣኝ፣ (ፈረደብኝ) ዮርዳኖስን እንዳል ሻገር ፈጣሪህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ ወደሚያወርስህ ወደ ከነዓንም እንዳልገባ አት ገባም ብሎ ማለ፤

፳፪፣ ናሁ አንሰ እመውት በዛቲ ምድር ወኢየዓድውዎ ለዮርዳኖስ ወአንትሙሰ ተዓድውዎ ለዮርዳኖስ ወትትዋረስዋ ለይእቲ ምድር ቡርክት፣



እነሆ እኔ በዚች አገር (በሞ ዓብ) እሞታለሁ፣ ዮርዳኖስንም አልሻገረውም፣ እናንተ ግን ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ያችን የከበረች አገር ትወርሳላችሁ፤

፳፫፤ ወዑቁ እንከ አንትሙ ኢትርስዑ ኪዳኖ ለእግዚአብሔር አምላክ ክሙ ዘተካየደ ምስሌክሙ፣

እንግዲህ እናንተም ፈጣሪያ ችሁ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር የተማማለውን መሐላ ሕጉን እንዳትዘነጉ ዕወቁ፤

ወእመ አበስክሙ ወገበርክሙ ለክሙ ግልፎ በአምሳለ ኵሉ ምስል ዘበእንቲአሁ ቀሠፈከ እግ ዚአብሔር አምላክከ፣

ብትበድሉ ፈጣሪህ እግዚአብ ሔር በሱ ምክንያት በቀሠ ፈህ አንተን ባጠፋበት ምስል አምሳል ጣዖት ሠርታችሁ ብታመልኩ፤

፳፬፤ እስመ እግዚአብሔር አምላ ክከ እሳት እንተ ታኀልቅ ውእቱ ወአምላክ ቀናዒ ውእቱ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ጥቂት ጥቂት እያለች የምታጠፋ እሳት ነውና፣ ለአምልኮቱም የሚቀና ፈጣሪ ነውና ሕጉን እንዳትዘነጉ ዕወቁ፤

፳፭፤ ወለእመ ወለድከ ደቂቀ ወአ ዋልደ ወደቂቀ ደቂቅከ ወኮን ደይክሙ ላዕለ ምድር ወአበስክሙ ወገበርክሙ ለክሙ በአምሳለ ኵሉ ወገበርክሙ እኩተ ቅድመ እግዚ አብሔር አምላክክሙ ከመ ታምዕ ዕዎ፣

መጽሐፍ አንድና ብዙ አይጠ ነቅቅምና ወለድከ ብሎ ጕንደ ይክሙ አለ ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ብትወልድ፣ የልጅ ልጅም ብታይ፣ በዚህ ዓለም ብዙ ዘመን ብትኖሩ፣ በሁሉ አምሳል ጣዖት ሠርታችሁ ብትበድሉ ታሳዝኑት ዘንድ በፈ ጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ብትሠሩ፤

፳፮፤ ናሁ አሰምዕ ለክሙ ሰማየ ወምድረ ከመ ትጠፍኡ ወትደመሰሱ እምድር እንተ ላቲ አንትሙ ተዓድውዋ ለዮርዳኖስ ህየ ከመ ትትዋረስዋ ወኢትጕንድዩ መዋዕለ ውስቴታ አላ ተቀጥቅጠ ትትቀ ጠቀጡ፣

ትወርሷት ዘንድ ዮርዳኖስን ከምትሻገሩላት አገር ፈጽማ ችሁ እንድትጠፉ እነሆ ሰማ ይና ምድርን ምስክር አድርጌ አዳኘባችኋለሁ ፣ ፈጥናችሁ ትጠፋላችሁ እንጂ በሷም ብዙ ዘመን አትኖሩም፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፯፤ ወይዘርወክሙ እግዚአብሔር ውስተ ኵሉ አሕዛብ ወትተርፉ ውሑዳን በኈልቈ ውስተ ኵሉ አሕዛብ እለ ውስቴቶሙ ያበውአ ክሙ እግዚአብሔር ህየ፤

እግዚአብሔር በአሕዛብ አገር ሁሉ ይበትናችኋል፤ አስማርኮም ይሰድዳችኋል፤ በተማረካችሁበትም አገር ጥቂት ሁናችሁ በቍጥር ትቀራላችሁ፤

፳፰፤ ወታመልኩ በህየ አማልክተ ባዕድ ግብረ እደ እጓለ እመሕያው ዕፀወ ወአዕባነ እለ ኢይሬእዩ ወኢይሰምዑ ወኢይሴብዉ ወኢያ ዌንዉ፤

በዚያም የማያዩ፣ የማይሰሙ፣ ልብ የማያደርጉ፣ የማያሸቱ የሰው እጅ ሥራ የሚሆኑ የአሕዛብን አማልክት እንጨትና ደንጊያውን ታመልካላችሁ፤

፳፱፤ ወእምዝ ተኀሥሥዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ በህየ ወትረክብዎ ሶበ ኀሠሥክምዎ በህየ በኵሉ ልብክሙ ወበኵሉ ነፍስክሙ በሕማምክሙ፤

ከዚህ በኋላ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮት ትሹታላችሁ፤ በመከራችሁ ጊዜም በፍጹም ልቡናችሁና ሰውነታችሁ በዚያ በምትሹት ጊዜ ታገኙታላችሁ፤

፴፤ ወይረክበክሙ ዝንቱ ኵሉ ነገር በደኃሪ መዋዕል ወትትመየጡ ኀበ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወይሰምዓክሙ፤

በኋላ ዘመን ይህ ሁሉ መከራ ያገኛችኋል፤ እናንተም በንስሐ ወደ ፈጣሪያችሁ ወደ እግዚአብሔር ትመለሳላችሁ፤ እሱም ልመናችሁን ይሰማችኋል፤

፴፩፤ እስመ አምላክ መሐሪ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ይቅር ባይ አምላክ ነውና፤ ይሰምዓክሙ ላሰው ኢየኃድገከ ማንኛ፤ አንድም ፈጣሪህ እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነውና፤

ኢየኃድገከ ወኢያጠፍአከ ወኢይረስዕ ኪዳኖሙ ለአበዊከ ዘመሐለ ሎሙ፤

በረድኤት ተለይቶ አያጠፋህም፤ ለአባቶችህ የማለላቸውን መሐላውንም አይዘነጋብህም፤

፴፪፤ ተሰአሉ ዘቀዲሙ መዋዕለ ዘኮነ እምቅድሜክሙ እምአመ



ፈጠሮ እግዚአብሔር ለዕጓለ እመ ሕያው ዲበ ምድር እምአጽናፈ ሰማይ እስከ አጽናፈ ሰማይ ለእመ ኮነ ከመ ዝንቱ ነገር፤

እናንተም እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ ከፈጠረው ጀምሮ ከሰማይ ዳርቻ እስከ ሰማይ ዳርቻ እንደዚህ ያለ ነገር ተደርጎ ያውቅ እንደሆነ ከናንተ አስቀድሞ የነበረውን ዘመን ጠይቁ፤

፴፫፤ ወለእመ ሰምዐ ሕዝብ ቃለ እግዚአብሔር አምላክ ዘሕያው እንዘ ይትናገር በማዕከለ እሳት በከመ ሰማዕከ አንተ ወሐየውከ፤

አንተ ከኔ ጋር ሲነጋገር ሰምተህ እንደ ዳንህ በእሳት መካከል ሲናገር ሕዝቡ ሕያወ ባሕርይ የሚሆን የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ድነው እንደሆነ ጠይቁ፤

፴፬፤ ለእመ አመከረ እግዚአብሔር ወቦአ ወነሥአ ሎቱ ሕዝበ እማዕከለ ሕዝብ በአመክሮ ወበተአምር ወበመድምም ወበቀትል ወበእድ ጽንዕት ወበመዝራዕት ልዑል ወመደንግፅ ዐቢይ በከመ ኵሉ ዘገብረ እግዚአብሔር በምድረ ግብጽ በቅድሜከ እንዘ ትሬኢ፤

እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው መቅሠፍት አምጥቶ እንደ ተፈታተናቸው አባቶቻችሁ ሰምተው ያውቁ እንደሆነ ጠይቁ፤ ዛሬ ግን አንተ እያየህ እግዚአብሔር በፊትህ ግብጻውያንን በመፈታተን ፍጹም ተአምራት በማድረግ ሰውን ሁሉ በሚያስደነግጥ በዘጠኝ መቅሠፍት፤ በአሥረኛ ሞተ በኵር፤ በአሥራ አንደኛ ሥጥመት ግብጻውያንን አጥፍቶ ወገኖቹ እስራኤልን ከግብጽ አውጥቶ ወደ ኤርትራ እንደ ወሰዳቸው ጠይቁ፤

፴፭፤ ከመ ታእምር ከመ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክ ወአልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌሁ፤

ይህን ሁሉ ያደረገ ገናና ፈጣሪ እሱ እንደሆነ ከርሱ በቀር ሌላ ፈጣሪ እንደሌለ ታውቅ ዘንድ ከናንተ አስቀድሞ የነበረውን ዘመን ጠይቁ፤

፴፮፤ እምሰማይ ተሰምዐ ቃሉ ከመ ይምሀርከ ወበምድር አርአየ እሳቶ ዐቢየ ወሰማዕከ ቃሎ እማዕከለ እሳት፤

አንተን ያስተምርህ ዘንድ ከሰማይ ወርዶ ሲናገር ቃሉ ተሰማ፤ በደብረ ሲናም የሚያስፈራራ እሳቱን አሳየ፤ በእሳት መካከል ቃሉን ሰማህ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፯፤ እስመ ያፈቅሮሙ ለአበዊከ ወኃረዮሙ ወለዘርኦሙ እምድኅሬሆሙ ኪያከ እምኵሉ አሕዛብ ወአውፅአከ ውእቱ በኃይሉ ዐቢይ እምግብጽ፤

አባቶችህን ወዷቸዋልና፣ መርጧቸዋልና፣ ከነሱም በኋላ ከአሕዛብ ሁሉ ይልቅ አንተን ልጃቸውን መርጧልና በጽኑ ከሃሊነቱ ከግብጽ አወጣህ፤

፴፰፤ ከመ ታጥፍኦሙ ለአሕዛብ ዐበይት ወጽኑዓን እምቅድመ ገጽከ ወከመ ያብእከ ወየሀብከ ምድሮሙ ትረስ በከመ ሀለወከ ዮም፤

ዛሬ እንደምትኖርበት መጠን ትወርስ ዘንድ፣ አገራቸውን ይሰጥህ ዘንድ፣ ወደሷም ያገባህ ዘንድ፣ ጽኑዓን ኃያላን የሚሆኑ ሰብአ ከነዓንን ከፊትህ እልም ድርግም አድርገህ ታጠፋቸው ዘንድ ከግብጽ አወጣህ፣

፴፱፤ ወተአምር ዮም ከመ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ውእቱ እግዚአብሔር በሰማይ በላዕሉ ወበምድር በታሕቱ ወአልቦ ባዕድ ዘእንበሌሁ፤

እንዲህም ባደረገልህ ጊዜ ከምድር በላይ ባለ በሰማይ ከሰማይ በታች ባለ በምድር መልቶ የሚኖር ፈጣሪህ እግዚአብሔር እንደሆነ ከርሱም በቀር ሌላ ፈጣሪ እንደሌለ ታውቃለህ፤

፵፤ ወዕቀቡ ትእዛዞ ወኵነኔሁ ዘአኤዝዘክሙ አነ ዮም ከመ ሠናየ ይኩንክሙ ወለውሉድክሙ እምድኅሬክሙ ወከመ ይኑኁ መዋዕሊክሙ ውስተ ምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ በኵሉ መዋዕል፣

ረድኤቱን ይሰጣችሁ ዘንድ፣ ሠናይ ቢል ረድኤቱ፣ ይሰጣችሁ ዘንድ፣ ከናንተም በኋላ ለልጆቻችሁ ይሰጣቸው ዘንድ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በሚያወርሳችሁ በከነዓንም ዘመናችሁ ይበዛ ዘንድ፣ ዛሬ እኔ የማዝዛችሁን ኢታምልክንና ዘጠኙን ሕግጋት ጠብቁ፤

፵፩፤ ወይእተ አሚረ ፈለጠ ሙሴ ሠላሰ አህጉረ በማዕዶተ ዮርዳኖስ መንገለ ሠርቀ ፀሐይ፣

ሙሴም ያን ጊዜ በዮርዳኖስ ማዶ በፀሐይ መውጫ አንፃር ሦስት ሀገረ ምስካይ ለየ፤

፵፪፤ ከመ ይስኪ ህየ ቀታሊ ዘቀተለ ካልኦ እንዘ ኢየአምር ወኢ



ኮነ ጸላኢሁ ትካት ወይስኪ ውስተ አሐቲ እምእላንቱ አህጉር ወየሐዩ፤

ይሕየው ሲል ነው፣ ሳያውቅ ጥንተ ጠላቱ ሳይሆን ለወፍ ለዛፍ (ለዓላማ) ብሎ ነፍስ የገደለ ሰው ከነዚያ ባንዲቱ ተማፅኖ ይድን ዘንድ ሦስት የመማፀኛ አገሮችን ለየ፤

፵፫፤ ባሶር በገዳም ውስተ ምድረ ሐቅል ዘሮቤል ወአራሞት ዘገለዓድ ዘጋድ ወአውሎን በባሳን ዘምናሴ፣

እነዚህም የሮቤል ዕጣ በምትሆን ምድረ በዳ ያለች በባሶርና የጋድ ዕጣ በምትሆን በገለዓድ ያለች አራሞት በምናሴ ዕጣ በባሳን ያለች አውሎን ናቸው፤ አንድም ባሶር ውስተ ምድረ ሀቅል ለሮቤል ወአራሞት በገለዓድ ለጋድ ወአውሎን በባሳን ለምናሴ ይላል አብነት፣ ባሶር ለነገደ ምናሴ መማፀኛ ናት፣ በገለዓድ ያለች አራሞት ለነገደ ጋድ መማፀኛ ናት፣ በባሳን ያለች አውሎንም ለነገደ ምናሴ መማፀኛ ናት፤

፵፬፤ ዝንቱ ውእቱ ሕግ ዘአዘዞሙ ሙሴ በቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

ሙሴ የእስራኤልን ልጆች በፊታቸው ያዘዛቸው ሕግ ይህ ነው አለ ያለፈውን፤ አንድም የሚያመጣውን፤

፵፭፤ ወዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወኵነኔ ወፍትሕ ዘነገሮሙ ሙሴ ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል በገዳም ወፂአሙ እምድረ ግብጽ፣

ከግብጽ አገር በወጡ ጊዜ በምድረ በዳው ሳሉ ሙሴ ለእስራኤል ልጆች ሁሉ ጠብቁ ብሎ የነገራቸው (ፍትሕ) ኢታምልክ (ወኵነኔ) ዘጠኙ ቃላት ትእዛዝ ፳፻፩ ወነበቦ ይህ ነው፤

፵፮፤ በማዕዶተ ዮርዳኖስ በቈላት ዘቅሩበ ቤተ ፌጎር በምድረ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘይነብር ውስተ ሀሴቦን ዘቀተልዎ ሙሴ ወደቂቀ እስራኤል ወፂአሙ እምድረ ግብጽ፣

ይህንም የነገራቸው ከግብጽ አገር ከወጡ በኋላ የእስራኤል ልጆችና ሙሴ የገደሉት በሐሴቦን የሚኖር በአሞሬዎን ንጉሥ በሴዎን አገር በጣዖቱ ቤት አቅራቢያ በቆላው ሳሉ ዮርዳኖስን ሳይሻገሩ ነው፤

፵፯፤ ወተዋረሱ ምድሮ ወምድረ አግ ንጉሠ ባሳን ክልኤቱ ነገሥተ

www.ethiopianorthodox.org

አሞሬዎን እለ ይነብሩ ማዕዶተ ዮርዳኖስ መንገለ ሠርቀ ፀሐይ፤

የሴዎንን ምድሩን ወረሱ፣ የባሳን ንጉሥ የዓግንም አገር ወረሱ፣ እነዚህም በፀሐይ መውጫ አንፃር ባለ በዮርዳኖስ ማዶ የሚኖሩ ሁለቱ የአሞሬዎን ነገሥታት ናቸው፤

፵፰፤ እምአሮኤር እንተ ማዕዶተ ፈለገ አርኖን እስከ ደብረ ሴዎን ዘኤርሞን፣

በአርኖን ወንዝ ካለች ከአሮኤር ጀምሮ የኤርሞን ዕጣ ክፍል እስከምትሆን እስከ ሴዎን ተራራ ድረስ ወረሱ፤ አንድም የሁለቱን ነገሥታት አገር የወረሱ የኤርሞን ክፍል እስከምትሆን እስከ ሴዎን ተራራ ሂደው ነው፤

፵፱፤ ወኵሎ ዐረባ ለማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ሠርቀ ፀሐይ ዘመትሕተ አሴዶን ዘቦ መንደቅ፣

ቅጽር (ግንብ) ካለበት ከአሴዶን በታች በፀሐይ መውጫ አንፃር ያለ የዮርዳኖስን ምዕራቧን ሁሉ ወረሱ፤ አንድም ዓረባ ዘዮርዳኖስ ይላል፣ በዮርዳኖስ አጠገብ ያለ ዓረባ የተባለውን አገር ሁሉ ወረሱ።

ምዕራፍ ፭

፩፤ ወጸውዖሙ ሙሴ ለኵሎሙ ማኅበረ እስራኤል ወይቤሎሙ ስምዑ እስራኤል ኵሎ ኵነኔ ወፍትሐ ዘአነ እነግረክሙ ዮም ውስተ እዘኒክሙ በዛቲ ዕለት ወተመሀሩ ገቢሮቶ ወዓቂቦቶ፣

ዮምና ዛቲ ዕለት አንድ ወገን፣ ሙሴ የእስራኤልን ወገኖች ሁሉ ጠርቶ በጆሯችሁ እየሰማችሁ በዚች ቀን እኔ የምነግራችሁን (ፍትሕ) ዓሥሩን ቃላት (ወኵነኔ) ፭፻፸፭ ወነበቦ የሚለውን ስሙ፣ ሕጉን መጠበቅንና ሥርዓቱን መፈጸ ምንም ተማሩ አላቸው፤

፪፤ እግዚአብሔር አምላክክሙ አቀመ ኪዳኖ ምስሌክሙ በኮሬብ፣

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በደብረ ኮሬብ መሐላውን ከናንተ ጋር አጸና፤ አንድም ሕጉን ለናንተ አጸና፣ ብትጠብቁት ይጠብቃችኋልና ብሎ ተከያይ ዶበታልና፤

፫፤ አኮ ለአበዊክሙ ዘአቀመ ዘንተ ኪዳነ አላ ለክሙ እስመ አንትሙ ሀለውክሙ ዝየ ዮም ኵልክሙ ሕያዋን፣

እናንት ሁላችሁ በዚህ ቦታ በሕይወት አላችሁና ሕጉን



ያጸና ለናንት ነው እንጂ ለአባቶቻችሁ አይደለም፤

፬፤ ገጸ በገጽ ተናገረክሙ እግዚአብሔር በደብር ማዕከለ እሳት፣

ይህም ሲታወቅ እግዚአብሔር በደብረ ሲና በእሳቱ መካከል ፊት ለፊት ተናገራችሁ፤

፭፤ ወአንሰ እቀውም ማዕከለ እግዚአብሔር ወማዕከሌክሙ በይእቲ ዕለት ከመ እንግርክሙ ቃሎ ለእግዚአብሔር እስመ ፈራህክሙ እምቅድመ ገጸ እሳት ወኢዓረግሙ ውስተ ደብር፣

እሳቱን ከመፍራታችሁ የተነሳ ወደ ደብረ ሲና አልወጣችሁም ነበርና፣ እኔ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እነግራችሁ ዘንድ በዚያች ቀን በናንተና በእግዚአብሔር መካከል ቆሜ ነበር፤

፮፤ ወይቤ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ዘአውፃእኩከ እምድረ ግብጽ እምቤተ ቅንየት ኢይኩንከ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ፣

ጽኑ አገዛዝ ካለበት ከፈርዖን ቤት ከግብጽ አገር ያወጣሁህ ፈጣሪህ እኔ ነኝና ያለኔ ሌላ ፈጣሪ አይኑርህ አለ፤

፰፤ ወኢትግበር ለከ አምላከ ዘግልፎ ወኢበኵሉ አምሳል ዘውስተ ሰማይ በላዕሉ ወኢዘውስተ ምድር በታሕቱ ወኢበኵሉ ዘውስተ ማይ ዘመትሕተ ምድር ወኢትስግድ ሎሙ ወኢታምልኮሙ፣

የተቀረጸ ጣዖትን ከምድር በላይ ባለ በሰማይ ያሉ የፀሐይ፣ የጨረቃ፣ የከዋክብትን ምስል ከሰማይ በታች ባለ በምድር ያሉ የሰዎችን የእንስሳትን፣ የአራዊትን፣ የዕፀው የአዕባንን ምስል ከምድር በታች ባለ በውሃ ውስጥ ያሉ የአዞ፣ የጕማሬውን ምስል ሁሉ አትሥራ፣ ለነዚህ ሁሉ አትስገድ አታምልካቸውም፤

፱፤ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላክከ አምላክ ቀናዒ ዘእኄልቆ ኃጣውአ ወላዲ ላዕለ ውሉድ እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ለእለ ይጸልኡኒ፣

በሚጠሉኝ ሰዎች በልጆቻቸው ላይ የአባቶቻቸውን ፍዳ እስከ ሦስትና እስከ አራት ማለት እስከ ሰባት ትውልድ የማመጣ፤

፲፤ ወእገብር ምሕረተ እስከ ፲ቱ ፻ት ትውልድ ለእለ ያፈቅሩኒ ወለእለ የዓቅቡ ትእዛዝየ፣

www.ethiopianorthodox.org

ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ ሰዎች ግን እስከ ሺህ ትውልድ ቸርነትን የማደርግ፣ ለአምልኮቱ የምቀና ፈጣሪህ እኔ እግዚአብሔር ነኝና አትስገድላቸው፣ አታምልካቸው፤

፲፩፤ ወኢትምሐል በስመ እግዚአብሔር አምላክከ በሐሰት እስመ ኢያነጽሖ እግዚአብሔር ለዘይምሕል በስሙ በሐሰት፣

እግዚአብሔር ስሙን በሐሰት ጠርቶ የሚምለውን ከፍዳ አያነጻውምና፣ የፈጣሪህን የእግዚአብሔርን ስም በሐሰት ጠርተህ አትማል፤

፲፪፤ ወዕቀብ ዕለተ ሰንበት ወቀድሳ በከመ አዘዘከ እግዚአብሔር አምላክከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር እንዳዘዘህ የሰንበትን ቀን ጠብቀህ አክብራት፤

፲፫፤ ሰዱሰ መዋዕለ ትገብር ኵሎ ግብረከ ወሳብዕት ዕለት ሰንበቱ ለእግዚአብሔር አምላክከ፣

ስድስት ቀን ሥራህን ሁሉ ሥራ፣ ሰባተኛዪቱ ቀን ግን የፈጣሪህ የእግዚአብሔር በዓል ናትና ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያከበራት በዓል ናት፤

፲፬፤ ወኢትግበር ባቲ ኵሎ ግብረከ ወኢወልድከ ወኢወለትከ ወኢገብርከ ወኢአመትከ ወኢላሕምከ ወኢዓድግከ ወኢኵሉ እንስሳከ ወኢግዩር ዘውስተ ዴዴከ ከመ ያዕርፉ ገብርከ ወአመትከ ከማከ፣

ሥራህን ሁሉ አትሥራባት፣ ወንድና ሴት ልጆችህም አይሥሩባት፣ ወንድ ባሪያህና ሴት ባሪያህም አይሥሩባት፣ በሬህ አይረስባት አህያህም አይጫንባት፣ በደጅህ የሚኖር መጻተኛም ሃይማኖቱ ልዩ ነው ብሎ አይሥራባት፣ ወንድ ባሪያህና ሴት ባሪያህ እንዳንተ ያርፉባት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያከበራት በዓል ናት፤

፲፭፤ ወተዘከር ከመ ገብር አንተ በምድረ ግብጽ ወአውፅአከ እግዚአብሔር አምላክከ እምህየ በእድ ጽንዕት ወበመዝራዕት ልዕልት ወበበይነዝ አዘዘከ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትዕቀባ ለዕለተ ሰንበት ወትቀድሳ፣

በግብጽ አገር ተገዥ እንደ ነበርህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም በጸናች ሥልጣን



ማለት ዘጠኝ መቅሠፍት፣ ዐሥረኛ ሞተ በኵር፣ ዓሥራ አንደኛ ሥጥመትን አምጥቶ ከግብጽ አወጣህ፣ ስለዚህም ነገር የሰንበትን ቀን ትጠብቃት ታከብራትም ዘንድ አዘዘህ፤

፲፮፤ ወአክብር አባከ ወእመከ በከመ አዘዘከ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይኩን ሠናይ ላዕሌከ ወይኑኅ መዋዕሊከ በዲበ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሚሰጥህ አገር ዘመንህ ይበዛ ዘንድ ረድኤቱ ይደረግልህ ዘንድ፣ ሠናይ ቢል በጎ ሆኖ ረድኤቱ ይደረግልህ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር እንዳዘዘ አባትህንና እናትህን አክብር (እርዳ)፤

፲፯፤ ወኢትሐር ኀበ ብእሲተ ብእሲ ፣

ወደ ጉልማሳ ሚስት አትሂድ፣ (ከጉልማሳ ሚስት አትድረስ)፤

፲፰፤ ወኢትቅትል ነፍሰ፣

ነፍስም አትግደል፤

፲፱፤ ወኢትስርቅ፣

የሰው ገንዘብ አትስረቅ (አታንሳ)፤

፳፤ ወኢትኩን ስምዐ በሐሰት ላዕለ ቢጽከ ወኢተሐሱ ስምዐ፣

ወኢትኩን ስምዐና ወኢተሐሱ ስምዓ አንድ ወገን፣ በባልንጀራህ ሐሰት አትመስክር፤

፳፩፤ ወኢትፍቱ ብእሲተ ካልዕከ ወኢትፍቱ ቤቶ ለካልዕከ ወኢገራህቶ ኢገብሮ ወኢአመቶ ኢላሕሞ ወኢአድጎ ወኢእምኵሉ እንስሳሁ፤

የባልንጀራህን ሚስቱን፣ ቤቱንና እርሻውን፣ ወንድ ባሪያውንና ሴት ባሪያውን፣ በሬውንና አህያውን፣ ከከብቶቹም ሁሉ ያለውን አትመኝ፤

ወእምኵሉ ዘቦቱ ለካልዕከ፣

ነሣሣለትና እንዲህ አለ፣ በባልንጀራህ ያለውን ሁሉ፤ አንድም ካለው ገንዘብ ሁሉ አትመኝበት፤

፳፪፤ ዝንቱ ነገር ዘተናገረ እግዚአብሔር እምኵሉ ተዓይኒክሙ በውስተ ደብር በማዕከለ እሳት ወጽልመት ወዓውሎ ወቆባር ወቃል ዐቢይ፣

በእሳትና በጨለማ በጥቅል ነፋስና በጭጋግ መካከል በታ

www.ethiopianorthodox.org

ላት ቃል (ጎንትቶ በሚሰማ ቃል) በደብረ ሲና ለሠራዊታችሁ ሁሉ እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ይህ ነው፤

ወኢደገመ እንከ ወጸሐፎ ውስተ ክልኤ ጽላት ዘዕብን ወወሀበኒ እግዚአብሔር፤

ይህንም ቃል ከደብረ ሲና በኋላ ዳግመኛ አልተናገረም፤ የዕንቍ በሚሆኑ በሁለቱ ጽላት ጽፎ ምክርበት፤ አስተምርበት ብሎ እግዚአብሔር ለኔ ሰጠኝ እንጂ፤

፳፪፤ ወኮነ ሶበ ሰማዕክሙ ውእተ ቃለ እማዕከለ እሳት ወደብሩሂ ይነድድ በእሳት ወመጻእክሙ ኀቤየ ኵልክሙ መላእክተ ነገድክሙ ወአዕሩጊክሙ፤

ከእሳቱ መካከል ሁኖ ይህን ቃል ሲናገር በሰማችሁ ጊዜ እንዲህ ሆነ፤ ተራራውም በእሳት ይቃጠል ነበር፤ ያን ጊዜ በየነገዳችሁ የተሾማችሁ አለቆችና ሽማግሎች ሁላችሁም ተሰብስባችሁ ወደኔ መጣችሁ፤

፳፫፤ ወትቤሉኒ ናሁ አርአየነ እግዚአብሔር አምላክነ ስብሐቲሁ ወቃሎሂ ሰማዕነ እማዕከለ እሳት ወዮም አእመርነ በዛቲ ዕለት ከመ ይትናገር እግዚአብሔር ምስለ ሰብእ ወየሐዩ፤

ወደኔ መጥታችሁም እንዲህ አላችሁኝ፤ እነሆ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ጌትነቱን ገልጦ አሳየን፤ ከእሳቱ መካከልም ሁኖ ሲነጋገር ቃሉን ሰማነ፤ እግዚአብሔር ከሰው ጋር እየተነጋገረ እንዲኖር፤ አንድም ከሰው ጋር እንዲነጋገር ሰውንም ደስ እንዲያሰኝ በዚች ቀን አወቅነ፤

፳፬፤ ወይእዜኒ ኢንሙት ወኢታጥፍአነ ዛቲ እሳት ዐባይ ለእመ ደገምነ ንሕነ ሰሚዖተ ቃሉ ለእግዚአብሔር አምላክነ ዓዲ ንመውት እንከ፤

የፈጣሪያችን የእግዚአብሔርን ቃሉን ዳግመኛ ከሰማነው ያች በደብረ ሲና ያየናት እሳት እንዳታጠፋን እኛም እንዳንሞት አንተ ከፈጣሪያችን ጋር ተነጋገርልን፤ ዳግመኛ ቃሉን ከሰማን እንሞታለንና አላችሁኝ፤

፳፭፤ ወመኑ ውእቱ ዘሥጋ ዘይሰምዕ ቃሎ ለእግዚአብሔር ሕያው እንዘ ይትናገር እማዕከለ እሳት ከማነ ወየሐዩ፤



ከእሳት መካከል ሆኖ ሲነጋገር የሕያው የእግዚአብሔርን ቃል እንደኛ ሰምቶ የሚድን ሥጋዊ ደማዊ ሰው ማነው?

፳፮፤ ሑር አንተ ወስማዕ ኵሎ ዘይብል እግዚአብሔር አምላክነ ወንግረነ አንተ ኵሎ ዘይቤለከ እግዚአብሔር አምላክነ ወንሰምዕ ወንገብር፤

አንተ ሂደህ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ ሰምተህ እግዚአብሔር የነገረህን ሁሉ ንገረን፤ እኛም ሰምተን እናደርጋለን አላችሁኝ፤

፳፯፤ ወሰምዐ እግዚአብሔር ቃለ ነገርክሙ ዘነበብክሙ ወዘትቤሉኒ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ሰማዕኩ ቃሎሙ ዘይቤሉ ዝንቱ ሕዝብ ኵሉ ዘይቤሉከ ወርቱዕ ኵሉ ዘይቤሉ፤

እግዚአብሔርም የነገራችሁኝን ቃል ሰምቶ እኒህ ወገኖች (የሚሉትን) የነገሩህን ነገር ሰማሁ፤ የተናገሩትም ነገር ሁሉ የሚገባ ነው አለኝ፤

፳፰፤ መኑ እምወሀቦሙ ከመዝ ይኩን ላዕሌሆሙ ከመ ይፍርሁኒ ወይዕቀቡ ትእዛዝየ በኵሉ መዋዕሊሆሙ ከመ ሠናይ ትኩኖሙ ወለውሉደሙ እስከ ለዓለም፤

ይፈሩኝ ያመልኩኝ ዘንድ፤ ባለ ዘመናቸውም ሁሉ ትእዛዜን ይጠብቁ ዘንድ እንዲህ ያለ ዕውቀት ማን በሰጣቸው? ረድኤቱ ለጊዜው ለነሱ፤ ከነሱም በኋላ ለልጆቻቸው ትሰጣቸው ዘንድ፤

፳፱፤ ሑር ወበሎሙ እትዉ ውስተ አብያቲክሙ፤

ሂደህ በየቤታችሁ ግቡ በላቸው አለኝ፤

፴፤ ወአንተሰ ቁም ኀቤየ እንግርከ ትእዛዝየ ወኵነኔየ ወፍትሕየ ኵሎ ዘትሜህሮሙ ይግበሩ ከማሁ ውስተ ምድር እንተ አነ እሁቦሙ ርስቶሙ፤

አንተ ግን የምታስተምራቸውን ኢታምልክን፤ ዘጠኙን ሕግጋት፤ ፮፻፲፫ ወነበቦ የሚሰውን እነግርህ ዘንድ እኔ ባለሁበት ቦታ ቁም፤

፴፩፤ ወይግበሩ ከማሁ ውስተ ምድር እንተ አነ እሁቦሙ ርስቶሙ፤

እነሱም ርስት አድርጌ በምሰጣቸው አገር በከነዓን እንደዚሁ ያድርጉ አለኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፪፤ ወዕቀቡ ከመ ትግበሩ በከመ አዘዝከክሙ በከመ አዘዘኒ እግዚ አብሔር አምላክክሙ፤

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ መጠን እኔም የእግዚአብሔርን ሕግ ጠብቁ ብዬ እንዳዘዝኳችሁ ልትሠ ሩት ያስተማርኋችሁን ሕጉን ጠብቁ፤

፴፫፤ ወኢትትገኃሡ ኢለየማን ወኢለፀጋም እምኵሉ ፍኖት ዘአዘ ዘክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ከመ ትሑሩ ባቲ ከመ ሠናይት ትኩንክሙ ወከመ ታዕርፉ ወይ ኑኅ መዋዕሊክሙ ውስተ ምድር እንተ ትትዋረሱ፣

ረድኤቱ ትደረግላችሁ ዘንድ፣ ከመከራውም ታርፉ ዘንድ፣ በምትወርሷትም አገር ዘመ ናችሁ ይበዛ ዘንድ፣ ጸንታች ሁባት ትኖሩ ዘንድ ፈጣ ሪያችሁ እግዚአብሔር ከአዘዛ ችሁ ሥርዓት (ሕግ) ሁሉ ወደቀኝም ወደ ግራም አት በሉ፣ ፀጋምን ሲያይ ነው፣ እንጂ የማንንስ አይጠላም፣ እንዲህ ማለት ከሕገ እግዚአ ብሔር ወጥታችሁ ወደ ሕገ ጣዖት አትሂዱ ሲል ነው።

ምዕራፍ ፮

፩፤ ወዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወኵነኔ ወፍትሕ ዘአዘዘ እግዚ አብሔር አምላክነ ከመ እምህ ርክሙ ትግበሩ በውስተ ምድር እንተ ውስቴታ ትበውኡ ትትዋ ረስዋ፣

ትወርሷት ዘንድ በምትገ ቡባት አገር ልታደርጉት እኔ ለናንተ አስተምራችሁ ዘንድ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ያዘ ዘው (ፍትሕ) ኢታምልክ (ወኵነኔ) ዘጠኙ ሕገጋት (ትእዛዝ) ፳፪፻ ወነበቦ ይህ ነው፤

፪፤ ከመ ትፍርህዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወከመ ትዕቀቡ ኵሎ ኵነኔሁ ወትእዛዞ ዘአነ እኤዝ ዘክሙ ዮም አንትሙ ወደቂቅክሙ ወደቂቀ ደቂቅክሙ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትክሙ ከመ ይኑኅ መዋዕ ሊክሙ፤

እናንተም ልጆቻችሁም የልጅ ልጆቻችሁም ዘመናችሁ ይበዛ ዘንድ በሕይወት በኖራችሁበት ዘመን ሁሉ ዛሬ እኔ የማስተምራችሁን ዓሥሩን ቃላት ፳፪፻ ወነበቦ የሚለውን ትጠብቁ ዘንድ፣



እግዚአብሔርንም ትፈሩት ዘንድ ፈጣሪያችን እግዚአብ ሔር ያዘዘው ትእዛዝ ይህ ነው፤

፫፤ ስምዑ እስራኤል ከመ ትግበሩ ወከመ ትዕቀቡ ከመ ሠናይተ ትኩንክሙ ወከመ ይኑኅ መዋ ዕሊክሙ ወከመ ትትባዝኁ ጥቀ በከመ ይቤ እግዚአብሔር አም ላክሙ ለአበዊክሙ ከመ የሀብ ክሙ ምድረ እንተ ትውኅዝ (ታውኅዝ) ሐሊበ ወመዓረ፣

እስራኤል ስሙ፣ ታደርጉት ዘንድ፣ ሠናይት ረድኤቱ ልት ደረግላችሁ፣ ሠናይተ ቢል ረድኤቱ በጎ ሁና ልትደረግላ ችሁ ሕጉን ትጠብቁ ዘንድ፣ ዘመናችሁ ይበዛ ዘንድ፣ ፈጽማችሁም ትበዙ ዘንድ፣ የአባቶቻችሁ ፈጣሪ እግዚ አብሔር ተድላ ደስታ የምታ ስገኝ አገርን ይሰጣችሁ ዘንድ እንደተናገረ ስሙ፤ አንድም ወከመ ትትባዝኁ ጥቀ በከመ ይቤ እግዚአብሔር አምላኮሙ ለአበዊክሙ፣ እጅግ ትበዙ ዘንድ የአባቶቻችሁ ፈጣሪ ልጆቻችሁን እንደ ሰማይ ኮከብ እንደ ባሕር አሸዋ አበዛቸዋለሁ ብሎ እንደተ ናገረ ስሙ፤

፬፤ ወዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወኵነኔ ኵሉ ዘአዘዞሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል በገዳም ወፂኦሙ እም ድረ ግብጽ፤

ከግብጽ አገር ከወጡ በኋላ ሙሴ ለእስራኤል ልጆች ያዘዛቸው ሁሉ አሥሩ ቃላት ፳፪፻ ወነበቦ ይህ ነው፤

ጉባኤ

፭፤ ስማዕ እስራኤል እግዚአብሔር አምላክከ አሐዱ ውእቱ፣

እስራኤል ስማ፡ ፈጣሪህ እግዚአብሔር አንድ ነው፤ አንድም እስራኤል ፈጣሪህ እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ ስማ፤

፮፤ ወአፍቅሮ ለእግዚአብሔር አም ላክከ በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ ወበኵሉ ኃይልከ ወበኵሉ ሕሊናከ፣

በፍጹም ልቡናህ፡ በፍጹም ሰውነትህ፡ በፍጹም አእ ምሮህ፡ በፍጹም አሳብህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ውደደው፤

ወየሀሉ ውስተ ልብከ ወውስተ ነፍስከ ዝንቱ ኵሉ ነገር ዘአነ እነግረከ ዮም፣

አሁን እኔ የምነግርህ ይህም ነገር ሁሉ በሰውነትህ በል ቡናህ ጸንቶ ይኑር፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፡ ወመሀሮ ሰወልድከ ወንግሮ ኪያሁ እንዘ ትነብር ውስተ ቤት ወእንዘ ተሐውር ውስተ ፍኖት ወሰእመ ሰከብከኒ ወሰእመ ተንሣእ ከሂ፤

በቤት ተቀምጠህ፣ በጎዳናም ስትሄድ ፣ ተኝተህም ተቀ ምጠህም ቢሆን ይህን ነገር ለልጅህ ንገረው ፣ አስተ ምረው፤

፰፤ ወግበሮ ከመ ትእምርት ውስተ እዴከ ወይኩንከ ዘኢይትሐወስ እምቅድመ አዕይንቲከ፤

ለጣትህ እንደ ቀለበት፣ በፊትህ እንደ መስተዋት፣ ይሁን፤ አንድም እንዲህ እንዲሆንልህ፤

፱፤ ወጸሐፎ ውስተ ምርፋቃተ ኆኅተ አብያቲከ ወውስተ ዴዴ ያቲከ፤

በደጅህና በቤትህ ደጃፍ መቃን መድረክ ጻፈው፤

፲፤ ወአመ አብአከ እግዚአብሔር ውስተ ምድር እንተ መሐለ ለአበዊከ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ከመ የሀብከ አህጉረ ዐበይተ ወሠናይተ ዘኢነደቀ፤

አንተ ያላቀናሃቸው ያማሩ የተወደዱ ታላላቅ አገሮችን ሊሰጥህ ለአባቶችህ ለአብር ሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ለልጆቻችሁ አወርስላችኋለሁ ብሎ ወደ ማለላቸው ወደ ከነዓን ምድር ፈጣሪህ እግዚአብሔር ባገባህ ጊዜ፤

፲፩፤ ወአብያተ ዘምሉዕ እምኵሉ በረከት ዘኢዘገብከ ወዓዘቅተ ዘውቅሮ ዘኢወቀርከ ወአዕፃዳተ ወይን ወአዕፃዳተ ዘይት ዘኢተ ከልከ፤

አንተ ካላደለብኸው (ካል ሰበሰብኸው) በረከት ወደተ መሉ ቤቶች፣ አንተ ወደ አልቆፈርኸው በኖራ ወደ ተሠራ የውሃ ጉድጓድ፣ አንተ ያልተከልኸው የዘይትና የወይን ቦታ ወደ አለበት ቦታ ባገባህ ጊዜ፤

፲፪፤ ወእምድኅረ በላዕከ ወጸገብከ ዑቅ እንከ ኢትርስዖ ለእግዚ አብሔር አምላክከ ዘአውፅአከ እምድረ ግብጽ እምቤተ ቅንየት፤

ይህን ሁሉ በልተህ ከጠ ገብህ በኋላ ጽኑ አገዛዝ ካለ በት ከግብጽ አገር ያወጣህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን እንዳ ትዘነጋው ዕወቅ፤

፲፫፤ ወፍርሆ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወሎቱ ለባሕቲቱ አምልኮ ወሎቱ ትልዎ ወበስመ ዚአሁ መሐል፤



አንተስ ይህን ሁሉ ስላደ ረገልህ ፈጣሪህ እግዚአብሔ ርን ፍራው፣ እሱን ብቻ አም ልከው፣ በሕግ በአምልኮት እሱን ብቻ ተከተል፣ የሱን ስም ጠርተህ ማል እንጂ በስመ ጣዖት አትማል፤

፲፬፤ ወኢትሖር ድኅረ አማልክተ ባዕድ ኀበ አማልክተ አሕዛብ እለ ዓውድከ እስመ አምላክ ቀናዒ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ለአም ልኮቱ የሚቀና አምላክ ነውና በዙሪያህ ያሉ የአሕዛብን ጣዖ ታት አታምልክ፤

፲፭፤ ወዐቅ ኢይትመዓዕከ እግዚአ ብሔር አምላክከ በመዓቱ ወኢይ ሥሩከ እምገጸ ምድር፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ፈርዶ ከዚህ ዓለም እንዳያጠፋህ እወቅ፤

፲፮፤ ወኢታመክሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ በከመ አመከርካሁ አመ ዕለተ መንሱት፤

ጥፋት በታዘዘበት ቀን እንደ ተፈታተንኸው ፈጣሪህ እግዚ አብሔርን አትፈታተነው፤

፲፯፤ ተዓቀብ ወዕቀብ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወስማዕ ኵሎ ኵነኔሁ ዘአዘዘከ፤

ከጣዖት ተጠበቅ፣ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ፣ ያዘዘህንም ሕጉን ሁሉ ስማ ማለት አጽንተህ ያዝ፤

፲፰፤ ከመ ትግበር ዘሠናይ ወዘአዳም በቅድሚሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ ከመ ሠናይተ ትኩንከ ወትባእ ወትትዋረስ ምድረ ቡርክተ ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊከ፤

‹ሠናይት› ረድኤቱ ልትደረ ግልህ ‹ሠናይተ ቢል› ረድ ኤቱ በጎ ሁና ልትደረግልህ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር በጎ ውን ሥራ ሁሉ ትሠራ ዘንድ እግዚአብሔር ለአባቶ ችህ የማለላቸውን የከበረች አገር ከነዓንን ገብተህ ትወርስ ዘንድ፤

፲፱፤ ወከመ ይስድድ ለከ ኵሎ ፀረከ እምቅድመ ገጽከ በከመ ይቤ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር አጠፋልሃለሁ ብሎ እንደ ተናገረ ጠላቶ ችህን ሁሉ ከፊትህ ያጠፋ ልህ ዘንድ ያዘዘህን ሕጉን ሁሉ ስማ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፤ ወሶበ ተስእለከ ወልድከ ጌሠመ ወይቤለከ ምንት ውእቱ ዝንቱ ትእዛዝ ወኵነኔ ወፍትሕ ኵሉ ዘአዘዘነ እግዚአብሔር አምላክነ፤

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ያዘዘን ‹ኢታምልክ› ዘጠኙ ሕገጋት ፳፱፰ ወነበቦ ምንድነው ብሎ ልጅህ ነገ ቢጠይቅህ፤

፳፩፤ ትብሎ ለወልድከ አግብርቲሁ ንሕነ ለፈርዖን በብሔረ ግብጽ ወአውፅአነ እግዚአብሔር አምላክነ እምህየ በእድ ጽንዕት ወበመ ዝራዕት ልዕልት፤

በግብጽ አገር ለፈርዖን ተገዥዎች ሁነን ስንኖር ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በዘጠኝ መቅሠፍት በዓሥረኛ ሞተ በኵር ከዚያ መከራ አወጣን ብለህ ለልጅህ ንገረው፤

፳፪፤ ወፈነወ እግዚብሔር ተአምረ ወመድምመ ዐቢየ ወእኩየ ላዕለ ግብጽ ወላዕለ ፈርኦን ወመገብቱ ወአግብርቲሁ ወላዕለ ቤቱ በቅድሜነ፤

እግዚአብሔር ድንቅ የሆነ ደገኛ ተአምራቱን፤ ገልጾ በፈርኦንና በግብጻውያን በሹማምቱና በባሮቹ፤ በወገኖቹም ላይ ዓይናችን እያየ ጽኑ መቅሠፍትን አደረገ፤

፳፫፤ ወኪያነሰ አውፅአነ እምህየ ከመ ያብአነ ውስተ ዛቲ ምድር ወየሀበነሃ ዘመሐለ ከመ የሀቦሙ ለአበዊነ፤

እኛን ግን ለአባቶቻችን ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ አወርሳችኋለሁ ብሎ የማለላቸውን አገር ያወርሰን ዘንድ፤ ወደ ከነዓንም ያገባን ዘንድ ከግብጽ አወጣን፤

፳፬፤ ወአዘዘነ እግዚአብሔር ዘንተ ኵሎ ኵነኔ ወፍትሐ ከመ ይግበር ወከመ ንፍርሆ ለእግዚአብሔር አምላክነ ከመ ሠናይት ትኩን በኵሉ መዋዕሊነ ላዕሌነ ወከመ ንሕየው በከመ ዮም፤

ኢታምልክን፤ ዘጠኙን ሕገጋት እንሠራ ዘንድ፤ በዘመናችን ሁሉ ረድኤቱ ልትደረግልን ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን እንፈራው ዘንድ፤ እንደ ዛሬም በሕይወት እንኖር ዘንድ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር አዘዘን፤

፳፭፤ ወከመ ንርከብ ምሕረተ ለእመ ዓቀብነ ከመ ንግበር ኵሎ ዘንተ ትእዛዘ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ በከመ አዘዘነ እግዚአብሔር፤



ሕጉን ብንጠብቅ ይቅርታን እናገኝ ዘንድ፤ እግዚአብሔር እንዳዘዘን በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር ፊት ሕጉን ሁሉ እንሠራ ዘንድ ይህን ሁሉ ትእዛዝ አዘዘን።

## ምዕራፍ ፯

፩፤ ወለእመ አብአከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ ምድር እንተ ባቲ ተሐውር ህየ ከመ ትረሳ፤

ትወርሳት ዘንድ ወደምት ሄድባት አገር ፈጣሪህ ቢያገባህ፤

ወአሰሰለ አሕዛበ ዐበይተ ወብዙኃነ እምቅድመ ገጽከ ኬጤዎን ወጌርጌሴዎን ወአሞሬዎን ወከናኔዎን ወፌርዜዎን ወኤዌዎን ወኢያቡሴዎን ሰብዓተ አሕዛበ ዐበይተ እለ ይጸንኡከ፤

የሚበረታቱብህ ሰባቱን ነገሥተ አሕዛብ እሊህም ኢያቡሴዎንና ኤዌዎን፤ ፌርዜዎንና ከናኔዎን፤ አሞሬዎንና ጌርጌሴዎን፤ ኬጤዎን ናቸው፤ ታላላቅ የሆኑ እነዚህን አሕዛብ ከፊትህ ቢያርቅልህ፤

፪፤ ወአግብኦሙ ውስተ እዴከ ወቀተልካሆሙ ወአጥፍኦ አጥፍኦሙ ወኢትትካየድ ምስሌሆሙ ኪዳነ ወኢትምሐሮሙ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር እነዚህን በእጅህ ቢጥላቸው፤ አንተም ብትወጋቸው፤ እልምድርግም አድርጎ ቢያጠፋቸውያን ጊዜ ከነሱ ጋር አትማማል አትዘንላቸው፤ አትራራላቸው ፤

፫፤ ወኢትትሐመዎሙ ወለተከ ኢተሁብ ለወልዱ ወወለቶ ኢትንሣእ ለወልድከ፤

ሴት ልጅህን ለወንድ ልጁ አትስጥ፤ የሱንም ሴት ልጅ ለአንተ ወንድ ልጅ አጋብተህ አምቻ አትሁናቸው ማለት አትጋባቸው፤

፬፤ እስመ ያግኅሦ ለወልድከ እምኔየ ወያመልክ ባዕዳነ አማልክተ ወይትመዓዕ እግዚአብሔር መዓተ ላዕሌክሙ ወይሤርወክሙ ፍጡነ፤

ከአሕዛብ ከተጋባ ልጅህን በአምልኮት ከኔ ያርቀዋልና፤ የአሕዛብንም ጣዖታት ያመልካልና፤ በዚህ እግዚአብሔር በናንተ ላይ ፈጽሞ ይቆጣልና ፈጥኖም ያጠፋችኋልና፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፤ አላ ከመዝ ግበርዎሙ ምሥዋዓቲሆሙ ንሥቱ ወምስላቲሆሙ ቀጥቅጡ ወአዕዋማቲሆሙ ግዝሙ ወአማልክቲሆሙ ዘግልፎ አውዕዩ በእሳት፤

እንዲህ አድርጉባቸው እንጂ ማለት መሠዊያቸውን አፍርሱ፤ ምስላቸውን ስበሩ፤ ዛፋቸውን ቁረጡ፤ ተመትቶ የተሠራ ጣዖታቸውንም በእሳት አቃጥሉ እንጂ፤

፮፤ እስመ ሕዝብ ቅዱስ አንተ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወኪያከ አብደረ ወኃረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትኩኖ ሕዝበ ሎቱ እምኵሉ አሕዛብ እለ ሀለዉ ዲበ ገጸ ምድር፤

አንተ ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር የከበረ ወገን ስለሆንህ በዚህ ዓለም ከሚኖሩ ከአሕዛብ ሁሉ ለይቶ ለሱ ወገን ትሆነው ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ፈጽሞ አንተን መረጠ፤

፯፤ ወአኮ እስመ ትበዝኁ እንትሙ እምኵሉ አሕዛብ ዘአብደረ ኃርዮተክሙ እግዚአብሔር አንትሙሰ ትውሕዱ እምኵሉ አሕዛብ፤

እግዚአብሔር እናንተን ከአሕዛብ ለይቶ የመረጣችሁ ከአሕዛብ ትበዛላችሁ ብሎ አይደለም፤ እናንተስ ከአሕዛብ ሁሉ ታንሳላችሁ፤

፰፤ አላ እስመ ያፈቅረክሙ እግዚአብሔር ወእስመ የዓቅብ መሐላሁ ዘመሐለ ለአበዊክሙ ወበበይነ ዝንቱ አውፅአክሙ በእድ ጽንዕት ወበመዝራዕት ልዕልት ወቤዘወክሙ እምቅንየት ወእም እዴሁ ለፈርዖን ንጉሠ ግብጽ፤

እግዚአብሔር ይወዳችኋልና ለአባቶቻችሁ የማለውንም፤ መሐላ ይጠብቃልና ስለዚህ ነገር በጽኑ ሥልጣኑ ከግብጽ አወጣችሁ እንጂ፤ ከግብጽ ንጉሥ ከፈርኦን እጅ ከጽኑ አገዛዙም አዳናችሁ እንጂ፤

፱፤ ወተአምር ከመ እግዚአብሔር ውእቱ አምላክከ ውእቱ እግዚአ ወውእቱ አምላክ ማእምን ዘየዓቅብ ኪዳኖ ወምሕረቶ ለእለ ያፈቅርዎ ወየዓቅቡ ትእዛዞ እስከ ዓሠርቱ ምእት ትውልድ፤

እስከ ዐሥር ትውልድ ድረስ ትእዛዙን ለሚጠብቁና ለሚወዱት ሰዎች ቸርነቱን፤ መሐላውን የሚጠብቅ የታመነ አምላክ ገዥ ፈጣሪ እንደሆነ ታውቃለህ፤



፲፤ ወይትቤቀሎሙ ለእለ ይጸልእዎ በቅድመ ገጾሙ ወይሤርዎሙ ወኢያገኅዲ ሠርዎቶሙ ለእለ ይጸልእዎ በቅድመ ገጾሙ፤

የሚጠሉትን ሰዎች በፊታቸው ይበቀላቸዋል ያጠፋቸዋል፤ የሚጠሉትን ሰዎች በፊታቸው ተገልጾ ማጥፋትንም አይዘገይም፤

፲፩፤ ወዕቀቡ ትእዛዞ ወኵነኔሁ ወፍትሖ ኵሎ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም ከመ ትግበርዎ፤

ትሠሩት ዘንድ ዛሬ እኔ የማገዛችሁን አምልኮቱንና ሕጉን ትእዛዙን ጠብቁ፤

፲፪፤ ወእምከመ ሰማዕክሙ ዘንተ ኵነኔሁ ወዓቀብክምዎ ወገበርክምዎ እግዚአብሔርኒ የዓቅብ ለክሙ ኪዳኖ ወምሕረቶ ዘመሐለ ለአበዊክሙ፤

ይህን ሕጉን ሰምታችሁ ከጠበቃችሁት ከሠራችሁትም እግዚአብሔር ወዳጁን ያውቃልና ለአባቶቻችሁ የማለውን መሐላውን ቸርነቱን ይጠብቅላችኋል፤

፲፫፤ ወያፈቅረከ ወይባርከከ ወያስተባዝኃከ ወይባርክ ለከ ፍሬ ከርሥከ ወፍሬ ምድርከ ወሥርናየከ ወወይነከ ወቅብዕከ ወአዕባዱተ ላሕምከ ወመራዕየ አባግዒከ ላዕለ ምድር ዘመሐለ ለአበዊከ ከመ የሀብከ፤

ይህን ሁሉ ብታደርግ ይወድሃል ያከብርሃል ያበዛኃል፤ የልጅ ልጅህንም ይባርክልሃል፤ የምድርህን ፍሬ ስንዴህንና ወይንህን ዘይትህን ያበዛልሃል፤ የላሞችህንና የበጎችህን መንጋ መስማሪያ ይሰጥህ ዘንድ ለአባቶችህ በማለላቸው ምድር ያበዛሃል፤

፲፬፤ ወትከውን ቡሩከ እምኵሉ አሕዛብ ወአልቦ መካን እምአንስትያከ ወአመት እንተ አልባቲ ውሉድ ወኢመካን እምእንስሳከ፤

ከአሕዛብ ሁሉ ተለይተህ አንተ የከበርህ ትሆናለህ ከሚስቶችህም የማይወልድ የለም፤ ልጅ የሌላትም ባሪያ የለችም፤ ከከብቶችህም የማይወልድ የለም ፤

፲፭፤ ወያሴስል እግዚአብሔር እምኔከ ኵሎ ደዌ ወኵሎ ሕማመ እኩየ ዘርኢከ ዘመጽአ ላዕለ ግብጽ፤

በግብጽ ላይ መጥቶ ያየኸውን ክፉውን መከራ ሁሉ እግዚአብሔር ከአንተ ያርቃል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢያመጽኦ ላዕሌከ ለውእቱ ኵሉ ዘርኢከ ወይመይጦ እምኔከ ወይወስዶ ላዕለ ፀርከ ወላዕለ ኵሎሙ እለ ይጸልኡከ፤

ይህን ያየኸውን መከራ ሁሉ በአንተ ላይ አያመጣውም፣ ከአንተ መልሶ ወስዶ አንተን አጽንተው በሚጣሉህ በጠላቶችህ ሁሉ ያሳድረዋል፤

፲፮፤ ወትበልዕ ምህርካሆሙ ለአሕዛብ ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ወኢትምሐኮሙ ዓይንከ ወኢታምልክ አማልክቲሆሙ እስመ እኩይ ውእቱ ለከ ዝንቱ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር የሚሰጥህን የአሕዛብን ምርኮ ትበላለህ፣ ዓይንህም አትራራላቸው፣ ይህ ለአንተ ክፉ ነውና ጣዖቶቻቸውንም አታምልክ፤

፲፯፤ ወለእመሰ ትብል በልብከ ይበዝኀ እምኔየ ዝንቱ ሕዝብ ወእፎ እክል አጥፍኦቶ ኢትፍርሆ፣

በልቡናህ ይህ ወገን ከኔ ይበዛል፣ ማጥፋት እንዴት እችላለሁ ብለህ ግን አትፍራው ፤

፲፰፤ ተዘክሮ ተዘከር ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር አምላክከ ላዕለ ፈርዖን ወላዕለ ኵሉ ግብጽ ዐቢየ መንሱተ ዘርእያ አዕይንቲከ፣

አላ ያለበት ነው፣ ዓይኖችህ ያዩትን ፈጣሪህ እግዚአብሔር በፈርዖንና በግብጻውያን ላይ ያደረገውን ጽኑ መቅሠፍት አስብ እንጂ፤

፲፱፤ ወውእተ ተአምረ ወመድምመ አበይተ ወበእድ ጽንዕት ወበመዝራዕት ልዕልት ዘከመ አውፅአከ እምህየ ከማሁ ይገብሮሙ እግዚአብሔር አምላክከሙ ለኵሎሙ አሕዛብ እለ ትፈርሁ አንትሙ እምቅድመ ገጾሙ፣

ድንቅ ሥራውን ተአምራቱን ሁሉ አስብ፣ በጽኑ ሥልጣኑ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከግብጽ እንዳወጣህ ከፊታቸው የተነሣ ትፈሯቸው የነበሩ አሕዛብን ሁሉ ያጠፋቸዋል፤

፳፤ ወይፈኑ እግዚአብሔር አምላክከ ቅድሜከ መቅሠፍተ ላዕሌሆሙ እስከ ያጠፍኦሙ ለእለ ተርፉ ወለእለ ተኀብኡ እምኔከ፣

ከአንተ የተሠወሩትን፣ ከጦር የተረፉትን እስኪያጠፋቸው ድረስ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በላያቸው ላይ መቅሠፍትን ይልካል፤



፳፩፤ ወኢትደንግፅ እምቅድመ ገጾሙ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ሀለወ ምስሌከ ወውእቱ እግዚአብሔር አምላክ ዐቢይ ወጽኑዕ፤

ከፊታቸው የተነሣ አትደንግጥ፣ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በረድኤት ከአንተ ጋር አለና፣ እሱም ወዳጆቹን ለመርዳት ጽኑ ከሃሊ ነውና፤

፳፪፤ ወያጠፍኦሙ ለእሉ አሕዛብ እምቅድመ ገጽከ በበንስቲት ንስቲተ ወኢትበል አጠፍኦሙ ፍጡነ ከመ ኢትኩን ምድር ሐቅለ ወኢይብዝኁ ላዕሌከ አራዊተ ገዳም፣

ጥቂት ጥቂት እያለ እሊህን አሕዛብ ያጠፋቸዋልና አገሪቱ ምድረ በዳ እንዳትሆን በምድረ በዳ ያሉ አራዊትም እንዳይሠለጥኑብህ ፈጥኜ አጠፋቸዋለሁ አትበል፤ አንድም ጠላቶቼን ፈጥኜ ባጠፋቸው ምን ይጎዳል ትለኝ እንደሆነ ‹‹ትከውን ምድር ሐቅለ ወይበዝኁ አራዊተ ገዳም ይላል›› አገሪቱ ምድረ በዳ ትሆናለች፣ አራዊትም ይሠለጥኑብሃል፤

፳፫፤ ወያገብኦሙ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ እዴከ ወይደመስሶሙ በዐቢይ ሕርትምና እስከ ያጠፍኦሙ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በእጅህ ይጥላቸዋል፣ እስኪያጠፋቸውም ድረስ በጽኑ ጉስቍልና ያጠፋቸዋል፤

፳፬፤ ወያገብኦሙ ለነገሥቶሙ ውስተ እዴከ ወይደመስስ ስሞሙ እምውእቱ መካን ወአልቦ ዘይትቃወም ቅድመ ገጽከ እስከ ያጠፍኦሙ እግዚአብሔር፣

ከዚህ ቀድሞ ሠራዊቱን ሕዝቡን በእጅህ እንደጣለልህ ነገሥታቱንም በእጅህ ይጥላቸዋል፣ ከሚኖሩበት አገርም ስም አጠራራቸውን ያጠፋል፣ እግዚአብሔር እነሱን እስኪያጠፋቸው ድረስ በፊትህ ባጭር ታጥቆ ጋሻ ዘገር ነጥቆ የሚቃወምህ ‹የሚዋጋህ› የለም፤

፳፭፤ ወኵሎ ግልፎ አማልክቲሆሙ አውዕዩ በእሳት ወኢትፍቱ ኢወርቀ ወኢብሩረ ወኢብርተ እምኔሆሙ ወኢትንሣእ ለከ ከመ ኢትጌጊ ቦሙ እስመ ርኵሳን እሙንቱ በኀበ እግዚአብሔር አምላክከ፣

www.ethiopianorthodox.org

የተቀረጹ ጣዖቶቻቸውንም በእሳት አቃጥሉ፣ ከነሱም ወርቁን ብሩን ብርቱን አት ውደዱ፣ በፈጣሪህ በእግዚ አብሔር ዘንድ የረከሱ ናቸ ውና በነዚህ እንዳትስት ‹እን ዳትበድል› ይህን ሁሉ ለአ ንተ አትውሰድ፤

፳፮፤ ወኢታብእ ርኩሰ ውስተ ቤትከ ወኢትኩን ርጉመ ከማሁ አርኩሶ ታረኩሶ ወአስቆርር ታስ ቆርር እስመ ርጉም ውእቱ፣

የረከሰ ጣዖትን ወደቤትህ አታግባ፣ ይህንም አድርገህ የተረገምህ አትሁን፣ ጣዖቱ የተረገመ ነውና አሁን እንደ ተናገርኩት ርኩስ በሰው፣ ፈጽመህም ተጸየፈው እንጂ።

## ምዕራፍ ፰

፩፤ ወዕቀቡ ከመ ትግበሩ ኵሉ ትእዛዘ ዘአኤዝዘክሙ እነ ዮም ከመ ትሕየዉ ወትትባዝኁ ወትባኡ ትትዋረስዋ ለምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊ ክሙ፣

እግዚአብሔር ለአባቶቻችሁ የማለላቸውን ምድር ገብታ ችሁ ትወርሱ ዘንድ፣ በዝታ ችሁም ትኖሩ ዘንድ እኔ ዛሬ የማዝዛችሁን ትእዛዝ ትሠሩ ዘንድ ጠብቁ፤

፪፤ ወተዘከር ኵሎ ፍኖተ ዘወሰደከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ ገዳም ከመ ያሕምምከ ወከመ ያመክርከ ወከመ ያእምር ልበከ ለእመ ተዓቅብ ትእዛዞ ወለእመ አልቦ፣

ትእዛዙን ትጠብቅ እንደሆነ አትጠብቅም እንደሆነ ልቡ ናህን መርምሮ ያውቅ ዘንድ ሊፈትንህና ሊያሳዝንህ ፈጣ ሪህ እግዚአብሔር በምድረ በዳ የወሰደህን ጎዳና ሁሉ አስብ፤

፫፤ ወአሕመመከ ወአርኀበከ ወእምገዘ መና ሴሰየከ ዘኢየአምሩ አበዊከ ከመ ያርኢከ ከመ ኢኮነ በእክል ባሕቲቱ ዘየሐዩ ሰብእ አላ በኵሉ ቃል እንተ ትወፅእ እምአፉሁ ለእግዚአብሔር የሐዩ ሰብእ፤

አስቀድሞ መከራ አጸናብህ አስራበህ፣ ከዚህ በኋላ ግን እግዚአብሔር ዳን ያሰው ይድናል እንጂ ‹ሰው የሚድን እግዚአብሔር ያዘዘውን ትእ ዛዝ በመጠበቅ ነው እንጂ› በእህል ብቻ እንዳይደለ ያስ ረዳህ ዘንድ አባቶችህ የማያ ውቁትን መናውን መገበህ፤



፬፤ ወአልባሲከኒ ኢበልየ በላዕሌከ ወእገሪከኒ ኢረስሐ ናሁ ፵ ዓም ፤

በጫንቃህ ያለ ልብስህ አላ ረጀም? እግርህም አልነቃም? እነሆ ዘመኑም አርባ ዘመን ነው፤

፭፤ ወአእምር በልብከ እስመ በከመ ይጌሥጽ ብእሲ ወልዶ ከማሁ ይጌሥጸከ እግዚአብሔር አምላክከ ፣

አባት ልጁን እንዲገሥጽ እንዲመክር ፈጣሪህ በመከራ ይገሥጽሃልና በልብህ ዕወቅ፤

፮፤ ወዕቀብ ኵሎ ትእዛዞ ለእግዚ አብሔር አምላክከ ከመ ትሑር በፍኖቱ ወትፍርሆ ለእግዚአብሔር አምላክከ፣

በሕጉ ጸንተህ ትኖር ዘንድ፣ ፈጣሪህ እግዚአብሔርንም ትፈራው ዘንድ የፈጣሪህ የእ ግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ፤

፯፤ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ያበውአከ ውስተ ምድር ቡርክት ወብዝኅት ዘአፍላገ ማይ ወዓዘ ቃቲሃ ከመ ቀላይ ወይትከዓው ውስተ ገዳም ወውስተ አድባር፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር የውሀ ጉድጓዷ ብዙ የሚሆኑ ፈሳሾቿም ምድረበዳውን ተራ ራውን ዘረው የሚያጠጡ ወደ ሆኑ ወደ ከበረች አገር ወደ ከነዓን ያገባሃልና፤

፰፤ ምድረ ሥርናይ ወሰገም ወአፀደ ወይን ወበለስ ወሮማን ምድረ ቅብዕ ወዘይት ወመዓር፣

ያችውም የስንዴና የገብስ፣ የወይን የበለስና የሮማን፣ የቅቤና የዘይት፣ የመዓር፣ አገር ናት፤

፱፤ ምድር እንተ ኢኮነት በአስተአክሎ ዘትበልዖ ለእክላ ወአልቦ ዘተኀጥእ ምንተኒ ውስቴታ ምድር እንተ ዕበኒሃ ሐፂን ወእምውስተ አድባሪሃ ይኤልድዎ ለብርት፣

እህሏን በማብቃቃት የምትብ ላው ያይደለች፣ በውስጧም ምንም የሚታጣ የሌለ፣ ድን ጊያዋም ብረት የሆነ፣ ከተራ ራዋም የናስ ብርትን የሚያ ገኙባት አገር ናት፤

፲፤ ወብላዕ ወጽገብ ወባርኮ ለእግዚአብሔር አምላክከ በውስተ ምድር ቡርክት ዘወሀበከ፣

ባወረስህ በከበረች አገር በከ ነዓን ይህን ሁሉ ተመግበህ ጠግበህ ፈጣሪህ እግዚአብ ሔርን አመስግነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፤ ዑቅ ርእሰከ ወኢትርስዮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትዕቀብ ትእዛዞ ወፍትሖ ወኵነኔሁ ወኵሎ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም፣

ዛሬ እኔ የማዝዝህን ኢታም ልክን ዘጠኙን ቃላት ፳፻፸ ወነበቦን ትጠብቅ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን እንዳ ትዘነጋው ለራስህ ዕወቅ፤

፲፪፤ ዮጊ ሶበ በላዕከ ወጸገብከ ወነደቀ አብያተ ሠናያነ ወነበርከ ውስቴቶሙ ወበዝኀ ለከ አባግዒከ ወአልሕምቲከ፣

ይህን ሁሉ በልተህ በጠገብህ ጊዜ፣ ያማሩ ያጌጡ ቤቶችን ሠርተህ በውስጣቸው ገብተህ በተቀመጥህ ጊዜ በጉ ላሙ በበዛልህ ጊዜ፤

፲፫፤ ወሶበ በዝኃ ለከ ወርቅ ወብሩር ወበዝኀ ለከ ኵሉ ንዋይከ ዮጊ ታዓቢ ልበከ ወትረስኦ ለእግዚአብሔር አምላክከ ዘአውፅአከ እምድረ ግብጽ እምቤተ ቅንየት፣

ወርቁ ብሩ ሌላው ገን ዘብህም ሁሉ በበዛልህ ጊዜ ወይም እንጂ ልቡናህን ታስ ታብይ ይሆናል ፣ጽኑ አገዛዝ ካለበት ከግብጽ አገር ያወጣህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርንም ትዘ ነጋው ይሆናል፤

፲፬፤ ወወሰደከ ውስተ ገዳም ዓቢይ ወግሩም ዘውስቴቱ አራዊተ ምድር ዘይነስኩ ወአቃርብት ወጽምዕ ዘአልቦ ማይ ለሰትይ ዘአውፅአ ለከ እምውስተ እብነ ኰኵሕ ነቅዓ ማይ ጥዑም፣

በውስጡ የሚናደፉ አውሬ ዎች ጊንጦች ወዳሉበት የሚ ጠጣ ውሀ ወደሌለበት የውሀ ጥም ወደ ጸናበት ምድረ በዳ የወሰደህ የጠራ የውሀ ምንጭ ከደንጊያ ያፈለቀልህ፤

፲፭፤ ወሴሰየከ መና በገዳም ዘኢየአምሩ አበዊከ ከመ ያሕምምከ ወያመክርከ ወያሠኒ ለከ በደኃ ሪትከ፣

በኋላ ዘመን በጎ ነገር ሲያደርግልህ መከራ አምጥቶ ይፈትንህ ዘንድ አባቶችህ የማያውቁትን መናውን የመ ገበህ ፈጠሪህ እግዚአብ ሔርን ትዘነጋው ይሆናል፤

፲፮፤ ወኢትበል በልብከ በኃይልየ ወበጽንዓ እዴየ ገበርኩ ዘንተ ኵሎ ኃይለ ዓቢየ፣

በልቡናህም በኃይሌ በሥል ጣኔ ጽናት ይህን ሁሉ ደገኛ ነገር አደረግሁ አትበል፤



፲፯፤ ወተዘከሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ እስመ ውእቱ ይሁበከ ኃይለ ከመ ያቅም ኪዳኖ ዘመሐለ ለአበዊከ በከመ ዮም፣

እንደ ዛሬ ለአባቶችህ የማለ ውን መሐላውን ያጸናልህ ዘንድ እሱ ኃይልን ይሰጠ ሃልና ፈጣሪህ እግዚአብሔ ርን አስበው፤

፲፰፤ ወለእመ ረሲዐ ረሳዕካሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወሖርከ ድኅረ ባዕዳን አማልክት ወአምለክካሆሙ ወሰገድከ ሎሙ አሰምዕ ላዕሌከ ዮም ሰማየ ወምድረ ከመ ጠፊአ ትጠፍእ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ፈጽ መህ ብትዘነጋው፣ ልዩ የሆኑ ጣዖታትንም ተከትለህ ብት ሄድ ብታመልካቸውም፣ ብት ሰግድላቸውም ፈጽመህ እንድ ትጠፋ ሰማይና ምድርን አዳ ኝብሃለሁ፤

፲፱፤ በከመ አሕዛብ ኵሎሙ እለ ደምሰሶሙ እግዚአብሔር እም ቅድመ ገጽከ ከማሁ ትደመስስ ለእመ ኢሰማዕከ ቃለ እግዚ. አብሔር አምላክከ፣

የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ካልሰማህ ከፊትህ እልም ድርግም አድርጎ እንዳ ጠፋቸው እንደ አሕዛብ ትጠ ፋለህ ፤ እንድም የእግዚአብ ሔርን ቃል ካልሰማህ እንደ አሕዛብ እንድትጠፋ ሰማይና ምድርን አዳኝብህአለሁ።

## ምዕራፍ ፱

፩፤ ስማዕ እስራኤል ናሁ ተዓድዎ አንተ ዮም ለዮርዳኖስ ከመ ትሖር ትትዋረሶሙ ለአሕዛብ ዐበይት እለ ይጸንዑከ ወአህጉረ ዐበይተ ዘዓረፍተ ቅጽሮን ይበጽሕ እስከ ሰማይ፣

እስራኤል ስማ፣ ከአንተ የሚ በረቱ አሕዛብን አጥፍተህ ቅጽራቸው እስከ ሰማይ የሚ ደርስ ታላላቅ አገራቸውን ልትወርስ ትሄድ ዘንድ እነሆ ዛሬ ዮርዳኖስን ትሻገራለህ፤

፪፤ ሕዝብ ዐቢይ ወብዙኀ ወነ ዋኃት ደቂቀ ኤናቅ እለ ትብሎሙ አንተ፣

እሊህም ወገኖች ቁመታቸው ረጃጅም ቍጥራቸውም ብዙ እንደ ሆኑ አንተ የተናገ ርህላቸው የአርበኞች ልጆች ናቸው፤

፫፤ ወተአምር ዮም ከመ እግዚአ ብሔር አምላክከ የሐውር ቅድመ ገጽከ እሳት ዘይዌድእ ውእቱ፣

www.ethiopianorthodox.org

አሁንም ፈጣሪህ እግዚአብ ሔር በፊትህ ፊታውራሪ ሆኖ እንደሄደ እሱም የሚያጠፋ እሳት እንደሆነ ታውቃለህ፤

ወውእቱ ይሜርዎሙ ወያነትዮሙ እምቅድመ ገጽከ ወያጠፍኦሙ ወይደመስሶሙ ፍጡነ በከመ ይቤለከ፤

እሱም ጠላቶችህን አጠፋልሃ ለሁ ብሎ እንደነገረህ ከፊትህ ፈጽሞ ያጠፋቸዋል፤

፬፤ ወኢትበል በልብከ ሶበ አጥፍ ኦሙ እግዚአብሔር ለውእቶሙ አሕዛብ እምቅድመ ገጽከ በበይነ ጽድቅየ አብአኒ እግዚአብሔር እትዋረሳ ለዛቲ ምድር ቡርክት፤

እግዚአብሔር እሊህን አሕዛ ብን ከፊትህ በአጠፋቸው ጊዜ ያችን የከበረች አገር እወር ሳት ዘንድ እግዚአብሔር ስለ እውነተኛነቴ አገባኝ አትበል፤

አኮ በበይነ ጽድቅከ ወአኮ በበይነ ንጽሐ ልብከ ዘትበውእ አንተ ትትዋረሳ ለምድሮሙ፤

አገራቸውን ትወርሳት ዘንድ ወደሷ የምትገባ ስለልቡናህ ንጽሕና ስለእውነተኛነትህም አይደለም፤

፭፤ አላ በበይነ ኃጢአቶሙ ለውእቶሙ አሕዛብ ያጠፍኦሙ እግዚአብሔር እምቅድመ ገጽከ ወከመ ያቅም ኪዳኖ ዘመሐለ ለአበዊከ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ፤

ለአባቶችህ ለአብርሃም ለይስ ሐቅ ለያዕቆብ የማለውን መሐላ ያጸና ዘንድ እግዚ አብሔር እነዚያን አሕዛብ ስለ ኃጢአታቸው እልም ድርግም አድርጎ አጠፋቸው እንጂ፤

፮፤ ወተአምር ዮም ከመ አኮ በእንተ ጽድቅከ ዘይሁበከሃ ለዛቲ ምድር ቡርክት አኮኑ ሕዝብ ዘያገዝፍ ክሣዶ አንተ፤

አንተ ክሣደ ልቡናውን የሚያጸና ወገን ነህና ያችን የከበረች ምድር የሚያወርስህ ስለውነተኛነትህ እንዳይደለ ታውቃለህ፤

፯፤ ወተዘከር ወኢትርሣዕ ሚመ ጠነ አምዓዕካሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ በገዳም እምአመ አው ፅአከ እምድረ ግብጽ እስከ በጻ ሕከሙ ውስተ ዝንቱ መካን እንዘ ትከሀድዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ፤

ከግብጽ አገር ካወጣህ ጀምሮ ከዚህ ቦታ እስክትደርሱ ድረስ



ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን እየካዳችሁት በምድረ በዳ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ምን ያህል እንዳሳዘንኸው አትዘ ንጋ አስብ፤ (አስብ እንጂ አትዘንጋ)፤

፰፤ ወበኮሬብኒ አምዓዕክምዎ ለእ ግዚአብሔር ወተምዓ እግዚአብ ሔር ላዕሌክሙ ከመ ያጥፍ ዕክሙ፤

በኮሬብም እግዚአብሔርን አሳ ዘናችሁት እሱም ለአምል ኮቱ ቀንቶ ያጠፋችሁ ዘንድ ፈረደባችሁ፤

፱፤ አመ ዓረጉ አነ ውስተ ደብር ከመ እንሣእ ክልኤተ ጽላተ ዘዕብን ጽላተ ዘኪዳን ዘተካየደ እግዚአ ብሔር ምስሌክሙ፤

እግዚአብሔር ከናንተ ጋር የተ ማማለባቸውን አሥሩ ቃላት የተጻፋባቸውን ሁለት የዕንቍ ጽላት እቀበል ዘንድ እኔ ወደ ተራራው ወደ ደብረ ሲና በወጣሁ ጊዜ ፈረደባችሁ፤

ወነበርኩ ውስተ ደብር ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ እክለ ኢበላዕኩ ወማየ ኢሰተይኩ፤

ያን ጊዜም እህል ሳልበላ ውሀ ሳልጠጣ አርባ ቀን በደብረ ሲና ተቀመጥኩ፤

፲፤ ወወሀበኒ እግዚአብሔር ፪ተ ጽላተ ዘዕብን ዘተጽሕፋ በአፅባፅቲሁ ለእግዚአብሔር ወጽሑፍ ውስ ቴቶን ኵሉ ቃል ዘነገረነ እግዚ አብሔር በውስተ ደብር አመ ተጋባእክሙ፤

እግዚአብሔርም በእግዚአብሔ ርነቱ ሥልጣን የተቀረጹ ሁለት የዕንቍ ጽላት ሰጠኝ፤ በውስጣቸውም እናንተ በደ ብረ ሲና በተሰበሰባችሁ ጊዜ እግዚአብሔር የነገረን ነገር ሁሉ ተጽፎባቸዋል፤

፲፩፤ በአርብዓ መዓልት ወበአርብዓ ሌሊት ወሀበኒ እግዚአብሔር ክልኤ ጽላተ ዘዕብን ወጽላተ ዘኪዳን፤

አርባው መዓልት አርባው ሌሊት ሲፈጸም እግዚአ ብሔር አሥሩ ቃላት የተጻ ፉባቸው ሁለቱን የዕንቍ ጽላት ሰጠኝ፤

፲፪፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ተንሥእ ወሑር ፍጡነ እምዝየ እስመ አበሱ ሕዝብከ ዘአውፃእከ እምድረ ግብጽ ወፍጡነ ክሕዱ እምፍኖት ዘአዘዝኮሙ ወገብሩ ሎሙ ስብከ፤

እግዚአብሔርም ከግብጽ ያወ ጣሃቸው ወገኖችህ በድለዋልና

www.ethiopianorthodox.org

ጠብቁ ብለህ ካዘዝሃቸው ሕግም ወጥተው ክደዋልና፤ የተቀረጸ ጣዖትንም አቁመዋልና ከዚህ ተነሥተህ ፈጥነህ ሂድ አለኝ፤ (ሐተታ) ሕዝብየ ይላቸው የነበረ ሕዝብከ አለው፤ ጠብ ያን ጊዜ ተጀምሯል፤ አባት ልጁን በተጣላው ጊዜ ያ ልጅሽ እንዲህ አደረገ እንዲላት ለእናቱ፤

፲፫፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር እቤለከ ምዕረ ወካዕበ እንዘ እብል ርኢክዎ ለዝንቱ ሕዝብ ከመ ሕዝብ ግዙፈ ክሣድ ውእቱ፤

እግዚአብሔር ይህን ወገን ክሣደ ልቡናውን ያጸና እንደሆነ አወቅሁት ብሎ አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ ነገረኝ፤

፲፬፤ ኅድገኒ አጥፍኦ ወእደምስስ ስሞ እምታሕተ ሰማይ ወእገብረከ ውስተ ሕዝብ ዐቢይ ወጽኑዕ ወዘይበዝኅ እምዝንቱ ፈድፋደ፤

ክሣደ ልቡናውን ያጸናውን ወገን ተወኝ ላጥፋው፤ ስሙንም ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ላጥፋው፤ አንተን ግን ጽኑ ገናና በሆነ ከዚህም ፈጽሞ በሚበዛ ወገን መካከል እሾምሃለሁ አለኝ፤

፲፭፤ ወተመየጥኩ ወወረድኩ እምደብር ወደብሩ ይነድድ በእሳት ወእልክቱሂ ክልኤ ጽላት ውስተ ክልኤሆን እደውየ፤

እኔም ተመልሼ ከተራራ ወረድሁ፤ ተራራውም እንደ እሳት ይነድ ነበር፤ እነዚያም ሁለቱ ጽላት በሁለቱ እጆቼ ተይዘው ነበር፤

፲፮፤ ወሶበ ርኢኩ ከመ አበስክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወገበርክሙ ለክሙ ስብኮ ወኀደግሙ ፍኖተ ዘአዘዘክሙ እግዚአብሔር፤

በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት እንደ በደላችሁ፤ እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ሕግ ትታችሁ ለእናንተ ጣዖትን እንደ ሠራችሁ ባየሁ ጊዜ፤

፲፯፤ ነሣእክዎን ለክልኤቲ ጽላት ወገደፍክዎን እምውስተ ክልኤሆን እደውየ ወቀጥቀጥክዎን በቅድሜክሙ፤

እሊህን ሁለቱን ጽላት አንስቼ ከሁለቱ እጆቼ ጥዬ ሰበርኋቸው ፤ አንድም ደንግጬ ከእጆቼ በመጣል ሰብርኋቸው፤

፲፰፤ ወሰአልኩ ዳግመ ቅድመ እግዚአብሔር በከመ ቀዲሙ ፵



መዓልተ ወ፵ ሌሊተ እክለ ኢበላዕኩ ወማየ ኢሰተይኩ በእንተ ኵሉ ኃጣውኢክሙ ዘአበስክሙ ወገበርክሙ እኩየ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ከመ ታምዕዕዎ፤

ታሳዝኑት ዘንድ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ስለ ሠራችሁ፤ ስለ በደላችሁት፤ በደላችሁም ሁሉ እህል ሳልበላ፤ ውሀ ሳልጠጣ እንደ ቀደመው አርባ ቀን አርባ ሌሊት ዳግመኛ በእግዚአብሔር ፊት ለመንሁ፤

## ጉባኤ

፲፱፤ ወፈራህኩ በእንተ መዓቱ ዘተምዓ እግዚአብሔር ላዕሌክሙ ከመ ያጥፍዕክሙ ወሰምዓኒ እግዚአብሔር በውእቱ መዋዕል፤

ያጠፋችሁ ዘንድ (ኀድገኒ እጥስዮሙ በመዓትየ) ብሎ እናንተን ለማጥፋት በናንተ ላይ ስለ ተቆጣው ቍጣ ያጠፋችኋል ብዬ ፈራሁ፤ በዚያም ወራት እንዳያጠፋችሁ ብለምነው ቸርነት የባሕርዩ ነውና ልመናዬን ሰማኝ፤

፳፤ ወላዕለ አሮንሂ ተምዓ እግዚአብሔር ጥቀ ከመ ይሥርዎ ወጸለይኩ በእንተ አሮንሂ በውእቱ መዋዕል፤

ያጠፋው ዘንድ እግዚአብሔር በአሮንም ላይ አጥብቆ ተቈጣ እኔም በዚያ ወራት ስለ አሮን ጸለይኩ፤

፳፩፤ ወበእንተ ጌጋይክሙ ዘገበርክሙ ላሕመ ወነሣእክዎ ወቀጥቀጥክዎ ወሐረጽክዎ ጥቀ እስከ አድቀቅዎ በሕቁ ወኮነ ከመ ፀበል ወወደይክዎ ለውእቱ ሐሪጽ ውስተ ነቅዕ ዘይወርድ እምደብር፤

የላም ምስል ስለ ሠራችሁበት ኃጢአት ለመንሁ፤ ጣዖቱንም አንሥቼ ሰበርሁት ፈጽሜ እስካደቀውም ድረስ ፈጨሁት፤ እንደ ትቢያም ሆነ፤ ዱቄቱንም ከተራራው በሚወርደው ውሀ ጨመርሁት፤

፳፪፤ ወበኀበ ውዕየትኒ ወአመ መንሱትኒ ወበኀበ መቃብረ ፍትወትኒ አምዓዕክምዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ፤

(ወወረደት እሳት እምሰማይ ወበልዓት ፩ደ ኀብረ እም ሕዝብ እንዲል)፤ እሳት ከሰማይ ወርዳ ከእስራኤል አንዱን ወገን በበላችበት ወራት፤ ቸነፈርም አምጥቶ እናንተን ባጠፋበት ቦታ «መኑ እምአብልዓነ ሥጋ» ብላችሁ ሥጋ ተመኝታችሁ

www.ethiopianorthodox.org

በተቀበራችሁበት ቦታም ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን አሳዘናችሁት።

፳፫፤ ወአመሂ ፈነወክሙ እግዚአብሔር እምቃዴስ በርኔ ወይቤለክሙ ዕርጉ ወተዋረስዋ ለይእቲ ምድር ዘእሁበክሙ ክሕድክሙ ቃለ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወኢአመንክምዎ ወኢሰማዕክሙ ቃሎ፤

እግዚአብሔር ከቃዴስ በርኔ ተነሥታችሁ እንድትሄዱ ባደረጋችሁ ጊዜ የማወርሳችሁ ከነዓንን ወጥታችሁ ውረሷት ባላችሁም ጊዜ አንገባም ብላችሁ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ካዳችሁ እንጂ ቃሉን ሰምታችሁ አላመናችሁትም፤

፳፬፤ ወኮንክሙ ከሐድያነ እግዚአብሔር እምይእቲ ዕለት እንተ ተአምረ ለክሙ፤

ለእናንተ ከተገለጠባት ከዚያች ቀን ጀምሮ እግዚአብሔርን የምትክዱ ሆናችሁ፤

፳፭፤ ወሰአልኩ ለክሙ ቅድመ እግዚአብሔር ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ በከመ ሰአልኩ ቀዲሙ እስመ ይቤ እግዚአብሔር ከመ ያጥፍእክሙ፤

ያጠፋችሁ ዘንድ እግዚአብሔር ሳጥፋቸው ብሎ ተናግሯልና ከዚህ ቀድሞ እንደ ለመንሁ በእግዚአብሔር ፊት አርባ ቀን፣ አርባ ሌሊት ለመንሁላችሁ፤

፳፮፤ ወጸለይኩ ኀበ እግዚአብሔር ወእቤ እግዚኦ ወንጉሦ ለአማልክት ኢትሥርዎሙ ለሕዝብከ ወለመክፈልትከ ዘቤዘውከ በኃይልከ ዐቢይ ዘአውፃእከ እምድረ ግብጽ በዐቢይ ኃይልከ ወበእዴከ ጽንዕት ወበመዝራዕትከ ልዑል፤

የካህናት ንጉሣቸው ጌታቸው የምትሆን አቤቱ በገናና ኃይልህ ያዳንሃቸው፤ በብዙ ተአምራት በጽኑ ሥልጣን ከግብጽ ያወጣሃቸው፤ ዕድል ፈንታ ያደረግሃቸው ወገኖችህን አታጥፋቸው ብዩ ወደ እግዚአብሔር ማለድሁ፤ ለመንሁ፤

፳፯፤ ተዘከር አብርሃምሃ ወይስሐቅሃ ወያዕቆብሃ አግብርቲከ ዘመሐልከ ሎሙ በርእስከ ወኢትነጽር እከዮሙ ለእሉ ሕዝብከ ወአበሳሆሙ ወጌጋዮሙ፤

ለልጆቻችሁ ምድረ ርስትን አወርስላችኋለሁ ብለህ የማልህላቸው አገልጋዮችህ የሆኑ



አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብን አስብ እንጂ የሊህን የወገኖችህን በደላቸውንና ኃጢአታቸውን አታስብ፤

፳፰፤ ከመ ኢይበሉ እለ ይነብሩ ውስተ ምድር እለ እምነቤሆሙ አውፃእከነ እስመ ስእነ እግዚአብሔር አብእቶሙ ውስተ ምድር እንተ ይቤሎሙ ወእስመ ይጸልእሙ አውፅእሙ ከመ ይቅትሎሙ በገዳም፤

ከነሱ ለይተህ ያወጣኸን በግብጽ የሚኖሩ ሰዎች እግዚአብሔር አገባቸዋለሁ ወዳለበት ምድረ ርስት እነሱን ማግባት ተስኖታልና በዚያውም ላይ ጠልቷቸዋልና በምድረ በዳ ያጠፋቸው ዘንድ ከግብጽ አወጣቸው እንዳይሉ የወገኖችህን ፍጹም በደላቸውን አታስብ፤

፳፱፤ ወእሉሰ ሕዝብከ እሙንቱ ወርስትከ እለ አውፃእከ እምግብጽ በዐቢይ ኃይልከ ወበጽኑዕ ወልዑል መዝራዕትከ፤

እሊህስ በብዙ ተአምራት በገናና ሥልጣንህ ማለት በዘጠኝ መቅሠፍት በዓሥረኛ ሞተ በኵር በአሥራ አንደኛ ሥጥመት ጠላቶቻቸውን አጥፍተህ ከግብጽ ያወጣሃቸው ወገኖችህ ናቸው፤ እስራኤልን መክፈልተ ርስትከ በማለት ተናገረ፤ ሰው በርስቱ በዕድል ፈንታው አድሮበት እንዲኖር እግዚአብሔርም በእስራኤል አድሮባቸው ይኖራልና።

## ምዕራፍ ፲

፩፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር በውእቱ መዋዕል ቀር ለከ ክልኤ ጽላተ ዘዕብን ከመ እለ ቀዲሙ ወዕርግ ኀቤየ ውስተ ደብር ወግበር ታቦተ እምዕፅ፤

እግዚአብሔር በዚያ ወራት እንዲህ አለኝ እንደ ቀደመው አድርገህ ሁለት የዕንቍ ጽላት ቀርጸህ እኔ ወዳለሁበት ይዘህ ውጣ፤ የጽላቱንም ማኖሪያ ሣጥን ከማይነቅዝ እንጨት ሥራ፤

፪፤ ወእጽሕፍ ውስተ ውእቶን ጽላት ኵሎ ቃለ ዘሀለወ ውስተ እልክቱ ጽላት እለ ቀዲሙ ቀጥቀጥከ ወደዮን ውስተ ታቦት፤

ቀድሞ አንተ በሰበርኻቸው በሁለቱ ጽላት ተጽፎ የነበረውን ቃል ሁሉ ዛሬ በቀረጽሃቸው ጽላቶች እጽፍል

www.ethiopianorthodox.org

ሃለሁ፣ እነዚያንም ጽላቶች በሣጥኑ ውስጥ አኑራቸው አለኝ፤

፫፤ ወገበርኩ ታቦተ እምዕፀ ዘኢይነቅዝ ወወቀርኩ ክልኤ ጽላተ ዘዕብን ከመ እለ ቀዲሙ ወዓረጉ ውስተ ደብር ወውስተ እዴየ ውእቶን ክልኤሆን ጽላት፤

እኔም ከማይነቅዝ ሽምሸር ሰጢን ከሚባል እንጨት ታቦትን ሠራሁ፣ እንደ ቀደሙት ያሉ ሁለት የዕብነ በረድ ጽላት ቀርጬ ወደ ደብረ ሲና ወጣሁ፣ እነዚያም ጽላቶች በእጄ ተይዘው ነበር፤

፬፤ ወጸሐፈ ውስተ ውእቶን ጽላት ዘከመ ውእቶን ጽላት ዘቀዲሙ ዓሥሩ ቃላተ ዘነገረነ እግዚ አብሔር በደብረ ሲና በማዕከለ እሳት፣

በደብረ ሲና በእሳቱ መካከል ሁኖ እግዚአብሔር የነገረንን ዓሥሩን ቃላት እንደ ቀድሞው አጻጻፍ በግብር አምላካዊ በነዚህ በሁለቱ ጽላ ቶች ላይ ጻፈልኝ፤

፭፤ ወወደይክዎን ውስተ ታቦት ለውእቶን ጽላት ዘገበርኩ ወነበራ ህየ በከመ አዘዘኒ እግዚአብሔር፣

የቀረጽኋቸውን እነዚያንም ጽላቶች በሣጥኑ ውስጥ አኖርኋቸው፣ እግዚአብሔርም እንዳዘዘኝ በዚያ ኖሩ፤

፮፤ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል እምነ ቤሮሱ ዘደቂቀ ኢያቅም ዘማሰቤ ወበህየ ሞተ አሮን ወተቀብረ ወተ ሠይመ በህየ አልዓዛር ወልዱ ካህነ ህየንቴሁ፣

እስራኤልም የማሰቤ ወገን የሚሆኑ የዓርበኞች ልጆች ካሉበት ከቤሮሱ ተጓዙ፣ አሮንም ሙቶ በዚያ ተቀበረ፣ ልጁ ፡ልዓዛርም ስለሱ ፈንታ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ በዚያ ተሾመ፤

፯፤ ወእምህየ ግዕዙ ውስተ ገድገድ ወእምገድገድ ውስተ ኤጤቦታ ምድር ዘአንቅዕተ ማይ፤

ከዚያም ተነስተው ወደ ገድ ገድ ተጓዙ፣ ከገድገድም የውሀ ምንጭ ወዳለበት አገር ወደ ኤጤቦታ ተጓዙ፤

፰፤ ወበውእቱ መዋዕል ፈለጠሙ እግዚአብሔር ለነገደ ሌዊ ከመ ይፁሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወከመ ይቁሙ ቅድመ እግዚ አብሔር ወይግበሩ ወይጸልዩ በስመ ዚአሁ እስከ ዛቲ ዕለት፣



የእግዚአብሔር የሕጉ ማደ ሪያ ታቦትን ይሸከሙ ዘንድ በእግዚአብሔርም ፊት ቁመው ሥራቸውን ይሠሩ ዘንድ፤ ስሙንም ጠርተው እስከዚያች ቀን ይለምኑ ዘንድ በዚያ ወራት እግዚ አብሔር የሌዊን ወገኖች ለያቸው፣

፱፤ ወበበይነ ዝንቱ አልቦሙ ለሌ ዋውያን ክፍል ወርስት ምስለ አኃ ዊሆሙ እስመ እግዚአብሔር ውእቱ ክፍሎሙ በከመ ይቤሎሙ፣

አስቀድሞ እንደ ነገራቸው ዕድል ፈንታቸው እግዚ አብሔር ነውና ስለዚህ ለሌ ዋውያን ከወንድሞቻቸው ከእ ስራኤል ጋር ዕፃ ርስት የላ ቸውም፤

፲፤ ወአንሰ ቆምኩ ውስተ ደብር ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ ወሰምዓኒ እግዚአብሔር በውእቱ መዋዕል ወኀደገክሙ እግዚአብሔር ወኢ ያጥፍአክሙ፤

እኔ ግን አርባ ቀን አርባ ሌሊት በተራራ ላይ ቆምሁ፣ በዚያም ወራት እግዚአብሔር ልመናዬን ሰምቶ ይቅር አላ ችሁ እንጂ አላጠፋችሁም፤

፲፩፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ሑር ወንግር ቅድሜሆሙ ለእሉ ሕዝብ ይባኡ ወይትዋረሱ ምድረ ዘመ ሐልኩ ለአበዊሆሙ ከመ አሁቦሙ፣

እግዚአብሔርም እሰጣቸው ዘንድ ለአባቶቻቸው የማል ሁላቸውን አገር ከነዓንን ገብተው ይወርሱ ዘንድ ሂደህ በእሊህ ወገኖች ፊት ተናገር አለኝ፣

፲፪፤ ወይእዜኒ እስራኤል ምንተ ይፈቅድ እግዚአብሔር እምኔከ ዘእንበለ ከመ ትፍርሆ ወትሑር በኵሉ ፍናዊሁ ወከመ ታፍቅሮ ወታምልኮ በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ፣

አሁንስ እስራኤል እግዚ አብሔር ከአንተ ዘንድ ምን ይሻል ትፈራው ዘንድ፣ በሕጉ ሁሉ ጸንተህ ትወደው ዘንድ፣ በፍጹም ልቡናህ በፍጹም ሰው ነትህ ታመልከው ዘንድ ነው እንጂ፤

፲፫፤ ወትዕቀብ ትእዛዞ ወኵነኔሁ ኵሎ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ከመ ሠናይ ይኩንከ፣

በጎ ረድኤቱ ሊደረግልህ (ሠናየ) ቢል ረድኤቱ በጎ ሁኖ ሊደረግልህ እኔ ዛሬ

www.ethiopianorthodox.org

የማገዝዝህን ዘጠኙን ሕግጋት፤ ፳፻፫ ወነበቦን ትጠብቅ ዘንድ ነው እንጂ ካንተ ዘንድ ምን ይሻል፤

፲፬፤ ወናሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ ሰማይ ወሰማየ ሰማያት ወምድር ወኵሉ ዘውስቴታ፤

እነሆ (ሰማይ) ጠፈር ከጠፈር በላይ ያሉ ሰባቱ ሰማያት ምድርም በውስጧ ያለው ፍጥረት ሁሉ የፈጣሪህ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው፤

፲፭፤ ወዳዕሙ አበዊክሙ አብደረ ያፍቅሮሙ ወኀረየ ዘርኦሙ እምድኅሬሆሙ ኪያክሙ እምኵሉ አሕዛብ እስከ ዛቲ ዕለት፤

ሊወዳቸው አባቶቻችሁን ብቻ መረጠ፤ እስከዚች ቀን ድረስ ከአሕዛብ ሁሉ፤ ከነሳቸውም በኋላ እናንተን ልጆቻቸውን መረጠ፤

፲፮፤ ወግዝሩ እከዮ ልብክሙ ወኢትግዝሩ ክሣድክሙ እንከ፤

ይህንስ ትታችሁ የልቡናችሁን ክፋት ግዘሩ ማለት የልቡናችሁን ክሕደት ጥርጥር በሃይማኖት አርቁ፤ ክሣደ ልቡናችሁንም በኃጢአት አታጽኑ፤

፲፯፤ እስመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ውእቱ አምላክ አማልክት ወእግዚአ አጋእዝት ውእቱ እግዚአብሔር ዐቢይ ወጽኑዕ ወግሩም ዘኢያደሉ ለገጽ ወኢይነሥእሕልያነ፤

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር የካህናት ፈጣሪ ነውና፤ የጌቶችም ጌታ ነውና፤ እግዚአብሔር ገናና ከሃሊ የሚያስፈራ፤ እንደ ሰው ፊት አይቶ የማያደላ፤ መማለጃም የማይቀበል ነውና፤

፲፰፤ ወይገብር ፍትሐ ለግዩር ወለዕጓለ ማውታ ወለዕቤር ወያፈቅሮ ወይሁቦ ሲሳዮ ወአራዘ፤

ለስደተኛው፤ እናት አባቱ ለሞቱበት፤ ለባልቴቲቱም እውነት ይፈርዳል፤ ይህም ሲታወቅ ስደተኛውን ይወዳል፤ ምግቡንና ልብሱንም ይሰጠዋል፤

፲፱፤ ወአፍቅርዎ ለግዩር እስመ አንትሙኒ ግዩራነ ኮንክሙ በምድረ ግብጽ፤

እናንተም በግብጽ ሳላችሁ መጻተኞች (ስደተኞች) ነበራችሁና ስደተኛውን ውደዱት፤

፳፤ ለእግዚአብሔር አምላክከ ፍርሆ ወሎቱ ለባሕቲቱ አምልክ ወሎቱ ትልዎ ወበስመ ዚአሁ መሐል፤



ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ፍራው፤ እሱን ብቻ አምልከው፤ አምልኮተ ጣዖት ሳትቀላቅል በሕግ በአምልኮት እሱን ተከተል፤ ሌላ አትጨምር፤ የሱን ስም ጠርተህ ማል፤

፳፩፤ እስመ ውእቱ ትምህርትከ ወውእቱ አምላክከ ዘገብረ ለከ ዐቢያተ ወእላንተ ክቡራተ ዘርእየ አዕይንቲከ፤

መመኪያህ እሱ ነውና ዓይኖችህ ያዩዋቸውን የከበሩ ድጋግ ተአምራት ያደረገልህ ፈጣሪህ እሱ ነውና የሱን ስም ጠርተህማል፤

፳፪፤ ሰብዓ ነፍስ ወረዱ አበዊከ ውስተ ምድረ ግብጽ ወይእዜሰ ገብረከ እግዚአብሔር ከመ ከዋክብተ ሰማይ ብዙኀ፤

አባቶችህ ሰባ ሰው ሁነው ወደ ግብጽ አገር ወረዱ፤ ዛሬ ግን ፈጣሪህ እግዚአብሔር በቸርነቱ እንደ ሰማይ ኮከብ እንደ ባሕር አሸዋ ብዙ አደረገህ፤ አንድም በሰብዓ ነፍስ ወረዱ፤ አበዊከ ይላል፤ ጥንቱን አባቶችህ በሰባ ሰዎች ቁጥር ወደ ግብጽ ወረዱ፤ ወይእዜሰ ገብረከ ከመ ከዋክብተ ሰማይ በብዝኀ ይላል፤ ዛሬ ግን ፈጣሪህ እግዚአብሔር በብዛት እንደ ሰማይ ኮከብ እንደ ባሕር አሸዋ አደረገህ።

## ምዕራፍ ፲፩

፩፤ ወአፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወዕቀብ ሕጎ ወኵነኔሁ ወትእዛዞ ወፍትሖ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትከ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ውደደው፤ እሱንም ለመውደድህ ምልክቱ በኖርህበት ዘመን ሁሉ ሕጉን ትእዛዙን ዘጠኙን ሕገጋት ኢታምልክን ጠብቅ፤

፪፤ ወተአምሩ ዮም ከመ አኮ ደቂቅክሙ ዘርእዩ ወአእመሩ ተግሣፆ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወዕበያቲሁ ወእደ ጽንዕት ወመዝራዕት ልዑለ፤

የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን ምክር እዝናቱን ገናናነቱን፤ የጸናች ረቂቅ ሥልጣኑን ያዩ ያወቁ ልጆቻችሁ እንዳይደሉ ዕወቁ፤

፫፤ ወተአምሪሁ ወመድምሞ ወኵሎ ዘገብረ በማዕከለ ግብጽ ወበፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ወበኵሉ ምድሩ፤

በፈርዖንና በግብጻውያን በአገሩም ሁሉ ያደረገውን ተአምራቱን ድንቅ ሥራውን፤

www.ethiopianorthodox.org

፬፤ ወኵሎ ዘገብረ በኃይሎሙ ለግብጽ ወበሠረገላቲሆሙ ወበአፍራሲሆሙ፤

በግብጻውያንና በሠራዊቶቻቸው በሠረገላዎቻቸውና በፈረሶቻቸው ላይ ያደረገውን ሁሉ ያዩ ልጆቻችሁ እንዳይደሉ ዕወቁ፤

ዘከመ ከደኖሙ ማየ ባሕረ ኤርትራ ላዕለ ገጾሙ እንዘ ይዴግኑክሙ እሙንቱ እምድኅሬክሙ ወአጥፍኦሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ እስከ ዛቲ ዕለት፤

እነሱ በኋላችሁ ሲከተሏችሁ የኤርትራ ባሕር ፊታቸውን እንደ ሸፈናቸው ማለት እንደ አሠጠማቸው መጠን ያደረገውን ተአምራት ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርም እስከዚች ቀን ድረስ እንደ አጠፋቸው እወቁ፤

፭፤ ወኵሎ ዘገብረ ለክሙ በገዳም እስከ በጻሕክሙ ውስተ ዝንቱ መካን፤

ወደዚህ ቦታ እስክትደርሱ ድረስ በምድረ በዳ ያደረገላችሁን ሁሉ፤

፮፤ ወኵሎ ዘገብረ በዳታን ወበአቤሮን ደቂቀ ኤልያብ ወልደ ሮቤል እንተ ፈትሐት ምድር አፉሃ ወውኅጠቶሙ ወለአብያቲሆሙ ወለደባትሪሆሙ ወለኵሉ ንዋያቲሆሙ ዘምስሌሆሙ እማዕከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል፤

ምድር አፏን ከፍታ ባሠጠመቻቸው ወገኖቻቸውንና ድንኳናቸውን ከነሱ ጋር ያለ ገንዘባቸውንም ሁሉ ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይታ ባሠጠመችባቸው በሮቤል ልጅ በኤልያብ ልጆች በዳታንና በአቤሮን ያደረገውን ሁሉ እወቁ፤

፯፤ እስመ አዕይንቲክሙ ርእያ ኵሎ ግብረ ዐቢያተ ዘገብረ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር ያደረገውን ታላቅ ሥራ ሁሉ ዓይኖቻችሁ አይተዋልና፤

፰፤ ወዕቀቡ ኵሎ ትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም ከመ ትሕየዉ ወትትባዝኁ ወትባኡ ትትዋረሱ ምድረ እንተ ላቲ ተዓድዉ ዮርዳኖሰ ከመ ትትዋረስዋ በህየ፤

ከመከራው ትድኑ ዘንድ፤ የብዙ ብዙም ትሆኑ ዘንድ፤ በዚያም ልትወርሷት ዮርዳኖስን የምትሻገሩላት አገርን ገብታችሁ ትወርሱ ዘንድ እኔ ጠብቁ ብዬ የማዛችሁን ትእዛዙን ሁሉ ጠብቁ፤



፱፤ ወከመ ያኑኁ መዋዕሊክሙ በዲበ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊክሙ ከመ የሀቦሙ ወለዘርኦሙ እምድኅሬሆሙ ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ፤

አስቀድሞ ለነሱ ከነሱም በኋላ ለልጆቻቸው ይሰጣቸው ዘንድ እግዚአብሔር ለአባቶቻችሁ በማለላቸው ተድላ ደስታ በምታስገኝ አገር በከነዓን ዘመናችሁ ይበዛ ዘንድ ትእዛዙን ጠብቁ፤

፲፤ ወከመዝ ይእቲ ምድር እንተ ትበውእ ህየ ከመ ትትዋረሳ፤

ትወርሳት ዘንድ ወደሷ የምትገባበት አገርም እንዲህ ናት፤

አኮ ከመ ምድረ ግብጽ ይእቲ እንተ እምኔሃ ወፃእክ ሶበ ይዘርኡ ዘርዓ ይሰቅዩ በእገሪሆሙ ከመ ዐፀደ ሐምል፤

ከሷ እንደወጣህባት እንደ ግብጽ ምድር አይደለችም፤ እነሱ ዘር በዘሩ ጊዜ እንደ ተክል ቦታ በእግራቸው እየጫሩ ውሀን ያጠጡታል፤ አንድም እህሉን በእግር በእግሩ ያጠጡታል፤

፲፩፤ ወምድርሰ እንተ ህየ ትበውእ ከመ ትትዋረሳ ምድር ይእቲ እንተ ባቲ አድባር ወአምዳር ወእምዝናመ ሰማይ ትሰቲ ማየ፤

ትወርሳት ዘንድ የምትገባባት ምድር ግን ተራራና ሜዳ ቆላና ደጋ ያለባት ምድር ናት፤ ከሰማይ ከወረደውም ዝናም የምትጠጣ ናት፤

፲፪፤ ምድር እንተ ዘልፈ ይሐውጻ እግዚአብሔር አምላክከ ወአዕይንቲሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ ላዕሌሃ እምርእሰ ዓመት እስከ ማኅለቅተ ዓመት፤

ይችውም የምትወርሳት አገር ፈጣሪህ እግዚአብሔር በረድኤት የሚጎበኛት ናት፤ የፈጣሪህ የእግዚአብሔር ዓይኖቹም ከዘመን መባቻ ጀምሮ እስከ ዘመን መጨረሻ ድረስ ይመለከቷታል፤

፲፫፤ ወለእመሰ ሰሚዓ ሰማዕከ ኵሎ ትእዛዘ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ከመ ታፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወታምልኮ በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ትወደው ዘንድ በፍጹም ልቡናህ፤ በፍጹም ሰውነትህ ታመልከው ዘንድ እኔ ጠብቅ ብዬ የማዝዝህን ትእዛዝ ብትሰማ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፤ ይሁብ ዝናመ በበመዋዕሊሁ ላዕለ ምድርክሙ ዘነግህኒ ወዘሠርክኒ፤

በሀገራችሁ በየዘመኑ ጊዜ ማታ፤ አንድም በዘር ጊዜም፣ በመከር ጊዜም ዝናምን ይሰጣል፤

፲፭፤ ወአስተጋቢአከ እክለከ ወወይነከ ወቅብዓከ ይሁብ ሣዕረ ውስተ ገዳም ለእንስሳከ ወትበልዕ ወትጸግብ፤

ይህን ሁሉ አድርጎልህ እህልህን፣ ወይንህን፣ ዘይትህን ከሰበሰብህ በኋላ የለቀውን (የበልጉን) ዝናም ሰጥቶህ ለከብቶችህ በምድረ በዳ ሣሩን ያበቅላል፣ በልተህ ትጠግባለህ፤ አንድም ይሁብ ሣዕረ ውስተ ገዳም፣ ለአንተ የበልግ አዝመራ ይሰጥሀል፣ ‹ወለእንስሳከ› ለከብቶችህም ሣሩን ያበቅላል፣ ይህን ሁሉ አድርጎልህም ትጠግባለህ፤

፲፮፤ ወዑቁ ባሕቱ ኢታስብሑ ልበክሙ ወኢትክሀዱ ወኢትሑሩ ወኢታምልኩ ባዕዳነ አማልክተ ወኢትስግዱ ሎሙ፤

ነገር ግን ልቡናችሁን እንዳታጸኑ፣ እንዳትክዱ፣ ሂዳችሁም ልዩ የሆኑ ጣዖታትን እንዳታመልኩ፣ ለነሱም እንዳትሰግዱ ዕወቁ፤

፲፯፤ ወይትመዓዕ እግዚአብሔር ላዕሌክሙ መዓተ ወየዓፅዋ ለሰማይ ወኢያመጽእ ዝናመ ወምድርኒ ኢትሁብ ፍሬሃ ወትጠፍዑ ፍጡነ እምድር ቡርክት ዘወሀበክሙ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔርም በናንተ ተቆጥቶ ፈርዶ ሰማይን ይዘጋታል ማለት ሰማይ ዝናም ለዘር፣ ጠል ለመከር እንዳይሰጥ ምድርም የዘሩባትን እንዳታበቅል፣ የተከሉባትን እንዳታጸድቅ ያደርጋል፣ እግዚአብሔር ካወረሳችሁ ከከበረች አገርም ፈጥናችሁ ትጠፋላችሁ፤

፲፰፤ ወዕቀብዎ ለዝንቱ ነገር ውስተ ልብክሙ ወውስተ ነፍስክሙ ወረስይዎ ተአምረ ውስተ እዴክሙ ወይኩን ዘኢይትሐወስ እምቅድመ አዕይንቲክሙ፤

ይህን ነገር በልቡናችሁ በሰውነታችሁ አስተውሉት፣ በጣታችሁ እንደ ቀለበት አድርጉት፣ በፊታችሁም እንደ መስታዋት ይሁን ማለት በፊት ያለ እንዲታይ እንዲታሰብ



ሕጉንም በየጊዜው አስቡት ሲል ነው፤

፲፱፤ ወመሀርዎሙ ለደቂቅክሙ ከመ ይትናገሩ ቦቱ ለእመ ነበሩ ውስተ ቤት ወለእመኒ ሖሩ ውስተ ፍኖት ወሶበኒ ትሰክብ ወሶበኒ ትትነሣእ፣

በቤትም ቢቀመጡ፣ ወደ ጎዳናም ቢሄዱ ይህን ነገር ይነጋገሩት ዘንድ ለልጆቻችሁ አስተምሯቸው፣ በተኛህም ጊዜ፣ በተነሣህም ጊዜ ይህን ስልጆችህ አስተምራቸው ፤ አንድም አንተ ተኝተህም ተቀምጠህም ሕጉን አስበው፤

፳፤ ወጸሐፍዎ ውስተ መርፈቀ ኆኅተ ቤትክሙ፣

በቤታችሁም ደጃፍ መቃን መድረክ ጻፉት፤

፳፩፤ ከመ ይብዛህ መዋዕሊክሙ ወመዋዕለ ውሉድክሙ ውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊክሙ በአምጣነ መዋዕለ ሰማይ ውስተ ምድር፣

ይሰጣቸው ዘንድ እግዚአብሔር ለአባቶቻችሁ በማለላቸው አገር የልጆቻችሁና የናንተም ዘመን ጠፈር በአድማስ ላይ ጸንቶ የሚኖረውን ያህል ይበዛ ዘንድ በቤታችሁ መቃን መድረክ ጻፉት፤

፳፪፤ ወለእመ ሰሚዓ ሰማዕክሙ ኵሎ ትእዛዘ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም ከመ ትግበሩ ወታፈቅርዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወከመ ትሑሩ በኵሉ ፍናዊሁ ወከመ ትትልውዎ፣

ፈቃዱን ታደርጉ ዘንድ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን ትወዱት ዘንድ፣ በሕጉም ጸንታችሁ ትኖሩ ዘንድ፣ በሕግ በአምልኮት እሱን ትከተሉ ዘንድ ዛሬ እኔ የማዝዛችሁን ትእዛዙን ሁሉ ብትሰሙ፤

፳፫፤ ያወፅኦሙ እግዚአብሔር ለኵሉ አሕዛብ እምቅድመ ገጽክሙ ወትትዋረስዎሙ ለአሕዛብ ዐቢይት እለ ይጸንዑ ፈድፋደ እምኔክሙ፣

እግዚአብሔር አሕዛብን ሁሉ ከፊታችሁ አስወጥቶ ይሰዳቸዋል፣ ፈጽመው ከናንተ የሚበረቱ ታላላቅ አሕዛብን ትወርሷቸዋላችሁ(ትገዟቸዋላችሁ)፤

፳፬፤ ወኵሉ መካን ኀበ ኬደ መከየደ እገሪክሙ ለክሙ ውእቱ እምገዳም ወእምአንጢሊባኖን ወእምፈለግ ዐቢይ ፈለገ ኤፍራጥስ እስከ ባሕር እንተ መንገለ ዐረብ ይከውን ደወልክሙ፣

www.ethiopianorthodox.org

እግራችሁ የረገጠውን ቦታ ሁሉ ከምድረ በዳው ከአንጢሊባኖንና ከታላቁ ወንዝ ከኤፍራጥስ ጀምሮ በምዕራብ በኩል እስከአለው ባሕር ድረስ ለናንተ አውራጃ ይሆናል፤

፳፭፤ ወአልቦ መኑሂ ዘይትቃወም ቅድመ ገጽክሙ ወይወዲ እግዚአብሔር ፍርሃተክሙ ወርዕደተክሙ ላዕለ ኵሉ ገጸ ምድር እንተ ዓረግሙ ላዕሌሃ በከመ ይቤለክሙ እግዚአብሔር፣

ባጭር ታጥቆ ዘገር ነጥቆ ‹ነቅንቆ› እናንተን የሚቋቋ ምንም ማን የለም፣ እግዚአብሔር እንደነገራችሁ ልትወርሷት በሄዳችሁባት አገር ሁሉ ቀድሞ እናንተ ትፈሯቸው እንደነበረ ዛሬም እግዚአብሔር እነሱ እንዲፈሯችሁ ያደርጋል፤

፳፮፤ ወናሁ አነ አቀውም ዮም ቅድሜክሙ በረከተ ወመርገመ፣

እነሆ እኔ አሁን በረከትንና መርገምን በፊታችሁ አጸናለሁ፣ ሁለቱም አርእስት ነው ለሁለቱም ያመጣል፤

፳፯፤ በረከትሰ ለእመ ሰማዕክሙ ኵሎ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም፣

በረከት ያልሁት ዛሬ እኔ ጠብቁ ብዬ የማዝዛችሁ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ብትሰሙ ነው፤

፳፰፤ ወመርገምሰ ለእመ ኢሰማዕክሙ ኵሎ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም፣

መርገም ያልሁት ግን ዛሬ እኔ ጠብቁ ብዬ የማዝዛችሁ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባትሰሙ፤

ወኃደግምዎ ለፍኖት ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም ወሖርክሙ ወአምለክሙ ባዕዳነ አማልክተ ዘኢተአምሩ፣

ጠብቁ ብዬ ያዘዝኋችሁን ሕጉን ትታችሁ ሄዳችሁ የማታውቋቸው የአሕዛብን ጣዖታት ብታመልኩ ነው፤

፳፱፤ ወሶበ አብአከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ ምድር እንተ ላቲ ተዓዱ ዮርዳኖስ ከመ ትትዋረሳ በህየ ታገብእ በረከተ ላዕለ ደብረ ገሪዛን ወመርገመ ላዕለ ደብረ ጌባል፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ትወርሳት ዘንድ ዮርዳኖስን ወደም ትሻገርላት አገር ወደ ከነዓን



በገባህ ጊዜ በረከቱን በገሪዛን ተራራ ተናገሩት፣ መርገሙንም በጌባል ተራራ ተናገሩት፤

፴፤ ዘሀለዉ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ድኅረ ፍኖት ዘመንገለ ዐረበ ፀሐይ በምድረ ከነዓን እለ ሀለዉ ውስተ ዓረብ ወአንፃረ ጎልጎል ቅሩበ ዕፀት ነዋኅ፣

‹‹ዘሀለዉና እለ ሀለዉ አንድ ወገን›› እነዚህም ለረጅም ዛፍ አቅራቢያ በሆነ ሜዳ መያያገር በሆነ በፀሐይ መግቢያ በከነዓን ምድር ከመንገዱ አንፃር በዮርዳኖስ ማዶ ያሉ ናቸው፤

፴፩፣ ወናሁ ተዓድውዎ ለዮርዳኖስ አንትሙ ከመ ትባኡ ትትዋረስዋ ለምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ መክፈልተክሙ በኵሉ መዋል ዘትነብሩ ውስቴታ፣

በሷ በምትኖሩባት ዘመን ሁሉ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ዕድል ፈንታ አድርጎ የሚሰጣችሁን አገር ልትወርሷት ወደሷ ትገቡ ዘንድ እነሆ እናንተ ዮርዳኖስን ትሻገሩታላችሁ፤

፴፪፤ ወዕቀቡ ከመ ትግበሩ ኵሎ ትእዛዞ ወፍትሖ ዘአነ እሁበክሙ ቅድሜክሙ ዮም፣

ዛሬ እኔ በፊታችሁ የማስተምራችሁ አምልኮቱንና ዘጠኙን ሕግጋት ታደርጉ ዘንድ ሕጉን ጠብቁ አለ፣ ታገዙ የማይጠብቅ አለና።

## ምዕራፍ ፲፪

፩፤ ወዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወፍትሕ ዘተዓቅቡ ከመ ትግበሩ በምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ መክፈልተክሙ በኵሉ መዋዕል ዘተሐይዉ አንትሙ ላዕለ ምድር፣

እናንተ በምትኖሩበት አገር በዘመኑ ሁሉ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ዕድል ፈንታ አድርጎ በሚሰጣችሁ አገር ትሠሩት ዘንድ የምትጠብቁት ኢታምልክና ዘጠኙ ቃላት ይህ ነው፤

፪፤ ወደምስሶ ደምስስዎ ለኵሉ መካን ዘውስቴቱ አምለኩ አማልክቲሆሙ አሕዛብ ዘአንትሙ ትወርስዎሙ በዲበ አድባር ነዋኃት ወአውግር ወበታሕተ አዕዋም ዘቦቱ ቈጽል፣

እናንተ የምትወርሷቸው አሕዛብ ረጃጅም በሆኑ ተራሮችና ኮረብቶች ላይ ቅጠል ባላቸው ዛፎችም ሥር ጣዖታቱን ያመለኩበትን ቦታ ሁሉ ፈጽማችሁ አጥፉት፤

www.ethiopianorthodox.org

፫፡ ወንሥቱ ምሥዋዓቲሆሙ ወቀጥቅጡ ምስላቲሆሙ ወግዝሙ አዕዋማቲሆሙ ወአውዕዩ በእሳት ግልፎ አማልክቲሆሙ ወደምስሱ አስማቲሆሙ እምውእቱ መካን፡

መሠዊያቸውን አፍርሱ፤ ምስላቸውን ስበሩ፤ መስገጃቸውን ቁረጡ፤ እጅ እግር የተቀረጸላቸውን ጣዖታቱንም በእሳት አቃጥሉ፤ የሰዎቹን ስም፤ አንድም የጣዖቱን ስም ከዚያ ቦታ እልም ድርግም አድርጋችሁ አጥፉ፤

፬፤ ወኢትግበሩ ከመዝ ለእግዚ አብሔር አምላክክሙ በአሐቲ እምአህጉሪክሙ፡

ከአገሮቻችሁ በአንዲቱ አገር ለፈጣሪያችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ አታድርጉ፤

፭፤ ዘእንበለ ውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ፤

በዚያ ስሙ ይጠራ ዘንድ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ ነው እንጂ፤

፮፤ ወትወስዱ መሥዋዕቶክሙ ወቍርባነክሙ ወቀዳምያቲክሙ ወብፅዓቲክሙ ወዘበፈቃድክሙ ወዘዓሥራቲክሙ ወበኵረ አልሕምቲክሙ ወዘአባግዒክሙ፤

መሥዋዕታችሁንና ቍርባናችሁን፤ ስለታችሁንና የአዝመራችሁን መጀመሪያ ከዓሥር አንድ የምታወጡትንና በፈቃዳችሁ የምታወጡትን ከላሞቻችሁና ከበጎቻችሁም መጀመሪያ የተወለደውን ወደ ቤተ መቅደስ ውሰዱ እንጂ ወደ ቤተ ጣዖት አትውሰዱ፤

፯፤ ወብልዑ በህየ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወተፈሥሑ በኵሉ ዘወስቴቱ ወደይክሙ እዴክሙ አንትሙ ወቤትክሙኒ እስመ ባረከክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ፤

ይህንም ሁሉ በቅጽረ ቤተ እግዚአብሔር ሁናችሁ ብሉት፤ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር አክብሯችኋልና፤ እናንተና ወገኖቻችሁ እጃችሁን በጫናችሁበት ሁሉ ደስ ይበላችሁ ማለት ለእግዚአብሔር የምትሰጡትን ሁሉ ደስ እያላችሁ ስጡት፤

፰፤ ወኢትግበሩ ኵሎ ዘንሕነ ንገብር ዮም በዝየ አሐዱ አሐዱ ዘአደሞ በቅድሜሁ፤

አንዱም አንዱ በፊት የወደደውን ዛሬ እኛ የምናደርገውን ሁሉ በዚያ አታድርጉ፤



፱፤ እስመ ኢበጻሕክሙ እስከ ይእዜ ውስተ ምዕራፍክሙ ወውስተ ርስትክሙ ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ፤

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ወደሚያደርሳችሁ ወደርስታችሁና ወደማረፊያችሁ እስከ አሁንና አልደረሳችሁምና ዛሬ እንዲህ አታድርጉ ፤ (ሐተታ) በጉዞ ሳሉ ጥቂት ጥቂት ይሰጡ ነበር፤ ምድረ ርስትን ከወረሱ በኋላ ግን አብዝታችሁ ስጡ ሲል ነው፤

፲፤ ወዕድዉ ዮርዳኖስ ወንበሩ ውስተ ምድር ዘያወርሰክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወያዐርፈክሙ እምኵሉ ፀርክሙ እለ ዓውድክሙ ወትነብሩ ተአሚነክሙ፡

ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ሂዳችሁ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በሚያወርሳችሁ አገር ኑሩ፤ እሱም ቸር ነውና በዙሪያችሁ ካሉ ከጠላቶቻችሁ ሁሉ ያሳርፋችኋል፤ ከመከራውም ተዘልላችሁ ትኖራላችሁ፤

፲፩፤ ወይኩን ዝንቱ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክክሙ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ፡

ስሙ በዚያ ይጠራ ዘንድ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር የመረጠው ያ ቦታ የከበረ ይሁን ማለት መሥዋዕት የምትሠዉበት ይሁን፤

ወትወስዱ ኵሎ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም መሥዋዕቶክሙ ወቍርባነክሙ ወቀዳምያተ እደዊክሙ ወህብተክሙ ኅሩየ ወኵሎ መባዓክሙ ወኵሎ ዘበፃዕክሙ ለአምላክክሙ፤

እኔ ስጡ ብዬ ዛሬ የማገዛችሁን ሁሉ መሥዋዕታችሁንና ቍርባናችሁን፤ በእጃችሁ ያለ ቀዳምያቱን፤ የተመረጠ ስጦታችሁን፤ ወዳችሁ የምትሰጡትን ገንዘባችሁን፤ ለፈጣሪያችሁ የተሳላችሁትን ሁሉ ወደዚያ ውሰዱ፤

፲፪፤ ወተፈሥሑ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ አንትሙ ወደቂቅክሙ ወአዋልዲክሙ ወአግብርቲክሙ ወአእማቲክሙ ወሌዋውያን እለ ውስተ አንቀጽክሙ እስመ አልቦሙ ክፍል ወርስት ምስሌክሙ፤

እናንተ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም፤ ወንዶችና ሴቶች ባሮቻችሁም ደስ ይበላችሁ፤ ከናንተ ጋር ርስትና ዕድል ፈንታ የላቸውምና በዙሪያ

www.ethiopianorthodox.org

ችሁ ያሉ ሌዋውያንም ደስ ይበላቸው፣ ከዓመት ሦስት ጊዜ ለገቢረ በዓል ወጥታችሁ በደብተራ ኦሪት ደስ ይበላችሁ ሲል ነው፤

፲፫፤ ወዑቅ ርእሰከ ወኢትግበር መሥዋዕተከ በኵሉ መካን በነበ ዘርኢከ፣

ባየኸው ቦታ ሁሉ መሥዋዕት እንዳትሠዋ ለራስህ እወቅ፤

፲፬፤ ዘእንበለ በውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ በውስተ አሐዱ መካን እምሕዝብከ ህየ ትገብር ኵሎ መሥዋዕተከ ወኵሎ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም፣

‹‹በውስተ መካንና በውስተ አሐዱ መካን አንድ ወገን›› ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ከወገኖችህ ቦታ በአንዱ መሥዋዕቱን ሠዋ እንጂ፣ እኔ የማዝዝህንም ሁሉ በዚያ አድርግ እንጂ፤

፲፭፤ ወባሕቱ በኵሉ መካን ዘወሀበከ ትጠብሕ በህየ ወትበልዕ ሥጋ በከመ በረከቱ ለእግዚአብሔር እግዚእ ዘወሀበከ በኵሉ አህጉር ዘርኵስኒ ወዘንጹሕኒ ኅቡረ ብልዕዎ ከመ ወይጠል አው ከመ ኀየል፣

ነገር ግን ገኘር የሆነ እግዚአብሔር እንዳከበረህ መጠን በሰጠህ ቦታ ሁሉ አርደህ ሥጋውን በዚያ ብላ፣ የሚገባውንና የማይገባውን እንደ ፌቆ እንደ ዋሊያ ያለውን ሁሉ ባንድነት ብሉት፣ (ሐተታ) ዘርኵስኒ፣ ከክብቱ መሥዋዕት የማይሆነውን፣ ዘንጹሕኒ መሥዋዕት የሚሆነውን፤ አንድም ዘርኵስኒ አውሬውን፣ ወዘንጹሕኒ ላሙን ፍየሉን በጉን፤ አንድም ዘርኵስኒ ዕውሩን፣ አንካሳውን፣ ወዘንጹሕኒ ደኅነኛውን፣ አንድም ዘርኵስኒ ከበረህ ታድኖ የመጣውን፣ ወዘንጹሕኒ ከቤት የተገኘውን አንድ ሁናችሁ ብሉት፤

፲፮፤ ወባሕቱ ደሞ ኢትብልዑ ውስተ ምድር ከዓውዎ ከመ ማይ፣

ነገር ግን የነዚህን ሁሉ ደሙን እንደ ውሀ አፍሱት እንጂ አትብሉት፤

፲፯፤ ወኢትክል በሊያቶ በኵሉ አህጉሪከ ወዓሥራተ ወይንከ ወእክልከ ወቅብዕከ ወበኵረ አልሕምቲከ ወዘአባግዒከ ወኵሎ ብፅዓቲከ ዘበፃዕከ ወዘበፈቃድከ ወዘቀዳም ያተ እደዊከ፣



የእህልህንና የወይንህን የዘይትህንም ዐሥራት ከበጎችህና ከላሞችህም መጀመሪያ የተወለደውን በፈቃድህ የምታደርገውንና የተሳልኸውን ስለትህን ሁሉ በእጅህ ያለ የአዝመራህንም መጀመሪያ ባገርህ ሁሉ ‹በየቦታው› መብላት አትችልም፤

፲፰፤ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ብላዕ በውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ አንተ ወደቂቅከ ወወለትከ ወገብርከ ወአመትከ ወግዩር ዘውስተ ሀገርከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ በቤተ መቅደስ አጠገብ አንተ ብላ፣ ሴት ልጅህና ወንድ ልጅህም፣ ሴት ባሪያህና ወንድ ባሪያህ በሀገርህ የሚኖር ስደተኛም (መጻተኛ) በዚህ ይብሉት፤

ወትትፌሣሕ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ብላዕ ውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ዘወደይከ ውስቴቱ እዴከ፣

እጅህ በጨበጠው ገንዘብ ሁሉ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበልህ፤

፲፱፤ ወዑቅ ርእሰከ ኢትኅድጎ ለሌዋዊ በኵሉ መዋዕል ዘሕያው አንተ ላዕለ ምድር፣

አንተ በአገርህ በሕይወት በኖርህበት ዘመን ሁሉ ካህኑን እንዳትተወው ለራስህ እወቅ፤

፳፤ ወለእመኒ አርኅበ ለከ እግዚአብሔር ደወለከ በከመ ይቤለከ ወትቤ እበልዕ ሥጋ እምኵሉ ዘፈተወት ነፍስከ፣

ጠላትህን አጠፋልሃለሁ፣ አውራጃህን አሰፋልሃለሁ እንዳለህ እግዚአብሔር አውራጃህን ካሰፋልህ (ጠላትህን ካጠፋልህ)፣ ሥጋ እበላለሁ ብትል ሰውነትህ የወደደችውን ብላ፤

፳፩፤ ወለእመሰ ርኁቅ ውእቱ መካን ኀበ ኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ትጠብሕ እምኵሉ አልሕምቲከ ወአባግዒከ እምዘወሀበከ እግዚአ ብሔር አምላክከ በከመ አዘዝኩከ ወብላዕ በሀገርከ ዘፈተወት ነፍስከ ፣

ነገር ግን በዚያ ቦታ ስሙ ይጠራ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአ ብሔር የመረጠው ቦታ የራቀ ቢሆን፣ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሰጠህ ከበጎችህና ከላሞችህ አርደህ እንዳዘዝሁህ በአገርህ ሰውነትህ የወደደችውን ብላ፤

፳፪፤ ወበከመ ትበልዑ ወይጠለ አው ኀየለ ከማሁ ብልዑ ዘርኵስኒ ወዘንጹሕኒ፣

www.ethiopianorthodox.org

ፈቆን ዋሊያን እንደምትበሉ መጠን የሚገባውንና የማይገባውን እንደሱ ብሉት፣ (ሐተታ) እንዳለፈው፤

፳፫፤ ወተዐቀብ ጥቀ ከመ ኢትብላዕ ደመ እስመ ደሙ ነፍሱ ውእቱ ወኢትብልዐ ነፍሰ ምስለ ሥጋ አላ ውስተ ምድር ከዓውዎ ከመ ማይ፣

ደሙ ነፍሱ ነውና ብርንዶ እንዳትበላ ፈጽመህ ተጠበቅ፤ አንድም በቁሙ ደሙን አር ግተው ቀቅለው ቆልተው ይበ ሉታልና ያን እንዳትበላ ተጠ በቅ፤ ውሀን ወደመሬት እንዲ ያፈሱት ደሙን ወደ መሬት አፍስሱት እንጂ ደማዊት ነፍ ሱን ከሥጋው ጋራ አትብሉ፣ ደም ካለ ዘንድ ደማዊት ነፍስ አትለይምና፤

፳፬፤ ወኢትብልዖ ከመ ሠናይት ትኩንከ ወለውሉድከኒ እምድኅሬከ ለእመ ገበርከ ዘሠናይ ወዘአዳም ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ፣

በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ያማረውንና የተወደደውን ብታ ደርግ በጎ ረድኤቱ ትደረግ ልህ ዘንድ፤ አንድም ረድኤቱ በጎ ሁና ትደረግልህ ዘንድ፣ ካንተም በኋላ ለልጆችህ ትደ ረግላቸው ዘንድ ደሙን አት ብላው፤

፳፭፤ ወባሕቱ ዘረሰይከ ቅዱስ ወዘበባዕከ ንሣእ ወሑር ውስተ መካን ኀበ ኃረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስመ፡ዘበህየ፣

ነገር ግን ከከብት ይህ ለእግዚአብሔር ይሁን ብለህ የለየኸውንና የተሳልኸውን ይዘህ ስሙ በዚያ ይጠራ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ቦታ ሂድ፤

፳፮፤ ወትገብር ሥጋሁ መሥዋ ዕተ ወትወዲ ላዕለ ምሥዋዕ ወደሞሰ ትክዑ ኀበ መንበረ ምሥዋዕ ዘእግዚአብሔር አምላክከ ወብላዕ እምነ ሥጋሁ፣

ሥጋውንም መሥዋዕት አድ ርገህ በመሠዊያው ላይ አኑር፣ ደሙን ግን በፈጣሪህ በእግዚአብሔር መሠዊያ መቀመጫ ማለት በእግረ ምሥዋዑ አፍስሰው፣ ተረፈ መሥዋዕቱንም ብላው፤

፳፯፤ ወዕቀብ ወስማዕ ኵሎ ቃለ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ከመ ሠናይ ይኩንከ ወለውሉድከ ለዓለም ለእመ ገበርከ ዘሠናይ ወዘአዳም ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ፣



ሕጉን ጠብቅ በፈጣሪህ በእግ ዚአብሔር ፊት ያማረውንና የተወደደውን ብታደርግ በጎ ረዲኤቱ ለአንተም ለልጆ ችህም ይደረግ ዘንድ አሁን እኔ የማዝዝህን ቃሉን ስማ፤

፳፰፤ ወለእመኒ አጥፍኦሙ እግዚአብሔር አምላክከ ለአሕዛብ ዘአንተ ትበውእ ህየ ከመ ትትዋረሶሙ እምቅድመ ገጽከ ወትነብር ውስተ ምድሮሙ፣

ትወርሳቸው ዘንድ አንተ ወደ ዚያ የምትገባባቸው አሕዛብን ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከፊ ትህ ባጠፋቸው ጊዜ፣ በሀገራ ቸውም በኖርህ ጊዜ፤

፳፱፤ ዐቅ ርእሰከ ኢትፍቅድ ተሊዎቶሙ እምድኅረ ተሠረዉ እምቅድመ ገጽከ ወኢትፍቅድ አማ ልክቲሆሙ ወኢትበል ከመ ዘይ ገብሩ አሕዛብ ለአማልክቲሆሙ እገብር አነኒ፣

ለራስህ እወቅ፣ አሕዛብ ከፊትህ ከጠፉ በኋላ እነሱን በግብር መከተልን አትው ደድ፣ ጣዖቶቻቸውን አታም ልክ፣ አሕዛብ ለጣዖታቱ ልጆ ቻቸውን ይሠዉ እንደነበር እኔም ልጄን ለጣኦት እሠዋ ለሁ አትበል፤

፴፤ ወኢትግበር ከማሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ እስመ ጸልአ እግዚአብሔር ርኵሰ ዘይገብሩ አሕዛብ ለአማልክቲሆሙ እስመ ደቂቆሙ ወአዋልዲሆሙ ያውዕዩ በእሳት ለአማልክቲሆሙ፣

ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻ ቸውን ለጣዖቶቻቸው በእሳት የሚያቃጥሉ ስለሆነ እግዚአ ብሔር አሕዛብ ለጣዖታቱ የሚያደርጉትን ኃጢአት ጠል ቷልና ለፈጣሪህ ለእግዚአብ ሔር ግን እንዲህ አታድርግ፤

፴፩፤ ወኵሎ ቃለ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ኪያሁ ዕቀብ ለገቢር ኢት ወስክ ላዕሌሁ ወኢታንኪ እምኔሁ፣

እሱን ለማድረግ ዛሬ እኔ የማዝዝህን ቃል ሁሉ ጠብቅ እንጂ በሱ ላይ አትጨምር ከሱም አታጉድል፡፡

## ምዕራፍ ፲፫

### ጉባኤ

፩፤ ወለእመኒ ተንሥአ እምኔከ ነቢይ አው ሐላሜ ሕልም ወወሀበከ ተአምረ አው መድምመ፣

ከአንተ ወገን ነቢየ ሐሰት ወይም የሐሰት ሕልም አለምሁ የሚል ቢነሣ እሱም

www.ethiopianorthodox.org

በምታት ምልክት ቢያሳይህ ወይም ድንቅ ነገር ቢያደር ግልህ፤

፪፤ ወበጽሐ ተአምሪሁ አው መድምሙ ዘይቤለከ እንዘ ይብል ነዓ ንሑር ወናምልክ ለአማልክተ ባዕድ ዘኢተአምር፤

የነገረህ ምልክቱ ድንቅ ሥራ ውም ቢደርስ ና ሂደን የማ ታውቃቸውን ጣዖታት እና ምልክ ቢልህ፤

፫፤ ኢትስማዕ ቃሎ ለውእቱ ነቢይ አው ለውእቱ ሐላሚ ሕልም እስመ ያሜክረክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ከመ ይርአይ ለእመ ታፈቅርዎ እምኵሉ ልብክሙ ወእምኵሉ ነፍስክሙ፤

በፍጹም ልቡናችሁ በፍጹም ሰውነታችሁ ትወዱት እንደ ሆነ ያይ ዘንድ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ይፈታተናችኋ ልና ሐሰተኛ ሕልምን አለ ምሁ አለምሁ የሚል የዚያን የነቢዩ ሐሰት ቃል አትስማ፤

፬፤ ወትልውዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወኪያሁ ፍርሁ ወትእዛዞ ዕቀቡ ወቃሎ ስምዑ ወነቢሁ ተማኅፀኑ፤

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮት ተከተሉት፤

እሱንም ፍሩት፤ ሕጉን ጠብቁ፤ ቃሉንም ስሙ፤ በሱም አም ናችሁ ጸንታችሁ ኑሩ፤ አን ድም እንደ አደራ ከብት በሱ ሥልጣን ተጠብቃችሁ ኑሩ፤

፭፤ ወዝኩቱሰ ነቢይ አው ሐላሚ ሕልም ለይሙት እስመ ነገረከ በዘ ያስሕተከ እምእግዚአብሔር አምላ ክከ ዘአውፅአከ እምድረ ግብጽ ወቤ ዘወከ እምቅንየት፤

ከፈርዖን አገዛዝ ካዳነህ ከግ ብጽ አገር ካወጣህ ከፈጣሪህ ከእግዚአብሔር በሚለይህ ገን ዘብ ይለይህ ዘንድ ሐሰት ነገ ርን ነግሮሃልና ያ ነቢዩ ሐሰት ወይም ሐሰት ሕል ምን አለምሁ አለምሁ የሚል ያ ሰው ይሙት፤

እስመ ፈቀደ ያኅድግ ፍኖተ ዘአዘዘከ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትሑር ባቲ ወታሴስል ወታማስን እኩየ እምኔከ፤

በሷ ጸንተህ ትኖር ዘንድ ክፉ ውን ነገር ሁሉ ከአንተ ልታርቅበት ፈጣሪህ እግዚአ ብሔር ጠብቅ ብሎ ያዘዘህን ሕግ ሊያስተውህ ወዷልና ያ ሰው ይሙት፤



፮፤ ወለእመኒ አስተብቍዓከ እኁከ ዘእምአቡከ አው ዘእምእምከ አው ወልድከ አው ወለትከ አው ብእ ሲትከ እንተ ውስተ ሕፅንከ አው ዐርክከ ዘከመ ነፍስከ፤

ከአባትህ ወይም ከናትህ የተወለደ ወንድምህ ጣዖት እናምልክ ብሎ ቢማልድህ ወይም ወንድ ልጅህና ሴት ልጅህ ወይም ከአንተ ጋር የምትኖር ሚስትህ ወይም እንደ ራስህ አድርገህ የም ትወደው ወዳጅህ ጣዖት እና ምልክ ብሎ ቢማልድህ፤

ወይቤለከ በጽሚት ነዓ ንሑር ወናምልክ ባዕዳነ አማልክተ ዘኢተአምር አንተ ወአበዊከ፤

አባቶችህና አንተ የማታው ቁትን ጣዖት እናምልክ ብሎ በቆይታ (በስውር) ቢለምንህ፤

፯፤ እምአማልክተ አሕዛብ እለ ዓውድክሙ ወእለ ቅሩብክሙ አው እለ ርኁቃን እምኔክሙ እም አጽናፈ ምድር እስከ አጽናፈ ምድር፤

በዙሪያችሁ ባጠገባችሁ ካሉ ከምድር ዳርቻ እስከ ምድር ዳርቻ ከናንተ ከራቁ ከአሕዛብ ያሉ ጣዖታትን በማምለክ፤

፰፤ ኢትኅበር ምስሌሁ ወኢት ስምዖ ወኢትምሐኮ ዓይንከ ወኢት ሠውሮ፤

ከሱ ጋራ አንድ አትሁን፤ ነገሩንም አትቀበለው፤ ዓይን ህም አትራራለት፤ የሠራው ንም ኃጢአት አትሠውርለት፤

፱፤ አይድዕ ወንግር በእንቲአሁ ወእዴከ ይቅድማ ቀቲሎቶ ወእምዝ ዕደው ኵሉ ሕዝብ ይውግሩሁ በአዕባን ወይቅትልዎ፤

የሱን ነገር ፈጽመህ ገልጠህ ተናገር፤ ኃጢአቱን ስለ አወቅህበት እጅህ አስቀ ድመው ደንጊያ ይጣሉበት፤ ከዚያ በኋላ ሕዝቡ ሁሉ በደ ንጊያ ወግረው በእሳት አቃጥ ለው ይግደሉት፤

፲፤ እስመ ፈቀደ ያርኅቀ እምእግዚአብሔር አምላክከ ዘአው ፅአከ እምድረ ግብጽ ወእምቤተ ቅንየት፤

ከፈርዖን አገዛዝ ከግብጽ አገር ካወጣህ ከፈጣሪህ ከእግ ዚአብሔር በሕግ በአምልኮት ሊለይህ ወዷልና፤

፲፩፤ ወኵሉ እስራኤል ሰሚዖ ይፍራህ ወኢይድግም እንከ ገቢረ እኩይ ውስቴትክሙ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስራኤልም ሁሉ ይህን ነገር ሰምቶ ይፍራ፣ በናንተ ዘንድም ክፉውን ነገር ዳግመኛ አያድርግ፣ በስሕተት የሚሠራ ሥራ አለና ኢይድግም አለ፤

፲፪፤ ወለእመ ሰማዕከ በውስተ አሐቲ እምአህጉሪከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትንበር ህየ እንዘ ይብሉ ወፅኡ ዕደው ኃጥአን እምኔነ፣

በዚያ ልትኖር ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሰጠህ አገሮች በአንዲቱ አገር ከኛ ተለይ ተው ክፉ ሰዎች ወጡ ማለት ሰውን ለማሳት ተነሡ፤

፲፫፤ ወአክሐድክዎሙ ለኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ አህጉሪሆሙ ወይቤልዎሙ ንዑ ንሑር ወናምልክ ባዕዳነ አማልክተ ዘኢተአምሩ ትሴአል ወተሐትት ጥቀ፣

ኑ ሂደን የማታውቋቸውን ሌሎች አማልክትን እናምልክ ብለው በሀገራቸው የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ አስካዷቸው ሲሉ ብትሰማ ጠይቅ፣ ፈጽመህም መርምር፤

፲፬፤ ወእምከመ እሙነ ወጥዩቀ ኮነ ነገሩ ከመ ኮነ ርኵስ ውስቴትክሙ፣

በናንተ ዘንድ ኃጢአት እንደ ሆነ ነገሩ የታመነ የተረዳ ከሆነ፤

፲፭፤ ቀቲለ ትቀትል በሐፂን ኵሎ እለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ ሀገር ወረጊመ ትረግም ኵሎ ዘሀለወ ውስቴታ ወኵሎ ንዋያ ታስተጋብዕ ማዕከለ መርሕባ ወታውዒ በእሳት፣

በዚች አገር የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ በጦር ግደል፣ በሷም ያለውን ሁሉ እርገም፣ ገንዘቧን ሁሉ ሰብስበህ በአደ ባባይዋ መካከል በእሳት አቃጥለው፤

፲፮፤ ወሀገራኒ ምስለ ኵሉ ንዋያ ወለኵሉ ሀገር ከማሁ ትገብራ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ወአልቦ ዘይነብር ውስቴታ ለዓለም ወኢይትነደቅ፣

አገሯንም ከገንዘቧ ሁሉ ጋራ ከሷ ጋር በክፋት የተባበረውን ሌላውንም አገር ሁሉ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት እንደሷ አድርገህ አጥፋ፣ ለዘለዓለሙ የሚኖርባት አይኑር፣ ያችም አገር ዳግመኛ አትሠራ አትቅና፤



፲፯፤ ወኢትግሥሥ በእዴከ ምንተኒ ዘርጉም እምዘውስቴታ ከመ ይሚጥ እግዚአብሔር መዓቶ ወየሀብከ ምሕረቶ ወይምሕርከ ወያስተባዝኀከ በከመ መሐለ ለአበዊከ፣

እግዚአብሔር ቍጣውን መልሶ ይቅርታውን ይሰጥህ ዘንድ፣ ይቅርም ይልህ ዘንድ ለአባ ቶችህም እንደማለ ያበዛኅ ዘንድ በሷ ካለው የተረገመ ውን ምንም በእጅህ አትንካ፤

፲፰፤ ወለእመ ሰሚዐ ሰማዕከ ቃሎ ወዐቀብከ ኵሎ ትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ወገበርከ ዘሠናይ ወዘአዳም ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ወልደ ትከውን ሎቱ፣

ቃሉን ከሰማህ፣ እኔ አሁን የማዝዝህን ትእዛዙን ሁሉ ከጠበቅህ፣ በፈጣሪህ በእግዚአ ብሔር ፊት ያማረውንና የተወደደውን ካደረግህ የሱ ልጅ ትሆናለህ።

## ምዕራፍ ፲፬

፩፤ ወኢትትላጸይ ርእሰከ ለዘሞተ እስመ ሕዝብ ቅዱስ አንተ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወኪያከ ኀረየ ከመ ትኩኖ ሕዝበ ለርእሱ እምኵሉ አሕዛብ ዘውስተ ገጸ ምድር፣

ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር አንተ ልዩ ወገኑ ነህና ለሱም ወገን ትሆነው ዘንድ በዚህ ዓለም ካሉ አሕዛብ ሁሉ አንተን መርጧልና ለሞተ ሰው ራስህን አትላጭ፤

፪፤ ወኢትብልዐ ዘንተ ኵሎ ርኵሰ፣

የማይገባውን ሁሉ አትብላ፣

፫፤ ወዝንቱ ውእቱ ዘትበልዐ እምእንስሳ ላሕም ወበግዕ ወጠሊ፣

ከእንስሳ ወገን የምትበሉት ይህ ነው፣ ላም በግ ፍየል ነው፤

፬፤ ወኀየል ወወይጠል ወቶራ ወደ ስከን ወውዕላ ወአሪጋ ወዛራት፣

ፈቆና ዋሊያ፣ ቶራ በቁሙ፣ አንድም አጋዘን (ደስከን)፣ ዲፋሳ ውዕላ ቡኽር (አሪጋ) ሰሳ፤ አንድም ጅራተ ቀጭኔ (ዛራት) ሚዳቋ፤

፭፤ ወኵሉ እንስሳ ዘንፉቅ ሰኰናሁ ወንፉቅ ጽፈሪሁ ወክልዔቱ ጽፈሪሁ ወያመስኵዕ ዝንቱ ዘትበልዐ እምእንስሳ ፣

www.ethiopianorthodox.org

ሰኰናው የተለየ ጥፍሩ የተሰነጠቀ ጥፍሩ ሁለት የሆነ ውን የሚያመሰኳውን እን ስሳ ሁሉ ከእንስሳ የምት በሉት ይህ ነው፤

፯፤ ወዝንቱ ዘኢትበልዑ እምዘ ያመስኩዕ ወዘንፉቅ ስኰናሁ ወዘኩፉል ጽፌሪሁ ገመል ወዳስጲዳ እስመ ያመስኩዑ ወኢኮነ ንፉቀ ሰኰናሆሙ ወርኩሳን እሙንቱ ለክሙ፣

ከሚያመሰኳው ሰኰናው ከተ ለየው ጥፍሩ ከተሰነጠቀው የማትበሉት ይህ ነው፣ ግመል፣ ጥንቸል ያመሰኳ ሉና፣ ሰኰናቸውም አልተለየ ምና እነዚህ ለናንተ የረከሱ ናቸው፤

፯፤ ወኪሮግልዮስኒ ወሐራውያ እስመ ንፉቅ ሰኰናሆሙ ወኢያ መስኩዑ ርኩሳን እሙንቱ ለክሙ፣

እሪያና አሳማ ሰኰናቸው የተለየ ነውና፣ አያመሰኩምና እነሱም ለናንተ የረከሱ ናቸው፤

፰፤ ወገዐብኒ እስመ ንፉቅ ሰኰናሁ ወክፉል ጽፌሪሁ ወኢያመስኩዕ ርኩሳን እሙንቱ ለክሙ እምነ ሥጋሆሙ ኢት ብልዑ ወበድኖሙ ኢትግሥሡ፣

ጅብም ሰኰናው ከሁለት የተለየ ነውና ጥፍሩም የተሰ ነጠቀ ነውና፣ ነገር ግን አያመስኳምና እነዚህ ሁሉ ለናንተ የረከሱ ናቸው፣ ሥጋ ቸውን አትብሉ፣ ወደቃቸ ውንም አትንኩ፤

፱፤ ወገወእቱ ዘትበልዑ እምእ ንስሳ ወዘኢትበልዑ እምእንስሳ ወገ ዘትበልዑ ዘእምውስተ ማይ ኵሉ ዘቦ ክንፍ ወቅሣር ብልዑ፣

ከእንስሳ ወገን የምትበሉትና የማትበሉት ይህ ነው፤ በውሀ ውስጥ ካለውም የምትበሉት ይህ ነው፣ ክንፍ ማጉርጥ (ገለፈት) ያለውን ሁሉ ብሉ፤

፲፤ ወኵሉ ዘአልቦ ክንፍ ወቅሣር ኢትብልዑ ርኩስ ውእቱ ዝንቱ ለክሙ፣

ክንፍ ማጉርጥ የሌለውን ሁሉ አትብሉ፣ ይህ ለናንተ የረከሰ ነውና፣

፲፩፤ ወኵሉ ዖፈ ንጹሐ ብልዑ፣

ንጹሕ የሆነውን ወፍ ሁሉ ግን ብሉ፤

፲፪፤ ወዝንቱ ዘኢትበልዑ እምኔ ሆሙ ንስር ወጊጳ ወአልያጦን ወግሪጳ ወሆባይ ወዘአምሳሊሁ፣



ከአዕዋፍ ወገን የማትበሉት ይህ ነው፤ ንስር አሞራ (ጊጳ) አገዳ ሰበር፣ ወአልያጦን) እባብ፣ ዋጭ፣ አሞራ ወግሪጳ፣ ዘማች አሞራ፣ ወሆባይ፣ አን ጭት አሞራ ይህን የመሰ ለውን ሁሉ ነው፤

፲፫፤ ወቋዕ ወዘአምሳሊሁ፣

ቁራ እሱን የመሰለውን ሁሉ ነው፤

፲፬፤ ወሰገኖ ወገላውቃ ወሰሮን ወአሮድዮን ወቀቀኖ ወኢብን ወቅጥራቅጥሬን ወጉዛ ወዘአም ሳሊሁ፣

ሰገኖ፣ ሰጎን፣ ገላውቃ አራት ራስ አሞራ፣ ሰሮን ይብራ፣ አሮድዮን ዖፊ ያሬድ (ቀቀኖ) እርኩም ፣ (ኢብን) የመስቀል ዖፍ (ሳቢሳ) ቅጥሪቅጥሬን ድንቢጥ፣ ጉዛ ጭላት፣ ይህን የመሰለውን ሁሉ ነው፤

፲፭፤ ወሄጳጳ ወጕጋ፣

ታላቅ አሞራ ጉጉት፤

፲፮፤ ወአባጕንባሕ ወከራድዮን ወዘአምሳሊሁ፣

እርኩም ነጭ ወፍ የሚመስ ለውም ሁሉ ነው፤

፲፯፤ ወጵርፍርዮን ወጽግንት፣

ሳቢሳ፤ አንድም ፍላፀት፣ ወጽግንት፣ የሌት ወፍ ነው፤

፲፰፤ ወእሉ ኵሎሙ አዕዋፍ ርኩሳን እሙንቱ ለክሙ ወኢት ብልዑ እምኔሆሙ፣

ሲናገረው የመጣው ነው፣ እነ ዚህ አዕዋፍ ሁሉ የረከሱ ናቸውና ከነሱ አትብሉ፤

፲፱፤ ወእምኵሉ አዕዋፍ ዘንጹሕ ብልዑ፣

ንጹሐን ከሆኑ አዕዋፍ ወገን ግን ብሉ፤

፳፤ ወኵሉ ማውታ ኢትብልዑ ለፈላሲ ዘውስተ ሀገርክሙ አው ለባዕድ ሁብዎሙ ይብልዑ፣

ሙቶ ያደረውን (በክቱን) አትብሉ፣ ይበሉ ዘንድ ባገ ራችሁ ላለ ስደተኛ ለሌላ ወገንም ስጧቸው እንጂ፤

፳፩፤ እስመ ሕዝብ ቅዱስ አንተ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወኢታብ ስል መሐሥዐ በሐሊበ እሙ፣

አንተ ለፈጣሪህ ለእግዚ አብሔር የተለየህ ወገን ነህና ጠቦቱን በናቱ ወተት በናቱ ቅቤ አትቀቅለው ፤ አንድም

www.ethiopianorthodox.org

ጥጃውን (ግልገሉን) የናቱን ጡት እየጠባ ሳለ አትረደው አለ ርኅራኄ ነው፤ አንድም ለቤተ እግዚአብሔር የምትሰጠው ከብት ሲጠባ አይቆይ፣ ሹም አይቶት ይደግ ሲል ነው፤

፳፪፤ ዓሥራተ ትዔሥር እምኵሉ እክልከ ዘዘራእከ ዘታዓቱ እም ውስተ ገራውሂከ በበዓመቱ፣

በየዓመቱ በርሻህ ከምትዘራው ከምታገባው አዝመራህ ዐሥራት አውጣ፤ አንድም በርሻህ ዘርተህ ከምታገባው እህልህ ባመት ባመት ዐሥራት አውጣ፤

፳፫፤ ወብልዖ በበዓመት በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ በመካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ፣

ስሙ በዚያ ይጠራ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ባመት ባመት ብላው፣

ወታበውእ ዓሥራቲሁ ለእክልከ ወለወይንከ ወለቅብዕከ ወለበኵረ አልሕምቲከ ወአባግዒከ ከመ ትትመሀር ፈሪሆቶ ለእግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ መዋዕል፣

በዘመኑ ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን መፍራትን ትማር ዘንድ የእህልህን፣ የወይንህንና የዘይትህን ዓሥራት ከላሞችህና ከበጎችህም መጀመሪያ የተወለደውን አግባ (ስጥ)፤

፳፬፤ ወለእመሰ ርሑቅ ውእቱ እምኔከ ፍኖቱ ወኢትክል ወሲደ እስመ ውእቱ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ እስመ ባረከከ እግዚአብሔር አምላክከ፣

ነገር ግን ጎዳናው ካንተ የራቀ ቢሆን በዚያ ስሙ ይጠራ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር የመረጠው ቦታ የራቀ ነውና መውሰድ ባይቻልህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ስለባረከህ፤

፳፭፤ ወትሬስዮ ለብሩር ወትነሥእ ብሩር በእዴከ ወተሐውር ኀበ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ፣

እህሉን ሉብር (በብር አቅንተህ) ብሩን በእጅህ ይዘህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ቦታ ሂድ፤

፳፮፤ ወትሁብ ብሩረ ለኵሉ ዘፈተወት ነፍስከ አው ለላሕም አው ለበግዕ አው ለወይን አው



ለሜስ አው ለኵሉ ዘፈተወት ነፍስከ፣

ወይን ሜስ አንድ ወገን ነው፣ ብሩንም ወስደህ ላም ወይም በግ ወይም ወይንና ጠጅ ሰውነትህ የወደደችውን ሁሉ ግዛ፤

ወብላዕ በህየ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ወተፈሣሕ አንተ ወቤትከ፣

ይህን በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት በልተህ አንተም ወገኖችህም ደስ ይበላችሁ፤

፳፯፤ ወለሌዋዊ ዘውስተ ሀገርከ ኢትኅድጎ እስመ አልቦቱ ርስት ወክፍል ምስሌከ፣

ካንተ ጋር ርስት ዕድል ፈንታ የለውምና ባገርህ ያለ ካህኑንም አትተወው ማለት አብረህ አብላው፤

፳፰፤ ወበሣልስ ዓም ታብውእ ኵሎ ዓሥራተ እክልከ ወዘዓመታቲሁሰ ታነብር ውስተ ቤትከ፣

በሦስተኛው ዓመት የእህልህን ሁሉ ዓሥራት አውጥተህ ያንዱን ዓመት እህል በቤትህ አኑረው፤

፳፱፤ ወእምዝ ይመጽእ ምስሌከ ሌዋዊ እስመ አልቦቱ ርስት ወክፍል ምስሌከ፣

ካንተ ጋር ዕድል ፈንታ ርስት የለውምና ከዚህ በኋላ ካህኑ ከአንተ ጋር ይምጣ፤

ወግዩር ወእጓለማውታ ወዕቤር ዘውስተ ሀገርከ ይብልዑ ከመ ይባርከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ግብርከ ዘገበርከ፣

ባደረግኸው ሥራ ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያከብርህ ዘንድ እናት አባቱ የሞቱበት ልጅና ስደተኛ በሀገርህ ያለች ባልቴትም ይብሉት ።

## ምዕራፍ ፲፭

፩፤ ወበሳብዕ ዓም ትገብር ኅድገተ፣

በሰባተኛው ዓመት ዕረፍትን አድርግ አለ፣ ዓመተ ኅድገት ነው፤

፪፤ ወከመዝ ውእቱ ትእዛዙ ለኅድገት ዘይትኃደግ ኵሎ ንዋየከ ዘይፈድየከ ካልእከ ወእኁከ ኢትትፈደይ እስመ ኅድገተ ተሰምየት ለእግዚአብሔር አምላክከ፣

የሚደረግ የዕረፍት ሥራትም እንዲህ ነው፣ ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ዕረፍትን ተብላለችና ባልንጀራህ ወንድምህ የሚከፍልህን ገንዘብ ሁሉ አትከፈል፤

www.ethiopianorthodox.org

፫፡ ወዘንበ ነኪርሰ ትትፌደይ ኵሎ ዘብከ ኀቤሁ ወዘንበ እኁከሰ ኅድገት ትገብር ኵሎ ዘይፈድየከ፡

ከአሕዛብ ዘንድ ያለ ገንዘብህን ሁሉ ተቀበል ወንድምህ የሚ ከፍልህን በወንድምህ ዘንድ ያለውን ገንዘብ ግን ተው ለት፤

፬፡ እስመ አልቦ ነዳይ እምኔከ እስመ ባርኮ ይባርከከ እግዚ አብሔር አምላክከ በውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ርስተ ዘትወርስ፡

ርስት አድርገህ በምትወር ሳት አገር ፈጣሪህ እግዚአብ ሔር በሚሰጥህ በዚች በከነ ዓን አገር ፈጣሪህ እግዚአብ ሔር ፈጽሞ የሚያከብርህ ስለሆነ ካንተ ወገን ድኃ የለምና፤

፭፡ ወለእመ ሰሚዐ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ወዐቀብከ ወገበርከ ዘንተ ኵሎ ትእዛዘ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም፡

የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ፣ ሕጉንም ብት ጠብቅ እኔ አሁን የማዝዝ ህን ይህንን ትእዛዙን ሁሉ ብታደርግ፤

፮፡ እስመ ባረከከ እግዚአብሔር አምላክከ በከመ ይቤለከ ወትለቅሖ ለባዕዳን አሕዛብ ብዙኃን ወአንተሰ ኢትትለቃሕ ወትኴንኖሙ ለአሕ ዛብ ብዙኃን አንተ ወለከሰ ኢይኴንኑከ፡

በሁሉ አከብርሃለሁ እንዳለህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሀ ብት በንብረት ስለአከበረህ ብዙ ስለሆነ ለሌሎች አሕዛብ ሁሉ ታበድራለህ፣ አንተ ግን አትበደርም፣ አንተ ብዙ የሚ ሆኑ አሕዛብን ትገዛቸዋለህ፣ አንተን ግን እነሱ አይገዙ ህም፤

፯፡ ወለእመቦ ዘተጸነሰ እምአኃዊከ በአሐቲ እምአህጉሪከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ኢታጽንዕ ልበከ ወኢትሚጥ እዴከ እምው ሂቡቱ ለእኁከ፡

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ካወረ ሰህ አገሮች ባንዲቱ አገር ከወንድሞችህ የተቸገረ ቢኖር ልቡናህን አታጽና፣ ለወንድም ህም ከመስጠት እጅህን አትመልስ አለ፣ ስጠው ሲል ነው፤ አንድም በልቡናህ ልስ ጠው ብለህ ካሰብህ በኋላ አትንሣው፤



፰፡ ወፍታሕ ወአርኁ እዴከ ወሀቦ ለእኁከ እምዘሰአለከ፡

ጉታህን ከፍተህ፤ አንድም ቍልፍህን ፈትተህ ሣጥንህን ከፍተህ እጅህን ዘርግተህ ለወ ንድምህ የለመነህን ስጠው፤

፱፡ ወዑቅ ርእሰከ ኢይኩን ቃለ ኃጢአት ውስተ ልብከ እንዘ ትብል ቅሩብ ውእቱ ዓመተ ኅድገት ዘሳብዕ ዓም ወኢይሁቦ፡

ዕረፍት የሚደረግበት ሰባተ ኛው ዘመን ቀርቧልና ለወን ድሜ አልሰጠውም (አላበድረ ውም) እያልክ በልብህ የኃጢ አትን ነገር እንዳታስብ ለራ ስህ እወቅ ፤

ወያእኪ ዓይኖ እኁከ ወይጸርኀ ላዕሌከ ኀበ እግዚአብሔር ወይከ ውን ኃጢአተ ላዕሌከ ፡

ወንድምህ በዓይኑ ለማየት ይጠላሀል፣ ወደ እግዚአ ሔርም ይጮሃል፣ ባንተም ዕዳ በደል ይሆንብሃል ፤

፲፡ አላ ውሂበኒ ሀቦ ወለቅሖኒ ለቅሖ መጠነ ስአለከ ወኢይተከዝ ልብከ እንዘ ትሁቦ እስመ በበይነ ዝንቱ ይባርከከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ምግባሪከ በውስተ ኵሉ ዘወደይከ እዴከ ፡

ገንዘብህን ስጠው፣ የለመነ ህንም ያህል አበድረው፣ ስትሰጠውም ልቡናህ አይዘን ስለዚህ ነገር ፈጣሪህ እግዚአ ብሔር በሥራህ ሁሉ በእጅህም በያዝኸው ሁሉ ያከብርሃልና ፤

፲፩፡ እስመ ኢይትኃጣዕ ነዳይ ውስተ ምድር ወበበይነ ዝንቱ እኤዝዘከ አነ ዮም ትግበር ዘንተ ነገረ ወእቤለከ ከመ ትፍታሕ ወታርትዕ እዴከ ለእኁከ ነዳይ ወለዘይስእለከኒ ዘቅሩብከ ዘውስተ ምድርከ ሀቦ ፡

በሀገርህ ድሀ አይታጣምና ስለዚህ ነገር ይህን ታደርግ ዘንድ ጎታህን ከፍተህ እጅህን ዘርግተህ ለድሀው ወንድምህ በሀገርህ አቀራቢያ ላለው ለሚለምንህ ትሰጠው ዘንድ እኔ ዛሬ አዝዝሃለሁ ፤

፲፪፡ ወለእመኒ ተሠይጠ ኀቤከ እኁከ ዕብራዊ አው ዕብራዊት ስድስተ ዓመተ ይትቀነይ ለከ ወበሳብዕ ዓም ትፌንዎ አግዓዚከ እምኔከ ፡

እስራኤላዊ ወንድምህ በአንተ ዘንድ ቢገዛ ወይም እስራኤ ላዊት ሴት በአንተ ዘንድ ብትገዛ ስድስት ዓመት ይገዛ ልህ ትገዛልህ፥ በሰባተኛው ዓመት ከአንተ ነጻ አውጥተህ አሰናብተው አሰናብታት፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ ወኢትፈንዎ ዕራቆ አላ ስንቀ ታሰንቆ እምአባግዒከ ወእምእክልከ ወእምክያዲ ወይንከ በአምጣነ ባረከከ እግዚአብሔር አምላክከ ትሁብ ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያከበረህን ያህል ከበጎችህም ከእህልህም ከወይንህም አውድማ ስንቁን ስጠው እንጂ ባዶውን አታሰናብተው፤

፲፬፤ ወተዘከር ከመ ገብር አንተ በምድረ ግብጽ ወቤዘወከ እግዚአብሔር አምላክከ እምህየ ፤

በግብጽ አገር አንተ ተገዥ እንደ ነበርህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ከዚያ እንዳዳነህ አስብ ፤

፲፭፤ ወበበይነ ዝንቱ እኤዝዘከ አነ ዮም ትግበር ዘንተ ነገረ ፤

ስለዚህ ነገር ይህን ነገር ታደርግ ዘንድ እኔ አሁን አዝዝሃለሁ ፤

፲፮፤ ወለእመሰ ይቤለከ ለሊሁ ኢይወፅእ እምኔከ እስመ አፍቀረከ ወለቤትከኒ እስመ ኀየሶ ነቢር ኀቤከ ፤

እሱ ግን በአንተ ዘንድ መኖር ስለተሻለው ወድጄሃለሁና ፤ ቤትህንም ወድጃለሁና ከአንተ ዘንድ አልወጣም ቢልህ ፤

፲፯፤ ትነሥእ መስፌ ወትሰቁሮ እንዘ ኀበ ኆኅት በኀበ መድረክ ወይከውነከ ገብረ ለዓለም ወለእመኒ አመትከ ከማሁ ትገብር፤

ወስፌ አምጥተህ በደጃፉ መድረክ አፍንጫውን በስተህ ለዘለዓለም ተገዥ ይሁንህ፤ ሴት ተገዥም ብትሆን እንደ ዚሁ አድርግ ፤

፲፰፤ ወኢይዕዕብከ ፈንዎቱ አግዓዜ እምኀቤከ እስመ እምነ ዓመት ቅንየት ተቀንየ ለከ ስድስተ ዓመተ ወይባርከከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ዘገበርከ ፤

መገዛት ከጀመረበት ዓመት ጀምሮ ስድስት ዓመት ተገዝቶልሃልና በዓመቱ ኀድገት ከአንተ ነፃ አውጥቶ መስደዱ ጭንቅ አይሁንብህ፤ ባደረግኸውም ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያከብርሃል ፤

፲፱፤ ወኵሎ በኵረ ዘተወልደ እምአልሕምቲከ ወእምአባግዒከ ተባዕቶ ትቄድስ ለእግዚአብሔር አምላክከ ፤

ከበጎችህና ከላሞችህ መጀመሪያ የተወለደውን ወንድ



ወንዱን ከከብትህ ለይተህ ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ስጥ፤

ወኢትቅኒ በኵረ አልሕምቲከ ወኢትቅርጽ በኵረ አባግዒከ ፤

ከላሞችህ መጀመሪያ የተወለደውን አትረስበት፤ ከበጎችህም መጀመሪያ የተወለደውን አትሸልተው፤

፳፤ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ብልዖ በበዓመት በውስተ መካን ዘኀረዮ እግዚአብሔር አምላክከ አንተ ወኵሉ ቤትከ ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ አንተ ከቤተሰቦችህ ሁሉ ጋር በዓመት በዓመት በእግዚአብሔር ፊት ብላው ፤

፳፩፤ ወለእመሰ ቦቱ ነውር እመኒ ዕውር ውእቱ አው ሐንካስ አው እምዘከነ ነውር እኩይ ሳዕሌሁ ኢትሡዖ ለእግዚአብሔር አምላክከ፤

ነውር ነቀፋ ቢኖርበት ግን ዕውርም ቢሆን፤ ወይም አንካሳ ቢሆን ነግሣለትና አሁን ከተናገርነው በሱ ነቀፋ ያለበት ቢሆን ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር አትሠዋው ፤

፳፪፤ በሀገርከ ብልዖ ርኩስኒ ወንጹሕኒ ኅቡረ ይብልዕዎ ከመ ወይጠል አው ከመ ኀየል ፤

ነገር ግን ይህን በሀገርህ ብላው፤ የሚገባውንና፤ የማይገባውን ማለት ታድኖ የሚመጣውን እንደ ፌቆ ወይም እንደ ዋሊያ ያለውን በአንድነት ይብሉት፤

፳፫፤ ወዳዕሙ ደሞ ኢትብልዑ ውስተ ምድር ክዕውዎ ከመ ማይ፤

ደሙን ግን አትብሉት በምድር እንደ ውሀ አፍስሱት እንጂ።

## ምዕራፍ ፲፮

## ጉባኤ

፩፤ ወዕቀብ ወርኃ ኤሳን ወግበር ፋሲካሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ እስመ በወርኃ ኤሳን ወፃእከ እምብሔረ ግብፅ ሌሊተ፤

በሚያዝያ ወር ግብጽ ከሚባል አገር በሌሊት ወጥተሃልና የሚያዝያን ወር ጠብቀህ የእግዚአብሔርን በዓል አድርግ፤

፪፤ ወትጠብሕ ፋሲካሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ አባግዐ ወአልሕምተ በውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ፤

www.ethiopianorthodox.org

በዚያ ስሙ ይጠራ ዘንድ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ ሳሙን በጉን ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር በዓል ሠዋ፤

፫፤ ወኢትብላዕ ምስሌሁ ብሑአ ሰቡዓ መዋዕለ ናዕተ ብላዕ ምስሌሁ ኅብስተ ሕማም ፤

ከሱ ጋር የቦካ አትብላ፤ ሰባት ቀን ቂጣ ብላ ለሆድ ጤና አይሆንምና ኅብስተ ሕማም አለው ፤

እስመ በጉጉዓ ወፃእከ እምግብጽ ከመ ትዘክር ዕለተ ጻአትከ እምድረ ግብጽ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትከ፤

ከግብጽ በችኮላ ወጥተሃልና በሕይወትህ ባለህበት ዘመን ሁሉ ከግብጽ አገር የወጣህ በትን ቀን ታስብ ዘንድ ሰባት ቀን ቂጣ ብላ ፤

፬፤ ወኢያስተርኢ ብሑእ በኵሉ ደወልከ ሰቡዓ ዕለተ ወኢይቢት እምውእቱ ሥጋ ዘጠባሕከ ሠርከ በቀዳሚት ዕለት ለነግህ ፤

በአውራጃህ ሁሉ ሰባት ቀን መጻጻ አይታይ፤ በመጀመሪያዩቱ ቀን ማታ ካረድኸው ሥጋም ተርፎ ለነገ አይደር፤

፭፤ ወኢትክል ጠቢሖቶ ለፋሲካ በውስተ አሐቲ እምአህጉሪከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሰጠህ አገሮች በአንዷቱ አገር መሥዋዕት ሠውተህ በዓል ማድረግ አይገባህም ፤

፮፤ ዘእንበለ ውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ፤

በዚያ ስሙ ይጠራ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ ነው እንጂ ፤

ወበህየ ትጠብሕ ፋሲካ ሠርከ ጊዜ ተዓርብ ፀሐይ እስመ በውእቱ ጊዜ ወፃእከ እምድረ ግብጽ፤

በዚያ ጊዜ ከግብጽ አገር ወጥተሃልና ፀሐይ በምትገባበት ጊዜ ማታ በዚያ መሥዋዕት ሠዋ፤

፯፤ ወታበስል ወትጠብሕ ወትበልዕ በውእቱ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ወትገብእ በነግህ ወተዓቱ ውስተ ቤትከ ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ ጠብሰህ ቀቅለህ ብላ፤ ይህን ካደረግህ በኋላ በጧት ተመልሰህ ወደቤትህ ግባ ፤

፰፤ ሰዱሰ ዕለተ ብላዕ ናዕተ ወበሳብዕትስ ዕለት እንተ አስተዋፅኦ ይእቲ ዘበዓሉ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወኢትግበር ባቲ ኵሎ ግብረ እንበለ ዘይትገበር ለነፍስ፤



ስድስት ቀን ቂጣ ብላ፤ የፈጣሪህ የእግዚአብሔር በዓል መሰናበቻ በምትሆን በሰባተኛዪቱ ቀን ግን ለነፍስ ከሚሠራው ሥራ በቀር ሥራውን ሁሉ አትሥራባት፤

፱፤ ወትኌልቍ ለከ ሰቡዓ ሰናብተ እምዘአኀዝከ ትዕፅድ ማዕረረከ ወትእኅዝ ትኍልቍ ሰቡዐ ሰናብተ

ሰቡዐ ሰናብተና ሰቡዐ ሰናብተ አንድ ወገን ነው፤ አዝመራህን ታጭድ ዘንድ ከጀመርህበት ቀን ጀምሮ ሰባት ሱባዔ ቍጠር ፤

፲፤ ወትገብር በዓለ ሰንበት ለእግዚአብሔር አምላክከ በአምጣነ ትክል እዴከ ዘትሁብ ወበአምጣነ ባረከከ እግዚአብሔር አምላክከ ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር እንደ አከበረህ መጠን እጅህ መስጠት የምትችለውን ያህል ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር በሱባዔ የምትከበር በዓል አድርግ ማለት ከሰባተኛው ቀን በኋላ በዓለ ሰዊትን አክብር፤

፲፩፤ ወትትፌሣሕ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ አንተ ወደቂቅከ ወአዋልዲከ ወገብርከ ወአመትከ ወሌዊ ዘውስተ ሀገርከ ወግዩር ወእጓለማውታ ወዕቤር እንተ ሀለወት ኀቤከ ውስተ ውእቱ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ፤

ከዓመት ሦስት ጊዜ በዓል ለማክበር በዚያ ስሙ ይጠራበት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ቦታ ወጥተህ አንተ ደስ ይበልህ፤ ወንዶች ልጆችህና ሴቶች ልጆችህ፤ ወንድ ባሪያህና ሴት ባሪያህ፤ በሀገርህ ያለ ካህኑም ስደተኛውም ከአንተ ዘንድ ያለች ባልቴትና አባት እናት የሞቱበት ልጅም እግዚአብሔር በአወቀው ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ደስ ይበላቸው፤

፲፪፤ ወተዘከር ከመ ገብር አንተ በምድረ ግብጽ ወዕቀብ ወግበር ኵሎ ዘንተ ትእዛዘ ፤

በግብጽ ሳለህ ባሪያ እንደ ነበርህ አስብ፤ ሕጉን ጠብቅ ያዘዘህንም ትእዛዝ ሁሉ፤ አድርግ ፤

፲፫፤ ወትገብር ለከ በዓለ መጸለት ሰቡዐ ዕለተ ሶበ አስተጋባእከ እክለከ እምውስተ ዐውድ ወእም ውስተ ምክያደ ወይንከ፤

www.ethiopianorthodox.org

ከወይንህ አውድማና ከእህ
ልህ አውድማ እህልህንና
ወይንህን ከሰበሰብህ በኋላም
ሰባት ቀን በዓለ መጸለትን
አክብር ፤

፲፬፡ ወተፈሣሕ በበዓልከ ወወል
ድከኒ ወወለትከኒ ወገብርከኒ
ወአመትከኒ ወሌዋዊ ዘውስተ
ሀገርከ ወግዩር ወእጓለ ማውታ
ወዕቤር እንተ ሀለወት ውስተ
ሀገርከ ፡

በበዓልህም ቀን ደስ ይበ
ልህ፤ ወንድ ልጅህና ሴት
ልጅህ፤ ወንድ ባሪያህ፡ ሴት
ባሪያህም ደስ ይበላቸው፤
በሀገርህ ያለ ካህኑም ስደተ
ኛውም ደስ ይበላቸው፤
በሀገርህ የምትኖር ባሏ
ትና አባት እናት የሞቱበት
ልጅም ደስ ይበላቸው ፤

፲፭፡ ሰቡዐ ዕለተ ትገብር በዓለ
ለእግዚአብሔር አምላክከ በው
ስተ መካን ዘኀረየ እግዚአ
ብሔር አምላክከ በኵሉ ወይንከ
ወእክልከ ወበኵሉ ግብረ
እደዊከ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመ
ረጠው ቦታ በወይንህ በእ
ህልህ በእጅህ ሥራ ሁሉ
ሰባት ቀን ለፈጣሪህ ለእግዚ
አብሔር በዓል አድርግ፤

፲፮፡ ወትረኢ ሠለስተ ጊዜያተ
በዓመት ወያስተርኢ ኵሉ ተባዕ
ትከ ቅድመ እግዚአብሔር አም
ላክከ በውስተ መካን ዘኀረየ
እግዚአብሔር በበዓለ ናዕት ወበ
በዓለ ሰንበት ወበበዓለ መጸለት፤

ከዓመት ሦስት ጊዜ ለገቢረ
በዓል ወጥተህ ደስ ይበልህ፡
ወንድ ልጅህ ሁሉ እግዚ
አብሔር በመረጠው ቦታ
በፈጣሪህ በእግዚአብሔር
ፊት ይታይ አለ፤ ከዓመት
ሦስት ጊዜ በዓሉን ለማክ
በር ይውጣ፤ (ሐተታ) በዓለ
ናዕት በዓለ ፋሲካ ነው፤
በዓለ ሰንበት ሰባት ሱባዔ
ቈጥረው አርባ ዘጠኝ
ይሆናል፡ በአምሳኛዪቱ ቀን
የሚያከብሩት ስለሆነ በዓለ
ሰዊት ነው፤ በዓለ መጸለት
ዳስ ጥለው የሚያከብሩት
ነው፤ ይህን ለማክበር ወንድ
ልጅህ ሁሉ ከዓመት ሦስት
ጊዜ ይውጣ ሲል ነው ፤

ወኢታስተርኢ ቅድመ እግዚአብ
ሔር አምላክከ ዕራቅከ ፤



በፈጣሪህ በእግዚአብሔር
ፊት ራቁትህን አትታይ አለ፡
ወደ ቤተ እግዚአብሔር ስት
ሄድ ባዶ እጅህን አትሂድ፤

፲፯፡ አሐዱ አሐዱ በአምጣነ
ኀይሉ እዴከሙ ወበአምጣነ
በረከቱ ለእግዚአብሔር አምላክ
ከሙ ዘወሀበከሙ ታመጽኡ

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር
ሁሉን ሰጥቶ እንደ አከበ
ራችሁ መጠን አንዱም
አንዱ በእጃችሁ ያለውን
የተቻላችሁን ያህል አምጡ፤

፲፰፡ ወሚመ ለከሙ ፈታሕተ
ወጸሐፍተ መባእ በኵሉ አህጉ
ሪከሙ ዘወሀበከሙ እግዚአብሔር
አምላክከሙ በበዘመድክሙ ወበ
በነገድክሙ ወይኰንንዎ ለሕዝብ
ኵሉ ጽድቀ ፤

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር
ባወረሳችሁ አገሮች ሁሉ
በየነገዳችሁ ሹማምትን መባ
ውን የሚጽፉ ሰዎችንም
ሹሙ፤ ለሕዝቡም እውነት
ፍርድን ይፍረዱ፤ አንድም
ሕዝቡን እውነት ፈርደው
ይግዟቸው፤ (ሐተታ) ፈታ
ሕት ለቤተ እግዚአብሔር
የገባውን ገንዘብ አውቀው
ይህ ለዚህ ይሁን ብለው
የሚወስኑ ናቸው፡ ጸሐፍት
የገባውንና የወጣውን ቀሪው
ንም የሚጽፉ ናቸው ፤

፲፱፡ወኢይድልዉ ለገጽ ወኢይን
ሥኡ ሕልየነ እስመ ሕልየን
ያዓውሮሙ ለጠቢባን ወያስስሎ
ለቃለ ጻድቅ፤

ፊት አይተውም አያድሉ
ማለት ዕገሌ ባለጸጋ ነው፡
ዕገሌ ድኻ ነው ሳይሉ
በትክክል ይፍረዱ፡ መማለ
ጃም አይቀበሉ፤ መማለጃ
መቀበል አዋቂዎችን አላ
ዋቂ ያደርጋቸዋልና፡ እው
ነተኛውንም ነገር ያስለው
ጣልና፤

፳፡ ዘይጸድቅ በጽድቁ ለይትሉ
ከመ ትሕየዉ ወትባኡ ትትዋ
ረሱ ምድረ ዘይሁበክሙ እግዚአ
ብሔር አምላክክሙ፡

ልትወርሷት ፈጣሪያችሁ
እግዚአብሔር በሚሰጣችሁ
አገር ገብታችሁ በተድላ
በደስታ ትኖሩ ዘንድ እውነ
ተኛ ሰው በእውነቱ ጸንቶ
ይኑር ማለት ፍርድ በመጠ
ንቀቅ ደህ በመጠበቅ ጸንቶ
ይኑር፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፡ ወኢትትክል ለከ ዖመ እምውስተ ኵሉ ዕፅ ዘይመልክ ኵሉ አሕዛብ ኀበ ምሥዋዑ ለእግዚአብሔር አምላክከ፤

አሕዛብ ሁሉ ከሚያመልኩት እንጨት ቁርጠህ አምጥተህ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር መሠዊያ አጠገብ አታቁም አትትክል፤

፳፪፡ ወኢትግበር ምስለ ዘይጸልዮ እግዚአብሔር አምላክከ በጥቃ ምሥዋዑ ለእግዚአብሔር ዘትገብር ለከ ወኢታቅም ለከ ሐውልተ፤

ይረባኛል ይጠቅመኛል ብለህ በሠራኸው በእግዚአብሔር መሠዊያ አጠገብ ፈጣሪህ እግዚአብሔር የሚጠላውን ምስል (ጣዖት) አትሥራ፤ ደንጊያውንም ጣዖት አድርገህ አታቁም፡፡

## ምዕራፍ ፲፯

፩፤ ወኢትሠዕ ለእግዚአብሔር አምላክከ ላሕመ አው በግዐ ዘቦቱ ነውር ላዕሌሁ ወኵሉ ነገር እኩይ ርኵስ ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ፤

ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ዕውሩን አንካሳውን ሌላም ነውር ነቀፋ ያለበትን ላም በግ አትሠዋ፤ ክፉ ነገር ሁሉ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ዘንድ አጸያፊ ነውና ፡

፪፡ ወለእመኒ ተረክበ በውስተ አሐቲ እምአህጉሪከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ብእሲ አው ብእሲት ዘገብሩ እኩየ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ እለ ተዐወሩ ሕጎ ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ካወረሰህ አገሮች በአንዲቱ አገር በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ሕጉን ቸል ብለው ክፉ ሥራ የሠሩ ወንድ ወይም ሴት ቢገኙ ፤

፫፤ ወሖሩ ወአምለኩ ባዕዳነ አማልክተ ወሰገዱ ሎሙ ለፀሐይ አው ለወርኅ አው እምኵሉ ሠርዌቲሃ ለሰማይ ዘኢአዘዘከ እግዚአብሔር አምላክከ ፤

እኩዩ ያለውን አመጣው ሂደው ልዩ የሆኑ ጣዖታትን፣ ያመለኩ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ላላዘዘህ ለሰማይ ጌጦች ለከዋክብት ለፀሐይ ለጨረቃ ሁሉ የሰገዱ ቢገኙ፤

፬፤ ወእምከመ ሰማዕከ ተሐትት ጥቀ ወለእመ ከነ እሙነ ዝነገር ርኵስ በውስተ እስራኤል ፤



አንተ ከሰማህ አጥብቀህ መርምር፤ ይህም ነገር እውነት ከሆነ በእስራኤል ዘንድ የሚያጸይፍ ነው፤

፭፤ ወታወፅኦ ለውእቱ ብእሲ ወእመኒ ብእሲት ይእቲ ወይወግርዎሙ በዕብን ወይቅትልዎሙ ፤

ይህን የሠራውን ሰው አስቀድመህ ከወገኑ ለየው፤ ሴትም ብትሆን ለያት፤ ከዚያ በኋላ በደንጊያ መትተው ይግደሏቸው ፤

፮፤ በክልኤቱ ወሠለስቱ ሰማዕት ይመውቱ እለ ይመውቱ ወኢይመውቱ በአሐዱ ስምዕ ፤

የሚሞቱ ሰዎችም በሁለት በሦስት ምስክር ይሙቱ፤ በአንድ ምስክር ግን አይሙቱ፤

፯፤ ወእደዊሆሙ ለውእቶሙ ሰማዕት ይቅድማ ቀቲሎቶሙ ወእምድኅሬሆሙ ዕደው ኵሉ ሕዝብ ወታወፅኡ እኩየ እምኔክሙ ፤

የነዚያ ምስክሮች እጆች አስቀድመው ይፈልጓቸው፤ ከነሱ በኋላ ሕዝቡ ሁሉ በደንጊያ መትተው ይግደሏቸው፤

እንዲህ እያደረጋችሁ ከእናንተ ክፉ ክፉውን አጥፉ ፤

፰፤ ወለእመቦ ዘተስእነከ ቃል በውስተ ፍትሕ ዘማዕከለ ደም ወደም ወማዕከለ ንጹሕ ለአንጽሖ ወማዕከለ ላኳ ወላኳ ቃለ ፍትሕ በውስተ አህጉሪከ ትትነሥእ ወተዓርግ ውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ፤

እመቦ ዘተስእነከ ቃለ ፍትሕ ነው፤ ደምን ለማንጻት በደምና በደም መካከል ያልበደለውንም ለማንጻት፤ በንጹሑ መካከል በክርክርና በክርክር መካከል ማለት በከሳሽና በተከሳሽ መካከል በአገርህ ለፍርድ የቸገረህ ቢኖር በዚያ ስሙ ይጠራ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ቦታ ተነሥተህ ሂድ ፤

፱፤ ወተሐውር ኀበ ካህናት ወሌዋውያን ወኀበ መኳንንት እለ ሀለዉ በውእቱ መዋዕል ወትሴአል ወያየድዑከ ፍትሐ ወትገብር በከመ ቃል ዘነገሩከ ፤

ሂደህም ከሌዋውያን ካህናትና በዚያ ወራት ካሉ

www.ethiopianorthodox.org

ከመኪንንቱም ዘንድ ጠይቅ፡ እነሱ የጠመመውን ፍርድ አቅንተው ይነግሩሃል፤እንደ ነገሩህም አድርግ ፤

፲፡ በውእቱ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ ወዕቀብ ኵሎ ከመ ትግበር ዘመሀሩከ ሕጎ፤

በዚያ ስሙ ይጠራ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው በዚያ ቦታ የነገሩህን ቃል አድርግ፡ ያስተማሩህንም ሕጉን ታደርግ ዘንድ ሕጉን ሁሉ ጠብቅ ፤

፲፩፡ ወበከመ ፍትሑ ዘነገሩከ ግበር ወኢትትገኃሥ እምቃል ዘነገሩከ ኢለየማን ወኢለፀጋም ፤

ያስተማሩህን ፍርዱን አድርግ፤ እንድም ፍርዱን እንደ ነገሩህ፡ አድርግ ከነገሩህም ቃል ወደ ቀኝም ወደ ግራም ቢሆን አትውጣ፤

፲፪፡ ወዘከቱሰ ብእሲ ዘይገብር ትዕቢተ ከመ ኢይትአዘዝ ለካህን ዘይቀውም ወይገብር በስሙ ለእግዚአብሔር አምላክከ አው ለመኰንን ዘሀለወ በውእቱ መዋዕል ለይሙት ውእቱ ብእሲ ወአሰስሉ እኩየ እምእስራኤል ፤

ተሹሞ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ስም ሥራ ለሚሠራ ለሊቀ ካህናት ወይም በዚያ ወራት ለተሾመው ዳኛ እንዳይታዘዝ ትዕቢትን የሚ ያደርግ ያ ሰው ግን ይሙት፡ እንዲህም አድርጋችሁ ከእ ስራኤል ክፉውን አጥፉ ፤

፲፫፡ ወኵሉ ሕዝብ ሰሚዖ ይፍራህ ወኢይድግም እንከ አበሶ ፤

የእስራኤል ወገን ሁሉ ይህን ነገር ሰምቶ እሱን ያገኘ ያገኘኛል ብሎ ይፍራ፡ አንድ ጊዜ ቢበድልም ሁለ ተኛ አይበድል ፤

፲፬፡ ወለእመኒ ቦእከ ውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ መክፈልተከ ወተዋረ ስካሃ ወነበርከ ውስቴታ ወትቤ እሠይም ሊተ መልአከ ከመ ኵሉ አሕዛብ እለ ዓውድየ ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ዕድል ፈንታ አድርጎ ወደ ሚሰጥህ አገር ብትገባ ወርሰ ሃትም በዚ ብትኖር በዙሪ



ያዬ እንዳሉ አሕዛብም ሁሉ አለቃ እሾማለሁ ብትል ፤

፲፭፡ ወትሠይም ለከ መልአከ ዘኀረየ እግዚአብሔር ዘእምአኃዊከ ፡

ፈጣሪህ እግዚአብሔር የመረጠውን ከወገኖችህ ሹም ፤

፲፮፡ ወኢትክል ሠይመ ለከ ብእሴ ነኪረ ዘኢኮነ እኁከ ከመ ኢያብዝኅ ሎቱ አፍራሰ ወከመ ኢያግብእ ለሕዝብ ውስተ ግብጽ ፡

ለራሱ ፈረሶችን እንዳያበዛ፡ ሕዝቡንም ወደ ግብጽ እን ዳይመልሳቸው፡ ወንድምህ ያልሆነውን ማለት በሃይ ማኖት በምግባር ያልመሰ ለህን ሰው ግን አትሹም ፤

እስመ እግዚአብሔር ይቤ ኢትድግም እንከ ገቢአታ ለዪ እቲ ፍኖት ፡

እግዚአብሔር ዳግመኛ ወደ ግብጽ ጎዳና አትመለስ ብሏልና ፤

፲፯፡ ወኢያብዝኅ ሎቱ አንስተ ወኢይሚጥ ልቦ ወኢያብዝኅ ሎቱ ወርቀ ወብሩረ ጥቀ ፡

ካላመነው ወገን የሆነውን አትሹም፤ ማለቱ ሚስቶችን እንዳያበዛ፡ ልቡናውንም ወደ አምልኮተ ጣዖት እንዳ ይመልስ፡ ወርቅና ብርንም ፈጽሞ እንዳያበዛ ነው ፤

፲፰፡ ወሶበ ነበረ ውስተ ምኵናኑ ለይጽሐፍ ሎቱ ዘንተ ዳግመ ኦሪተ ውስተ መጽሐፍ እምኀበ ካህናት ወሌዋውያን ፤

ከወገንህ መርጠህ የሾምኸው ሰው ባደባባይ ለፍርድ በተ ቀመጠ ጊዜ ዳግም ሕግን ከካህናትና ከሌዋውያን ዘንድ ጽፎ ይያዝ ፤

፲፱፡ ወየንብሮ ኀቤሁ ወየንብብ ቦቱ በኵሉ መዋዕለ ሕይወቱ ከመ ይትመሀር ፍሪሆቶ ለእግዚ አብሔር አምላኩ ወይዕቀብ ኵሎ ትእዛዞ ወይግበር ኵነኔሁ ፤

ከሱ ዘንድም ያኑረው፡ የፈጣ ሪው የእግዚአብሔርን ሕግ ይማር ዘንድ ባለበት ዘመን ሁሉ እሱን ይመልከት፡ ትእዛዙን ሁሉ ይጠብቅ ዘንድ፤ ሕጉንም ያደርግ ዘንድ ማለት ኢታምልክን፤

www.ethiopianorthodox.org

ዘጠኙን ሕገጋት ይጠብቅ ዘንድ ይህን ጽፎ ይያዝ፤

፳፤ ከመ ኢያዕቢ ልቦ እም አኃዊሁ ወከመ ኢይኅድግ እምት እዛዙ ለእግዚአብሔር አምላኩ ወኢይትገኃሥ ኢለየማን ወኢለፀ ጋም ፤

እንዲህም ማለቱ ከወን ድሞቹ መካከል ልቡን እንዳ ያስተአብይ የፈጣሪው የእግዚ አብሔርንም ትእዛዝ እንዳያፈ ርስ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ብሎ ከሕጉ እንዳይወጣ ነው፤

ወከመ ያኑኅ መዋዕለ በውስተ ምኩናኑ ውእቱ፣ ወውሉዱ በውስተ ደቂቀ እስራኤል፣

እሱ በግዛቱ ሆኖ ዘመኑን ያበዛ ዘንድ፣ ልጆቹም በእስራ ኤል ልጆች መካከል ዘመና ቸውን ያበዙ ዘንድ በሕይወት በኖረበት ዘመን ሁሉ ያንን ይመልከት።

## ምዕራፍ ፲፰

፩፤ ወአልቦሙ መክፈልት ለካህ ናት ወለሌዋውያን ወለኵሉ ሕዝበ ሌዊ ምስለ እስራኤል መባዑ ለእግዚአብሔር ክፍሎሙ ወኪያሁ ይሴሰዩ፣

ለሌዋውያን ካህናት ለሌዊ ወገኖችም ሁሉ ከእስራኤል ጋር ዕድል ፈንታ የላቸውም፣ ለእግዚአብሔር የሚገባው መባ ዕድል ፈንታቸው ነውና እሱን ይመገቡ፤

፪፤ ወባሕቱ ክፍል አልቦሙ በውስተ አኃዊሆሙ እስመ እግዚአብሔር ውእቱ ክፍሎሙ በከመ ይቤሎሙ፣

ነገር ግን ዕድል ፈንታችሁ እኔ ነኝ እንዳላቸው ዕድል ፈንታቸው እግዚአብሔር ነውና በወንድሞቻቸው በእስ ራኤል ዘንድ ዕድል ፈንታ የላቸውም፤

፫፤ ወዝንቱ ውእቱ ሕጎሙ ለካህናት ዘእምኀበ ሕዝብ እለ ይጠብሑ ጥብሐ፣

መሥዋዕት በሚያቀርቡ በሕ ዝቡ ዘንድ ለካህናት የተ ሠራላቸው ሥርዓት ይህ ነው፤

እመኒ ላሕመ ወእመኒ በግዓ ዘይሁብዎ ለካህን መዝራዕተ ወሀልቀ ወቈስጤ፣

በሬንም በግንም ቢያርዱ ለካህኑ ወርቹን ጎኑን ቆሽቱን፣ አንድም ሻኛውን ይስጡት፤



፬፤ ወቀዳሜ እክልከ ወቀዳሜ ወይንከ ወቀዳሜ ቀብዕከ አው እምዘቀረጽከ አባግዒከ ትሁቦ፣

የእህልህንና የወይንህን የዘይ ትህንም መጀመሪያ ከበጎች ህም የሸለትኸውን ስጠው፤

፭፣ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ እምኵሉ ሕዝብከ ከመ ይቁም ቅድሜሁ ወይትለአኮ ወይባርክ በስመ ዚአሁ ውእቱ ወደቂቁ በኵሉ መዋዕል፤

በፊቱ ቁሞ ያገለግለው ዘንድ፣ በዘመኑም ሁሉ እሱ ከልጆቹ ጋር ስሙን ያመሰግን ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከወገኖ ችህ ሁሉ ለይቶ መርጦ ታልና፤

፮፤ ወለእመ መጽአ ሌዋዊ እምውስተ አህጉሪክሙ ዘእምኵሉ ደቂቀ እስራኤል ዘኀበ ይነብር ውእቱ እስመ ፈተወ በነፍሱ ከመ ይትለአክ በውእቱ መካን ኀበ ኃረየ እግዚአብሔር አምላክከ፣

ሌዋዊ ከሚኖርበት አገር የእስ ራኤል ልጆች ሁሉ ወደ ሚኖሩባቸው አገሮቻችሁ ቢመጣ ፈጣሪህ እግዚአብ ሔር በመረጠው በዚያ ቦታ ያገለግል ዘንድ በልቡናው ወዷልና፤

፯፤ ይትቀነይ ለስ[illegible] እግዚአብሔር አምላኩ ከመ [illegible] አኃዊሁ ሌዋውያን እለ [illegible]ሙ ህየ ቅድመ እግዚአብሔ[illegible]

በእግዚአብሔር [illegible] በዚያ ጸንተው እንደሚ[illegible]ገሉ እን ደወንድሞቹ ሌ[illegible]ን ሁሉ በፈጣሪው በእግዚአብ ሔር ስም ያገልግል፤

፰፤ ወይትካፈል [illegible]ልቶ ወይ ሴሰይ ዘእንበለ ዘበ[illegible]ሙቱ ዘበ ሀገሩ፣

በተሾመበት አገር ከሚያ ገኘው ገንዘብ በቀር ለቤተ እግዚአብሔር ከ[illegible]ባው ፈን ታውን ተካፍሎ ይ[illegible]ገብ፤

፱፤ ወለእመ ቦእከ [illegible]ውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብ[illegible] አምላክከ ኢትትመሀር [illegible] [illegible]ርኵሶሙ ለውእቶሙ አሕዛብ[illegible]

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደ ሚያወርስህ ወ[illegible]ን ብት ገባ አሕዛብ የሚ[illegible]ትን ኃጢ አት አትሥራ፣ [illegible]ቸውንም አታምልክ፤

፲፤ ወኢይትረከብ በውስቴትክሙ ዘይሠውዕ ወልዶ [illegible] ወለቶ በእሳት ወዘያስ[illegible] መቅ ሥመ ወዘያስተሰ[illegible]ል ወዘይጤየር ወዘሥራይ፣

www.ethiopianorthodox.org

ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን በእሳት ለጣዖት የሚሠዋ፣ ሟርትንም የሚያሟርት፣ የሚያስጠነቁል፣ ጣዖትንም የሚያመልክ፣ ሥር የሚምስ፣ ቅጠል የሚበጥስ ሰው በናንተ ዘንድ አይገኝ፤

፲፩፤ ወዘሐረስ ወዘበጻውዕ ወዘያነቅሕ ምውተ ወዘያስተሰግል በዖፍ፣

ሟርተኛ በምታት ሙት አስነሣለሁ የሚል፣ በወፍም የሚያሟርት ሰው በናንተ ዘንድ አይገኝ፤

፲፪፤ እስመ ርኩስ ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር ኵሉ ዘይገብሮ ለዝንቱ እስመ በበይነ ዝንቱ ርኵሶሙ ያጠፍኦሙ እግዚአብሔር አምላክከ እምኔከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ስለዚህ ኃጢአታቸው ከአንተ ለይቶ የሚያጠፋቸው ስለሆነ ይህን የሚያደርግ ሰው ሁሉ በእግዚአብሐር ዘንድ የሚያጸይፍ ነውና፤

፲፫፤ ወኩን ፍጹመ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ እስመ እልክቱ አሕዛብ ዘአንተ ትትዋረሶሙ እሙንቱ ያስተሰግሉ ወያጸምዑ መቅሠመ፣

እነሱን አጥፍተህ አንተ ወርሰሃቸው የምትኖር እነዚያ አሕዛብ ያስጠነቁላሉና፣ ሟርትንም ያሟርታሉና አንተ ግን ፈጣሪህ እግዚአብሔር ባወቀው ነገር በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት በምግባር በሃይማኖት ፍጹም ሁን፤

፲፬፤ ወለከሰ አኮ ከማሁ ነቢየ ወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ እምአኃዊከ ዘከማየ፣

ለአንተ ግን እንዲህ አይደለም፣ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከወንድሞችህ ለይቶ እንደኔ ያለ መምህር ይሰጥሃል፤

፲፭፤ ወያነሥእ ለከ እግዚአብሔር አምላክከ ወሎቱ ስምዕዎ በኵሉ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ደግ ሰው ያስነሣልሃልና በሁሉ እሱን ስሙት አለ፣ ሲመክራችሁ ሲያስተምራችሁ ትምህርቱን ስሙት፤

፲፮፤ ወበኵሉ ዘሰአልክምዎ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ በኮሬብ አመ ዕለተ ተጋባእክሙ ወትቤሉ ኢንድግም እንከ ሰሚዖተ ቃሉ ለእግዚአብሔር አምላክነ፣

በኮሬብ በተሰበሰባችሁበት ቀን ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን



በለመናችሁት ሁሉ የፈጣሪያችሁን የእግዚአብሔርን ቃል ዳግመኛ እንስማ አላችሁ፤

ወለዛቲኒ እሳት ዐባይ ኢንርአያ እንከ ከመ ኢንሙት፣

ፈጽማ የነደደች በደብረ ሲና ያያችኋት ያችንም እሳት እንዳንሞት ዳግመኛ እንያት አላችሁ፤

፲፯፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር አማን ኵሉ ዘይቤሉ፣

እግዚአብሔርም ሕዝቡ የተናገሩት ነገር ሁሉ እውነት ነው አለኝ፤

፲፰፤ ነቢየ አነሥእ ሎሙ እም አኃዊሆሙ ዘከማከ ወአነብር ቃልየ ውስተ አፉሁ ወይነግሮሙ ዘከመ አዘዝክዎ፣

ከወንድሞቻቸው እንደ አንተ ያለ መምህር አስነሣላቸዋለሁ፣ ሕጌንም በአንደበቱ አኖራለሁ ማለት እንዲያስተምር አደርገዋለሁ፤ አንድም ለአንተ የነገርሁህን ሁሉ እነግረዋለሁና ነገራቸው ብዬ ያዘዝኩትን ሁሉ እንዳዘዝሁት ያስተምራል፤

፲፱፤ ወብእሲ ዘኢይሰምዖ ለውእቱ ነቢይ ኵሎ ዘ ነገረ በስመ ዚአየ አነ እትበቀል እምኔሁ፣

ይህን ሁሉ ነገር በኔ ስም የተናገረ ያነን መምህር የማይሰማውን ሰው እኔ ተበቅዬ አጠፋዋለሁ፤ አንድም ከወንድሞቻቸው እንደ አንተ ያለ ሰው አድርጌ ሥጋን አዋሕጄ ክርስቶስን አስነሳላቸዋለሁ፣ ሕገ ወንጌል በሱ ቃል እንድትነገር አደርጋለሁ፣ (ሐተታ) ቃልየ አላት፣ ምንም ሰው ሆኖ የሠራት ወልድ ቢሆን ወንጌል የሦስቱ ሕግ ናትና፣ (ትምህርትየሰ ኢኮነት እንተ፡ አየ አላ እንተ፡አሁ ለዘፈነ ወኒ) እንዲል ዮሐ፡ ም፡ ፯ ቁ፡ ፲፯፡

፳፤ ወባሕቱ ነቢይ ዘይኤብስ ወይነብብ ቃለ በስምየ ዘኢአዘዝክዎ ይንብብ ወዘነበበሂ በስመ ባዕዳን አማልክት ለይሙት ውእቱ ነቢይ፣

ነገር ግን ኃጢአት ሠርቶ የሚበድል ተናገር ብዬ ያላዘዝሁትን በኔ ስም የሚናገር በጣዖቱም ስም ትንቢት የሚናገር ያ ነቢየ ሐሰት ይሙት፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፤ ወለእመሰ ትብል በልብከ እፎ አአምር ቃለ ዘኢይቤ እግዚአብሔር፣

በልብህ እግዚአብሔር ያልተ ናገረውን ቃል እንደምን አውቃለሁ? ብትል ግን፤

፳፪፤ ወእምኵሉ ዘነበበ ነቢይ በስመ እግዚአብሔር እምከመ ኢበጽሐ ቃሉ ወኢኮነ በከመ ነበበ ኢነበቦ እግዚአብሔር ለውእቱ ቃል ወበሐሰት ነበበ ውእቱ ነቢይ ወኢትስምዕዎ፣

በእግዚአብሔር ስም ነቢዩ ከተናገረው ነገር ሁሉ ቃሉ ካልደረሰ እንደ ተናገረውም ካልሆነ ግን ያን ቃል እግዚአብሔር አልተናገረው ምና ያ ነቢይም ሐሰተኛ ነውና አትስሙት።

## ምዕራፍ ፲፱

፩፤ ወለእመ አጥፍኦሙ እግዚአብሔር አምላክከ ለአሕዛብ ዘይሁበከ ምድሮሙ ወወረስኮሙ ወነበርከ ውስተ ምድሮሙ ወውስተ አህጉሪሆሙ ወውስተ አብያቲሆሙ፣

አገራቸውን የሚሰጥህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር አሕዛብን ባጠፋቸው ጊዜ ወርሰኻቸው በአገራቸው በቤታቸው በኖርህ ጊዜ፤

፪፤ ሠላሰ አህጉረ ትፈልጥ ለከ በማዕከለ ምድርከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሰጠህ አገሮች መካከል ሦስት ሀገረ ምስካይን ለይ፤

፫፤ ወተአምር ለሊከ ፍኖቶን ወትከፍል ደወለ ምድርከ መሥልስተ ዘአስተካፈለከ እግዚአብሔር አምላክከ ወይኩን ህየ ምስካዩ ለኵሉ ቀታሊ፣

አንተ ጎዳናቸውን አውቀህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያካፈለህ ያገርህን አውራጃ ሦስት አድርገህ ክፈል፣ ነፍስ ለገደለ ሰውም በዚያ መማፀኛ ይሁን፤

፬፤ ወዝንቱ ውእቱ ሕጉ ለቀታሊ እምከመ ሰከየ ህየ ይሕየው ወለእመ በኢያእምሮ ቀተሎ ለካልኡ ወለእመ ኢኮነ ጸላኢሁ ቀዲሙ፣

የነፍሰ ገዳይ ሀገረ ምስካይ ገብቶ የሚማጠንበት ሕጉ ይህ ነው፣ በዚያ ከተማጠነ ይዳን፣ ባልንጀራውንም ባለ ማወቅ ከገደለው ቀድሞ ጥንተ ጠላቱ ካልሆነ ተማ ጥኖ ይዳን፤

፭፤ ወለእመቦ ዘሖረ ምስለ ካልኡ ሐቅለ ይሕጥብ ዕፀ ወወድቀ እምእዴሁ ጉድብ እንዘ ይገዝም ዕፀ ወወድቀ ሐፂኑ እምዕፁ ወወረደ ላዕለ ካልኡ ወቀተሎ፣

እንጨት ይለቅም ዘንድ ከባልንጀራው ጋር ወደ ምድረ በዳ የሄደ ሰው ቢኖር እንጨት ሲቆርጥ ገጀሞው ከእጁ ወድቆ ባልንጀራውን ቢገድለው፤

ይስኪ ውእቱ ውስተ አሐቲ እምእላንቱ አህጉር ወየሐዩ፣

ያ ሰው ከነዚህ አገሮች ባን ዲቱ ተማጥኖ ይዳን፤

፮፤ ከመ ኢይዴግኖ አበ ደም ወኢይቅትሎ ለቀታሊ እስመ ተቀየሞ በልቡ ወይረክቦ ለእመ ርኁቅ ፍኖት ወይቀትሎ እንዘ ኢኮነ አበሳሁ ለሞት እስመ ኢኮነ ጸላኢሁ ለምውት ቀዲሙ፣

ለሟቹ ጥንተ ጠላቱ ስላልሆነ ለሞት የሚያበቃ በደል ሳይ ኖርበት ደመኛው በልቡ ተቀ ይሞታልና፣ መንገድ ቢርቀው ባልሆነ ቦታ አግኝቶ ይገድ



ለዋልና ተከትሎ እንዳይገ ድለው ከነዚያ አገሮች ባን ዲቱ ተማጥኖ ይዳን፤

፯፤ ወበበይነ ዝንቱ አዘዝኩከ አነ ትግበር ዘንተ ነገረ ወእቤለከ ሠላሰ አህጉረ ፍልጥ ለከ፣

ስለዚህ ነገር ይህን ታደርግ ዘንድ እኔ አዘዝኩህ፣ ሦስት ሀገረ ምስካይ ለይተህ ሥራ አልኹህ፤

፰፤ ወለእመ አርኀበ ለከ እግዚአብሔር ደወለከ በከመ መሐለ ለአበዊከ ወወሀበከ ኵሎ ምድረ ዘይቤ እሁቦሙ ለአበዊከ፣

ለአባቶችህ እንደማለ እግዚአብሔር አውራጃዎችህን ካሰፋልህ ለአባቶችህ እሰጣቸ ዋለሁ ያለውንም አገር ከሰ ጠህ፤

፱፤ ወለእመ ሰማዕከ ከመ ትግበር ዘንተ ኵሎ ትእዛዘ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም፣

አሁን እኔ የማዝህን ይህን ሁሉ ትእዛዝ ታደርግ ዘንድ ከሰማህ፤

ከመ ታፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወከመ ትሑር በኵሉ ፍናዊሁ በኵሉ መዋዕል ወትዌስክ ለከ ዓዲ ሠላሰ አህጉረ ላዕለ እልክቱ ሠላስ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ትወደው ዘንድ፣ በዘመኑ ሁሉ በሕጉ ጸንተህ ትኖር ዘንድ በነዚያ በሦስቱ መማጠኛ አገሮች ላይ ዳግመኛ ሦስት መማጠኛ አገር ጨምር፤

፲፤ ወኢይትከዓው ደም ንጹሕ ውስተ ምድርከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ መክፈልተከ ወኢየሀሉ ውስቴትከ ቀታሌ ነፍስ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር እድል ፈንታ አድርጎ በሰጠህ አገር ንጹሕ ደም አይፍሰስ ነፍሰ ገዳይም ባንተ ዘንድ አይኑር፤

፲፩፤ ወለእመቦ ብእሲ ዘይጸልኦ ለካልኡ ወይጸንሖ ወእምዝ ተንሥአ ላዕሌሁ ወቀተሎ ወሰከየ ውስተ አሐቲ እምእላንቱ አህጉር፣

ባልንጀራውን የሚጠላው የሚሸምቅበት ሰው ቢኖር ከዚህ በኋላ በጠላትነት ተነሥቶ ቢገድለው ከነዚያ መማጠኛዎች ባንዲቱ ቢማጠን፤

፲፪፤ ይልእኩ ሊቃናተ ሀገሩ ወያመጽእዎ እምህየ ወይሜጥውዎ ኪያሁ ለአበ ደም ወይቀትሎ፤

የአገሩ ሽማምት ልከው ከሀገሬ ምስካይ አስወጥተው እሱን ይዘው አሳልፈው ለደመኛው ይስጡት፣ ደመኛው ተቀብሎ ይግደለው፤

፲፫፤ ወዓይንከ ኢትምሐኮ ወታነጽሕ ደመ ንጹሐ እምእስራኤል ወትከውን ሠናይት ላዕሌከ፣

እንዲህ ያለውን ነፍሰ ገዳይ ዓይንህ አይታ አትራራለት፣ እንዲህም አድርገህ ደምን አንፃ፣ ለአንተም በጎ ረድኤት ትደረግልሃለች፤

፲፬፤ ወኢትትኃለፍ ደወለ ቢጽከ ዘሠርዑ አበዊከ በውስተ ርስትከ ዘተዋረስከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ መክፈልተከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ዕድል ፈንታ አድርጎ በሰጠህ በወረስኸት አገር በከነዓን አባቶችህ የሠሩትን የባልንጀራህን ድንበር አታፍርስ፤ አንድም አባቶችህ ያቆዩትን እውነተኛውን ሕግ አታፍርስ፤

፲፭፤ ወኢይከውን አሐዱ ሰማዕት ከመ ይኩን ስምዐ ላዕለ ሰብእ በኵሉ ጌጋይ ወበኵሉ አበሳ ዘአበሱ፣ በአፈ ክልኤቱ ወሠለስቱ ሰማዕት የኃልቅ ኵሉ ነገር፣



ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ትወደው ዘንድ፣ በዘመኑ ሁሉ በሕጉ ጸንተህ ትኖር ዘንድ በነዚያ በሦስቱ መማጠኛ አገሮች ላይ ዳግመኛ ሦስት መማጠኛ አገር ጨምር፤

፲፤ ወኢይትከዓው ደም ንጹሕ ውስተ ምድርከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ መክፈልተከ ወኢየሀሉ ውስቴትከ ቀታሌ ነፍስ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር እድል ፈንታ አድርጎ በሰጠህ አገር ንጹሕ ደም አይፍሰስ ነፍሰ ገዳይም ባንተ ዘንድ አይኑር፤

፲፩፤ ወለእመቦ ብእሲ ዘይጸልኦ ለካልኡ ወይጸንሖ ወእምዝ ተንሥአ ላዕሌሁ ወቀተሎ ወሰከየ ውስተ አሐቲ እምእላንቱ አህጉር፣

ባልንጀራውን የሚጠላው የሚሸምቅበት ሰው ቢኖር ከዚህ በኋላ በጠላትነት ተነሥቶ ቢገድለው ከነዚያ መማጠኛዎች ባንዲቱ ቢማጠን፤

፲፪፤ ይልእኩ ሊቃናተ ሀገሩ ወያመጽእዎ እምህየ ወይሜጥውዎ ኪያሁ ለአበ ደም ወይቀትሎ፤

የአገሩ ሽማምት ልከው ከሀገሬ ምስካይ አስወጥተው እሱን ይዘው አሳልፈው ለደመኛው ይስጡት፣ ደመኛው ተቀብሎ ይግደለው፤

፲፫፤ ወዓይንከ ኢትምሐኮ ወታነጽሕ ደመ ንጹሐ እምእስራኤል ወትከውን ሠናይት ላዕሌከ፣

እንዲህ ያለውን ነፍሰ ገዳይ ዓይንህ አይታ አትራራለት፣ እንዲህም አድርገህ ደምን አንፃ፣ ለአንተም በጎ ረድኤት ትደረግልሃለች፤

፲፬፤ ወኢትትኃለፍ ደወለ ቢጽከ ዘሠርዑ አበዊከ በውስተ ርስትከ ዘተዋረስከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ መክፈልተከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ዕድል ፈንታ አድርጎ በሰጠህ በወረስኸት አገር በከነዓን አባቶችህ የሠሩትን የባልንጀራህን ድንበር አታፍርስ፤ አንድም አባቶችህ ያቆዩትን እውነተኛውን ሕግ አታፍርስ፤

፲፭፤ ወኢይከውን አሐዱ ሰማዕት ከመ ይኩን ስምዐ ላዕለ ሰብእ በኵሉ ጌጋይ ወበኵሉ አበሳ ዘአበሱ፣ በአፈ ክልኤቱ ወሠለስቱ ሰማዕት የኃልቅ ኵሉ ነገር፣

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፳

፩፤ ወለእመ ወፃእከ ሀብዓ ላዕለ ሀርከ ወርኢከ አፍራሰ ወመስተ ዕዕናነ ወሕዝበ ዘይበዝኁከ ኢትፍ ራህ እምኔሆሙ፡፡

ጠላትህን ለማጥፋት ወደ ሰልፍ ብትወጣ ፈረሶችንና በፈረስ የተቀመጡትን ከአንተ የሚበዛ ወገንም ብታይ ከነሱ የተነሣ አትፍራ፤

እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ዘአውፅአከ እምድረ ግብጽ ምስሌከ ውእቱ፡፡

ከግብጽ አገር ያወጣህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር በረድኤት አለና አትፍራ፤

፪፤ ወሶበ አንገዝከ ትትቃተል ይምጻእ ካህን ወይንግር ለሕዝብ ወይበሎሙ፡፡

ትዋጋ ዘንድ በጀመርህ ጊዜም ሊቀ ካህናቱ መጥቶ ለሕዝቡ እንዲህ ብሎ ይንገራቸው፤

፫፤ ስማዕ እስራኤል ናሁ ተሐውሩ አንትሙ ዮም ከመ ትቅትሉ ፀረ ክሙ ወኢይደንግፅክሙ ልብክሙ ወኢትፍርሁ ወኢትመምዑ ወኢት ትገኃሡ እምቅድመ ገጾሙ፡፡



የእስራኤል ወገን ስማ፡ እነሆ ጠላቶቻችሁን ልትወጉ ትሄዳ ላችሁና ልቡናችሁ አይደን ግጥባችሁ፡ አትፍሩ፡ አት ሸበሩ፡ ፊታቸውን ከማየት የተነሳም አትሸሹ፤

፬፤ እስመ እግዚአብሔር አምላክ ክሙ የሐውር ፍጽመ ለክሙ ከመ ይቅትል ፀረክሙ ወለክሙሰ ያድ ኅነክሙ፡፡

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ጠላቶቻችሁን ሊያጠፋላችሁ በፊት በፊታችሁ ይሄዳልና እናንተን ግን ያድናችኋልና አትፍሩ፤

፭፤ ወይቤልዎሙ ጸሐፍትኒ ለሕ ዝብ ለእመቦ ብእሲ ዘነደቀ ቤተ ሐዲሰ ወኢገብረ መድቅሐ ቤቱ ለይሑር ወይግባዕ ውስተ ቤቱ ከመ ኢይሙት በውስተ ቀትል ወካልእ ብእሲ ኢይግበር መድቅሐ ቤቱ፡፡

ሹማምቱም ሕዝቡን እንዲህ ይበሏቸው፡ አዲስ ቤት ሠርቶ የቤቱን መመረቂያ ያላደረገ ሰው ቢኖር በሰልፍ እንዳይሞት ወደቤቱ ይመለስ፡ ሌላ ሰውም የቤቱን መመረቂያ አያድርግ ይበሏቸው፤



፮፤ ወለእመቦ ብእሲ ዘተከለ ዐፀደ ወይን ወኢተፈሥሐ ቦቱ ለይሑር ወይግባእ ውስተ ቤቱ ከመ ኢይሙት በውስተ ቀትል ወካልእ ብእሲ ኢይትፌሣሕ ቦቱ፡፡

የወይን ሐረግ የተከለ፡ በሱም ደስ ያላለው ሰው ቢኖር ማለት ወይኑ አፍርቶ ፍሬውን በልቶ ደስ ያላለው ሰው ቢኖር እሱ በሰልፍ ሙቶ ሌላ ሰው እሱ በተከ ለው ደስ እንዳይለው ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ፤

፯፤ ወለእመቦ ብእሲ ዘፈኃረ ብእ ሲተ ወኢነሥኣ ለይሑር ወይግባእ ውስተ ቤቱ ከመ ኢይሙት በውስተ ቀትል ወካልእ ብእሲ ኢይንሥኣ፤

ሚስት አጭቶ ያላገባ ሰው ቢኖር፡ በሰልፍ እንዳይሞት እርሱ ተመልሶ ወደ ቤቱ ይሂድ፡ ሌላ ሰውም እንዳያ ገባት፤

፰፤ ወይድግሙ ብሂሎቶሙ ጸሐፍት ለሕዝብ ለእመቦ ብእሲ ፈራህ ለይግባእ ውስተ ቤቱ ከመ ኢያፍርህ ልበ ቢጹ ከማሁ፡፡

ዳግመኛ ሹማምቱ ለሕዝቡ እንዲህ ይበሏቸው፡ ፈሪ ሰው ቢኖር የባልጀራውን ልቡና እንደሱ እንዳያስፈራ ተመልሶ ወደ ቤቱ ይሂድ ብለው ይንገሯቸው፤

፱፤ ወሶበ አኅለቁ ነጊሮቶሙ ጸሐፍት ለሕዝብ ይሢሙ መላ እክተ ሠራዊት እምዐበይተ ሕዝብ፡፡

ሹማምቱም ለሕዝቡ ይህን ነግረው በጨረሱ ጊዜ ከሕዝቡ ከሚበልጡ ሰዎች የሠራዊት አለቆችን ይሹሙ፤

፲፤ ወሶበ ትቀርብ ውስተ ሀገር ከመ ትትቃተል ትጼውዖሙ በቃለ ሰላም፡፡

ትዋጋ ዘንድ ወደ ጠላቶችህ አገርም በቀረብህ ጊዜ በፍቅር ቃል ጥራቸው፤

፲፩፤ ወለእመ አውሥኡከ በቃለ ሰላም ወአርነዉ ለከ ይኩኑከ ኵሉ ሕዝብ እለ ተረክቡ ውስቴታ እለ ያገብኡ ለከ ጸባሕተ ወምኵናኒከኒ ይኩኑከ፡፡

የፍቅር ቃል ቢመልሱልህ፡ በሩንም ቢከፍቱልህ በዚያ የተገኙት ወገኖች ሁሉ የሚገዙልህና ግብር የሚያገ ቡልህ ይሁኑ፤

፲፪፡ ወለእመሰ ኢያውሥኡከ ሰላመ ወገብሩ ፀብዐ ምስሌከ ትነብር ላዕሌሃ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የፍቅር ቃል ባይመልሱልህ ከአንተም ጋራ ጦርነት ቢያደርጉ ግን አገሪቱን ከብበህ ተቀመጥ፤

፲፫፤ ወያገብኣ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ እዴከ ወትቀትል ኵሎ ተባዕተ በቅትለ ሐፂን ዘእንበለ አንስት ወንዋይ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር አገሪቱን በእጅህ አሳልፎ ይሰጣታልና ከንዝና ከሴቶች በቀር ወንድ ወንዱን ሁሉ በጦር ግደል፤

፲፬፤ ወኵሎ እንስሳ ወኵሎ ዘሀለወ ውስተ ሀገር ወኵሎ ጥሪቶሙ ትበረብር ለከ ወብላዕ ኵሎ በርበረ ፀርከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ፣

ላሙን በጉን ሁሉ በአገር ያለውን ገንዘባቸውንም ሁሉ ዝረፍ፣ ፈጣሪህ እግዚአብሔር የሰጠህ የጠላቶችህን ገንዘብ ሁሉ ዘርፈህ ብላ፤

፲፭፤ ወከመዝ ትገብር ኵሎ አህጉረ እለ ጥቀ ርኁቃን እምኔከ ዘኢኮኑ እምአህጉሪሆሙ ለእሉ አሕዛብ ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ምድሮሙ ከመ ትትዋረስ ፣

አገራቸውን ትወርስ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሚሰጥህ ከነዚህ ከአሕዛብ አገሮች ያልሆኑትን ከአንተ እጅግ የራቁትን አገሮች ሁሉ እንዲህ አድርግ አለ፣ አጥፋቸው፤

፲፮፤ ወኢታሕዩ ኵሎ ዘነፍስ አላ መርገመ ትረግምዎሙ ለኬጤዎን ወለአሞሬዎን ወለከናኔዎን ወለፌርዜዎን ወለኤዌዎን ወለኢያቡሴዎን ወለጌርጌሴዎን በከመ አዘዘከ እግዚአብሔር አምላክከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር እንዳዘዘህ አሞሬዎንንና ኬጤዎንን፣ ኢያቡሴዎንንና ኤዌዎንን ጌርጌሴዎንን ፈጽመህ አጥፋቸው እንጂ ከነዚህ ወገን ሰውን ሁሉ አታድን፤

፲፯፤ ከመ ኢይምሀሩከ ገቢረ ኵሎ ርኵሶሙ ወኵሎ ዘይገብሩ ለአማልክቲሆሙ ወትጌግዩ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ፣

ለጣዖቶቻቸው እንደሚያደርጉት የሚሠሩትን ኃጢአታቸውን ሁሉ እንዳያስተምሩህ ይህንም አድርጋችሁ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን እንዳትበድሉ እነዚህን አጥፉ፤

፲፰፤ ወለእመ ነበርከ ውስተ ሀገር ብዙኃ መዋዕለ ከመ ትትቃተላ



ወከመ ትንሥኣ ኢትግዝም ዖማ ወኢታውርድ ሐፂነ ላዕሌሁ አላ እምኔሁ ብላዕ፣

አሕዛብን አጥፍተህ አገሪቱን እጅ አድርገህ በሀገሩ ብዙ ቀን ብትኖር ፍሬዋን ብላ እንጂ በምሳር ዛፏን አትቁረጥ፤

፲፱፤ቦኑ ሰብእ ውእቱ ኦመ ገዳም ከመ ይምጻእ ቅድሜከ ወይባእ ውስተ ቅጽርከ፣

ወደ አንተ ይመጣ ዘንድ ወደ ቅጽርህም ይገባ ዘንድ የምድረ በዳ እንጨት በውኑ ሰው ነውን፤

፳፤ ወባሕቱ ዕፀ ዘተአምር ከመ ኢይፈሪ ኪያሁ ትገዝም ወትመትር ወትነድቅ ሐፁረ ላዕለ ይእቲ ሀገር እንተ ትገብር ፀብዓ ምስሌከ እስከ ታስተጋብኣ፤

ነገር ግን እንዳያፈራ የምታውቀውን እንጨት ቁረጥ፣ ጠላትህን ወግተህ እስክትወርሳትም ድረስ ከአንተ ጋራ ሰልፍ ባደረገች በዚያች አገር ዙሪያ አጥር እጠር።

## ምዕራፍ ፳፩

፩፤ ወለእመ ተረክበ ቅቱል ውዱቀ ውስተ ገዳም በውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚብሔር አምላክከ ትትዋረሳ ወኢያእመሩ ቀታሊሁ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ልትወርሳት በሰጠህ አገር ሰው ሙቶ ወድቆ ቢገኝ፣ የሀገሪቱ ሰዎችም ገዳዩን ባያውቁት፤

፪፤ ይወፅኡ ሊቃውንቲክሙ ወመኳንንቲክሙ ወይሜጥኑ አህጉረ ዘዓውዱ ለውእቱ ቅቱል ወሀገር እንተ ቅርብት ይእቲ መንገሌሁ ለውእቱ ቅቱል፣

ነገር ዓዋቂዎች ሽማግሎቻችሁና ሹማምቶቻችሁ ወጥተው ያ ሰው በሞተበት ዙሪያ ያሉ አገሮችንና ለሞተው ሰው አቅራቢያ የምትሆን ያችን አገር ይስፈሩ፤

፫፤ ወአዕሩጊሃ ለይእቲ ሀገር ያመጽኡ ዕጕልተ እምአልሕምት እንተ ኢተቀንየት ወእንተ ኢሰሐበት አርዑተ፣

የዚያች አገር ሽማግሌዎችም ያልቀናች ቀንበር ያልተሸከመች ቀይ ጊደርን ከላሞች መካከል መርጠው ያምጡ፤

፬፤ ወያወርድዋ አዕሩጊሃ ለይእቲ ሀገር ለይእቲ ዕጕልት ውስተ ቈላ መብዕስ ዘኢተሐርሰ ወዘኢተዘርአ ውስቴቱ ወይመትሩ ሥረዊሃ ለይእቲ ዕጕልት በውስተ ቈላ፣

የዚያች አገር ሽማግሌዎችም ያችን ቀይ ጊደር ወዳልታረሰ

www.ethiopianorthodox.org

ዘርም ወዳልተዘራበት ጎባጉዕ ወደ ሆነው በረሀ አውርደው ቋንጃዋን ይቍረጧት፤ አባላ ይምታት ማለት በቁሟ ይቍረጧት ነገሯ ጎባጉዕ ነው፤ የቀና አይደለም ሲል ውስተ ቆላ መብዕስ አለ፤

፭፤ ወይመጽኡ ካህናት ወሌዋውያን እስመ ኪያሆሙ ኀረየ እግዚአብሔር ይቁሙ ቅድሜሁ ወይባርኩ በስመ ዚአሁ ወበቃለ ዚአሆሙ ይቀውም ኵሉ ተስናን ወኵሉ ዘይትኃደግ፤

በፊቱ ይቆሙ ዘንድ፤ ስሙንም ያመሰግኑ ዘንድ እግዚአብሔር እነሱን መርጧልና፤ ፀብ ክርክር ሁሉ በይቅርታ የሚተወው ነገር ሁሉ በነሱ ቃል ይፈረዳልና ሌዋውያንና ካህናቱ ይምጡ፤

፮፤ ወኵሉ አዕሩጊሃ ለይእቲ ሀገር እንተ ቅርብት መንገሌሁ ለውእቱ ቅቱል ይትሐፀቡ እደዊሆሙ ላዕለ ርእሳ ለይእቲ ዕጉልት ዘመተሩ ሥረዊሃ በውስተ ቈላ፤

በዚያ በሞተው ሰው አገር ቅርብ የምትሆን የዚያች አገር ሽማግሌዎችም ሁሉ መጥተው በበረሀ ቦታ አባላ

በተመታችው ጊደር ራስ ላይ እጃቸውን በውሀ ይታጠቡ፤

፯፤ ወይነብቡ ወይብሉ እደዊነ ኢክዓዋ ደሞ ለዝንቱ ወአዕይንቲነ ኢርእያ፤

እጃቸውንም ሲታጠቡ የዚህን ሰው ደም እጆቻችን አላፈሰሱም፤ ዓይኖቻችንም አላዩም ብለው ይናገሩ፤

፰፤ ወሥረይ ለሕዝብከ እስራኤል እግዚኦ ዘቤዘውካሆሙ እምድረ ግብጽ ከመ ኢይኩን ጌጋየ ነፍስ ላዕለ ሕዝብከ እስራኤል ወይሠረ ሎሙ በእንተ ውእቱ ነፍስ፤

የዚህ ሰው ነፍስ ፍዳ በወገኖችህ በእስራኤል እንዳይሆን አቤቱ ከምድረ ግብጽ ያወጣኻቸው ወገኖችህ እስራኤልን ይቅር በላቸው ይበሉ፤ ስለዚያም ሰው ነፍስ ይቅር ይላቸዋል፤ ሽማግሌች ቀይ ጊደር በረሀ ወስደው አባላ መትተው በራሷ ላይ ይታጠባሉ፤ ካልገደለው ወገን ጥሩ ውሀ ሁኖ ይወርዳል፤ ከገዳዩ ወገን ሲደርስ ይወይባል፤ ከገዳዩ ሲደርስ ውሀው ደም ይሆናል



ወዲያው ደብድበው ይገድሉታልና እንዲህ አለ፤

፱፤ ወአንተሰ አሰስል ጌጋየ ውእቱ ነፍስ እምላዕሌከ ወትከውን ሠናይት ላዕሌከ ለእመ ገበርከ ዘሠናይ ወዘአዳም ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ፤

አንተ ግን የዚያን ሰው ደም ፍዳ እንዲህ አድርገህ ከአንተ አርቅ ፤ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ያማረውንና የተወደደውንም ብታደርግ ለአንተ በጎ ነገር ትደረግልሃለች፤

## ጉባኤ

፲፤ ወለእመኒ ወጻእከ ፀብአ ላዕለ ፀርከ ወአግብኦሙ እግዚአብሔር ውስተ እዴከ ወዔወውከ ዔዋሆሙ፤

ጠላቶችህን ልታጠፋ ወደሰልፍ ብትወጣ፤ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ጠላቶችህን በእጅህ ቢጥልልህ፤ ምርኮም ብትማርክ፤

፲፩፤ ወርኢከ በውስተ ዔዋ ብእሲተ እንተ ሠናይ ርእየታ ወፈተውካሃ፤

በምርኮኞችም መካከል መልኳ ያመረ ሴት ብታይ እሷንም ብትወዳት፤

፲፪፤ ወነሥእካሃ ለከ ትኩንከ ብእሲተ ወታበውኣ ውስተ ጽርሐ ቤትከ ወትላጽያ ርእሳ ወትጸፍራ፤

ለአንተም ሚስት ትሆንህ ዘንድ ብታገባት ወደ እልፍኝህ አግብተህ ራሷን ላጯት፤ ጥፍሯንም ቁረጣት፤

፲፫፤ ወታሴስል አልባሲሃ ዘቦቱ ተዔወወት ወታነብራ ውስተ ቤትከ ወትበኪ ለአቡሃ ወለእማ ሠላሳ መዋዕለ ወእምድኅረ ዝንቱ ትብውእ ኀቤሃ ወትነብር ምስሌሃ ወትከውነከ ብእሲተ፤

የተማረከችበትን ልብሷን አውልቀህ በቤትህ አኑራት፤ አንድም የተማረከችበትን ልብስ አውልቃ ሌላ ልብስ ትልበስ፤ ለአባትና ለእናቷም ሠላሳ ቀን ታልቅስ ማለት ከነሱ ስለተለየች ነው ፤ ከዚህ በኋላ ወደሷ ግባ ማለት በግብር ዕወቃት፤ ከርሷ ጋር ኑር ማለት ሚስትም ትሁንህ፤ አንድም ወትነብር ምስሌከ ይላል፤ እርሷ ላንተ ሚስት ሁና ካንተ ጋር ትኑር፤

፲፬፤ ወእምዝ ለእመ ኢፈቀድካሃ ትፌንዋ አግዓዚተ ወሢይጠስ ኢትሠይጣ በወርቅ ወኢትክሐዳ ከመ አውሰብካሃ፤

ከዚህ በኋላ ባትወዳት ግን ነፃ አውጥተህ አሰናብተህ ስደዳት፤ ነገር ግን በፈረስ፤

www.ethiopianorthodox.org

አንገት በጦር አንደበት የማ ረክኒት ባርያዪ ናት ብለህ በወርቅ አትሽጣት፤ እንዳገባ ሃትም አሲ አትበላት፤

፲፭፤ ወለእመኒ አውሰበ ብእሲ ክልኤተ አንስተ ለአሐተ ይጸልኣ ወለአሐተ ያፈቅራ ወወለደት ሎቱ በኵረ እንተ ይጸልኣ፤

ከዚህ አያይዞ ሥርዓት ይሠ ራል፤ አንድ ሰው ሁለት ሚስት ቢያገባ፤ አንዷቱን ጠልቶ አንዷቱን ቢወድ፤ የሚጠላትም ሴት የበኩር ልጅ ብትወልድለት፤

፲፮፤ አመ ያስተዋርሶሙ ንዋዮ ለደቂቁ ኢይክል አዕብዮቶ ለወልዳ ለእንተ ያፈቅራ ወተዓውሮቶ ለወልዳ ለእንተ ይጸልኣ፤

ለልጆቹ ገንዘቡን በሚያወርስ በት ጊዜ የሚወዳት ሚስቱን ልጅ አለቃ ማድረግ አይች ልም፤ የሚጠላት ሚስቱንም ልጅ (ቸል ማለት) ማሳነስ አይችልም፤

፲፯፤ ወይሁብ ምክዕቢተ እምኵሉ ዘተረክበ ሎቱ እስመ ውእቱ ቀዳሚ ውሉዱ ወሎቱ ይሬሲ ዘበኵሩ፤

የልጆቹ አለቃ (የበኩር ልጁ) ነውና ከተገኘው ገንዘብ ሁሉ ለሱ ዕጥፍ አድርጎ ይስጠው፤ ያስቀነቱንም ገንዘብ ለሱ ያድርግለት ፤ አንድም አለቃ አድርጎ ይሹመው፤

፲፰፤ ወለእመቦ ዘቦቱ ወልድ ከሐዲ ወዝኑር ወኢይትኤዘዝ ለቃለ አቡሁ ወለቃለ እሙ ወይጌሥጽዎ ወኢይሰምዖሙ፤

አሉተኛ ትዕቢተኛ ለአባት ለእናቱ የማይታዘዝ ልጅ ቢኖር ቢመክሩትም የማይ ሰማ ቢሆን፤

፲፱፤ ወይሰድዎ ኀበ ሊቃናተ ሀገሩ ወውስተ አንቀጸ ብሔሩ፤

ወደ አገሩ አደባባይ ከሀገሩ አለቆች ዘንድ ይውሰዱት፤

፳፤ ወይበልዎሙ ለሰብአ ሀገሮሙ ዝንቱ ወልድነ ይክሕደነ ወያዐቢ ርእሶ ወኢይሰምዕ ቃለነ ወይሜግር ወይሰክር፤

ለሀገራቸው ሰዎችም እንዲህ ይበሏቸው፤ ይህ ልጃችን አሌ ይለናል፤ ራሱን ያስታብያል (ያከብራል)፤ ቃላችንንም አይ ሰማም ይዛለላል፤ በነገርም ይሰክራል ይበሏቸው፤



፳፩፤ ወይውግርዎ በዕብን ሰብአ ሀገሩ ወይቅትልዎ ወታሴስሉ እኩየ እምኔክሙ ወኵሉ እስራኤል ሰሚዖ ይፍራህ፤

የሀገሩም ሰዎች በደንጊያ መትተው ይግደሉት፤ እንዲ ህም እያደረጋችሁ ከናንተ ክፉ ክፉውን አጥፉ፤ እስራኤል ሁሉ ይህን ሰምቶ ይፍራ፤

፳፪፤ ወለእመቦ ብእሲ ዘአበሰ ወበ ጽሐ ጌጋዩ ለኵነኔ ሞት ትሰቅልዎ ዲበ ዕፅ ወትቀትልዎ፤

የበደለ በደሉም ለሞት የሚ ያበቃው ሰው ቢኖር በእን ጨት ሰቅለው ይግደሉት፤

፳፫፤ ወኢይቢት ሥጋሁ ዲበ ዕፅ አላ ቀቢረ ቅብርዎ በይእቲ ዕለት እስመ ርጉም ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር ዘስቁል ዲበ ዕፅ ወኢታርኵስዋ ለምድር ዘይ ሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክ ክሙ ርስተ፤

በእንጨት የተሰቀለ ሰው በእ ግዚአብሔር ዘንድ ርጉም ነውና በዚያች ቀን ቅበሩት እንጂ ሬሳው በእንጨት ላይ እንደ ተሰቀለ አይደር፤ የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ በማፍረስ (ባለማክበር) ፈጣ ሪያችሁ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ የሰጣችሁን ምድር አታጐስቁሏት፡፡

## ምዕራፍ ፳፪

፩፤ ወለእመ ርኢከ ላሕመ ቢጽከ አው በግዖ ኀበ ተገድፈ በፍኖት ኢትትዐወር አግብኦ ሎቱ ለካልእከ ወአወፍዮ፤

የባልንጀራህን ላሙን ወይም የጠፋ በጉን በጎዳና ወድቆ ብታይ ቸል አትበል፤ ‹‹አላ ያለበት ነው››፤ መልሰህ ለባ ልንጀራህ ስጠው እንጂ፤

፪፤ ወለእመኒ ኢኮነ ቅሩበ ኀቤከ ካልእከ ወለእመኒ ዘኢተአምሮ ታስ ተጋብኦ ወታአቱ ቤተከ ወታነብር ኀቤከ እስከ አመ የኃሥሦ ካልእከ ወታገብኦ ሎቱ፤

ባልንጀራህ በአንተ ዘንድ የቀ ረበ ባይሆን፤ ሰውየውንም አገሩንም የማታውቀው ቢሆን ሰብስበህ ወደቤትህ አግባለት፤ ባልንጀራህ እስኪፈልገውም ድረስ በአንተ ዘንድ አኑረው፤ እየፈለገ ከመጣ በኋላ ግን ከኔ ዘንድ አለልህ ብለህ መል ስለት፤

፫፤ እመኒ ዓድጉ አው ላሕሙ ከመዝ ትገብር ወእመኒ ልብሱ

www.ethiopianorthodox.org

ከማሁ ትገብር በእንተ ኵሉ ዘገደፈ ካልእከ ወዘተገድፈ እምኀቤሁ ወረከብካሁ ኢትክል ተዐውሮ፤

አኽያውም ቢሆን ወይም ላሙ ቢጠፋበት፤ ልብሱም ቢሆን ባልንጀራህ ስለጣለው ገንዘብ ሁሉ እንዲህ አድርግ፤ ከሱ እጅ ወድቆ የጠፋውን ብታገኝ ቸል አትበለው፤

፬፤ ወለእመ ርኢከ ዐድገ ቢጽከ አው ላሕሞ እንዘ ውዱቅ ውስተ ፍኖት ኢትትዓወሮሙ ታነሥእ ወታስተላዕል ምስሌሁ፤

የባልጀራህን አኽያ ወይም በሬውን በጎዳና ወድቆ ብታይ ቸል አትበል፤ አሳ ያለበት ነው፤ አንሥተህ ከሱ ጋራ አጫጭ ነው እንጂ፤

፭፤ ወኢትትረሰይ ብእሲት በትርሲተ ብእሲ ወኢይልበስ ብእሲ ልብሰ ብእሲት እስመ ርኩስ ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ኵሉ ዘይገብር ለዝንቱ፤

ሴት በወንድ መሣሪያ (ልብስ) አታጊጥ፤ ወንዱም የሴት ልብስ አይልበስ ፤ ይህን የሚሠራው ሰው ሁሉ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ዘንድ የረከሰ ነውና፤ አንድም በጥምቀት ጊዜ ሴቲቱ ወንዱን ልጅ ክርስትና አታንሣ፤ ወንዱም ሴቲቱን ክርስትና አያንሣ፤

፮፤ ወለእመ ረከብከ ዕጓለ ዖፍ ቅድመ ገጽከ በውስተ ፍኖት ወእመኒ በውስተ ኵሉ ዕፀው አው በውስተ ኵሉ ምድር ወእመኒ አፍኀርት ዘኢይሠርር ወእመኒ አንቆቅሖ ኢትንሣእ እመ ምስለ ዕጐሊሃ፤

በፊትህ ባለ ጎዳና በእንጨትም ሁሉ፤ በምድሩም ሁሉ የወፍ ጫጩት ብታገኝ የማይበር ጫጩትም ቢሆን፤ ዕንቁላልም ብታገኝ እናቲቱን ከጫጩቶቿ ጋራ አትውሰድ፤

፯፤ ዳዕሙ ታሠርራ ወታግዕዛ ለእም ወእፍኀርቲሃ ትነሥእ ለከ ከመ ትኩን ሠናይት ላዕሌከ ወይብዛኀ መዋዕሊከ፤

እናቲቱን ነፃ አውጥተህ ሰድደህ ጫጭቶቿን (ግልገሎቿን) ውሰድ እንጂ በጎ ረድኤቱ ትደረግለህ ዘንድ ዘመንህም ይበዛ ዘንድ፤



፰፤ ወለእመ ነደቀ ቤተ ሐዲሰ ትገብር ተድባበ ለናሕስከ ወኢትገበር ቀትለ በውስተ ቤትከ ከመ ኢይደቅ እመቦ ዘይወድቅ እምኔሁ፤

አዲስ ቤት ብትሠራ ከሱ የሚወድቅ ሰው ቢኖር የሚደግፈው አጥቶ እንዳይወድቅ፤ በቤትህም ሰልፍ እንዳታደርግ ለሰገነትህ መከታ አብጅለት፤

፱፤ ወኢትትክል እምኵሉ ኀብር ዓፀደ ወይንከ ከመ ኢትቅሥም ፍሬሁ ወዘርአከኒ ዘትዘርእ ምስለ ፍሬ ወይንከ፤

ፍሬውን ለመልቀም እንዳትቸገር በሰሉን ከወይኑ ጋር ወይኑንም ከበለሱ ጋር ባንድ ቦታ አትትከል ፤ ስንዴውን ከገብሱ ጋር፤ ገብሱንም ከስንዴው ጋር ባንድነት አትዝራ፤ አንድም ሕገ እግዚአብሔርን ከሕገ ጣዖት ጋር አንድ አድርገህ አትያዝ፤

፲፤ ወኢትሕርስ በዓድግ ወበላሕም ኀቡረ ወኢትልበስ ልብሰ ዘተአንመ በፀምር ወበአጌ፤

አህያውንና በሬውን በአንድነት ጠምደህ አትረስ፤ በነጭ ሐርና በተልባ እግር የተሠራ ልብስ አትልበስ ፤ አንድም ከካህን ኦሪትና ከካህነ ጣዖት እማራለሁ አትበል፤ ሕገ እግዚአብሔርንና ሕገ ጣዖትንም አንድ አድርገህ አትያዝ፤

፲፩፤ ወትገብር ለከ ዘፈረ ፍቱለ ላዕለ አርባዕቱ መዓዝነ አልባሲከ ዘትለብስ፤

በምትለብሰው ልብስ በአራቱ መዓዝን በዘርፉ ሰማያዊ ሐር አድርግበት፤ (ሐተታ) ሰማይ የመሰለ ባሕር ከፍሎ አሻገረን ለማለት፤ ከግብጽ አውጥቶ በደብረ ሲና ሰማያዊ ሕግ ሠራልን ለማለት፤

፲፪፤ ወለእመ ጸልአ ብእሲ ለብእሲቱ ዘአውሰባ እምድኅረ ነበረ ምስሌሃ ወአምጽአ ላቲ ነገረ ምክንያት፤

አንዱም አንዱ ሰው ያገባት ሚስቱን ከርሷ ጋር ከኖረ በኋላ መልሶ ቢጠላት የምትፈታበትን ምክንያት ቢያመጣባት፤

፲፫፤ ወአውፅአ ላቲ ስመ እኩየ ወይቤ ነሣእክዋ ለዛቲ ብእሲት ወሶበ ቦእኩ ኀቤሃ ኢረከብኩ ድንግልናሃ፤

www.ethiopianorthodox.org

ያችን ሴት በሙሴ ሕግ አገ ብቻት ነበር፤ ነገር ግን ወደሷ በገባሁ ጊዜ ድንግልናዋን አላ ገኘሁም ብሎ ክፉ ስም ቢያ ወጣላት፤

፲፭፤ ወይንሥኡ አቡሃ ወእማ ልብሰ ድንግልናሃ ለወለቶሙ ወይ ሰዱ ኀበ ሊቃነ ካህናት ኀበ አንቀጽ፡

አባትና እናቷ የልጃቸውን የድንግልናዋን ልብስ ከባሏ ተቀብለው ባደባባይ ወዳሉ ወደ አለቆቹ ይውሰዱ፤

፲፮፤ ወይበሎሙ አቡሃ ለይእቲ ወለት ለሊቃናት ለዛቲ ወለትየ ወሀብክዎ ለዝንቱ ብእሲ ትኩኖ ብእሲተ፡

የዚያች ልጅ አባት አለቆችን እንዲህ ይበላቸው፡ ሚስት ትሆነው ዘንድ ይችን ልጄን ለዚህ ሰው ሰጥቼው ነበር፤

፲፯፤ ወሶበ ጸልኣ ይእዜ አምጽአ ላቲ ነገረ ምክንያት ወይቤ ኢረ ከብኩ ድንግልናሃ ለወለትከ ወናሁ ዝንቱ ውእቱ ልብሰ ድንግልናሃ ለወለትየ፡

ከርሷ ጋር ብዙ ዘመን ከኖረ በኋላ ቢጠላት የልጅህን ድን ግልናዋን አላገኘሁም ብሎ ምክንያት አመጣባት፡ እነሆ የልጄ የድንግልናዋ ደም የፈ ሰሰበት ልብስ ይኸውላችሁ ይበላቸው፤

ወይስፍሕዎ ለውእቱ ልብስ ቅድመ ሊቃናት ዘይእቲ ሀገር፡

ያንንም ልብስ አባት እናቷ በዚያች አገር አለቆች ፊት ይዘርጉት፤

፲፰፤ ወይእኀዝዎ ለውእቱ ብእሲ ሊቃናተ ይእቲ ሀገር ወይጌሥጽዎ፡

ያንንም ሰው የዚያች አገር አለቆች ይዘው ይሥሩት ይቆ ጡት፤

፲፱፤ ወይኅሥእዎ ምእተ ሰቅለ ወይሁብዎ ለአቡሃ ለይእቲ ወለት እስመ አውፅአ ስመ እኩየ ላዕለ ድንግለ እስራኤል ወትከውኖ ሎቱ ብእሲተ ወኢይክውኖ ኃዲጎታ መጠነ ሕያው ውእቱ፡

በእስራኤል ድንግል ላይ ክፉ ስም አውጥቷልና ማለት ድን ግልናዋን ካገኘ በኋላ አላገ ኘሁባትም ብሏልና ሹማም ንቱ ከሱ መቶ የብር ወቄት ተቀብለው ለዚያች ልጅ አባት ይስጡት ፤ ከዚያም በኋላ



ለሱ በግድ ሚስት ትሁነው፡ በሕይወተ ሥጋ ባለበት ዘመን ሁሉ እሷን መፍታት አይገባውም፤

፳፤ ወለእመሰ እሙነ ኮነ ዝንቱ ነገር ወኢተረክበ ድንግልናሃ ለይ እቲ ወለት ያውፅእዋ ኀበ ኆኅተ ቤተ አቡሃ ወይወግርዋ በእዕባን ሰብአ ይእቲ ሀገር፡

ነገር ግን ይህ ነገር እውነት ቢሆን የዚያች ልጅ ድንግል ናዋ ባይገኝ ከአባቷ ቤት ደጃፍ አውጥተው የዚያች አገር ሰዎች በደንጊያ መት ተው ይግደሏት፤

፳፩፤ እስመ ገብረት ዕበደ በውስተ ደቂቀ እስራኤል ወአዘመወት ቤተ አቡሃ ወአዕዓለት ወታሴስሉ እኩየ እምውስቴትክሙ፡

በእስራኤል ልጆች መካከል ስንፍናን አድርጋለችና ማለት ሕጓን አልጠበቀችምና ያባቷ ንም ወገን አሰስናለችና፡ ቤተ ዘማም አሰኝታለችና፡ እንዲ ህም አድርጋችሁ ክፉውን ሁሉ ከናንተ አርቁ፤

፳፪፤ ወለእመበ ዘተረክበ ብእሲ እንዘ ይሰክብ ምስለ ብእሲተ ብእሲ ይቅትልዎሙ ለክልኤሆሙ ለው እቱኒ ብእሲ ዘሰከበ ምስሌሃ ወለይእቲኒ ብእሲት ወታሴስሉ እኩየ እምእስራኤል፡

ከሰው ሚስት ደርሶ የተገኘ ሰው ቢኖር ያችን ሴትና ያን የደረሰባትን ሰው ሁለቱንም ሁሉ ይግደሏቸው፡ እንዲህ እያደረጋችሁ ከእስራኤል ክፉ ክፉውን አጥፉ፤

፳፫፤ ወለእመበ ወለት ድንግል እንተ ፍኅርት ይእቲ ለብእሲ ወረ ከባ ካልእ ብእሲ በውስተ ሀገር ወሰከበ ምስሌሃ፡

ለሰው የታጨች ድንግል ልጅ ብትኖር ሌላ ሰው በሀገር ቤት አግኝቷት ተስማምተው ቢደርስባት፤

፳፬፤ ለክልኤሆሙ ያውፅእዎሙ ኀበ አንቀጸ ለይእቲ ሀገር ወይወ ግርዎሙ በእዕባን ወይቅትልዎሙ ለወለትኒ እስመ ኢጸርሐት በው ስተ ሀገር ወለውእቱኒ ብእሲ እስመ አኅሠራ ለብእሲተ ካልኡ ወአሰስሉ እኩየ እምውስቴትክሙ፡

ጩኸት አላሰማችምና ያችን ልጅ እሱም የባልንጀራውን ሚስት አጎሳቍሏልና ያንንም ሰው ወደ አደባባይ አውጥ ተው በደንጊያ መትተው ይግ

www.ethiopianorthodox.org

ደሏቸው፣ እንዲህም እያደረ ጋችሁ ከናንተ ክፉ ክፉውን አጥፉ፤

፳፬፤ ወለእመሰ በገዳም ረከባ ብእሲ ለወለት እንተ ፍኅርት ይእቲ ወተኃየላ ወሰከበ ምስሌሃ ቅትልዎ ለዝኩቱ ዘሰከበ ምስሌሃ ለባሕቲቱ፣

የታጨችውን ሴት ልጅ አንድ ሰው በምድረ በዳ አግኝቶ ተበረታትቶ ያስ ፈቃዷ ቢደ ርስባት ግን ያን ሰው ብቻ ውን ግደሉት፤

፳፭፤ ወለወለትሰ አልቦ ዘትሬስይዋ እስመ አልባቲ ጌጋይ በዘት መውት ይእቲ ወለት ከመ ሶበ ይትነሣእ ብእሲ ላዕለ ካልኡ ወይቀትሎ ከማሁ ውእቱ ዝንቱ ነገር፣

በምትሞት ገንዘብ የምትሞት በት በደል የለባትምና ያችን ልጅ ግን የምታደርጓት ነገር የለም ፤ አንድ ሰው በጠላት ነት ተነሥቶ ባልንጀራውን እንዲገድለው በምድረ በዳ አግኝቶ ያስውድ በግድ ደር ሶባታልና፤

፳፮፤ እስመ በገዳም ረከባ ወጸር ሐት ይእቲ ወለት እንተ ፍኅርት ይእቲ ወአልቦ ዘይረድኣ፣

በዱር በገደል ሸምቆ አግኝቷ ታልና ያችም ልጅ ብትጮህ የሚረዳት አላገኘችምና በደል የለባትም፤

፳፯፤ ወለእመቦ ዘረከበ ወለተ ድንግለ እንተ ኢኮነት ፍኅርተ ወተ ኃየላ ወሰከበ ምስሌሃ ወረከብዎ፣

ያልታጨችውን ድንግሊቱን ልጅ አግኝቶ ተበረታትቶ ደር ሶባት ያገኙት ሰው ቢኖር፤

፳፰፤ ይሁቦ ለአቡሃ ውእቱ ብእሲ ዘሰከበ ምስሌሃ ለይእቲ ወለት ሃምሳ ዲድርክመ ብሩር ወትከውኖ ሎቱ ብእሲተ ወኢይከውኖ ይኅድጋ መጠነ ሕያው ውእቱ እስመ አኅ ሠራ፣

ያችን ልጅ በግድ የደረሰባት ያ ሰው ለአባቷ ካሳውን አምሳ ወቄት ብር ይስጠው፣ እሷንም በግድ፣ ያግባትና ሚስት ትሁነው፣ አጎስቍ ሏታልና ባለበት ዘመን ሁሉ አይፍታት፤

፳፱፤ ወኢይንሣእ ብእሲ ብእሲተ አቡሁ ወኢይክሥት ኀፍረተ አቡሁ፣

ሰው ከእንጀራ እናቱ አይድረስ፣ የአባቱንም ኃፍረት አይግ ለጥ፣ ያባቱንስ ሚስት ምንጊ



ዜም አያገባም፣ ብሎ አባቱ ከደረሰባት ሴት አይድረስ፣ ይህን አድርጎ ቢገኝ ያባቱን ኃፍረት መግለጡ ነውና፡፡

## ምዕራፍ ፳፫

፩፤ ወኢይባእ ዘቦቱ ነውር ወዘም ቱር ውስተ ቤተ እግዚአብሔር ከመ ኢያዘሙ ቤተ እግዚአብ ሔር፣

ነውር ነቀፋ ያለበት፣ ሰውነ ቱም በማናቸውም ምክንያት የጎደለ ሰው ቤተ እግዚአብ ሔርን እንዳያስነቅፍ ወደ ቤተ እግዚአብሔር አይግባ፤

፪፤ ወኢይባእ አሞናዊ ወሞዓባዊ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር እስከ ሣልስ ወራብዕ ትውልድ ወእስከ ዐሥር ኢይባእ ቤተ እግዚአብሔር ወእስከ ለዓለም፤

ከሞዓብና ከአሞን ልጆች ወገን የተወለደ እስከ ሦስትና እስከ አራት፣ እስከ ዓሥርም ትውልድ ቢሆን መሥዋዕት ለማቅረብ ወደ ቤተ እግዚአብ ሔር አይግባ፣ ካልተመለሰም እስከ ዘለዓለም ድረስ አይግባ፤

፫፤ እስመ ኢተቀበሉክሙ በእክል ወበማይ ውስተ ፍኖት አመ ወፃእ ክሙ እምግብጽ፤ ወእስመ ተዐሰ ብዎ ለበለዓም ወልደ ቢዖር ከመ ይርግምክሙ፤

ከግብጽ በወጣችሁ ጊዜ በጎዳና ሳላችሁ በእህል በውሀ አልተቀበሏችሁምና፣ ይረግማ ችሁም ዘንድ የቤዖር ልጅ በለዓምን በገንዘብ ገዝተው ታልና፤

፬፤ ወኢፈቀደ እግዚአብሔር ከመ ይስምዖ ለበለዓም ቃሎ ወሜጣ እግዚአብሔር ለመርገሙ ውስተ በረከት እስመ አፍቀረከ እግዚአ ብሔር አምላክከ፣

ነገር ግን እግዚአብሔር የበለ ዓምን ቃሉን ሊሰማው አልወ ደደም፣ ፈጣሪህ እግዚአብሔር አንተን ወዶሃልና እርግማኑን ወደበረከት መለሳት፤

፭፤ ወኢትትናገሮሙ ሰላመ በዘይ ደልዎሙ በኵሉ መዋዕሊከ ለዓ ለም፤

ባለ በዘመንህ ሁሉ ለዘለዓ ለሙ ሰላምታ በሚገባቸው ገንዘብ ፍቅር አንድነትን አት ናገራቸው፤

፮፤ወኢታስቈርሮ ለኤዶማዊ እስመ እኁከ ውእቱ ወኢታስቈርሮ ለግብጻዊ እስመ ፈላሴ ኮንከ በው ስተ ምድሮሙ፣

www.ethiopianorthodox.org

ወንድምህ ነውና የኤሳውን ልጅ አትጸየፈው፤ በአገራቸው ስደተኛ ሁነህ ኑረሃልና የግብጽንም ሰው አትጸየፈው።

፯፡ ወደቂቅ ለእመ ተወልዱ ሎሙ በሣልስ ትውልድ ይባኡ ቤተ እግዚአብሔር፡

ለኤዶምያስ ለግብጽ ሰዎች ልጆች ቢወለዱላቸው ግን በሦስተኛው ትውልድ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ይግቡ።

፰፡ ወለእመ ወፃእከ ትጽብዖሙ ለፀርከ ተዐቀብ እምኵሉ ቃል እኩይ፤

ጠላቶችህን ልታጠፋ ብትወጣ ከክፉ ነገር ሁሉ ተጠበቅ።

፱፡ ወለእመቦ እምውስቴትክሙ ብእሲ ዘኢኮነ ንጹሐ እምስዕቡተ ዘሌሊት ይፃእ አፍአ እምትዕይንት ወኢይባእ እምትዕይንት ፡

ከናንተ ወገን ከሌሊት ዝንየት ሕልመ ኃጢአት ንጹሕ ያይደለ ሰው ቢኖር ከከተማ ውጭ ይዋል እንጂ ወደ ከተማ አይግባ።

፲፡ ወፍና ሠርከ ተሐፂቦ ሥጋሁ በማይ ዐሪቦ ፀሐይ ይባእ ውስተ ትዕይንት፡

ፀሐይ ከገባ በኋላ ግን ማታ ጊዜ ሰውነቱን በውሀ ታጥቦ ወደ ከተማ ይግባ።

፲፩፡ ወአሐደ መካነ ረሲ ለከ አፍአ እምትዕይንት ኀበ ትወፅእ ህየ፤

የምትነፃፀበትን ቦታ ከከተማው በውጭ አንድ ቦታ አብጅ።

፲፪፡ ወዕፀ ንዋፅ ለከ ውስተ ቅናትከ ወሶበ ነበርከ ቀሠፋየ ትከሪ ወትነሥእ ወትደፍን ኃፍረተከ፤

በመታጠቂያህም መኳቻ (አንካሴን) ያዝ፤ እዳሪም በተቀመጥህ ጊዜ ቆፍረህ ተቀመጥ፤ አፈርም አምጥተህ ኃፍረትህን ሠውር።

፲፫፡ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ያንሶሱ ውስተ ትዕይንትከ ከመ ያድኅንከ ወያግብኦሙ ለፀርከ ውስተ እዴከ ቅድመ ገጽከ፤

ያድንህ ዘንድ ጠላቶችህንም በፊትህ በእጅህ ይጥልልህ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በከተማህ ይመላለሳልና።

ወትኩን ቅድስተ ተዓይኒከ ከመ ኢታስተርኢ ውስቴትከ ዘኮነ ኃፍረተ ወይትመየጥ እምኔከ ወየኃድገከ፤

የተደረገው ኃፍረትህ እንዳይታይ ከተማህ የነጻች ትሁን፤ እንዲህ ካልሆነ እግዚአብሔር በረድኤት ይለይሃልና።



፲፬፡ ወኢታግብእ ለገብር ኀበ እግዚኡ እምድኅረ ተሠይጠ ኀቤከ ይንበር ምስሌከ ኀበ አደሞ ወኢትግፍዖ፤

ኮበላይ ባሪያ፤ ኮብልሎ መጥቶ በአንተ ዘንድ ከተገዛ በኋላ ሳታስታርቅ ወደጌታው አትመልሰው፤ ከወደደህ ከአንተ ጋር ይኑር እንጂ፤ ከአንተ ጋርም ሲኖር መከራ አታጽናበት።

፲፭፡ ወኢትኩን ዘማ እምአዋልደ እስራኤል ወኢይኩን ዘማዊ እምደቂቀ እስራኤል፤

ከእስራኤል ሴቶች ልጆች አንዷ ስንኳ ሴሰኛ አትሁን፤ ከእስራኤል ወንዶች ልጆችም አንዱ ስንኳ ሴሰኛ አይሁን።

፲፮፡ ወአልቦ ዘያገብእ ጸባሕተ እምእስራኤል፤

ከእስራኤል ለባዕድ ሰው የሚገብር የለም።

፲፯፡ ወኢታብእ ደነሰ ዘማ ወኢቤዛ ከልብ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር አምላክከ በበይነ ኵሉ ብፅዓት እስመ ርኩሳን እሙንቱ በኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ክልኤሆሙ፤

ስለ ተሳልኸው ስለት ሁሉ የውሻ ዋጋና የሴሰኛ ሴት ዋጋ ወደ ቤተ እግዚአብሔር አታግባ፤ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ዘንድ እሊህ ሁለቱ የረከሱ ናቸውና።

፲፰፡ ወኢትትሌቀይ እምቢጽከ ኢርጸ ወርቅ ወኢርጸ እክል ወኢርጸ ኵሉ ዘኮነ ትትለቃሕ ለቢጽከ ለእመ ተለቅሐከ ቢጽከ፤

ባልንጀራህ ቸግሮት ቢበደርህ ከባልንጀራህ የእህልና የወርቅ አራጣ ግዳጁ የሆነውን ሁሉ አራጣ አትቀበል።

፲፱፡ ወእምነኪርከ ትትረደይ ወእምቢጽከስ ኢትትረደይ ከመ ይባርከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ግብርከ ላዕለ ምድር እንተ ትበውእ ውስቴታ ከመ ትትዋረሳ፤

ከአሕዛብ ግን አራጣ ተቀበል፤ ልትወርሳት ወደምትገባባት አገር በሥራህ ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ያከብርህ ዘንድ ከባልንጀራህ ግን አራጣ አትቀበል።

፳፡ ወለእመ በፃዕከ ብፅዓተ ለእግዚአብሔር ኢታጕንዲ ገቢሮቶ እስመ ተኃሥሦ ይትኃሠሠከ እግዚአብሔር አምላክከ ወይከውን ኃጢአተ ላዕሌከ፤

ለእግዚአብሔር ይህን እሰጣለሁ ብለህ ብትሳል፤ የተሳል

www.ethiopianorthodox.org

ኸውን አታስቀር፣ ፈጣሪህ እግ ዚአብሔር ፈጽሞ ይመራመ ርሃልና፣ በአንተም ዕዳ በደል ይሆንብሃልና፤

፳፩፤ ወለእመሰ ኢፈቀድከ ትብፃዕ አልብከ ኃጢአት፣

ትሳል ዘንድ ባትወድ ግን ዕዳ የለብህም፤

፳፪፤ ዳዕሙ እምከመ ወፅአ እምከ ናፍሪከ ተዐቀብ ወግበር በከመ በፃ ዕከ ተሀብ ለእግዚአብሔር አምላ ክከ በከመ ነበብከ በአፉከ ከማሁ ግበር፣

ነገር ግን እሰጣለሁ ብለህ ከአ ንደበትህ ከወጣ በኋላ ተጠን ቀቅ፣ ለፈጣሪህ ለእግዚአብ ሔር ትሰጥ ዘንድ እንደ ተሳልህ ስለትህን ስጥ፣ በአንደበትህም እንደ ተናገርከ እንደዚያው አድርግ፤

፳፫፤ ወለእመ ቦእከ ውስተ ገራህተ ካልዕከ መሐው ሠዊተ በእደዊከ ወማዕፀደ ኢታብእ ውስተ ገራህተ ካልእከ፣

ወደ ባልንጀራህም እርሻ ብት ገባ እሸት በጅህ አሽተህ ብላ፣ ነገር ግን ከባልንጀራህ አዝ መራ በማጭድ አትጨድ፤

፳፬፤ ወለእመ ቦእከ ውስተ ዐፀደ ወይኑ ለካልዕከ ብላዕ አስካለ እስከ ትጸግብ ነፍስከ ወውሰተ ሙዳይ ባሕቱ ኢትደይ፣

ወደ ባልንጀራህ የወይን ቦታ ብትገባ ሆድህ እስኪጠግብ እሸቱን ብላ፣ ወደ አገልግልህ ግን አታግባ ማለት ወደ ቤትህ አትውሰድ።

## ምዕራፍ ፳፬

፩፤ ወለእመቦ ዘነሥአ ብእሲተ ወነበረ ምስሌሃ ወእምዝ ለእመ ኢረከበት ሞገሰ በኀቤሁ እስመ ረከበ ኃፍረተ ላዕሌሃ፣

ሚስት አግብቶ ከርሷ ጋር የኖረ ሰው ቢኖር በርሷ ኃፍ ረት የሆነ ነገር አግኝቷልና ከዚህ በኋላ በርሱ ዘንድ ባለ ሟልነትን ባታገኝ፤

ይጽሐፍ ላቲ መጽሐፈ ኅዳጋቲሃ ወይመጥዋ ውስተ እዴሃ ወያው ፅአ እምነ ቤቱ፣

የምትፈታበትን ነውር የሚገ ልጽ ደብዳቤ ጽፎ በእጇ ይስ ጣት፣ ከዚያም ወዲያ ከቤቱ አስወጥቶ ይስደዳት፤

፪፤ ወሖረት ወአውሰበት ካልአ ብእሴ ወእምዝ ጸልኣ ውእቱኒ ብእሲ



ደኃራዊ ወጸሐፈ ላቲ መጽሐፈ ኅዳጋቲሃ ወመጠዋ ውስተ እዴሃ ወአውፅኣ እምቤቱ፣

ሂዳም ሌላ ሰው ብታገባ፣ ከዚህም በኋላ ያገባት ሰው ቢጠላት፣ የምትፈታበትን የነ ውር ደብዳቤ ጽፎ በእጇ ሰጥ ቶ ከቤቱ ቢያስወጣት፤

፫፤ ወለእመኒ ሞተ ውእቱ ብእሲ ደኃራዊ ዘነሥአ ሎቱ ትኩኖ ብእሲተ፣

ሚስት ትሆነው ዘንድ በኋላ ያገባት ያ ሰው ቢሞትም፤

፬፤ ኢይክሎ ለዝክቱ ብእሲ ቀዳማዊ ዘአውፅኣ ከመ ይግባእ ላዕሌሃ ወይንሥኣ ሎቱ ትኩኖ ብእሲተ እምድኅረ ረኰሰት፣

ከጐሰቈለች በኋላ ቀድሞ ለፈታት ለዚያ ሰው ወደርሷ ይመለስ ዘንድ ሚስት ልትሆ ነው አይገባውም፤

እስመ ርኵስ ውእቱ ዝንቱ ነገር በኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ወኢ ታርኵሱ ምድረ ዘይሁበክሙ እግ ዚአብሔር አምላክክሙ ርስተ፣

ይህ ነገር በፈጣሪህ በእግዚአብ ሔር ዘንድ የሚያጸይፍ ነውና ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ርስት

አድርጎ የሰጣችሁን ምድርም አታጕስቁሉ፤

፭፤ ወለእመቦ ዘነሥአ ብእሲተ ግብተ ኢይፃእ ፀብዓ ወአልቦ ምን ተኒ ዘያቀትውዎ፤

ድንገት ሚስት ያገባ ሰው ቢኖር ወደ ሰልፍ አይውጣ፣ ዘመቻ ፈሪ ብለው ምንም ምን ግብር አያስገብሩት፤

ድኅኑን ውእቱ ቤቱ አሐተ ዓመተ ከመ ይትፌሣሕ ምስለ ብእሲቱ እንተ አውሰባ፣

ካገባት ከሚስቱ ጋር ደስ ይለው ዘንድ ቤቱ አንድ ዓመት ከግ ብር ነጻ ይሁን፤

፮፤ ወኢትአንዝ ማሕረፀ ወኢመ ድሔ ማሐረፅ እስመ መብዕለ ነፍስ ውእቱ ወኢየአንዝዎ፣

መጅንና ወፍጮውን መያዣ አድርገህ አትያዝ፣ የሰውነት መመገቢያ ነውና አይያዙት፤

፯፤ ወለእመቦ ዘተረክበ ብእሲ ዘሰረቀ ነፍሰ እምአኃዊሁ እምደ ቂቀ እስራኤል ወተአገሎ ወሤጠ ለይቅትልዎ ለውእቱ ሰራቂ ወታ ሴስሉ እኩየ እምውስቴትክሙ፣

ከወንድሞቹ ከእስራኤል ልጆች ሰውን አፍኖ የሰረቀ፣ ቀምቶም

www.ethiopianorthodox.org

የሸጠ ሰው ቢኖር ያን የሰረቀውን ሰው ይግደሉት፤ እንዲህም እያደረጋችሁ ከእናንተ ክፉ ክፉውን አርቁ፤

፰፡ ወዑቅ ርእሰከ በእንተ ትእምርተ ለምጽ ተዓቀብ ጥቀ ከመ ትግበር ኵሎ ሕገ ዘይቤሉከ ካህናት ወሌዋውያን በከመ አዘዝኩከ ተዓቀብ ዘትገብር፡

ስለ ለምጽ ምልክት ለራስህ ዕወቅ፤ ሌዋውያንና ሊቃነ ካህናት ያስተማሩህን ሕግን ሁሉ ታደርግ ዘንድ ፈጽመህ ተጠበቅ፤ እንዳዘዝኩህ የምታደርገውንም ጠብቅ፤

፱፤ ወተዘከር ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር አምላክከ ላዕለ ማርያም በፍኖት አመ ወፃእክሙ እምግብጽ፤

ከግብጽ በወጣችሁ ጊዜ በጎዳና ሳለህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በማርያም እኅተ ሙሴ ላይ ያደረገውን አስብ፤

፲፤ ወለእመቦ ዘይፈድየከ ካልእከ ዕዳ ዘኮነ ኢትባእ ውስተ ቤቱ ከመ ተአኀዝ አኀዜከ ዳዕሙ አፍኣ ትቀውም፡

ባልንጀራህ የሚከፍልህ ዕዳ የሆነ ገንዘብ ቢኖር በውጭ ቁም እንጂ መያዣህን ትይዝ ዘንድ ወደ ቤቱ አትግባ፤

፲፩፡ ወብእሲ ዕዳከ ዝኩ ዘይፈድየከ ለሊሁ ያወፅእ አኀዜከ አፍኣ ኀቤከ፡

ዕዳህን የሚከፍልህ ያ ሰው ግን መያዣህን አንተ ወዳለህበት ወደ ውጭ ያውጣልህ፤

፲፪፤ ወለእመ ብእሲ ነዳይ ውእቱ ኢታቢት አኀዞ ኀቤከ፤

ያ ሰው ድሀ ከሆነ ግን መያዣውን ከአንተ ዘንድ አታሳድር፤

፲፫፤ ወታገብእ ሎቱ አኀዞ ዘእንበለ ይዕርብ ፀሐይ ወይበይት በልብሱ ወትትባረክ ወይከውንከ ምጽዋተ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ፤

ፀሐይ ሳይገባ መያዣውን መልስለትና ልብሱን ለብሶ ይደር፤ እንዲህ ብታደርግ ትከብራለህ፤ በፈጣሪህ በእግዚአብሔርም ፊት ከምጽዋት ይቈጠርልሃል፤

፲፬፤ ወኢታዓምፆ ዕስቦ ለዓሳብ ለነዳይ ዘነጡዕ ውእቱ እምአኃዊከ አው እምግዩራን ዘውስተ ሀገርከ፤

ከወንድሞችህ ወይም በሀገርህ ካሉ ስደተኞች ገንዘብ ያጣ ድሀ



የሆነ የምንደኛውን ደመወዙን አትክዳው፤ አሌ አትበለው፤

፲፭፤ እንተ ጸብሐት ትሁቦ ዕስቦ ወኢታዕርብ ፀሐየ ላዕሌሁ እስመ ነዳይ ውእቱ ወውእቱ ተስፋሁ ወኢይግዓር ላዕሌከ ኀበ እግዚአብሔር ወኢይኩንከ ኃጢአተ፤

ድሀ ነውና፤ አለኝታውም እሱ ነውና በአንተ ወደ እግዚአብሔር እንዳይጮህ ዕዳም እንዳይሆንብህ ፀሐይ ሳይገባ እየነጋ እየመሸ ደመወዙን ስጠው፤

፲፮፤ ወኢይመወቱ ወላድያን በበይነ ውሉዶሙ ወኢይመወቱ ውሉድ በበይነ ወላድያኒሆሙ አሐዱ አሐዱ በበይነ ጌጋዩ ይመውት፤

እናት አባቶቻቸው በልጆቻቸው በደል አይሞቱም፤ ልጆችም በእናት በአባቶቻቸው በደል አይሞቱም፤ አንዱም አንዱም በበደለው በደል ይሞታል እንጂ፤

፲፯፤ ወኢትሚጥ ፍትሐ ግዩር ወዘእጓለ ማውታ ወዘዕቤር፤

እናት አባት የሞቱበትን የስደተኛውን የባልቴቷንም ፍርድ በገንዘብ አትለውጥ፤

፲፰፤ ወተዘከር ከመ ገብር አንተ በምድረ ግብጽ ወቤዘወከ እግዚአብሔር አምላክከ እምህየ ወበበይነ ዝንቱ እኤዝዘከ አነ ትግበር ዘንተ ነገረ፤

በግብጽ አገር አንተ ተገዥ እንደ ነበርህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ከዚያ እንዳዳነህ አስብ፤ ስለዚህ ይህን ነገር ታደርግ ዘንድ አዝዝሃለሁ፤

፲፱፤ ወለእመ ዓፀድከ እክለ ገራህትከ ወረሳዕከ አሐተ ከልስስተ ውስተ ገራህትከ ኢትግባእ ከመ ትንሣእ፤

የእርሻህን አዝመራ ብታጭድ አንዲቱን ነዶ በእርሻህ ብትዘነጋ ያችን ታነሣት ዘንድ ወደ ኋላ አትመለስ ፤

ለግዩር ወለእጓለ ማውታ ወለዕቤር ይኩን ከመ ይባርከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ግብረ እደዊከ፤

በእጅህ ሥራ ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔረ ያከብርህ ዘንድ እናት አባቱ ለሞቱበት ልጅና ለስደተኛ ለመጻተኛ ለባልቴቲቱም ይሁን፤

፳፤ ወለእመኒ ቀሠምከ ዐፀደ ወይንከ ኢትድግም ተመይጦ ድኅሬከ ከመ ታስተናጽሕ ቀሢመ ለግዩር ወለዕጓለ ማውታ ወለዕቤር ይኩን፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይንህንም ብትለቅም አጥርተህ ትለቅም ዘንድ ወደ ኋላ አትመለስ፣ እናት አባቱ ለሞቱበት ልጅና ለስደተኛ ረዳት ለሌላት ባልቴትም ይሁን እንጂ፤

፳፩፤ ወለእመኒ ቀሠምከ ዘይተከ ኢትድግም ተመይጦ ድኅሪከ ከመ ታስተናጽሕ ቀሢመ ለግዩር ወለእጓለ ማውታ ወለዕቤር ይኩን ፣

ዘይትህንም በምትለቅምበት ጊዜ አጥርተህ ትለቅም ዘንድ ዳግመኛ ወደኋላህ አትመለስ፣ እናት አባት ለሞቱበት ልጅና ለስደተኛ ለባልቴቲቱም ይሁን እንጂ፤

፳፪፤ ወተዘከር ከመ ግዩር አንተ በምድረ ግብጽ ወቤዘወከ እግዚአብሔር አምላክከ እምህየ ወበበይነ ዝንቱ እኤዝዘከ አነ ከመ ትግበር ዘንተ ነገረ፣

በግብጽ አገር ሳለህ አንተ ስደተኛ እንደ ነበርህ አስብ፣ ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ከዚያ እንዳዳነህ አስብ፣ ስለ ዚህ ይህን ነገር ታደርግ ዘንድ እኔም አዝዝሃለሁ።

## ምዕራፍ ፳፭

፩፤ ወለእመ ኮነ ተስናን በማዕከለ ሰብእ ወመጽኡ ውስተ ዓውድ ወተሳነኑ ወአርትዑ ለዘይረትዕ ወዓዕልዉ ለዘይጌወግ፣

በሰዎች መካከል ጠብ ክርክር ቢደረግ ሰዎቹም ወደ ሸንጎ መጥተው ቢከራከሩ እውነቱን እውነት፣ ሐሰቱን ሐሰት ብላችሁ ፍረዱ፤

፪፤ ወለእመ ኮነ ለተቀሥፎ ያንብርዎ ቅድመ ዐውድ ለገዘኩ ለዘይጌወግ ወይቅሥፍዎ በቅድሜሆሙ በአምጣነ አበሳሁ ፣

ዕዳው ለመገረፍ የሚያበቃው ቢሆን ያን የሚገረፈውን ሰው በሸንጎ አስቀምጠው የበደለውን ያህል በፊታቸው ይግረፉት፤

፫፤ አርብዓ ይቅሥፍዎ በኍልቍ ወኢያብዝኑ እምኔሁ ወለእመ አብዝኑ ቀሢፎቶ እምዝንቱ አስተኃፈርከ እኅዋከ በቅድሜከ፣

በቍጥር አርባ ይግረፉት፣ ከአርባ ግን አትርፈው አይግረፉት፣ ከአርባ አትርፈው ቢገርፉት ግን በፊትህ ወንድምህን አሳፈርኸው ማለት አይገባም፤

፬፤ ወኢትፍጽሞ አፉሁ ለላሕም ሶበ ታከይድ እክለከ፣

እህልህን በወቃህ ጊዜ (በምታበራይበት ጊዜ) በሬውን አፉን አትሠረው፤



፭፤ ወለእመቦ አኃው እለ ይነብሩ ኅቡረ ብእሲ ምስለ እኁሁ ወሞተ አሐዱ እምኔሆሙ ወአልቦ ውሉድ ኢታውስብ ብእሲቱ ነኪረ ብእሴ እኁሁ ለምታ ለያውስበ ወውእቱ ለይባእ ኀቤሃ ወሎቱ ትኩኖ ብእሲቶ ወይንበር ምስሌሃ፤

በአንድነት የሚኖሩ ወንድማማች ቢኖሩ ከነሳቸው አንዱ ቢሞት ልጅ ባይኖረው የባሏ ወንድም ያግባት እንጂ ሚስቱ ሌላ ሰው አታግባ ፤ የባሏ ወንድም እሷ ወዳለችበት ይሂድና ሚስት ትሁነው ከርሷ ጋራም ይኑር፤

፮፤ ወሕፃንሰ ዘተወልደ ይኩን ለዘሞተ ወይሰመይ በስሙ ወኢይደመሰስ ስሙ እምእስራኤል፣

የተወለደው ልጅ ግን ለሞተው ሰው ይሁን፣ ከእስራኤል ስሙ እንዳይጠፋ በስሙ ይጠራ፤

፯፤ ወለእመ ኢፈቀደ ውእቱ ብእሲ ያውስባ ለብእሲተ እኁሁ ወተዓርግ ይእቲ ብእሲት ኀበ ሊቃናት ወኀበ አንቀጽ ወትብል ኢይፈቅድ እኁሁ ለምትየ ያቅም ስመ እኁሁ ውስተ እስራኤል፣

ያ ሰው ግን የወንድሙን ሚስት ሊያገባ ባይወድ ያች ሴት በአደባባይ ወዳሉ ሽማግሌዎች ወጥታ የባሌ ወንድም በእስራኤል ዘንድ የወንድሙን ስም ያስጠራ ዘንድ አልወደደም ትበል፤

፰፤ ወይጸውዕዎ ሊቃናተ ሀገር ወይበልዎ ኢትፈቅድኑ ታቅም ዘርአ ለእኁከ ውስተ እስራኤል ወይበል ቀዊሞ ኢይፈቅድ አውስባ፣

ያነን ሰው የአገር ሽማግሌዎች ጠርተው ከእስራኤል ወገን ለወንድምህ ልጅ ልትተካ አትወድምን ይበሉት፣ እሱም ቁሞ አገባት ዘንድ አልወድም ይበል፤

፱፤ ወትቅረብ ይእቲ ብእሲት ኀቤሁ ቅድመ ሊቃናተ ይእቲ ሀገር ወትፍታሕ አሣዕኖ ዘአሐቲ እግሩ ወትትፋዕ ውስተ ገጹ ወትብል ከመዝ ይግበርዎ ለብእሲ ዘኢይፈቅድ ይሕንፅ ቤተ እኁሁ፣

ያች ሴት በዚያች አገር ሽማግሌዎች ፊት ወደሱ ቀርባ የአንዲት እግሩን ጫማ ፈትታ በፊቱ ምራቋን እንትፍ ትበልበት የወንድሙን ቤት ሊሠራ የማይወደውን ሰው እንዲህ ያድርጉት ትበል፤

፲፤ ወይሰመይ ስሙ በውስተ እስራኤል ቤተ ፍቱሐ አሣዕን፣

www.ethiopianorthodox.org

ስሙም በእስራኤል ዘንድ ጫማውን ያወለቀ ሰው ወገን ይባል፤

፲፩፡ ወለእመ ተበዓሱ ክልኤቱ ዕደው ኅቡረ ብእሲ ምስለ ካልኡ ወመጽአት ብእሲቱ ለአሐዱ እምኔሆሙ ከመ ታኅድጎ ለምታ እምእደ ዘባጢሁ ወአልዓለት እዴሃ ወአኀዘቶ በእዴሃ እስኪቶ፡

ሁለት ሰዎች አንዱ ከአንዱ ጋራ ቢጣሉ፣ ከሚመታው ሰው እጅ ባሏን ታስጥለው ዘንድ ከነሱ የአንዱ ሚስት መጥታ እጇን ዘርግታ ብልቱን ብትይዘው፤

፲፪፤ ለይምትሩ እዴሃ ወኢትምሐክ ዐይንከ፣

እጇን ይቍረጧት፣ ዓይንህም አትራራላት፤

፲፫፤ ወኢታንብር ለከ መዳልወ ንዑሰ ወዐቢየ፣

ለአንተ ታላቅና ታናሽ ሚዛን አታኑር ማለት በውነተኛ ሚዛን አበድረህ በአባይ (በሐሰተኛ) ሚዛን አትቀበል፤

፲፬፤ ወኢትግበር ለከ በውስተ ቤትከ መስፈርተ ንዑሰ ወመስፈርተ ዐቢየ፤

በቤትህም ታላቅና ታናሽ መስፈሪያ አታድርግ ማለት በታናሽ መስፈሪያ አበድረህ በታላቅ መስፈሪያ አትቀበል፤

፲፭፤ መዳልወኒ ርቱዓ ወጽዱቀ ይኩንከ ከመ ታብዝኅ መዋዕለ በምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ርስተ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ በሚሰጥህ አገር ዘመንህ ይበዛ ዘንድ ሚዛንህ የቀናና እውነተኛ ይሁን፤

፲፮፤ እስመ ርኩስ ውእቱ በኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ኵሉ ዘይገብሮ ለዝንቱ ኵሉ ዘይገብር ዓመፃ፣

ይህን የሚያደርግ በደልንም የሚሠራ ሰው በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ዘንድ የረከሰ ነውና፤

፲፯፤ ወተዘከር ኵሎ ዘገብረ ላዕሌከ አማሌቅ በፍኖት አመ ወፃእከ እምድረ ግብጽ፣

ከግብጽ ምድር በወጣህ ጊዜ አማሌቅ በጎዳና ያደረገብህን ሁሉ አስብ፤

፲፰፤ ዘከመ ተቃወመከ በፍኖት ወአምተረከ ጋዕዘከ እለ ይፃምዉ በድኅሬከ፣



ባጭር ታጥቆ፣ ዘገር ነጥቆ በጎዳና እንደ ተከራከረህ ከአንተም የደከሙትን መንገደኞች ኋላቸውን እየነጠቀ እንዳስቀረ አስብ፤

ወአንተሰ ርኁብከ ወደክምከ ወኢፈርሆ ለእግዚአብሔር አምላክከ፣

አንተ ግን ያን ጊዜ ተርበህ ደክመህ ነበር፣ አማሌቃዊም ፈጣሪህ እግዚአብሔርን አልፈራውም፤

፲፱፤ ወአመ ያዐርፈከ እግዚአብሔር አምላክከ እምኵሉ ፀርከ ዘዓውድከ ውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ትትዋረሳ ርስተ ትደመስሶ ለአማሌቅ እምታሕተ ሰማይ ወኢትርስዖ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ርስት አድርገህ ትወርሳት ዘንድ በሰጠህ ምድር በዙሪያህ ካሉ ከጠላቶችህ ባሳረፈህ ጊዜ አማሌቅን ከሰማይ በታች እልም ድርግም አድርገህ አጥፋው፣ ያደረገብህንም ነገር ሁሉ አትዘንጋው።

## ምዕራፍ ፳፮

፩፤ ወለእመ ቦእከ ውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ ትትዋረሳ ርስተ ወነበርከ ውስቴታ፣

ርስት አድርገህ ትወርሳት ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወደሚሰጥህ ምድር ብትገባ በሷም ብትኖር፤

፪፤ ትነሥእ እምፍሬ ምድርከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ ወትወዲ ውስተ ሙዳየ ቀርጠሎን ወተሐውር ውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይሰመይ ስሙ በህየ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከሰጠህ ምድር የተገኘውን ፍሬ አምጥተህ ባገልግል አድርገህ ስሙ ይጠራበት ዘንድ ፈጣሪህ ወደመረጠው ቦታ ሂድ፤

፫፤ ወትበውእ ኀበ ካህን ዘሀለወ በውእቱ መዋዕል ወትብሎ አየድዕየ ዮም ቅድመ እግዚአብሔር አምላኪየ እስመ በጻሕኩ ውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊነ ከመ የሀበነ፣

በዚያ ወራት ተሹሞ ወዳለው ካህን ገብተህ ለኛ ለልጆቻቸው ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ወደማለላቸው ምድር ደርሻለሁና በፈጣሪዬ በእግዚአብሔር ፊት ይህን እናገራለሁ በለው፤

www.ethiopianorthodox.org

፬፤ ወይነሥእ ካህን ለውእቱ ሙዳየ ቀርጠሉን እምውስተ እደዊከ ወያነብሮ ቅድመ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር አምላክከ፤

ካህኑም ያን አገልግል ከእጅህ ተቀብሎ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር መሠዊያ አንፃር ያኑረው፤

፭፤ ወትብል ቅድመ እግዚአብሔር አበውየ ወፅኡ እምድረ ሶርያ ወወረዱ ውስተ ምድረ ግብጽ ወነበሩ ህየ እንዘ ውሑዳን እሙንቱ በኍላቈሆሙ ወኮኑ በህየ ሕዝበ ዐቢየ ወመልዕ ወአብዩ ብዙኃ፤

አባቶቼ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ከሶርያ ምድር ወጥተው ወደ ግብጽ ወረዱ፤ እነሱም በቍጥራቸው ጥቂት ሳሉ በግብጽ ኖሩ፤ በዚያም ብዙ ወገን ሁነው በዓለም መሉ እጅግም ከበሩ፤

፮፤ ወሣቀዩነ ግብጽ ወአሕመሙነ ወአገበሩነ ዕፁበ ግብረ፤

የግብጽ ሰዎች ግን ፈጽመው መከራ አጸኑብን፤ የሚያስጨንቅ ሥራን አሠሩን ማለት ጭቃ መርገጥ ኖራ መውቀጥ ነው፤

፯፤ ወጸራሕነ ኀበ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ወሰምዐ እግዚአብሔር ቃለነ ወርእየ ሕማመነ ወሥራሐነ ወሥቃየነ፤

እኛም ወደ አባቶቻችን ፈጣሪ ወደ እግዚአብሔር ጮኸን ለመንን፤ እግዚአብሔርም ልመናችንን ሰምቶ መከራችንንና ድካማችንን አይቶ ፤

፰፤ ወአውፅአነ ለሊሁ እምድረ ግብጽ በእድ ጽንዕት ወበመዝራዕት ልዑል በዐቢይ ግርማ ወበዐቢይ ተአምር ወመድምም፤

እሱ በጸናች ሥልጣን በገናና ኃይል በታላቅ መፈራት በድንቅ ተአምራት ማለት፤ በዘጠኝ መቅሠፍት፤ በአሥረኛ ሞተ በኵር፤ በአሥራ አንደኛ ሥጥመት ከግብጽ አወጣን፤

፱፤ ወአብአነ ውስተ ዝንቱ መካን ወወሀበናሃ ለዛቲ ምድር እንተ ትውኅዝ ሀሊበ ወመዓረ፤

ከግብጽ አውጥቶም ወደዚህ ቦታ አገባን፤ ተድላ ደስታ የሚገኝባት ይችንም ምድር ሰጠን፤

፲፤ ወይእዜኒ ናሁ አምጻእኩ ቀዳሜ እክለ ምድርየ ዘወሀበኒ እግዚአብሔር ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ወትሰግድ ቅድመ እግዚአብሔር እምላክከ፤



አሁንም እግዚአብሔር ከሰጠን ተድላ ደስታ ከሚገኝበት ምድር የተገኘ የምድሬን እህል መጀመሪያ አመጣሁ ብለህ ተናገር፤ ቀዳምያቱንም ከሰጠህ በኋላ ከቤተ እግዚአብሔር ገብተህ ስገድ፤

፲፩፤ ወትትፌሣሕ በኵሉ በረከት ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ አንተ ወቤትከ ወሌዋዊኒ ወግዩር ዘኀቤከ፤

ያን ጊዜ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሰጠህ በረከት ሁሉ አንተን ደስ ይበልህ፤ ቤተሰቦችህም ካህኑም በአንተ ዘንድ የሚኖሩ ስደተኞቹም ደስ ይበላቸው፤

፲፪፤ ወእምከመ ፈጸምከ ዓሥሮተ ኵሉ ዓሥራት ዘእክለ ኵሉ ምድርከ በሣልስ ዓም፤

በሦስተኛው ዘመን ከምድርህ የተገኘውን እህል ሁሉ ዓሥራት አውጥተህ ከጨረስህ በኋላ፤

ወእምዝ ዘዓመ ዳግም ትዔሥር ክልኤተ ዓሥራተ ወትሁቦ ለሌዋዊ ወለግዩርኒ ወለእጓለ ማውታ ወለዕቤር ይብልዕዎ በሀገርከ ወይጽገቡ፤

ከዚህ በኋላ ሁለተኛ ዓሥራት አውጥተህ ለካህኑ፤ ለስደተኛው፤ እናት አባቱ ለሞቱበትና ለባልቴቲቱ ስጥ፤ እነሱም በሀገርህ በልተው ይጥገቡ፤ (ሐተታ) የሦስተኛውን ዓመት ከሰጠህ በኋላ የአራተኛውን ዓመት ስጥ ለማለት ዳግመ አለ፤ ይህስ አይደለም ብሎ ከዓሥር አንድ ካወጣህ በኋላ ዳግመኛ ከዘጠኝ አንድ አውጣ ሲል ነው፤ ከዓሥር አንድ የወጣውን በሀገሩ ላለው ለካህኑ ይሰጠዋል፤ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዓመት ከዘጠኝ አንድ ያወጣውን ወርቅ አድርጎ ያስቀምጠዋል፤ ለፍሪዳ መግገ ሊሆን ነው፤ በሦስተኛው ከዘጠኝ አንድ ያወጣውን እህል ውሀ አድርጎ በሀገሬ ምስካይ ላሉ ለሌዋዊ ለግዩር ያበላዋል ያጠጣዋልና እንዲህ አለ፤

፲፫፤ ወትብል በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ አንጻሕኩ ዘእቁድስ ለከ እምነ ቤትየ ወወሀብክዎ ለሌዋዊ ወለግዩር ወለእጓለ ማውታ ወለዕቤር በከመ ኵሉ ትእዛዝከ ዘአዘዝከኒ ኢተዐደውኩ ትእዛዘከ ወኢረሳዕኩ፤

www.ethiopianorthodox.org

በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ማለት በቤተ እግዚአብሔር ከገንዘቤ ለይቼ የምሰጠውን አነጻሁ ማለት አጠናቀቄ ለካህኑ፣ ለመጻተኛው፣ እናት አባት ለሞቱበት ልጅ፣ ረዳት ለሌላት ባልቴት ሰጠሁት፣ ከገንዘብህ ለይተህ ስጥ ብለህ እንዳዘዝኸኝ፣ ትእዛዝህንም አላፈረስሁም አልዘነጋሁም ብለህ ተናገር፤

፲፬፤ ወበሕማምየኒ ኢበላዕኩ እም ኔሁ ወኢሦዕኩ መሥዋዕተ ኃጢ አት እምኔሁ ለርኩስየ፣

ታምሜም ሳለሁ አማረኝ ብዬ ከዓሥራቱ አልበላሁም፣ ኃጢአትም ሠርቼ ከሱ የኃጢአት መሥዋዕት አልሠዋሁም፤ አንድም ከሱ ለጣዖት መሥ ዋዕት አላቀረብኩም፤

ወኢወደይኩ ውስተ በድን እምኔሁ ወሰማዕኩ ቃለ እግዚአብሔር አም ላኪየ ወሰማዕኩ ኵሎ ዘአዘዝከኒ፣

ከሱም የቀባሪ (የኃዘን) እን ጀራ አልበላሁም፣ የፈጣሪዬ የእግዚአብሔርን ቃል ሰማሁ፣ ያዘዝኸኝንም ሁሉ ሰማሁ፤

፲፭፤ ወነጽር እምቤተ መቅደስከ እምሰማይ ወባርክ ሕዝበከ እስራ ኤለ ወምድረኒ እንተ ወሀብከነ ዘከመ መሐልከ ለአበዊነ ከመ ተሀበነ ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ፣

በሰማይ ሁነህ ማደሪያህ ቤተ መቅደስን ተመልከት፣ ወገና ችህ እስራኤልን አክብር፣ ተድላ ደስታ የሚገኝባትን አገር ትሰጠን ዘንድ ለአባቶ ቻችን እንደማልህ ያወረስኸ ነን ከነዓንንም አክብር ብለህ ጸልይ፤

፲፯፤ ወበዛቲ ዕለት እግዚአብሔር አምላክከ አዘዘከ ከመ ትግበር ኵሎ ዘንተ ኵነኔሁ ወትዕቀብ ፍትሖ ወትግበሮ በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ፣

ይህን ሁሉ ሕግን ታደርግ ዘንድ፣ ፍርዱንም ትጠብቅ ዘንድ፣ በፍጹም ልቡናህ በፍ ጹም ሰውነትህም ታደርገው ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በዚች ቀን አዘዘህ፤

፲፯፤ ወተሐርር በፍናዊሁ ወትዕቀብ ፍትሖ ወኵነኔሁ ወትስማዕ ቃሎ፣

በሕጉ ጸንተህ ትኖር ዘንድ፣ ሕጉን ፍርዱን ትጠብቅ ዘንድ፣ ቃሉንም ትሰማ ዘንድ አዘ ዘህ፤



፲፰፤ እስመ እግዚአብሔር ኀረየከ ዮም ከመ ትኩኖ ሕዝበ ለርእሱ በከመ ይቤለከ ከመ ትዕቀብ ኵሎ ትእዛዞ ወትኩን መልዕልተ ኵሉ አሕዛብ፣

ለራሱ ወገን ትሆነው ዘንድ ሕጌን ጠብቅ ብሎ እንደ አዘዘህ ትእዛዙንም ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ፣ ከአሕዛብም ሁሉ በላይ ትሆን ዘንድ እግ ዚአብሔር ዛሬ መርጦሃ ልና፤

፲፱፤ ወገብረ ለከ ስመ ዐቢየ ወምክሐ ወክብረ ከመ ትኩን ሕዝበ ቅዱሰ ለእግዚአብሔር አምላ ክከ በከመ ይቤለከ፣

(ቅዱሳን ኩኑ እስመ ቅዱስ አነ) ብሎ እንደ ነገረህ ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ልዩ ወገን ትሆን ዘንድ መመኪ ያና መከበሪያ የሚሆን ታላቅ ስም አወጣልህ ማለት ሕዝበ እግዚአብሔር እንድትባል አደ ረገህ፡፡

## ምዕራፍ ፳፯

፩፤ ወአዘዞሙ ሙሴ ለአዕሩገ እስራኤል ወይቤሎሙ ዐቁ ከመ ትግበሩ ዘንተ ኵሎ ትእዛዘ ዘአነ እኤዝዘክሙ ዮም፣

ሙሴ የእስራኤልን ሽማግ ሌዎች እኔ ዛሬ የማዝዛችሁን ይህን ሁሉ ትእዛዝ ታደርጉ ዘንድ ዕወቁ ብሎ አዘዛቸው፤

፪፤ ወአመ ተዐድውዎ ለዮርዳኖስ ውስተ ምድር ዘይሁበክሙ እግዚ አብሔር አምላክክሙ ወታቀ ውሙ ለክሙ አዕባነ ዓበይተ ወት መርግዎን መሬተ ፀዓዳ፣

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ወደሚያወርሳችሁ አገር ለመ ሄድ ዮርዳኖስን በተሻገራ ችሁ ጊዜ ለእናንተ ታላላቅ ደንጊያ አቁማችሁ ነጭ በረቅ ቅቧቸው፣ (የነጭ መሬት አፈር ቅቧቸው)፤

፫፤ ወትጽሕፉ ውስተ ውእቶን አዕባን ኵሎ ነገረ ለዝንቱ ሕግ፣

በነዚህም ደንጊያዎች ላይ የዳ ግም ሕግን ነገር፤ አንድም በዳግም ሕግ የተጻፈውን ነገር ሁሉ ጻፉባቸው፤

ዐዲወክሙ ዮርዳኖስ ሶበ ቦእክሙ ውስተ ይእቲ ምድር ዘይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክሙ ለአበዊ ክሙ በከመ መሐለ ሎሙ ከመ የሀበክሙ ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ በከመ ይቤለክሙ እግዚአብሔር አምላክሙ ለአበዊ ክሙ፣

www.ethiopianorthodox.org

ተድላ ደስታ የሚገኝባት አገርን ይሰጣችሁ ዘንድ የአባቶቻችሁ ፈጣሪ እግዚአብሔር ለአባቶቻችሁ እንደ ማለላቸው ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ እግዚአብሔር ወደሚያወርሳችሁ ወደዚያች አገር በገባችሁ ጊዜ ጻፉባቸው።

፬፤ ወሶበ ዐደውክሙ ዮርዳኖሰ ታቀውምዎን ውስተ ደብረ ጌባል ለውእቱን አዕባን እለ አነ እኤዝዘክሙ ዮም በእንተ፡አሆን ወትመርግዎን መሬተ ፀዓዳ።

ዮርዳኖስን በተሻገራችሁ ጊዜም አሁን እኔ ስለ እነሱ የማገዛችሁን እነዚያን ደንጊያዎች ጌባል በሚባል ተራራ አቁማችሁ ነጭ በረቅ ኖራ ቅቧቸው።

፭፤ ወትነድቅ በህየ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር አምላክከ በዕበን ዘኢገሠሥዎን ሐፂን እለ ኢኮና ውቁራተ።

በመጥረቢያ በድጅኖ ባልተጠረቡ ባልተለዘቡ ደንጊያዎች ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር በዚያ መሠዊያ ሥራ።

፮፤ ወቦቶን ትነድቅ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር አምላክከ።

በነሱም ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሥራ።

፯፤ ወትሠውዕ ላዕሌሆን መሥዋዕተ መድኃኒት ብላዕ ወጽገብ በህየ ወተፈሣሕ በቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ።

በነሱም ላይ ድኅነት የሚደረግበትን መሥዋዕት ሠዋ። በዚያም ተረፈ መሥዋዕቱን በልተህ ጠግበህ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበልህ።

፰፤ ወጸሐፍ ውስተ ውእቶን አዕባን ኵሎ ዘንተ ሕገ ጥዩቀ ጥቀ።

ፈጽሞ የታወቀ የተረዳ ይህንም ሕግ ሁሉ በነዚያ ደንጊያዎች ላይ ጻፍ።

፱፤ ወይቤሎሙ ሙሴ ለካህናት ወለሌዋውያን ወለኵሉ ሕዝበ እስራኤል አርምም ወስማዕ እስራኤል በዛቲ ዕለት ኮንከ ሕዝበ ለእግዚአብሔር አምላክከ።

ሙሴም ካህናቱንና ሌዋውያንን የእስራኤልን ወገኖችም ሁሉ እስራኤል ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ወገን ሁነሃልና በዚች ቀን ጸጥ ብለህ ስማ።



፲፤ ወስማዕ ቃሎ ወግበር ኵሎ ትእዛዞ ወኵነኔሁ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም።

ቃሉን ሰምተህ ዛሬ እኔ የማዝህን ሕጉን ትእዛዙን ሁሉ አድርግ።

፲፩፤ ወአዘዞሙ ሙሴ ለሕዝብ በይእቲ ዕለት ወይቤሎሙ።

በዚያች ቀን ሙሴ ሕዝቡን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው።

፲፪፤ እሉ እሙንቱ እለ ይቀውሙ ወይባርክዎ ለሕዝብ በደብረ ገሪዛን ዐዲወክሙ ዮርዳኖሰ ስምዖን ወሌዊ ወይሁዳ ወይሳኮር ወዮሴፍ ወብንያም።

ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ገሪዛን በሚባል ተራራ ቆመው ሕዝቡን የሚመርቁት የሚያከብሩት እነዚህ ናቸው። ሌዊና ስምዖን። ይሳኮርና ይሁዳ። ብንያምና ዮሴፍ ናቸው አላቸው።

፲፫፤ ወእሉ እሙንቱ እለ ይቀውሙ ለረጊም በደብረ ጌባል ሮቤል ወጋድ ወአሴር ወዛብሎን ወዳን ወንፍታሌም።

ለመራገም ጌባል በሚባል ተራራ የሚቆሙ እሊህ ናቸው። ጋድና ሮቤል። ዛብሎንና አሴር። ንፍታሌምና ዳን ናቸው።

፲፬፤ ወያወሥኡ ለሊሆሙ ሌዋውያን ወይብልዎሙ ለኵሉ እስራኤል በዐቢይ ቃል።

እነዚያ ሌዋውያንም ሰምተው ይመልሱላቸዋል። ለእስራኤል ሁሉ በታላቅ ቃል እንዲህ ይሏቸዋል።

፲፭፤ ርጉመ ለይኩን ብእሲ ዘይገብር ግልፎ ወስብኮ ዘርኩስ በኀበ እግዚአብሔር ግብረ ኬንያ ዘይሠይም ወየኀብዕ ወያወሥኡ ኵሉ ሕዝብ ወይብሉ አሜን ወአሜን።

በእግዚአብሔር ዘንድ አጸያፊ የሚሆን ጣዖትን የሚያመልክ። ሰው ሠራሽ ጣዖትንም ሠውሮ የሚያኖር ሰው የተረገመ ይሁን ብለው ይንገሯቸው። ሕዝቡም ሁሉ እውነት ነው ብለው ይመልሱላቸው።

፲፮፤ ርጉመ ለይኩን ዘያስተአኪ አባሁ ወእሞ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን።

እናት አባቱን የሚንቅ የሚያዋርድ ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው። ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፤ ርጉመ ለይኩን ዘይሰርቅ ደወለ ቢጹ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን፤

የባልጀራውን ድንበር የሚያፈርስ የተረገመ ይሁን ይበሏቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ፤

፲፰፤ ርጉመ ለይኩን ዘያስሕቶ ፍኖተ ለዕውር ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን፤

ዕውሩን ከመንገድ አውጥቶ ወደ እሾሁ፤ ወደ ደንጊያው፤ ወደ ገደሉ የሚሰደው ሰው፤ አንድም ዕውረ ልቡና ቤተ እስራኤልን በአምልኮ ጣዖት የሚያሳስት ሰው የተረገመ ይሁን ይበሉ፤ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ፤

፲፱፤ ርጉመ ለይኩን ዘይጌምጽ ፍትሐ ግዩር ወዘዕጓለ ማውታ ወዘዕቤር ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን፤

የመጻተኛውንና እናት አባቱ የሞቱበትን ልጅ የባልቴቲቱንም ፍርድ የሚለውጥ የተረገመ ይሁን ይበሏቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ፤

፳፤ ርጉመ ለይኩን ዘይሰክብ ምስለ ብእሲተ አቡሁ እስመ ከሠተ ኃፍረተ አቡሁ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን፤

ከእንጀራ እናቱ የደረሰ ሰው የአባቱን ኃፍረት ገልጧልና የተረገመ ይሁን ይበሏቸው ሕዝቡም ይሁን ይሁን ይበሉ፤

፳፩፤ ርጉመ ለይኩን ዘይሰክብ ምስለ ኵሉ እንስሳ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን፤

ከእንስሳም የሚደርስ ሁሉ የተረገመ ይሁን ይበሏቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ፤

፳፪፤ ርጉመ ለይኩን ዘይሰክብ ምስለ እኅቱ እመኒ እንተ እምአቡሁ ወእመኒ እንተ እምእሙ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን፤

ከአባቱ ከተወለደች ወይም ከናቱ ከተወለደች ከእኅቱ የደረሰ ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ፤

፳፫፤ ርጉመ ለይኩን ዘይሰክብ ምስለ እመ ብእሲቱ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን፤



ከሚስቱ እናት ከአማቱ የሚደርስ ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ፤

፳፬፤ ርጉመ ለይኩን ዘይዘብጥ ካልኦ በኅቡእ ጕሕሉት ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን፤

በቂም በበቀል ባልንጀራውን የሚመታ ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ፤

፳፭፤ ርጉመ ለይኩን ዘይነሥእ ሕልያነ ከመ ይቅትል ነፍሰ ወደመ ንጹሐ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን፤

ነፍስ ይገድል ዘንድ ንጹሕ ደምንም ያፈስ ዘንድ መማለጃ የሚቀበል ሰው የተረገመ ይሁን ይበሏቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ፤

፳፮፤ ርጉመ ለይኩን ኵሉ ብእሲ ዘኢይቀውም ይግበር ቃለ ዘውስተ ዝንቱ ሕግ ወይብሉ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን፤

በዚህ ሕግ ያለውን ቃል ያደርግ ዘንድ ያልጸና ሰው ሁሉ የተረገመ ይሁን ይበሏቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ይሁን ይሁን ይበሉ (ሐተታ) ይህ የተናገረው ቃለ መርገሙ አሥራ ሁለት ነው፤ ነገዱም አሥራ ሁለት ናቸውና፤ አሥራ ሁለቱ ነገድ ስድስቱ በገሪዛን ስድስቱ በጌባል ሁነዋል፤ ሌዋውያን በገሪዛን ሁነው ቃለ በረከቱን ይናገራሉ፤ በገሪዛን ያሉት ስድስቱ ነገድ አሜን ይላሉ፤ አሁንም በጌባል ቁመው ቃለ መርገሙን ይናገራሉ፤ በጌባል ያሉት ስድስቱ ነገድ አሜን ይላሉ፤ አንድም እኩሌቶቹ ሌዋውያን በገሪዛን እኩሌቶቹ ሌዋውያን በጌባል ይቆማሉ፤ በገሪዛን ያሉት ቃለ በረከቱን ሲናገሩ በገሪዛንም በጌባልም ያሉት ሕዝቡ አሜን ይላሉ፤ በጌባል ያሉት ሌዋውያን ቃለ መርገሙን ሲናገሩ በጌባልም በገሪዛንም ያሉ ይሁን ይሁን ይላሉ።

## ምዕራፍ ፳፰

፩፤ ወለእመሰ ሰሚዓ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ወዐቀብከ ከመ ትግበር ኵሎ ትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ይሬስየከ እግዚአብሔር አምላክከ መልዕልተ ኵሉ አሕዛበ ምድር፤

www.ethiopianorthodox.org

የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ፣ እኔም አሁን የማገዝዝህን ትእዛዙን ሁሉ ታደርግ ዘንድ ሕጉን ብትጠብቅ ግን ፈጣሪህ እግዚአብሔር በምድር ካሉ አሕዛብ ሁሉ በላይ ያደርግሃል፤

፪፤ ወይበጽሐከ ዝንቱ ኵሉ በረከት ወይረክበከ ለእመ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ፣

የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ከሰማህ ይህ ሁሉ በረከት ይደርስልሃል ይደረግልሃል፤

፫፤ ቡሩክ ትከውን በሐቅል ወቡሩክ ትከውን በሀገር፣

በዱርም፣ በርሻም፣ በቤትም የተመረቅህ ትሆናለህ፤

፬፤ ወቡሩክ ይከውን ፍሬ ከርሥከ ወቡሩክ ይከውን እክለ ምድርከ ወቡሩክ ይከውን መራዕየ አባግዒከ ወአልሕምቲከ፣

ልጅህም የተመረቀ ይሆናል፣ ከምድርህ የተገኘ አዝመራህም የበዛ ይሆናል፣ የላሞችህና የበጎችህም መንጋ የበዛ ይሆናል፤

፭፤ ወቡሩክ ይከውን መዛግብቲከ ወትራፋቲከ፣

ድልብህ ብዙ ያሆናል፤ ገንዘብህም የተባረከ ይሆናል፤

፮፤ ቡሩክ ትከውን በበዓትከ ወቡሩክ ትከውን በፀዓትከ፣

በመውጣትህም በመግባትህም የተመረቅህ ትሆናለህ፤

፯፤ ወያገብኦሙ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ እዴከ ለፀርከ ከመ ይትቀጥቀጡ በታሕተ እገሪከ በአሐቲ ፍኖት ይወፅኡ ይትቀበሉከ ወበሳብኡ ፍናው ይነትዑ እም ቅድመ ገጽከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ከእግርህ በታች ይወድቁ ዘንድ ጠላቶችህን በእጅህ ይጥልልሃል፣ ይቀበሉህ ዘንድ በአንዲት ወጥተው በሰባት ጎዳና ከፊትህ ይሸሻሉ፤

፰፤ ወይፌኑ እግዚአብሔር በረከቶ ውስተ አብያቲከ ወውስተ ኵሉ ዘወደይከ እዴከ በውስተ ምድር ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ፣

እግዚአብሔር በቤትህ በረከቱን ይልክልሃል፣ ባወረስህ አገር በእጅህ በያዝኸው ገንዘብ ሁሉ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በረከቱን ያሳድራል፤



፱፤ ወያቀውመከ እግዚአብሔር ሎቱ ሕዝበ ቅዱሰ በከመ መሐለ ለአበዊከ ለእመ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ወሖርከ በፍናዊሁ፣

የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከሰማህ በሕጉም ጸንተህ ከኖርህ ለአባቶችህ እንደማለ እግዚአብሔር ለሱ የተለየ ወገን ያደርግሃል፤

፲፤ ወይሬእዩ ኵሉ አሕዛበ ምድር ከመ ተሰምየ ላዕሌከ ስሙ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወይፈርሁከ፣

በዚህ ዓለም ያሉ አሕዛብ ሁሉ የፈጣሪህ የእግዚአብሔር ስም በአንተ እንደ ተጠራ አይተው ይፈሩሃል፤

፲፩፤ ወያስተባዝኃከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ ሠናይት በውሉደ ከርሥከ ወበእክለ ምድርከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከአብራክህ በተከፈሉ ልጆችህ ከምድርህም በተገኘ አዝመራህ በበጎ ረድኤት የብዙ ብዙ ያደርግሃል፤

ወያስተዋልዶን ለእንስሳከ በውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር አምላክከ ለአበዊከ ከመ የሀብከ በከመ መዋዕለ ሰማይ ዲበ ምድር፣

ጠፈር በአድማስ ላይ ጸንቶ እንዲኖር ለአንተ ይሰጥህ ዘንድ ለአባቶችህ የማለ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ከብቶችህን እንዲዋለዱ ያደርጋቸዋል፤

፲፪፤ ወይፈትሕ ለከ እግዚአብሔር መዝገበ ቡሩከ ሰማየ ከመ የሀብከ ዝናመ በመዋዕሊሁ ለምድርከ ከመ ይባርክ ለከ ኵሎ ተግባረ እደዊከ፣

ምድርህ በምታበቅልበት ወራት ሰማይ ዝናም ለዘር ይሰጥህ ዘንድ፣ የእጅህንም አዝመራ ይባርክልህ ዘንድ እግዚአብሔር ዝናምን የያዘ ደመናን ይሰጥሃል፤

ወትሌቅሕ አንተ ለብዙኃን አሕዛብ ወአንተሰ ኢትትሌቃሕ ወትኴንኖሙ አንተ ለብዙኃን አሕዛብ ወለከሰ ኢይኴንኑከ፣

አንተ ለአሕዛብ ታበድራለህ፣ አንተ ግን አትበደርም፣ አንተ ብዙ የሆኑ አሕዛብን ትገዛቸዋለህ፣ አንተን ግን አይገዙህም፤

፲፫፤ ወይሠይመከ እግዚአብሔር ውስተ ርእስ ወአኮ ውስተ ዘነብ ወትከውን መልዕልተ ወኢትከውን መትሕተ ለእመ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ወትእዛዞ ኵሎ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ከመ ትዕቀብ ወትግበር፣

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ተገዥ ያደርግሃል እንጂ ለሌላ ገዥ አይደርግህም፤ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ፣ ትጠብቀው ትሠራውም ዘንድ ዛሬ እኔ የማዝህን ትእዛዙንም ሁሉ ብትሰማ፤

፲፬፤ ወኢትትገኃሥ እምኵሉ ቃል ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ኢለየማን ወኢለፀጋም ከመ ትሖር ድኅረ አማልክተ ባዕድ ታምልኮሙ፤

የአሕዛብን ጣዖታት ታመልክ ዘንድ እኔ አሁን ካዘዝሁህ ቃል ወደቀኝም ወደግራም ባትወጣ ከሁሉ በላይ ትሆናለህ እንጂ ከሁሉ በታች አትሆንም፤

፲፭፤ ወለእመ ኢሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትዕቀብ ኵሎ ትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ይመጽእ ላዕሌከ ዝንቱ ኵሉ መርገም ወይረክበከ፤

እኔ አሁን የማዝህን ትእዛዙን ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ፣ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ባትሰማ ግን ይህ ሁሉ ርግማን ይደርስብሃል፣ መከራም ያገኝሃል፤

፲፮፤ ወትከውን ርጉመ አንተ በሐቅል ወበሀገር፣

አንተም በዱር በቤት የተረገምክ ትሆናለህ፤

፲፯፤ ወይከውን ርጉመ መዛግብቲከ ወትራፋቲከ፣

ድልብህም ብዙ ገንዘብህም ይጠፋል፤

፲፰፤ ወርጉመ ይከውን ፍሬ ከርሥከ ወእክለ ምድርከ ወመራዕየ አልሕምቲከ ወአባግዒከ፣

ከአብራክህ የተከፈለ ልጅህም የተረገመ ይሆናል፣ ከምድርህ የተገኘ አዝመራህም ይጠፋል፣ የበጎችህና የላሞችህ መንጋም ይጠፋል፤

፲፱፤ ወርጉም አንተ በበአትከ ወበፀአትከ፣

በመግባትህም በመውጣትህም አንተ የተረገምህ ትሆናለህ፤

፳፤ ወይፌኑ እግዚአብሔር ላዕሌከ ንዴተ ወረኃበ ወብድብደ ወይጠፍእ ኵሎ ዘወደይከ እዴከ ውስቴቱ ወይሜርወከ እስከ ይደመስሰከ ፍጡነ በበይነ እከየ ምግባሪከ እስመ ኃደገኒ፣

እግዚአብሔርም በአንተ ላይ ረኃብና ችግርን ቸነፈርንም ያመጣብሃል፣ በእጅህ የያዝኸውም ሁሉ ይጠፋል፣ እኔን በሕግ በአምልኮት ትተኸኛል ብሏልና፣ ስለሥራህ ክፋት ፈጥኖ እስኪያጠፋህ ድረስ ደርሶ ይፈርድብሃል፤

፳፩፤ ወያተሉ እግዚአብሔር ሞተ ላዕሌከ እስከ ያጠፍአከ ፍጡነ እምድር እንተ ውስቴታ ትበውእ ህየ ከመ ትትዋረሳ፣

ትወርሳት ዘንድ አንተ ከምትገባባት ምድር ፈጥኖ እስኪያጠፋህ ድረስ እግዚአብሔር ባንተ ሞትን ያመጣብሃል፤

፳፪፤ ወይቀሥፈከ እግዚአብሔር በደዌ ሲሕ ወበፈጸንት ወበአስፈር ወበፍርሃት ወበድንጋጼ ወበአባር ወበኃጢእ ወይሰድዱከ እስከ ያጠፍኡከ፣

በሆድ ደዌና በቍርጥማት በመፍራትና በደረቅ በሽታ፣ በድርቅና በድንጋጤ እህል ከብት በማጣት ያጠፉሃል፣ እስኪያጠፋህ ድረስ ደርሰው አሕዛብም ከሀገርህ አስወጥተው ይሰዱሃል፤

፳፫፤ ወትከውን ሰማይ በመልዕልተ ርእስከ ብርተ ወምድርኒ በታሕቴከ ሐጺነ፣

በራስህ በላይ ያለ ሰማይ ናስን ትሆናለች፣ በበታችህ ያለች ምድርም ብረት ትሆናለች፤

፳፬፤ ወይሬስዮ እግዚአብሔር ለዝናመ ምድርከ ቆባረ ወመሬት ይወርድ እምሰማይ ላዕሌከ እስከ ይቀጠቅጠከ ወእስከ ያጠፍአከ፣

እግዚአብሔር በምድርህ የሚዘንመውን ዝናም ጭጋግ ያደርገዋል፣ ፈጽሞ እስኪያጠፋህ ድረስ ከሰማይ ዋግ ያወርድብሃል፤

፳፭፤ ወይገብረከ እግዚአብሔር ከመ ትትቀተል በቅድመ ፀርከ በአሐቲ ፍኖት ትወፅእ ኀቤሆሙ ወበሰብዑ ፍናው ትነትዕ እምቅድመ ገጾሙ ወትከውን ዝርወ ውስተ ኵሉ መንግሥታተ ምድር፣

እግዚአብሔር በጠላቶችህ ፊት እንድትሞት ያደርጋል፣ በአንዲት ጎዳና ወደሳቸው ወጥተህ ከፊታቸው በሰባት ጎዳና ትሸሻለህ፣ በአሕዛብ መንግሥትም ሁሉ ትበተናለህ፤

፳፮፤ ወይከውኑ አብድንቲከ መብልዐ ለአዕዋፈ ሰማይ ወኢትረክብ ዘይቀብረከ፣

የሚቀብርህ አጥተህ ሬሳህ የሰማይ ወፎች ምግብ ይሆናል፤

፳፯፤ ወይቀሥፈከ እግዚአብሔር በመቅሠፍተ ግብጽ በዐበቅ እኩይ ውስተ ነፍስትከ ወበሐከክ ዘአልቦ ፈውስ፣

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርም ግብጻውያንን ባጠፋበት መቅሠፍት በክፉ ችፌ ድኅነት በሌለበት እከክ ሰውነትህን ያጠፋሃል፤

፳፰፤ ወይቀሥፌከ እግዚአብሔር በድቀት ወበዓዊር ወበድንጋፄ ልብ፣

እግዚአብሔር በመከራ፣ በድንብርብር፣ በልቡና ድንጋጤ ያጠፋሃል፤

፳፱፤ ወትገብእ ወታመረስስ መዓልተ ከመ ያመረስስ ዕውር በውስተ ጽልመት፣

ባሰጤና በጨለማ፣ ዕውር በቀን መንገዱ ጠፍቶት እንዲዳስስ አንተም የምትሄድበት መንገድ ጠፍቶህ ተመልሰህ በቀን ትዳስሳለህ፤

ወኢትረክብ ፍኖተ ወትትጋፋዕ ወትትበረበር በኵሉ መዋዕሊከ ወኢትረክብ ዘይረድአከ፣

የምትሄድበት ጎዳናን አታገኝም ትበደላለህ፣ በዘመንህም ሁሉ ገንዘብህን ትዘረፋለህ፣ የሚረዳህም አታገኝም፤

፴፤ ወታወስብ ብእሲተ ወየሀይደከሃ ካልእ ብእሲ ወትነድቅ ቤተ ወኢትነብር ውስቴቱ ወትተክል ወይነ ወኢትቀሥሞ፣

አጭተህ ሚስት ታገባለህ፣ ያገባሃትን ሚስትህን ዓይንህ እያየ ሌላ ሰው ቀምቶ ይወስድብሃል፣ ቤት ትሠራለህ ነገር ግን በውስጡ አትኖርበትም፣ ወይን ትተክላለህ ነገር ግን ፍሬውን አትለቅምም፤

፴፩፤ ወይጠብሑ ላሕመከ ወኢትበልዕ እምኔሁ ወየሐይዱ ዓድገከ ወኢያገብኡ ለከ ወይገብኡ አባግዒከ ለአግብርት ወለፀርከ ወኢትረክብ ዘይረድአከ፤

በሬህንም ጠላቶችህ ያርዱታል አንተ ግን ከእሱ አትበላም፣ አህያህን ይቀሙሃል አይመልሱልህም፣ በጎችህም ለጠላቶችህና ለባሮችህ ይሰጣሉ፣ የሚረዳህም አታገኝም፤

፴፪፤ ወይገብኡ ደቂቅከ ወአዋልዲከ ለካልዕ ሕዝብ ወትሬኢ በአዕይንቲከ እንዘ ይኰርዕምሙ ወአልቦ ዘትክል ገቢረ፣

ሴቶች ልጆችህና ወንዶች ልጆችህ ተማርከው ወደ አሕዛብ ይሄዳሉ፣ ራስ ራሳቸውን ሲቀጠቅጧቸው በዓይኖችህ ታያለህ፣ የምታደርገውም የለም ማለት ጠላቶችህን ለመበቀል አትችልም፤



፴፫፤ ወይበልዕ ሕዝብ ነኪር ዘኢተአምር እክለ ምድርከ ወፃማከ ወትከውን ዕሡረ ወሥቁየ በኵሉ መዋዕል፣

የማታውቀው ልዩ የሚሆን ወገን ከምድርህ የተገኘውን አዝመራህን፣ ገንዘብህን ይበላብሃል፣ በዘመንህ ሁሉ ፈጽመህ በመከራ የተጨነቅህ ትሆናለህ፤

፴፬፤ ወትከውን ምሑፀ በምርአየ አዕይንቲከ ወኢትሬኢ፣

ዓይኖችህ ባዩት አገር ትሸሻለህ፣ ጎዳናውን ግን አታውቀውም፤

፴፭፤ ወይቀሥፌከ እግዚአብሔር በደዌ እኩይ ውስተ ብረኪከ ወውስተ አቍያጺከ ወውስተ አዕማደ እገሪከ በዘኢትክል ሐይወ እምሰኰና እግርከ እስከ ርእስከ፣

ከእግርህ ጫማ ጀምሮ እስከ ራስህ ድረስ መዳን በማትችል ገንዘብ ጉልበትህን፣ ጭንህን ባትህን በሚያሳብጥ በክፉ ደዌ እግዚአብሔር ያጠፋሃል፤

፴፮፤ ወይወስደከ እግዚአብሔር ኪያከኒ ወመላእክቲከኒ ዘሤመከ ለከ ውስተ ሕዝብ ዐቢይ ዘኢተአምር አንተ ወኢአበዊከ ወታመልክ በህየ ባዕዳነ አማልክተ ዕፀወ ወአዕባነ፣

አንተን በብዙ ወገን ከሾመልህ ከአለቆችህ ጋራ አንተ ወደማታውቀው፣ አባቶችህም ወደማያውቁት አገር እግዚአብሔር አስማርኮ ይወስድሃል፣ በዚያም ልዩ የሆኑ ጣዖታትን እንጨቶችን ደንጊያዎችን ታመልካለህ፤

፴፯፤ ወትከውን በህየ ድንጉፀ ወትከውን አምሳለ ወነገረ ለኵሉ አሕዛብ ዘንቤሆሙ ይወስደከ እግዚአብሔር ህየ፣

በዚያም ትደነግጣለህ፣ እግዚአብሔር አስማርኮ በሚወስድህ አገርም ለአሕዛብ መተረቻ መዘበቻ ትሆናለህ፤

፴፰፤ ወታወፅእ ብዙኀ ዘርአ ውስተ ገራህትከ ወታበውእ ውሑደ እስመ አንበጣ በልዖ፣

በርሻህ ልትዘራው ብዙ ዘር ከቤትህ ታወጣለህ፣ አንበጣ በልቶታልና ብዙ ዘርተህ ጥቂት ታገባለህ፤

፴፱፤ ወትተክል ዓፀደ ወይን ወትትጌበሮ ወኢትሰቲ እምወይኑ ወኢትትፌሣሕ ቦቱ እስመ ዕፄ እኩይ በልዖ፣

www.ethiopianorthodox.org

ወይን ተክለህ ትከተክተዋለህ፤ ነገር ግን ከወይኑ አትጠጣም፤ የሚያጠፋ ትል በልቶታልና በሱ ደስ አይልህም፤ ትል የበላው እህል ደስ አያሰኝምና። አንድም ሕገ እግዚአብሔርን አፍርሰው፤ ኃጢአት ሠርተው፤ መከራ መጥቶባቸው አገኑዋልና ደስ አይልህም አለ።

፵፤ ወታጠሪ ዕፀወ ዘይት ውስተ ኵሉ ደወልከ ወኢትትቀባዕ ቅብዓ እምኔሁ እስመ ተነግፈ ፍሬሁ፤

በአውራጃህ ሁሉ ዘይት ትተክላለህ፤ ፍሬው ረግፏልና ከሱ ዘይትን አትቀባም።

፵፩፤ ወትወልድ ደቂቀ ወአዋልደ ወኢያተርፍዎሙ ለከ እስመ ይነሥእዎሙ ወይዔውውዎሙ፤

ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ትወልዳለህ፤ አሕዛብ ማርከው ይወስዷቸዋልና ላንተ አያስቀሩልህም።

፵፪፤ ወለኵሉ እክለ ምድርከ ወለኵሉ ተክለ ዕፀዊከ አናኵዕ ያጠፍኦ፤

በርሻህ የዘራኸውን አዝመራህን ተክልህንም ሁሉ ኩብኩባ ያጠፋዋል።

፵፫፤ ወፈላሲ ዘሀለወ ኀቤከ የዓርግ መልዕልቲከ ወአንተሰ ትከውን መትሕቶ፤

ከአንተ ዘንድ ያለ ስደተኛም ከአንተ በላይ ይሆናል ማለት ገዥ ይሆንሃል፤ አንተ ግን ተገዥ ትሆናለህ።

፵፬፤ ወውእቱ ይሌቅሐከ ወአንተ ኢትሌቅሖ ውእቱ ይከውነከ ርእሰ ወአንተ ትከውኖ ዘነበ፤

እርሱ ያበድርሃል አንተ ግን አታበድረውም፤ እርሱ ራስ ይሆንሃል፤ አንተ ጅራት ትሆነዋለህ ማለት እርሱ ገዥ ይሆንሃል አንተ ግን ተገዥ ትሆናለህ።

፵፭፤ ወይመጽእ ላዕሌከ ዝንቱ ኵሉ መርገም ወይዴግነከ ወይረክበከ እስከ ያጠፍአከ ወይደመስሰከ እስመ ኢሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትዕቀብ ትእዛዞ ወኵነኔሁ ወኵሎ ዘአዘዘከ፤

ይህ ሁሉ ርግማን በአንተ ይደርስብሃል፤ ዘጠኙን ሕገጋት «ኢታምልክ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌየ» ያለውን ያዘዘኽንም ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማህምና ፈጽሞ



እስኪያጠፋህ ድረስ መከራው ተከታትሎ ያገኝሃል።

፵፮፤ ወይከውን ተአምር ላዕሌከ ወመድምም ላዕለ ዘርእከ እስከ ለዓለም እስመ ኢያምለከሁ ለእግዚአብሔር አምላክከ በትፍሥሕት ወበሠናይ ልብ፤

ደስ ብሎህ በበጐ ልቡና ፈጣሪህ እግዚአብሔርን አላመለክኸውምና በአንተ ድንቅ ተአምራት ይደረግብሃል፤ በልጆችህም ለዘለዓለሙ ይህ ይደረግባቸዋል።

፵፯፤ ወበገብ ኵሉ ትትቀነይ ለጸላእትከ ዘይፌኑ እግዚአብሔር ላዕሌከ በረኃብ ወበጽምዕ ወበዕርቃን ወበኃጢአ ኵሉ ወይወዲ ለከ ጋጋ ዘሐፂን ውስተ ክሣድከ እስከ ያጠፍአከ፤

በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ለሚያመጣብህ ጠላትህ ትገዛለህ፤ በውሀ ጥምና በረኃብ ከልብስ በመራቆት፤ ሁሉን በማጣት ትገዛለህ። አንድም እግዚአብሔር እስኪያጠፋህ ድረስ በሰውነትህ ጽኑ አገዛዝ ያመጣብሃል።

፵፰፤ ወያመጽእ እግዚአብሔር ላዕሌከ ሕዝበ እምርኁቅ እምአጽናፈ ምድር ከመ ርደተ ንስር ሕዝበ ዘኢትሰምዕ ነገሮሙ፤

እግዚአብሔርም ከሀገር ዳርቻ ከሩቅ አገር ቋንቋቸውን የማታውቀውን አሕዛብን እንደ አሞራ አወራረድ በአንተ ፈጥኖ ያመጣብሃል።

፵፱፤ ሕዝብ ግሩመ ገጽ ዘኢያከብር ገጸ ልሂቅ ወኢይምሕር ንዑሰ፤

ፊቱ የሚያስፈራ ሽማግሌ የማያከብር፤ ለሕፃኑ የማይራራ አሕዛብን ያመጣብሃል።

፶፤ ወያጠፍዕ ዕጓለ መራዕይከ ወእክለ ምድርከ እስከ ኢያተርፍ ለከ እክለ ወኢወይነ ወኢቅብዐ ወኢመራዕየ አልሕምቲከ ወአባግዒከ እስከ ያጠፍአከ፤

እህልህን፤ ወይንህን፤ ዘይትህን፤ የበጎችህንና የላሞችህን መንጋ ሳያስቀር እስኪያጠፋ ድረስ ደርሶ የመንጋዎችህን ግልገሎች ከምድርህም የተገኘውን አዝመራ ያጠፋል።

፶፩፤ ወይደመስሰከ እምውስተ ኵሉ አህጉሪከ እስከ ያወድቅ አረፋቲከ ዐበይተ ወአጽዋኒከ ዘቦቱ ትትአመን ዘውስተ ኵሉ በሐውርቲከ ወይሣቅየከ በውስተ ኵሉ አህጉሪከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ፤

www.ethiopianorthodox.org

በሀገሮችህ ሁሉ የምትታመን ባቸው አምባዎችን፣ ከፍ ከፍ ያሉ ቅጽሮችህን እስኪያ ፈርሷቸው ድረስ ደርሶ ከአገ ሮችህ ሁሉ ያጠፋሃል፣ ፈጣ ሪህ እግዚአብሔር በሰጠህ አገርም ሁሉ መከራ ያጸና ብሃል፤

፶፫፤ ወትገብእ ትብላዕ ውሉደ ከርሥከ ሥጋ ደቂቅከ ወአዋልዲከ ዘወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ በምንዳቤከ ወበሥቃይከ ዘሣቀየከ ጸላኢከ በውስተ አህጉሪከ፣

በሀገርህ ሳለህ ጠላትህ በአጸና ብህ መከራ ሁሉ ፈጣሪህ እግዚብሔር የሰጠህን ከአ ብራክህ የተወለዱ የሴቶች ልጆችህንና የወንዶች ልጆች ህን ሥጋ ትበላለህ፤

፶፬፤ ርኅጽከሂ ወለምለምከሂ ወትደነፁ ዓይኑ ለእኁሁ ወለብእ ሲቱ እንተ ውስተ ሕፅኑ ወለዘ ተርፉ ውሉድ ዘአትረፉ ሎሙ፣

ከዚህ አስቀድሞ ተደላድለህ ተቀማጠልህ በተድላ በደስታ ኖርህ፣ ዓይኑም ባጠገቡ የም ትተኛ ሚስቱንና ወንድሙን ትነፍጋቸዋለች፣ አሕዛብ ያስ ቀሩላቸው የቀሩ ልጆቻቸው ንም ትነፍጋለች፤

፶፭፤ ይሁብዎሙ ለለአሐዱ እም ኔሆሙ ሥጋ ውሉዶሙ ይሴሰዩ ወኢያትረፉ ሎሙ ወኢምንተኒ በሥቃይ ወበምንዳቤ ዘሣቀዩከ ጸላ እትከ በኵሉ አህጉሪከ፣

በአገሮችህ ሁሉ ሳለህ ጠላቶ ችህ በአጸኑብህ መከራ ምንም ምን ሳላስቀሩላቸውምና ይመ ገቡ ዘንድ ከነሱ ለአንዱም ለአንዱም የልጆቻቸውን ሥጋ ይሰጧቸዋል፤

፶፮፤ ወእንተ ርኅጽትኒ ይእቲ እም ኔክሙ ወእንተሂ ድክምት ይእቲ ትሜህሮን ለእገሪሃ ሐዊረ ውስተ ምድር እስመ ርኅጽት ይእቲ ወድ ክምት ወትደነጽዎ ዓይና ለምታ ዘዲበ ሕፅና ወለወልዳ ወለወለታ፣

ድልድል ቅምጥል ነበረችና፣ ደካማም ናትና፣ ከናንተ ድል ድል ቅምጥል የነበረች ደካ ማም የነበረች ወይዘሮዪቱ በሀገር ለእግሮቿ መንገድ ታስተምራቸዋለች፣ ዓይኗ በአጠገቧ የሚተኛ ባሏን ትነ ፍገዋለች፣ ሴት ልጇንና ወንድ ልጇንም ትነፍጋቸዋለች ማለት ከባሏና ከልጆቿ ተሸሽጋ ትበላለች፤



፶፯፤ ወለሥጋሃ ዘእምውስተ አባላ ውእቱ ወሕፃና ዘወለደት ትበልዕ ጽሚተ ሶበ ኃጥአት ኵሎ በም ንዳቤ ወበሥቃይ ዘይሣቅየከ ጸላ ኢከ በውስተ አህጉሪከ፣

ከወገኗ የተወለደ ዘመዷንም ዓይኗ ይነፍገዋል፣ በሀገር ሳለህ ጠላትህ ባጸናብህ መከራ ተይዛ የምትበላው ባጣች ጊዜ ባራስ ቤቷ የወለደችውን ልጇን ተሰውራ ትበላለች፤

፶፰፤ ወለእመ ኢሰማዕከ ከመ ትግ በር ኵሎ ዘንተ ነገሮ ለዝንቱ ሕግ ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፍ ከመ ትፍራህ ስመ ክቡረ ወስቡሐ ዘእግዚአብሔር አምላክከ፣

በዚህ መጽሐፍ የተጻፈ የዚ ህን ሕግ ነገሩን ሁሉ ታደርግ ዘንድ የከበረ የተመሰገነ የፈጣ ሪህ የእግዚአብሔርንም ስም ትፈራ ዘንድ ባትሰማ፤

፶፱፤ ወይገብር እግዚአብሔር ነኪረ መቅሠፍትከ ወመቅሠፍተ ዘርእከ መቅሠፍተ ዐቢየ ወመድምመ ወደዌ እኩየ ወሕማመ ያመጽእ ላዕሌከ፣

እግዚአብሔር የልጆችህንና የአ ንተን መቅሠፍት ልዩ ልዩ ያደርግብሃል፣ የሚያስደንቅ ጽኑ መቅሠፍትና ጽኑ ደዌን መከራን ያመጣብሃል፤

፷፤ ወይገብእ ላዕሌከ ኵሉ ደዌ ሆሙ ለግብጽ እኩይ ዝክቱ ዘኢ ፈራህከ እምኔሁ ወኢፈራህከ እም ቅድመ ገጹ፣

ከመገለጡ የተነሣ ያልፈራ ኸው ያ ጽኑ የሆነ የግብጻው ያን መከራ በአንተ ይመለ ሳል፤

፷፩፤ ወያተሉ ኵሎ ደዌ ወኵሎ መቅሠፍተ ዘኢኮነ ጽሑፈ ውስተ ዝንቱ መጽሐፈ ሕግ ወያ መጽእ እግዚአብሔር ላዕሌከ እስከ ያጠፍአከ ወእስከ ትደመሰሱ፣

እስኪያጠፋህ ድረስ ሁላችሁ ፈጽማችሁ እስክትጠፉ ድረስ የእግዚአብሔር ሕግ በተጻፈ በት በዚህ መጽሐፍ ያልተ ጻፈ መቅሠፍቱን መከራውን ሁሉ አከታትሎ በአንተ ያመ ጣብሃል፤

፷፪፤ ወትተርፉ ኅዳጣነ በኊልቍ እምድኅረ ኮነ ከመ ከዋክብተ ሰማይ ብዝኀከ እስመ ኢሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ፤

የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማህምና ብዛትህ እንደ ሰማይ ኮከብ ከሆነ በኋላ በቍጥር ጥቂት ትቀራ ላችሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፱፤ ወበከመ ተፈሥሐ እግዚአብሔር ላዕሌከ ከመ ይግበር ሠናይተ ለከ ወአብዝኃከ ከማሁ ይትፌሣሕ እግዚአብሔር ዲቤከ ከመ ይሥሩከ ወትጠፍእ እምድር እንተ ውስቴታ ትበውእ ህየ ከመ ትትዋረሳ፣

በጎ ነገርን ያደርግልህ ዘንድ እግዚአብሔር በአንተ ደስ እንዳለው እንዳበዛህም ያጠፋህ ዘንድ እግዚአብሔር ባንተ ጥፋት ደስ ይለዋል፣ ትወርሳት ዘንድ ወደሷ ከምትገባባትም ምድር ትጠፋለህ፤

፴፤ ወይዘርወከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ አሕዛብ እምአጽናፈ ምድር እስከ አጽናፈ ምድር ወትትቀነይ በህየ ለባዕዳን አማልክት ለዕፀው ወለአዕባን ዘኢተአምር አንተ ወኢአበዊከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔርም ከምድር ዳርቻ ጀምሮ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ በአሕዛብ አገር ይበትንሃል፣ በዚያም አንተ ለማታውቃቸው አባቶችህም ለማያውቋቸው ከእንጨት ተጠርበው፣ ከድንጊያ ተለዝበው ለተሠሩ ልዩ ለሆኑ ጣዖታት ትገዛለህ አለ ታመልካቸዋለህ፣

፴፩፤ ወበህየኒ በውስተ ውእቱ አሕዛብ ኢያዐርፊከ ወኢያበውህከ ትቁም በእግርከ ወይሁበከ በህየ እግዚአብሔር ልበ ኅዙነ ወአዕይንተ ጥፉአተ ወነፍሰ ሙስንተ፣

በዚያም በአሕዛብ አገር ከመከራው አያሳርፍህም፣ በእግርህም ትቆም ዘንድ አያሰለጥንህም እግዚአብሔርም በዚያ ልቡናህን ያሳዝነዋል፣ ዓይንህን ያጠፋዋል፣ ሰውነትህንም ያደክመዋል፤

፴፪፤ ወትከውን ሕይወትከ ስቅልተ ቅድመ አዕይንቲከ ወትደነግጽ ለሊከ መዓልተ ወሌሊተ ወኢትትአመና ለሕይወትከ፣

ድኅነትህም ከአንተ የራቀች ትሆናለች፣ አንተም በመዓልትም በሌሊትም ትደነግጣለህ፣ ድኅነትኽንም አገኛታለሁ ብለህ አታምናትም፤ አንድም ስቅልተ ትሬእያ ለሕይወትከ ይላል፣ ከመከራው ጽናት የተነሣ ድኅነትህን የተሰቀለች ሁና ታያታለህ ማለት የተሰቀለ እንዲርቅ ካንተ ትርቃለች ፤ አንድም ወበከመ ተፈሥሐ እግዚአብሔር ላዕሌከ ወአብዝኃከ ከማሁ ይትፌሣሕ እግዚአብሔር ዲቤከ ከመ ይሥሩከ ወትጠፍእ ምድር እንተ ውስቴታ ትበውእ ህየ ከመ ትትዋረሳ፣ አዳም ሰባቱን ዓመት በገነት ሳለህ ጸጋን ክብርን ሲሰጥህ ደስ እንዳለው፣ በኋላም አምላክነትን ሽተህ ዕፀ በለስን በልተህ በበደልህ ጊዜ ሲፈርድብህ ደስ ይለዋል፣ ወርሰኻት ልትኖር ከገባህባት ገነት ወደ ምድረ ፋይድ ትወርዳለህ፤ ወይዘርወከ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ አሕዛብ፣ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በዓለሙ ሁሉ ያሉ አጋንንትን ያሠለጥንብሃል፣ በዚያም ለአጋንንት ተገዢ ትሆናለህ፤ ወበህየኒ በውስተ አሕዛብ ኢየዓርፊከ ወኢያበውህከ ትቁም በእግርከ ፣ በሲኦል ሳለህ በተቀሙራኝህ በአጋንንት ዘንድ አያሳርፍህም፣ በእግረ ነፍስ ትቆም ዘንድም አያሰናብትህም፣ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ያዘነ ልብ ይሰጥሃል ዓይነ ልቡናህን የጠፋ ያደርገዋል፣ በንዴተ ነፍስም ትኖራለህ ፤ ስቅልተ ትሬእያ ለሕይወትከ ቅድመ አዕይንቲከ ፤ ከዚያ በኋላ ሕይወትህ ወልድን ስላንተ በቀራንዮ ተሰቅሎ ታያለህ፣ በዘመነ ኦሪት በዘመነ ወንጌል በመከራ ነፍስ ትደነግጣለህ፣ ሌሊት ያላት ኦሪት ናት፣ በሌሊት ጨለማ እንጂ ብርሃን እንዳይገኝ፣ በኦሪትም ፍዳ መርገም እንጂ ሀብት ልጅነት አልተገኘባትምና ፣ መዓልት ያላት ወንጌል ናት በመዓልት ብርሃን እንዲገኝ በወንጌልም ሀብት ልጅነት ተገኝቶባታልና ወኢትትአመና ለሕይወትከ ፤ ሕይወትህ ወልድ ሲያድንህ ሰው ሁኖ ባየኸው ጊዜ አታምንበትም፣ ሕይወት አለው በግ ብሩ ሕይወተ ሥጋ ሕይወተ ነፍስ ነውና፤

፴፫፤ ወለእመ ጸብሐ ትብል እፎ እንጋ ይመሲ ወለእመ መስየ ትብል እፎ እንጋ ይጸብሕ እምፍርሃተ ልብ ዘትደነግፅ ወእምዘ ያስተርእየከ ውስተ አዕይንቲከ ወዘትሬኢ፣



www.ethiopianorthodox.org

በዓይንህ ከሚታይህ አንተም ከምታየው ከሚያስደነግጥ ከል ቡናህ ፍርሀት የተነሣ የነጋ እንደሆነ እንዴት ይመሽ ይሆን ትላለህ፣ የመሸም እንደ ሆነ እንዴት ይነጋ ይሆን እንጃ ትላለህ፤

፷፰፤ ወያገብእከ እግዚአብሔር ውስተ ግብጽ በአሕማር ወእንተ ምድርኒ በእግር ዝንቱ ዘእቤለከ ኢትደግም እንከ ርእዮታ ዓዲ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በባሕሩ በመርከብ፣ በየብሱ በእግር ወደ ግብጽ ይመልስሃል፣ ዳግመኛ ተመልሰህ ግብጽን አታያትም፤ ያልኩህ ይህ ነው፤

ወትከውኑ በህየ አግብርተ ወአእማተ ለፀርክሙ ወአልቦ ዘይምሕረክሙ ፤

ተማርካችሁ በሄዳችሁበት አገር ለጠላቶቻችሁ ወንድ ባሪያ ሴት ባሪያ ትሆናላችሁ፣ ከጠላቶቻችሁ የሚራራላችሁ የለም ።

## ምዕራፍ ፳፱

### ጉባኤ

፩፤ ወዝንቱ ውእቱ ነገረ ኪዳን ዘአዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ከመ ይትካየዶሙ ለደቂቀ እስራኤል በምድረ ሞዓብ ዘእንበለ ዝክቱ ዘተካየዶሙ በኮሬብ ፤

በኮሬብ ሳሉ፤ አንድም በኮሬብ ተገልጾ ከተማማላቸው መሐላ ሌላ በሞዓብ አውራጃ ሳሉ የእስራኤልን ልጆች ይማማላቸው ዘንድ እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘው የሕግ ነገር ይህ ነው ፤

፪፤ ወጸውዖሙ ሙሴ ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል ወይቤሎሙ ለሊክሙ ርኢክሙ ኵሎ ዘገብረ ለክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ በምድረ ግብጽ ፤

ሙሴም የእስራኤልን ልጆች ሁሉ ጠርቶ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በግብጽ አገር ያደረገላችሁን ሁሉ አይታችኋል፤

ላዕለ ፈርዖን ወላዕለ መገብቱ ወላዕለ ኵሉ ዐበይቱ ወላዕለ ኵሉ ምድሩ፤

በፈርዖንና በሹማምቱ፣ በመኳንንቱና በአገሩ ሁሉ ያደረገውን ተአምራት አይታችኋል፤

፫፤ መቅሠፍተ ዐቢየ ዘርእያ አዕይንቲክሙ ወዝክተ ተአምረ ወመድምመ ዐቢየ ወእደ ጽንዕተ ወመዝራዕተ ልዑለ ፤



ዓይኖቻችሁ ያዩትን ጽኑ መቅሠፍት፣ ደጋጉን ተአምራት ማለት ዘጠኝ መቅሠፍት አሥረኛ ሞተ በኵር አሥራ አንደኛ ስጥመትን አይታችኋል ፤

፬፤ ወወሀበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ልበ ከመ ታእምሩ ወአዕይንተ ከመ ትርአዩ ወዕዝነ ከመ ትስምዑ እስከ ዛቲ ዕለት ፤

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ልታውቁበት ልብን ፤ ልታዩበት ዓይንን ፤ ልትሰሙበት ጆሮን እስከ ዛሬ ድረስ ሰጥቷችሁ ነበር፣ እናንተ ግን አላዋቆች ሆናችሁ ፤

፭፤ ወወሰደክሙ እግዚአብሔር አርብዓ ዓመተ ውስተ ገዳም አልባሲክሙኒ ኢበልየ ወአሣዕኒክሙኒ ኢበልየ እምእገሪክሙ ፤

እግዚአብሔር አርባ ዘመን ሙሉ በምድረ በዳ አዞራችሁ፣ ልብሳችሁም አላለቀም፣ የእግራችሁም ጫማ አላረጀም ፤

፮፤ እንዘ እክለ ኢትበልዑ ወወይነ ወሜሰ ኢትሰትዩ እስከ በጻሕክሙ ውስተ ዝንቱ መካን ከመ ታእምሩ ከመ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክ ክሙ ፤

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እንደሆነ ታውቁ ዘንድ ገበሬ የዘራውን እህል ሳትበሉ፤ የተከለውን ወይን ሳትጠጡ፤ እስከዚህ ቦታ እስክትደርሱ ድረስ ልብሳችሁም አላለቀም ጫማችሁም አላረጀም ፤

፯፤ ወወፅአ ሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን ወዓግ ንጉሠ ባሳን ወተቀበሉክሙ ይትቃተሉክሙ ወቀተልናሆሙ ፤

የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎንና የባሳን ንጉሥ አግ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ሊወጓችሁ ወጥተው በጦር ተቀበሏችሁ ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ረድቶን እኛ ድል አደረግናቸው ፤

፰፤ ወነሣእነ ምድሮሙ ወወሀብክዎሙ ይእተ ምድረ ለሮቤል ወለጋድ ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴ፤

እነሱንም ወግተን አገራቸውን እጅ አድርገን ለነገደ ሮቤልና ለጋድ፣ ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ሰጠኋቸው ፤

፱፤ ወዕቀቡ ከመ ትግበሩ ኵሎ ነገረ ዝንቱ ኪዳን ከመ ታዕምሩ ኵሎ ዘትገብሩ ፤

www.ethiopianorthodox.org

የምትሠሩትን ሥራ ሁሉ መርምራችሁ ታውቁ ዘንድ መሐላው ያለበትን ነገር ፤ አንድም የሕጉን ነገር ትሠሩት ዘንድ ጠብቁ፤ አንድም የሕጉን ነገር ጠብቃችሁ ሥሩት ፤

፲፤ ወናሁ ቆምክሙ አንትሙ ኵልክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወዓበይተ ነገድክሙ ወሊቃውንቲክሙ ወመኳንንቲክሙ ወጸሐፍቲክሙ ወኵሉ ተባዕተ እስራኤል ፤

ይህ ሁሉ ሲደረግላችሁ እናንት ሁላችሁ በወገኖቻችሁ የተሾሙ አለቆቻችሁ ሹማምቱና መኳንንቱ የእስራኤል ወንዱ ሁሉ ማለት አርበኛው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ቆማችሁ ፤

፲፩፤ ወአንስቲያክሙ ወውሉድክሙ ወግዩር ዘሀለወ ማዕከለ ትዕይንቲክሙ እምሐጣቤ ዕፅክሙ እስከ ሐዋሬ ማይክሙ ፤

ሚስቶቻችሁና ልጆቻችሁ ፤ በከተማችሁ የሚኖር ስደተኛው ከእንጨት ሰባሪ ጀምሮ እስከ ውሀ ቀጂ ድረስ በእግዚአብሔር ፊት ቆማችሁ ነበር ፤

፲፪፤ ከመ ትስምዑ ኪዳና ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወመርገሞሂ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ዘተካየደ ምስሌክሙ ዮም ፤

መሰብሰባችሁም ዛሬ ከናንተ ጋር የተማማለውን የፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን መርገሙንና መሐላውን ሕጉን ትሰሙ ዘንድ ነው፤ ማለት ሕጉን ብትጠብቁ በረከቱን ታገኙ ዘንድ ባትጠብቁ ግን መከራውን ትቀበሉ ዘንድ ነው፤

፲፫፤ ከመ ይረሲከ ሕዝበ ሎቱ ወውእቱኒ ከመ ይኩንከ አምላከ በከመ መሐለ ለአበዊከ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ፤

ይኸውም አንተን ለሱ የተመረጠ ወገን ያደርግህ ዘንድ እሱም ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብ እንደ ማለላቸው መጠን እውነተኛ ፈጣሪህ ይሆንህ ዘንድ ፤ አንድም የፍቅር የሃይማኖት አባት ይሆንህ ዘንድ ነው፤ በሐሰት የሚመለክ አለና ከዚያ ሲለይ እንዲህ አለ ፤



፲፬፤ ወአኮ ለክሙ ለባሕቲትክሙ ዘአቀውም አነ ዘንተ ኪዳነ ወዘንተ መርገመ ፤

በእኔ ይህን መሐላና ይህን መርገም ማለት ሕጌን ብትጠብቁ የምሰጠውን በረከትና ረድኤት፣ ሕጌን ባትጠብቁ የማመጣውን መከራ የማጸና ለናንት ብቻ አይደለም ፤

፲፭፤ አላ ለእለሂ ሀለዉ ዝየ ዮም ምስሌክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ወለእለሂ ኢሀለዉ ዝየ ምስሌክሙ ዮም ፤

ዛሬ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ከናንተ ጋር ላሉትና ለሌሉትም ሰዎች ሁሉ ነው እንጂ ፤

፲፮፤ እስመ ለሊክሙ ተአምሩ ዘከመ ነበርነ ውስተ ግብጽ ወዘከመ ኃለፍነ እንተ ማዕከሎሙ ለአሕዛብ ወተዓደውናሆሙ ፤

በግብጽ አገር ሁለት መቶ አሥራ አምስት ዘመን በመከራ እንደ ኖርን በነዚህም አሕዛብ መካከል አልፈናቸው እንደ ሄድን ማለት ከግብጽ ወጥተን ሂደን ከአግና ከሴዎን አገር እንደ ደረስን እነሱንም ድል እንዳደረግናቸው እናንት ቀሉ ታውቃላችሁ እኮን ፤

፲፯፤ ወርኢክሙ ርኵሶሙ ወአማልክቲሆሙ ዕፀወ ወዕብነ ወብሩረ ወወርቀ ወብርተ ዘገብሩ ሎሙ፤

ከዚያም በደረሳችሁ ጊዜ እነሱ የሠሯቸው የብርና የወርቅ፣ የብርት የእንጨትና የድንጊያ የሚሆኑ ጣዖቶቻቸውንና ኃጢአታቸውን አያችሁ፤

፲፰፤ ወኢይኩን እምኔክሙ ኢብእሲ ወኢብእሲት ወኢሕዝብ ወኢነገድ ወኢመኑሂ ዘየኀድግ ልቦ እምእግዚአብሔር አምላክክሙ ወየሐውር ያምልኮሙ ለአማልክቲ አሕዛብ ፤

ከናንተ ወገን ወንድም ቢሆን፣ ሴትም ብትሆን፣ ማናቸውም ነገድ ቢሆን ከፈጣሪያችሁ ከእግዚአብሔር ልቡናውን አርቆ የአሕዛብን ጣዖታት ያመልካቸው ዘንድ ወደ ቤተ ጣዖት የሚሄድ አይኑር ፤

ወኢይኩን እምኔክሙ ሥርው እኪት እንተ ታበቍል ወታፈሪ ሐምዘ ወምረተ ፤

ከናንተ ወገን ፍዳ መርገምን የምታስከትል ኃጢአትን ክህ

www.ethiopianorthodox.org

ደትን የምታለማ ክፉ ልቡና ያለው ሰው አይኑር ፤

፲፱፤ ወሰሚዓክሙ ቃለ ዝንቱ መርገም ዘይቤ በልቡ ይሠሪ ሊተ እስመ በዕበደ ልብየ ገበርኩ ወሖርኩ ከመ ኢየዓሪ መዊተ መዓብስ ምስለ ዘኢአበሰ ፤

ይህን የመርገም ቃል ከሰማ ችሁ በኋላ ወደጥፋት ሂጄ በልቡናዬ ድንቁርና አድርጌዋ ለሁና በልቡ አስቦ እግዚአብ ሔር ኃጢአቴን ይቅር ይለ ኛል የሚል ሰው ቢኖር አውቆ የበደለ ሰው ሳያውቅ ከበደለ ሰው ጋር በፍዳ እንዳ ይተካከል ይወቅ ፤

፳፤ ኢይፈቅድ እግዚአብሔር ከመ ይሠሃሎ አላ በጊዜሃ መዓቱ ለእግዚአብሔር ወቅንዐ ያውዕዮ ለውእቱ ብእሲ ወይትልዎ ዝንቱ ኵሉ መርገም ዘዝንቱ ኪዳን ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፈ ሕግ ወይሰዕር እግዚአብሔር ስሞ እምታሕተ ሰማይ ፤

ለአምላክነቱ የቀናው ቅንአትና የእግዚአብሔር ቁጣ ያንን ሰው በጊዜው ጊዜ ያጠፋዋል እንጂ እግዚአብሔር ይቅር ሊለው አይወድም ፤ በዚህ በዳግም ሕግ የተጻፈ የመ ሐላው ርግማንም ሁሉ ይከ ተለዋል፤ እግዚአብሔርም ከሰ ማይ በታች ስሙን ያጠ ፋዋል እንጂ ይቅር አይለ ውም ፤

፳፩፤ ወያገብኦ እግዚአብሔር ውስተ እኪት ወይፈልጦ እምኵሉ ደቂቀ እስራኤል በኵሉ ዝንቱ መርገም ዘዝንቱ መርገመ ኪዳን ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፈ ሕግ ፤

በዚህ በዳግም ሕግ በተጻፈ በመሐላው መርገም ሁሉ ከእስራኤል ልጆች ሁሉ ለይቶ እግዚአብሔር በመከራ ይጥለዋል ፤

፳፪፤ ወይብሉ ድኅረ ትውልደ ደቂቅክሙ እለ ይትነሥኡ እምድኅሬክሙ ወነኪርኒ ዘይመጽእ እምርኁቅ ብሔር ወይሬእዩ መቅሠፍታ ለይእቲ ምድር ወደዌሃ ዘፈነወ እግዚአብሔር ላዕሌሃ ፤

ከናንተ በኋላ የሚነሡ ልጆቻ ችሁም ከሩቅ አገር የሚመጣ ባዕድም እግዚአብሔር ያመ ጣባት የዚያችን አገር መከራ ዋን አይተው ፤

፳፫፤ ተይ ወፄው ዘይነድድ ውስተ ኵለንታሃ ወኢትዘራእ ወኢታብ



ቊል ወኢይወፅእ ውስቴታ ኵሉ ሐመልማል በከመ ተገፍትዓ ሰዶም ወገሞራ ወአዳማ ወሲባዮን እለ ገፍትዖን እግዚአብሔር በመዓቱ ፤

በሁለንተናዋ ድኝ እሳት ሲነድባት ይኖራል እንጂ ዘር ሳይዘራባት፤ ቡቃያ ሳታበቅል እግዚአብሔር ተቆጥቶ ያጠ ፋቸው ገሞራና ሰዶም፤ ሲባዮንና አዳማ እንደጠፉ በእሷም ልምላሜ ሳታወጣ ባዩ ጊዜ ፤

፳፬፤ ወይብሉ ኵሉ አሕዛብ ለምንት ከመዝ ገብራ እግዚአብ ሔር ለዛቲ ምድር ወምንት ውእቱ መንሱቱ ለዝንቱ መዓት ዓቢይ ፤

አሕዛብ ሁሉ እግዚአብሔር ይችን አገር ለምን እንዲህ አደረጋት? የዚህ የጽኑ ቁጣ ጥፋት ምንድር ነው ይላሉ ፤

፳፭፤ ወይብሉ እስመ ኀደጉ ኪዳኖ ለእግዚአብሔር አምላከ አበዊሆሙ ዘተካየደ ምስለ አበዊሆሙ አመ አውፅኦሙ እምድረ ግብጽ ፤

መላሾች እንዲህ ይላሉ፤ ከግ ብጽ አገር ባወጣቸው ጊዜ ከአባቶቻቸው ጋራ የተማማለ ውን የአባቶቻቸውን ፈጣሪ የእግዚአብሔርን መሐላ አፍ ርሰዋልና ስለዚህ ነው ይላሉ፤

፳፮፤ ወሖሩ ወአምለኩ ባዕዳነ አማልክተ ወሰገዱ ሎሙ ለዘኢ የአምሩ ወለዘኢይበቍዖሙ ፤

እግዚአብሔርን ማምለክ ትተው ሄደው ልዩ የሆኑ ጣዖታትን አምልከዋልና ለማ ይጠቅሟቸውና ለማያውቋ ቸው ለጣዖታቱ ሰግደዋልና ስለዚህ ነው ይላሉ ፤

፳፯፤ ወተምዓ መዓተ እግዚአ ብሔር ላዕለ ዛቲ ምድር ወአምጽአ ላዕሌሃ ኵሎ መርገመ ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፈ ሕግ ፤

እግዚአብሔር በዚች አገር ፈርዶ በዚህ ዳግም ሕግ የተ ጻፈውን መርገም ‹ርግማን› ሁሉ አመጣበት ፤

፳፰፤ ወሠዐሮሙ እግዚአብሔር እምገጸ ምድሮሙ በመዓት ወበ መንሱት ወበመቅሠፍት ዐቢይ፤

እግዚአብሔርም በጥፋትና በቁጣ ፤ በጽኑ መቅሠፍትም ከአገራቸው አጠፋቸው ይላሉ፤

፳፱፤ ከመ ይእዜ ዘኅቡዕ ለእግ ዚአብሔር አምላክነ ወዘያስተርኢስ ለነ ወለውሉድነ ለዓለም ከመ ንግበር ኵሎ ዘይብል ዝንቱ ሕግ፤

www.ethiopianorthodox.org

ዛሬ እኛ እንደምንቀበለው ያለ መቅሠፍት ለፈጣሪያችን ለእግዚአብሔር የተሠወረ መቅሠፍት አለው የተገለ ጸው መቅሠፍት ግን ይህ ዳግም ሕግ የሚያዘውን ሁሉ ለዘለዓለሙ እናደርግ ዘንድ ለልጆቻችንና ለኛ ነው ፤ አንድም መቅሠፍቱ ዛሬ ለኛ ፣ ኋላ ለልጆቻችን የተገለጠ ነው ፤ የተሠወረ መቅሠፍት የለውም ፤ አንድም ዛሬ በግብጽ ተሠውሮ የምንቀበለው መከራ ለኛ ነው ፤ ኋላ ግን በከነዓን ተገልጦ የሚደረገው አባር ቸነፈር ዌዋዌ ለልጆቻችን ነው ይላሉ አበው፤ አንድም ሰባ ዘመን በባቢሎን የምንቀበለው መከራ ለኛ ነው ይላሉ ውሉድ፤ አንድም ፈጣሪያችን በረድኤት ጉብኝቶን የሚደረገው ሚጠት ግን ለልጆቻችን ነው፤ አንድም ዛሬ በሲኦል ተሠውሮ ኋላ በገሃነም ተገልጦ የምንቀበለው መከራ ለኛ ለልጆቻችን ነው ይላሉ ኃጥአን ፤ አንድም ዛሬ በገነት ተሠውሮ የምንቀበለው ተድላ ደስታ ኋላም ተገልጦ በመንግሥተ ሰማያት የምናገኘው ጸጋ ክብር ለኛም ለልጆቻችንም ነው ይላሉ ምእመናን።

## ምዕራፍ ፴

፩፤ ወእመ መጽአ ላዕሌከ ኵሉ ዝንቱ ነገር በረከቱሂ ወመርገሙሂ ዘአቀምኩ ቅድሜከ ተዘከር በልብከ በውስተ ኵሉ አሕዛብ ኀበ ዘረወከ እግዚአብሔር በህየ ፤

ይህ ሁሉ ነገር በመጣብህ ጊዜ፣ በፊትህ ያጸናሁት መርገሙና በረከቱ በደረሰብህ ጊዜ እግዚአብሔር አስማርኮህ በተበተንህበት በዚያ በአሕዛብ አገር ሁሉ በልብህ አስበው ፤

፪፤ ወተመየጥ ኀበ እግዚአብሔር አምላክከ ወስማዕ ቃሎ ኵሎ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ ፤

እኔ አሁን የማዝህን ቃሉን ሁሉ ሰምተህ በፍጹም ሰውነትህና በፍጹም ልቡናህ ወደ ፈጣሪህ ወደ እግዚአብሔር ተመለስ ፤

፫፤ ወየኃድግ ለከ እግዚአብሔር ኵሎ ኃጣውኢከ ወይሣሃለከ ወካዕበ ያስተጋብአከ እግዚአብሔር እምኵሉ አሕዛብ እለ ውስቴቶሙ ዘረወከ ህየ ፤

እግዚአብሔር ይቅር ብሎ ኃጢአትህን ያስተሠርይልሃል፤ ዳግመኛም እግዚአብሔር ወደሱ አስማርኮ ከሰደደህ ከአሕዛብ አገር ሁሉ ሰብስቦ ይመልስሃል ፤

፬፤ ወለእመኒ ውስተ አጽናፈ ሰማይ ዘረወከ ያስተጋብአከ እምህየ እግዚአብሔር አምላክከ ፤

በሰማይ ዳርቻም ቢበትንህ ማለት በአራት መዓዝን ቢበትንህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከዚያ ይሰበስብሃል ፤

፭፤ ወይወስደከ ውስተ ይእቲ ምድር እንተ ተዋረሱ አበዊከ ወትወርሳ ወይገብር ሠናይተ ላዕሌከ ወያበዝኃከ ወይፈድየከ ፈድፋደ እምአበዊከ ፤

አባቶችህ ወደ ወረሷት ወደ ዚያችም አገር ይወስድሃል፣ አንተም ትወርሳታለህ፣ በጎ ረድኤትንም ያደርግልሃል፣ ከአባቶችህም ይልቅ አንተን ፈጽሞ እንድትበዛ ያደርግሃል፤ አንድም ከአባቶችህ ቤት ንብረት ይልቅ ያንተ ቤት ንብረት ባለጸግነትህ ፈጽሞ እንዲበዛ ያደርግልሃል ፤

፮፤ ወያሴስሎ እግዚአብሔር ለገዝኑ ልብከ ወልበሙ ለዘርእከ ከመ ታፍቅሮ በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ ከመ ትሕየው አንተ ወዘርእከ ፤

አንተ በሕይወት ትኖር ዘንድ፣ ከአንተም በኋላ ልጆችህ በሕይወት ይኖሩ ዘንድ በፍጹም ልቡናህ፣ በፍጹም ሰውነትህ ትወደው ዘንድ፣ ኃጢአት ሥራ፣ ጣዖት አምልክ የሚል የአንተን ልቡና ፣ ኃጢአት ሥሩ ጣዖት አምልኩ የሚል የልጆችህንም ክፉ ልቡና እግዚአብሔር ያርቀዋል ፤

፯፤ ወያገብኦ እግዚአብሔር አምላክከ ለዝንቱ መርገም ላዕለ ፀርከ ወላዕለ እለ ይጸልኡከ ወላዕለ እለ ይሰድዱከ ፤

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ይህንን መርገም ከአገር አስወጥተው በሚያሰድዱህና በጠላቶችህ ላይ ይመልሰዋል፤ ‹ሐተታ› ፀርከ የጊዜው፣ ይጸልኡከ የዘገየው ነው ፤

፰፤ ወአንተሰ ተመየጥ ወስማዕ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ወግበር ኵሎ ትእዛዞ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም፤



www.ethiopianorthodox.org

አንተ ግን ተመልሰህ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስማ፤ እኔ አሁን የማዝህን ትእዛዙን ሁሉ አድርገው ጠብቀው ፡፡

፱፡ ወብዙኃ ያጸንዓከ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ተግባረ እደዊከ ወበውሉደ ከርሥከ ወበዘርአ ምድርከ ወበአስተዋልዶ እንስሳከ እስመ ይትመየጥ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ይትፌሣሕ ላዕሌከ በሠናይ በከመ ተፈሥሐ ላዕሌከ በእከይ ወበከመ ተፈሥሐ ላዕለ አበዊከ ፡፡

በእጅህ ሥራ ሁሉ ከባሕር ይህ በተከፈሉ ልጆችህም ከምድርህ በሚገኝ አዝመራህ ከብቶችህንም በማዋለድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ፈጽሞ ያጸናሃል፤ በአንተ ጥፋት በአባቶችህም ጥፋት ደስ እንዳለው በአንተ ድኅነት ደስ ይለው ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በረድኤት ወደ አንተ ይመለሳል ፡፡

፲፡ ለእመ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ከመ ትዕቀብ ወከመ ትግበር ኵሎ ትእዛዞ ወኵሎ ኵነኔሁ ወፍትሖ ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ መጽሐፈ ሕግ ወለእመ ገባእከ ኀበ እግዚአብሔር አምላክከ በኵሉ ልብከ ወበኵሉ ነፍስከ ፡፡

በኦሪት የተጻፉ ፍትሐ ፤ አምስቱ መቶ ሰባ ወነበቦ ፤ ኵነኔሁ ፤ ኢታምልክ ፤ ትእዛዙ ዘጠኙን ቃላት ትሠራው ትጠብቀውም ዘንድ፤ የፈጣሪህ የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ በፍጹም ሰውነትህና በፍጹም ልቡናህ ወደ ፈጣሪህ ወደ እግዚአብሔር ብትመለስ፡፡

፲፩፡ እስመ ዛቲ ትእዛዝ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ኢኮነት ክብደ ወኢኮነት ርኁቅተ እምኔከ ፡፡

እኔ ዛሬ ጠብቃት ብዬ የማዝዝህ ይች ትእዛዝ የጸናች አይደለችም እኮን፤ ከአንተም የራቀች አይደለችም እኮን ፡፡

፲፪፡ ወኢኮነት ውስተ ሰማይ ከመ ኢትበል መኑ የዓርግ ውስተ ሰማይ ወያመጽእ ለነ ወንስምዓ ወንግበራ ፡፡

ሕጊቱን ሰምተን እንሠራት ዘንድ ወደ ሰማይ ወጥቶ ማን ያመጣልናል? እንዳትል ሕጊቱ በሰማይ የምትኖር አይደለችም ፡፡



፲፫፡ ወኢኮነት ማዕዶተ ባሕር ወእመ ትብል መኑ እምዓደዎ ለነ ማዕዶተ ባሕር ወያምጽኣ ወያሰምዓነሃ ወንግበራ ፡፡

ሕጊቱን እንሠራት ዘንድ ወንዙን ተሻግሮ ሂዶ አምጥቶ ማን ባሰማን ነበር? ብትል ሕጊቱ ከባሕር ማዶ አይደለችም ፡፡ አንድም ከመ ኢትበል ይላል፤ እንዲህ እንዳትል ከባሕር ማዶ አይደለችም ፡፡

፲፬፡ እስመ ናሁ ቅርብት ይእቲ ለከ ጥቀ ቃል ውስተ አፉከ ወውስተ ልብከኒ ወውስተ እደዊከኒ ከመ ትግበራ ፡፡

ባንደበትህ ልትናገራት፤ በልቡናህ ልታስባት፤ በእጅህ ልትሠራት ‹ይዘህ ልትመለከታት› እነሆ ይች ቃል ለአንተ እጅግ የቀረበች ናት እኮን ፡፡

፲፭፡ ወናሁ ሜምኩ ቅድመ ገጽከ ዮም ሕይወተ ወሞተ ሠናይተ ወእኪተ ፡፡

እንዲህ ብዬ ከነገርኩህ በኋላ ሕይወትንና ሞትን፤ በጎውንና ክፉውን ነገር እነሆ በፊትህ አኖርሁ፤ ‹ሐተታ› ሕይወት ያለውን ሠናይት፤ ሞት ያለውን እኪት ብሎ ገለጸው፡፡

፲፮፡ ወሕይወትሰ ለእመ ሰማዕከ ቃለ እግዚአብሔር አምላክከ ወዓቀብከ ትእዛዘ ኵሎ ዘአነ እኤዝዘከ ዮም ከመ ታፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወትሑር በኵሉ ፍናዊሁ ወትዕቀብ ኵነኔሁ ወፍትሖ ፡፡

ሕይወትም ታገኛለህ ያልኩህ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ትወደው ዘንድ፤ በሕጉም ጸንተህ ትኖር ዘንድ ዘጠኙን ቃላትና ኢታምልክንም ትጠብቅ ዘንድ፤ እኔ ዛሬ የምነግርህን ትእዛዙን ሁሉ ብትጠብቅ የእግዚአብሔርንም ቃል ብትሰማ ነው፡፡

ወትትባዛኅ ወተሐዩ ወይባርከከ እግዚአብሔር በኵሉ ምድር እንተ ውስቴታ ትበውእ ህየ ከመ ትትዋረሳ ፡፡

እንዲህ ብታደርግ በልጅ በከብት ትበዛለህ ፡፡ አንድም በጸጋ በክብር ፍጹም ትሆናለህ፤ በሕይወትም ትኖራለህ፤ ትወርሳት ዘንድ በምትገባባትም አገር ሁሉ እግዚአብሔር ያከብርሃል ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፤ ወለእመ ተመይጠ ልብከ ወአበይከ ሰሚዓ ወስሕትከ ወሰገድከ ለባዕዳን አማልክት ወተቀነይከሙ ናሁ አይዳዕኩከ ዮም ከመ ጠፊአ ትጠፍእ ፤

ልቡናህ ወደ ገቢረ ኃጢአት ወደ አምልኮ ጣዖት ቢመለስ፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መስማትን እምቢ ብትል፣ ከሕጉም ወጥተሕ ልዩ ለሆኑ ጣዖታት ብትሰግድ ግን እልም ድርግም ብለህ እንድትጠፋ እነሆ ዛሬ ነገርኩህ ፤

፲፰፤ ወኢይነውኅ መዋዕሊከ ውስተ ምድር እንተ ውስቴታ ዓዲወ ተዓዱ ዮርዳኖስ ህየ ከመ ትትዋረሳ ፤

ትወርሳት ዘንድ ወደሷ ለመሄድ ዮርዳኖስን በምትሻገርበት ምድርም ዘመንህ አይበዛም ፤

፲፱፤ ወናሁ አሰምዕ ለከ ዮም ሰማየ ወምድረ ከመ ሤምኩ ቅድሜከ ሕይወተ ወሞተ በረከተ ወመርገመ ወኅረያ ለከ ለሕይወት ከመ ትሕየው አንተ ወዘርእከ ፤

ሕይወትንና ሞትን፣ በረከትንና መርገምን በፊትህ እንዳኖርኩልህ እነሆ ዛሬ ሰማይንና ምደርን አዳኝብሃለሁ ፣ ምስክር አደርግብሃለሁ ፤ አንተም ከልጆችህ ጋር በሕይወት ትኖር ዘንድ ሕይወትን ምረጣት ፤

፳፤ ወአፍቅሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ ወስማዕ ቃሎ ወአጽንዖ ኪያሁ ፤

ወአጽንዖ ሎቱ ሲል ነው፣ ፈጣሪህ እግዚአብሔርን ውደደው፣ ቃሉን ስማው፣ እርሱንም አጽናው ፤

እስመ ውእቱ ሕይወትከ በዘቦቱ ይነውኅ መዋዕሊከ ከመ ትንበር ውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊከ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ከመ የሀቦሙ፤

እግዚአብሔር ያወርሳቸው ዘንድ ለአባቶችህ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ በማለላቸው ምድር በከነዓን ጸንተህ ትኖር ዘንድ ዘመንህ በሚበዛ ገንዘብ እሱ ሕይወትህ ነውና ፈጣሪህን ውደደው፣ ቃሉንም ሰምተህ አጽናው።።

## ምዕራፍ ፴፩

፩፤ ወፈጸመ ሙሴ ተናግሮቶሙ ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል ዘንተ ኵሎ ነገረ፣

ሙሴ ለእስራኤል ልጆች ይህን ነገር ሁሉ ተናግሮ ጨረሰ፤



፪፤ ወይቤሎሙ ምእት ወዕሥራ ዓመት ሊተ ዮም ወእክል እንከ በዊአ ወወፂአ ወባሕቱ ይቤለኒ እግዚአብሔር ኢትዓድዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ፣

ዛሬ መቶ ሃያ ዓመት ሁኖኛል፣ መውጣት መግባትም እችላለሁ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ይህን ዮርዳኖስን አትሻገረውም አለኝ፤

፫፤ ውእቱ እግዚአብሔር ዘየሐውር ቅድሜከ ያጠፍኦሙ እምቅድመ ገጽከ ለኵሉ አሕዛብ ወኢያሱኒ ዘየሐውር ቅድመ ገጽከ በከመ ይቤ እግዚአብሔር፣

ፊታውራሪ ሁኖ በፊትህ የሚሄድ እግዚአብሔር አሕዛብን ሁሉ ከፊትህ ያጠፋቸዋል፣ በፊትህ የሚሄድ ኢያሱም እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል እንዳለ፣ ከፊትህ ያጠፋቸዋል፤

፬፤ ከማሁ ይገብሮሙ በከመ ገብሮሙ ለሴዎን ወለአግ ክልኤቱ ነገሥተ አሞሬዎን እለ ይነብሩ ውስተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ወለምድሮሙ በከመ ሠረዎሙ፣

በዮርዳኖስ ማዶ የሚኖሩ ሁለቱን የአሞሬን ነገሥታት አግንና ሴዎንን እንዳጠፋቸው እንዲሁ ያጠፋቸዋል፣ የነዚያን አገራቸውንም እንደአጠፋባቸው የነዚህንም አገራቸውን ያጠፋባቸዋል፤

፭፤ ወአግብኦሙ እግዚአብሔር ለክሙ ወግበርዎሙ በከመ አዘዝኩክሙ፣

እግዚአብሔርም በእጃችሁ በጣለላችሁ ጊዜ እንደ አዘዝኋችሁ አድርጓቸው፤

፮፤ ትባእ ወጽናዕ ወኢትፍራህ ወኢትደንግፅ ወኢትጽብስ በቅድመ ገጾሙ እስመ እግዚአብሔር አምላክከ ውእቱ የሐውር ምስሌከ ወኢየኃድገከ ወኢያስትተከ፣

ቤተ እስራኤል ጨክን፣ በርታ፣ ጠላት ያጠፋኛል ብለህ አትፍራ፤ አትደንግጥ፣ እሱ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር በረድኤት ይኖራልና አይለይህምና፣ አያቃልልህምና በፊታቸው አትድከም፤

፯፤ ወጸውዖ ሙሴ ለኢያሱ ወይቤሎ በቅድመ ኵሉ እስራኤል ትባእ ወጽናዕ እስመ አንተ ትበውእ ቅድሜሁ ለዝንቱ ሕዝብ ውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊክሙ ከመ የሀቦሙ ወአንተ ታወርሶሙ፣

www.ethiopianorthodox.org

ሙሴም ኢያሱን ጠርቶ እንዲህ አለው፣ በእስራኤል ፊት ጨክን፣ በርታ ይሰጣቸው ዘንድ እግዚአብሔር ለአባቶቻችሁ ወደማለላቸው አገር አንተ በዚህ ወገን ፊት ትገባለህና አንተም ታወርሳቸዋለህና፤

፰፤ ወእግዚአብሔር የሐውር ምስሌከ ወኢየኀድገከ ወኢየሰትተከ ኢትፍራህ ወኢትደንግፅ፤

እግዚአብሔርም ከአንተ ጋራ በረድኤት ይኖራልና፣ አይለይህምና፣ ቸል አይልህምና አትፍራ አትደንግጥ፤

፱፤ ወጸሐፈ ሙሴ ለዝንቱ ነገረ ሕግ ውስተ መጽሐፍ ወወሀቦሙ ለካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ለደቂቀ ሌዊ ወለሊቃውንቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፤

ሙሴም በቃል ያለ ይረሳል፣ በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል እንዲሉ ለልጅ ልጅ ዘመን እንዲነገር ብሎ ይህን የሕግ ነገር በመጽሐፍ ጽፎ የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን ለሚሸከሙ ለሌዊ ልጆች፣ ለካህናቱ ለእስራኤል ልጆች አለቆችም ሰጣቸው፤

፲፤ ወአዘዞሙ ሙሴ በይእቲ ዕለት ወይቤ እምድኅረ ስድስቱ ዓመት በዓመተ ኅድገት አመ በዓለ መጸለት፣

ሙሴም በዚያች ቀን ከስድስት ዓመት በኋላ በዳስ በሚደረግ በዓል ጊዜ ዕረፍት በሚደረግበት ዘመን፤

፲፩፤ አመ የሐውር ኵሉ እስራኤል ከመ ያስተርኢ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ ውስተ መካን ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ አንብርዎ ለዝንቱ ሕግ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ፊት ይታይ ዘንድ እስራኤል ሁሉ ከዓመት ሦስት ጊዜ በዓል ለማክበር በሄደ ጊዜ፤

፲፪፤ አስተጋብኦሙ ሕዝበ ከመ ይስምዑ ዕደዊሆሙ ወአንስቲያሆሙ ወደቂቆሙ ወግዩራን እለ ውስተ ሀገርክሙ ከመ ይስምዑ ወያእምሩ ፈሪሆቶ ለእግዚአብሔር አምላክሙ ወሰሚዖሙ ከመ ይግበሩ ኵሎ ሕጎ ለዝንቱ ቃል፤

ወንዶችና ሴቶች፣ በሀገራችሁም ያሉ ስደተኞችና ልጆቻቸውም ይሰሙ ዘንድ ሕዝቡን ሰብስባችሁ ይህን ሕግ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር



ፊት አንብቡት፣ ሰምተውም የፈጣሪያቸውን የእግዚአብሔርን አምልኮቱን ያውቁ ዘንድ ከሰሙም በኋላ የዚህን ቃል ሥርዓት ሁሉ ይሠሩ ዘንድ፤

፲፫፤ ወደቂቆሙ እለ ኢያአምሩ ይስምዑ ወይትመሐሩ ፈሪሆቶ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ በኵሉ መዋዕሊሆሙ ዘየሐይዉ እሙንቱ ዲበ ምድር እንተ ውስቴታ ተዓድዉ ዮርዳኖስ አንትሙ ከመ ትትዋረስዋ በህየ፣

ሕጉን የማያውቁ ልጆቻቸውም በዚያ ትወርሷት ዘንድ እናንተ ዮርዳኖስን በምትሻገሩባት ምድር እነሱ በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔርን አምልኮቱን ሰምተው ይማሩ ዘንድ አንብቡት ብሎ አዘዛቸው፤

## ገባኤ

፲፬፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ ቀርበ መዋዕለ ሞትከ ጸውዖ ለኢያሱ ወቁሙ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወአዘዞ ወሖሩ ሙሴ ወኢያሱ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወቆሙ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው እነሆ የምትሞትበት ወራት ቀረበ፣ ኢያሱን ጠርተህ ልዩ በሆነች ድንኳን ደጃፍ ቁሙ ብሎ እዘዘው አለው፣ ኢያሱና ሙሴም ልዩ ወደሆነች ድንኳን ሄደው በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ቆሙ፤

፲፭፤ ወወረደ እግዚአብሔር በዓምደ ደመና ወቆመ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወቆመ ዓምደ ደመናሁ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፣

እግዚአብሔርም በዓምደ ደመና ወርዶ ልዩ በሆነች ድንኳን ደጃፍ ቆመ፣ ዓምደ ደመናውም ፈጣሪውን ተከትሎ ልዩ በሆነች ድንኳን ደጃፍ ቆመ፤

፲፮፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ናሁ ትነውም አንተ ምስለ አበዊከ ወይትነሣእ ዝንቱ ሕዝብ ወይዜሙ ድኅረ አማልክተ ባዕድ ዘውስተ ምድር እንተ ውስቴታ ይበውእ ወየኀድገኒ ወይትዌወሩ ኪዳንየ ዘተካየድክዎሙ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፣ እነሆ አንተ እንደ አባቶችህ ትሞታለህ «ወይትነሥእ እሉ ሕዝብ» ሲል ነው፣ እሊህ ወገኖች በአባቶ

ቻቸው ተተክተው ይነሣሉ፤ እኔን ትተው በሚገቡባት አገር ያሉ የአሕዛብን ጣዖታት ያመልካሉ፤ የተማማልኋቸው መሐላዬ ንም ቸል ይላሉ፤

፲፯፤ ወእትመዓዕ መዓተ ላዕሌሆሙ በይእቲ ዕለት ወአኀድጎሙ ወእመይጥ ገጽየ እምኔሆሙ ወይከውኑ መብልዓ ለፀርሙ፤

በዚች ቀን በነሱ ላይ ተቆጥቼ (ፈርጄ) እለያቸዋለሁ፤ ገጸ ረድኤቴንም ከነሱ እመልሳለሁ፤ ለጠላቶቻቸውም ምግብ ይሆናሉ፤

ወትረክቦሙ ብዙኀት እኪት ወሥቃይ ወይብሉ በይእቲ ዕለት እስመ ኀደገነ እግዚአብሔር አምላክነ ወኢሀለወ ምስሌነ ረከበተነ ዛቲ እኪት፤

ብዙ መከራ ታገኛቸዋለች፤ በዚያችም ቀን እንዲህ ይላሉ፤ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በረድኤት ተለይቶናልና፤ ከኛም ጋራ በረድኤት የለምና ይች መከራ አገኘችን ይላሉ፤

፲፰፤ ወአነሰ መይጠ እመይጥ ገጽየ እምኔሆሙ በይእቲ ዕለት በእንተ ኵሉ ኃጣውኢሆሙ ዘገብሩ ወገብኡ ኀበ አማልክተ ባዕድ፤

እኔም ስለሠሩት ኃጢአታቸው የአሕዛብን ጣዖታት ወደ ማምለክ ስለተመለሱ በዚያች ቀን ገጸ ረድኤቴን ከእነሱ እመልሳለሁ፤ አንድም ገጸ መዓቴን ወደነሱ እመልሳለሁ፤

፲፱፤ ወይእዜኒ ጸሐፍ ነገራ ለዛቲ ማኅሌት ወመሀርዎሙ ኪያሃ ለደቂቀ እስራኤል ወይደይዋ ውስተ አፉሆሙ ከመ ትኩነኒ ዛቲ ማኅሌት ስምዓ ላዕለ ደቂቀ እስራኤል፤

አሁንም የዚችን ምስጋና ነገር ጽፈህ አንተም ካህናቱም እሷን ለእስራኤል ልጆች አስተምሯቸው፤ ይች ምስጋና በእስራኤል ልጆች ላይ ምስክር ትሆነኝ ዘንድ ካህናቱ በቃላቸው ያስተምሯቸው፤

ገባኤ

፳፤ እስመ አበውኦሙ ውስተ ምድር ቡርክት ዘመሐልኩ ለአበዊሆሙ ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ፤

ተድላ ደስታን ወደምታስገኝ ለአባቶቻቸው ወደ ማልሁላቸው ወደ ከበረች ምድር ወደ ከነዓን አገባቸዋለሁና፤



ወበሊዖሙ ወጸጊቦሙ የዓብዱ ወይገብኡ ኀበ አማልክተ ባዕድ ወያመልክዎሙ ወያምዕዑኒ ወየኃድጉ ኪዳንየ፤

በልተው ከጠገቡም በኋላ ይስታሉና፤ ወደ አሕዛብ ጣዖትም ተመልሰው ያመልኳቸዋልና፤ እኔንም ያሳዝኑኛልና መሐላዬንም ያፈርሳሉና፤

፳፩፤ ወትቀውም ላዕሌሆሙ ዛቲ ማኅሌት ስምዐ ቅድመ ገጾሙ እስመ ኢትትረሳዕ እምውስተ አፉሆሙ ወእምውስተ አፈ ውሉዶሙ እስመ አነ አአምር እከዮሙ ኵሎ ዘይገብሩ በዝየ ዘእንበለ አብኦሙ ውስተ ይእቲ ምድር ቡርክት ዘመሐልኩ ለአበዊሆሙ፤

ቀድሞ ለአባቶቻቸው ወደማልሁላቸው ወደ ከነዓን ሳላገባቸው በዚያ የሚሠሩትን ኃጢአታቸውን ሁሉ አውቃለሁና ከልጆቻቸው አንደበትና ከነሱ አንደበት የማትዘነጋ ስለሆነች ይች ምስጋና በፊታቸው ምስክር ሁና ትነሣባቸዋለች አለው፤

፳፪፤ ወጸሐፋ ሙሴ ለይእቲ ማኅሌት በይእቲ ዕለት ወመሀሮሙ ኪያሃ ለደቂቀ እስራኤል፤

ሙሴም በዚያች ቀን ይችን ምስጋና ጽፎ ለእስራኤል ልጆች እሷን አስተማራቸው፤

፳፫ ወአዘዞ ሙሴ ለኢያሱ ወይቤሎ ጽናዕ ወትባእ እስመ አንተ ታበውኦሙ ለደቂቀ እስራኤል ውስተ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊሆሙ ወውእቱ ይሄሉ ምስሌከ፤

ሙሴም ኢያሱን አንተ የእስራኤልን ልጆች እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ወደ ማለላቸው አገር ታገባቸዋለህና፤ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር በረድኤት ይኖራልና ጨክን በርታ ብሎ አዘዘው፤

፳፬፤ ወሶበ አኅለቀ ሙሴ ጽሒፎታ ለዛቲ ነገረ ሕግ ውስተ መጽሐፍ እስከ ፈጸማ፤

ሙሴም እስኪጨርሳት ድረስ ደርሶ የዚችን የሕግን ነገር በመጽሐፍ ጽፎ ከጨረሰ በኋላ፤

፳፭፤ አዘዞሙ ለሌዋውያን እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕገ ለእግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔርን የሕጉ ማደሪያ ታቦትን የሚሸከሙ ሌዋውያንን አዘዛቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፵፮፤ ወይቤሎሙ ንሥኡ ዛተ መጽሐፈ ወአንብርዋ ውስተ ከርሣ ለታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ወይንበር ህየ ስምዐ ለከ፤

ይችን መጽሐፍ አምጥታችሁ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር በሕጉ ማደሪያ ታቦት ውስጥ አኑሯት፤ ለአንተ ምስክር ይሆንህ ዘንድ በዚያ ይኑር ብሎ አዘዛቸው፤

፵፯፤ እስመ አነ አአምር ውኂኦተከ ወክሣደከ ጽኑዓ ወእንዘ አነ ሀሎኩ ዐዲየ ሕያው ዮም አምዐዕክምዎ ለእግዚአብሔር እፎኬ ፈድፋደ እምድኅረ ሞትኩ፤

ቅሠፈኝ ቅሠፈኝ ብለህ መነሣ ሣትህን ክሣደ ልቡናህም ጽኑ እንደ ሆነ እኔ አውቃለሁና፤ ዛሬ እኔ ገና በሕይወተ ሥጋ ሳለሁ እግዚአብሔርን ያሳዘናችሁት ከሞትሁ በኋላማ ፈጽማችሁ እንዴት ታሳዝኑት ይሆን?

፵፰፤ አስተጋብኡ ኀቤየ ዐበይተ ነገድክሙ ወሊቃውንቲክሙ ወመኳንንቲክሙ ወጸሐፍቲክሙ ከመ እንግሮሙ ይስምዑ ዘንተ ኵሎ ነገረ፤

ይህን ሁሉ ነገር ይሰሙ ዘንድ እንድነግራቸው አለቆቻችሁንና በወገኖቻችሁ የተሾሙ ሹማምቱን ጸሐፊዎቻችሁንና ዳኞቻችሁን ወደኔ ሰብስቡ፤

፵፱፤ ወአሰምዕ ላዕሌሆሙ ሰማየ ወምድረ እስመ አነ አአምር ከመ እምድኅረ ሞትኩ አብሶ ትኤብሱ ወተኀድግዋ ለፍኖት እንተ አዘዝኩክሙ፤

እኔ ከሞትሁ በኋላ ፈጽማችሁ እንድትበድሉ ያዘዝኋችሁንም ሕግ እንድታፈርሷት እኔ አውቃለሁና ሰማይና ምድርን አዳኝባችኋለሁ፤

ወትመጽእ ላዕሌክሙ እኪት በደኃሪ መዋዕል እስመ ትገብሩ እኪተ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ከመ ታምዕዕዎ በግብረ እደዊክሙ፤

በእጃችሁ ሥራ (ጣዖት) ታሳዝኑት ዘንድ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ትሠራላችሁና፤ ኋላ በፍጻሜ ዘመን መከራ ትመጣባችኋለችና፤

፶፤ ወነገሮሙ ሙሴ ወአስምዖሙ ለኵሎሙ ማኅበረ እስራኤል ነገራ ለዛቲ ማኅሌት ፍጹመ፤

ሙሴም ለእስራኤል ወገኖች ሁሉ እውነት የሆነች የዚችን የምስጋና ነገር አሰምቶ ነገራቸው።



## ምዕራፍ ፴፪

፩፤ ወይቤ አጽምዕ ሰማይ ወእንግርከ ወትስማዕ ምድር ቃለ አፉየ፤

ሰማይ ስማኝ ልንገርህ፤ ምድርም ከአፌ የወጣውን ነገር ትስማ፤

፪፤ ወትሰፈዎ ከመ ዝናም ለነገርየ ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ ወከመ ዝናም ውስተ ገራህት ወከመ ጊሜ ውስተ ፀምር፤

የተጠማች ምድር ዝናሙን ተስፋ እንድታደርግ ነገሬን ተስፋ አድርጊት፤ ጠል ከሰማይ ወርዶ ከምድር እንዲስማማ፤ ዝናምም ከሰማይ ወርዶ ከእርሻ እንዲስማማ፤ ካፊያም ከመስክ ወርዶ እንዲስማማ ነገሬም ከልቡናችሁ ይስማማ አለ፤ (ሐተታ) የሰማይና የምድር መስማት እንደምን ነው ቢሉ ጌታ ሰውን በተጣላበት ወራት ሰማይን ዝናም ለዘር፤ ጠል ለመከር አትስጥ ይለዋል፤ ምድርንም የዘሩብሽን አታብቅዪ፤ የተከሉብሽን አታጽድቂ ይላታልና፤ እንድም አጽምዕ ሰማይ ወእንግርከ ቅዱስ ገብርኤል ስማኝ ልንገርህ፤ ወትስማዕ ምድር ቃለ አፉየ፤ ማርያምም በአንተ አድሬ የምነግራትን ብሥራት ትስማ፤ ወትሰፈዎ ከመ ዝናም ለነገርየ፤ ምድር ዝናምን እንድትቀበል ማርያምም ነገሬን ትቀበለው፤ ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ፤ ጠል ሳይሰማ እንዲወርድ፤ አካላዊ ቃሌ ሳይሰማ ሰው ይሁን፤ ወከመ ዝናም ውስተ ገራህት፤ የሚዘንም ዝናም ለስ ብሎ ሳይሰማ እንዲወርድ፤ ወከመ ጊሜ ውስተ ፀምር፤ ጠልም ሳይሰማ ከሰማይ ወርዶ ከመስክ እንዲስማማ አካላዊ ቃሌ ሳይሰማ ሰው ይሁን፤ (ሐተታ) ሰው የሆነበትን ጊዜ ያወቀ የለምና «መልአክኒ ኢያእመረ ዕለተ ትስብእቱ ለቃል ወሥርዓተ ዘገብሮ እግዚእ ወአልቦ ዘአእመረ እምእለ ሀለዉ ውስተ አርያም ምሥጢረ ምጽአቱ» እንዲል ፤ እንድም ወከመ ዝናም ውስተ ገራህት፤ ዝናም ምሳሌው እንደ መሆኑ ገራህት ምሳሌዋ በሆነች በማ

www.ethiopianorthodox.org

ኀፀነ ማርያም ሰው ይሁን እግዝእትየ ገራህተ ለአብርሃም እንዲል፣ ወከመ ጊሚ ውስተ ፀምር፣ ጠል ምሳሌው እንደ መሆኑ ፀምር ምሳሌዋ በሆነች በማኅፀነ ማርያም ሰው ይሁን፣ ፀምር ዘጌዴዎን እንዲል፣ (ታሪክ) ይህስ እንደ ምን ነው ቢሉ የምድያም ሰዎች እስራኤልን ሰባት ዓመት አስጨንቀው ገዟቸው፣ በዘር ወራት መጥተው ቅብ ቅቡን አስጠቅጥቀው ቡቃያውን ለከብቶቻቸው አብል ተውባቸው ይሄዳሉ፣ በመከርም ወራት መጥተው የደረ ሰውን አጭደው፣ ያልደረሰውን ለከብት አብልተውባቸው ይሄዳሉ፣ ከዕለታት በአንድ ቀን ይህ ጌዴዎን ስንዴ ደርሶለት እያጨደ ሲያሻሽ መልአክ መጥቶ «አ ጌዴዎን ጽኑዐ ኃይል እግዚአብሔር ምስሌከ»፣ ጌዴዎን ዕኑዓ ኃይል እግዚ አብሔር በረድኤት ከአንተ ጋር አለ አለው፣ ዘወር ብሎ ቢያይ አጣው፣ ተመልሶ ሥራውን ይዞ ሳለ ሁለተኛ መጥቶ «አ ጌዴዎን ጽኑዐ ኃይል እግዚአብሔር ምስሌከ» አለው፣ ዘወር ብሎ ቢያይ አገኘው፣ እግዚአብሔርማ በረድኤት ከኛ ጋር ካለ የምድያም ሰዎች እንዲህ አድርገው አገዛዝ ሲያጸኑብን መቼ ይተወን ነበር አለው፣ መልአኩም አይዞህ እግዚአብሔር በአንተ አድሬ አጠፋቸዋለሁ ብሎሃል አለው፣ እንኪያስ ምልክት አሳየኝ አለው፣ እስራኤል ምልክት ይሻሉና መልአኩም ጠቦት አርደህ ሥጋውን ባገልግል፣ ደሙን በመንቀል አድርገህ ይዘህ ና አለው፣ ጌዴዎንም ጠቦቱን አርዶ ሥጋውን ባገልግል፣ ደሙን በመንቀል አድርጎ ይዞ መጣ፣ መልአኩም ሥጋውን ወስደህ ከጠፍጣፋ ደንጊያ ላይ አድ ርገው ደሙንም በላዩ ላይ ረብርበው (አፍስበት) አለው፣ ጌዴዎንም ሥጋውን ወስዶ ከጠፍጣፋ ደንጊያ ላይ አደረገው፣ ደሙንም ረበረበው፣ (አፈሰሰው) ያን ጊዜ መልአኩ በዘንጉ ደንጊያውን ቢመታው እሳት ወጥቶ ሥጋውንም ደሙንም በልቶታል፣ ይኸውም ምሳሌ ነው፣ ዘንግ የሥልጣነ እግዚአብሔር፣ እሳት



የኵናተ ጌዴዎን፣ ሥጋው የአሕዛብ፣ ጌዴዎን ሰብአ ምድያምን ለማጥፋቱ ምሳሌ፣ ዳግመኛ ፀምር ልዘርጋ በመካከሉ ጠል ይውረድበት፣ በዳርና በዳሩ አይውረድበት አለው፣ ይሁንልህ አለው፣ ዘረጋ በመካከሉ ጠል ወር ዶበታል፣ በዳር በዳሩ አል ወረደበትም፣ ይህን ጥመቀው (ጭመቀው) አለው፣ ጠመቀው «ወመልዐ አይገኑ» ይላል መንቀል መልቷል ጠጣው አለው፣ ቢጠጣው ኃይል ሁኖታል፣ ዳግመኛ ተፈታተነኝ አትበለኝ ፀምር ልዘርጋ በዳር በዳሩ ጠል ይወረድበት፣ በመ ካከሉ አይውረደበት አለው፣ ይሁንልህ አለው፣ በዳር በዳሩ ጠል ወርዶበታል፣ በመካከሉ አልወረደበትም ፣ ይኸውም ምሳሌ ነው ፣ ፀምር የእስራ ኤል፣ ጠል የረድኤተ እግዚአ ብሔር፣ በመካከሉ መውረዱ ረድኤተ እግዚአብሔር ለእስ ራኤል ለመስጠቱ፣ በዳር በዳር አልመውረዱ ረድኤተ እግዚአ ብሔር ለአሕዛብ ያለመስጠቱ ምሳሌ፣ ሁለተኛውም ፀምር የእስራኤል፣ ጠል የመቅሠፍተ እግዚአብሔር፣ በዳር በዳር መውረዱ መዓተ እግዚ አብሔር በአሕዛብ የመታ ዘዙ፣ በመካከል አለመውረዱ በአሕዛብ የታዘዘው መዓተ እግዚአብሔር በእስራኤል ያለ መታዘዙ ምሳሌ፣ ለጊዜው ይህ ነው፣ ፍጻሜው ግን ፀምር የእመቤታችን፣ ጠል የጌታ፣ በመካከል መውረዱ ጌታችን ከእመቤታችን ሰው የመሆኑ ምሳሌ፣ በዳር በዳር አለመውረዱ ጌታ በተፈታሐ ማኅፀን ካሉ ሴቶች ያለመ ወለዱ ምሳሌ፣ ሁለተኛውም ፀምር የእመቤታችን፣ ጠል የዘርአ ብእሲ፣ በዳር በዳር መውረዱ፣ ሌሎች ሴቶች በዘር በሩካቤ የመውለዳቸው፣ በመ ካከል አለመውረዱ እመቤታ ችን እንበለ ዘርእ፣ እንበለ ሩካቤ ጌታን የመውለዷ ምሳሌ፤

፫፤ እስመ ስመ እግዚአብሔር ጸዋ ዕኩ ሀቡ ዕበየ ለአምላክነ፣

የእግዚአብሔርን ስም ጠርቻ ለሁና ለፈጣሪያችን ምስጋና አቅርቡ፤

፬፤ እግዚአብሔር ጻድቅ በምግባሩ ወርቱዕ ኵሉ ፍናዊሁ እግዚአ

ብሔር ጻድቅ ወአልቦ ዓመፃ ጻድቅ ወኄር እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር በሥራው እውነተኛ ነው፣ ሥራውም ሁሉ የቀና ነው፣ እግዚአብሔር እውነተኛ ነው፣ ሐሰትም የለበትም፣ እግዚአብሔር ቸርና እውነተኛ ነው፤

፭፤ አበሱ ወአኮ ሎቱ ትውልድ ርኩሳን ትውልድ ዕሉት ወግፍትዕት፣

ኃጢአተኞች ልጆች በደሉ፣ ነገር ግን የበደሉ እሱን የጐዱ አይደሉም ፤ ራሳቸውን ጎዱ እንጂ ቤተ እስራኤል አሉተኛ ገልበጥባጣ ወገን ናት፤

፮፤ ከመዝኑ ተዐሥይዎ ለእግዚአብሔር ዝሕዝብ አብድ ወአኮ ጠቢብ አኮኑ ዝንቱ አብ ዘፈጠረከ ፈጠረከሂ ወገብረከ፣

ለእግዚአብሔር እንዲህ ያለ ወረታ ትመልሱለትአላችሁን፣ ይህ ወገን ሰነፍ ነው፣ አዋቂ አይደለም፣ ጥንቱንስ የፈጠረህ እግዚአብሔር አብ አይደለምን በነፍስ በሥጋ የፈጠረህ እሱ አይደለምን፤

፯፤ ወተዘከር መዋዕለ ትካት ወሐሊ ዓመተ ለትውልደ ትውልድ ተሰአሎ ለአቡከ ወይነግረከ ወይዮ ድዓከ ወለሊቃውንቲከ ይዜንዉከ፣

የቀደመው የኖኅን ዘመን አስብ፣ ለልጅ ልጅ ጸንቶ የሚኖር ዘመንን አስብ ፣ አባትህን ጠይቀው፣ ፈጽሞ ይነግርሃል፣ አለቆችህንም ጠይቃቸው ይነግሩሃል፤

፰፤ አመ ከፈሎሙ ልዑል ለአሕዛብ ወዘከመ ዘርአሙ ለደቂቀ አዳም ሠርዖሙ ለአሕዛብ በበደወሎሙ ወበበኍልቆሙ ለመላእክተ እግዚአብሔር፣

ልዑል እግዚአብሔር አሕዛብን በቦታ እንደለያቸው፣ የአዳምን ልጆችም በቦታ እንደበተናቸው ይነግሩሃል፣ አሕዛብን እግዚአብሔር በሚያገለግሉ በመላእክተ ዑቃቢዎቻቸው ቍጥር በየአውራጃቸው እንደወሰናቸው ይነግሩሃል፤

፱፤ ወኮነ ያዕቆብ መክፈልተ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ወእስራኤልኒ ሐብለ ርስቱ፡

ያዕቆብ ለእግዚአብሔር እድልነት ያለው ወገን ሆነ፣ እስራኤልም ርስትነት ያለው ወገን ሆነ፣ (ታሪክ) ይህስ እንደምን ነው ቢሉ፣ ማየ አይኅ በሆነ



በዓመቱ ጌታ መልአኩን እንደ ዳኛ፣ ኖኅን እንደ ሽማግሌ አድርጎ ይህን ዓለም ከሦስት ከፍሎ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ቀኙ ቀኙን ለያፌት፣ ግራ ግራውን ለካም፣ መካከል መካከሉን፤ ለሴም አካፍሏቸዋል ጌታ ተአምራት ያደረገባቸው አህጉር ሁሉ የሴም ዕፃናቸውና፣ ያዕቆብ ለእግዚአብሔር ዕድልነት ያለው ወገን ሆነ፣ እስራኤልም ርስትነት ያለው ወገን ሆነ አለ፣

አንድም ወተዘከር መዋዕለ ትካት ወሐሊ ዓመተ ለትውልደ ትውልድ፣

የቀደመውን የናምሩድን ዘመን አስብ፣ ለልጅ ልጅ የሚሆን የናምሩድን ዘመን አስብ፣ (ተሰአሎ ለአቡከ) አንተም ባታውቅ አባትህን ጠይቅ፣ ይነገርሃል፣ ሽማግሎችንም ጠይቅ ይነግሩሃል፣ አመ ከፈሎሙ ልዑል ለአሕዛብ ልዑል እግዚአብሔር ደቂቀ አዳምን በቋንቋ በለያያቸው ጊዜ የተደረገውን ይነግሩሀል ፣ ሠርዖሙ ለአሕዛብ በበደወሎሙ ወበበኍልቆሙ ለመላእክተ እግዚአብሔር፣ በየአለቆቻቸው ቍጥር በቋንቋ እንደ ሠራራቸው ይነግሩሃል፣ ወኮነ ያዕቆብ መክፈልተ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ያዕቆብ ለቋንቋ ዕድልነት ያለው ሆነ፣ እስራኤልም በቋንቋው በዕብራይስጥ ቋንቋ የሚናገር ሆነ፣ ይህስ እንደምን ነው ቢሉ ደቂቀ ካም ቀድሞ ባንድነት ሳሉ ወደ ምሥራቅ አገር ተጉዘው ሂደው በሰናዖር ሰፈሜዳ አገኙ፣ ከዚያ ሁነው ማየ አይኅ በየጊዜው የሚመጣ መስሏቸው አባቶቻችን የጠፉ የሚጠጉበት ባያገኙ አይደ ለምን የምንጠጋበት ግንብ እንሥራ አሉ፤ አንድም ከሰማይ ሁኖ የውሀ ሻሻቴ እየሰደደ አባቶቻችንን ያጠፋቸውን እናጠፋ ዘንድ ግንብ እንሥራ ብለው መከሩ፣ ከዚህ በኋላ አሥራ ስምንት ምዕራፍ ሰፍረው፣ ሰባ ሁለት ጓኝ (አሠሪዎች አለቆች) ሹመው ሥራ ጀመሩ፣ የግንቡ ቁመቱ አምስት ሺሕ አራት መቶ ሠላሳ ሦስት ክንድ ከሁለት ስንዝር ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ከዚያ ላይ ሁነው ፍላፃቸውን ወደላይ ሲወረውሩ አጋንንት በምታት ደም እየቀቡ ይሰዱላቸው ጀመሩ፣ እነሱም አሁን አጋፋሪውን አሁን ባለቤቱን ወጋነው እያሉ ይናገሩ ጀመሩ፣ ያን ጊዜ ሥላሴ ይህ ሁሉ በቋንቋ አንድ ቢሆኑ አይደለምን ነዐ ንረድ ወንክዓው ነገሮሙ ብለው በቋንቋ ለያይተዋቸዋል፣ በሰባ ሁለት ጓኞች (አለቆች) ቍጥር ሰባ ሁለት ቋንቋ አምጥተውባቸዋል፣ እንጨት አምጣ ሲለው ደንጊያ፣ ደንጊያ አምጣ ሲለው እንጨት የሚያመጣ ሆነ፣ በቋንቋ የማይስማሙ ሲሆኑ ጥለውት ሂደዋል ፣ ያንም ግንብ ነፋስ ገልብጦ ጥሎታል ቦታዪቱም ባቢሎን ተብላለች፣ ዝሩት ማለት ነው፣ ቋንቋውንም ከፍለውታል፣ አሥራ አምስት ቋንቋ ለሤም፣ ሃያ አምስት ቋንቋ ለያፌት፣ ሠላሳ ሁለት ቋንቋ ለካም ደርሷል፣ ለሤም ከተሰጠው ከአሥራ አምስቱ ቋንቋ አንዱ የዕብራይስጥ ቋንቋ ነው፣

አብርሃምን ወተናገሮ እግዚአብሔር በልሳነ ፍጥረቱ ይለዋልና ስለዚህ ወኮነ ያዕቆብ መክፈልተ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ወእስራኤልኒ ሐብለ ርስቱ አለ፤

፲፤ ወአጽገቦሙ በምድረ ገዳም በብሔረ ጽምዕ ወሐፍ በብሔረ በድው፣

በምድረ ገዳም ያለውን በብሔረ በድው ብሎ ደገመው የውሃ ጥም ድርቅ በጸናበት ምድረ በዳ መና ከደመና አውርዶ፣ ውሀ ከደንጊያ አፍልቆ አጠገባቸው፣ በብሔረ ጽምዕ ወሐፍ ባለው በብሔረ ፋል ይላል ጥሬ፣ እንዲሁ ያስተረጉማል፤

መገቦሙ ወመርሆሙ ወዓቀቦሙ ከመ ብንተ ዐይን፣

መናውን እየመገበ ወደ ኢየሩሳሌም መራቸው፣ እንደ ዓይን ብሌንም ጠበቃቸው፣ ዓይን በሽፋሽፍት ተጠብቃ ሌላውን አካል እንድትጠብቅ በረድኤቱ ተጠብቀው እንዲኖሩ አደረገ፤

፲፩፤ ወከመ ንስር ዘይከድን ወያተስጋብእ ዕጕሊሁ በታሕተ ክነፊሁ ፣ ወከመ የሐቅፍ ዕጕሊሁ



በገበዋቲሁ ወሐዘሎሙ በክነፊሁ ወፆሮሙ በእንግድዓሁ፣

ንስር አሞራ ገላግልቱን ሰብስቦ በክንፉ እንዲሠውር በክንፈ ረድኤቱ ሠወራቸው፣ በጎኑም ገላግልቱን እንዲያቅፍ በገቦ ረድኤቱ አቅፎ ደግፎ ከግብጽ አወጣቸው፤

፲፪፤ እግዚአብሔር ባሕቲቱ መርሆሙ ወአልቦ ምስሌሆሙ አምላክ ነኪር፣

እግዚአብሔር ብቻ መራቸው፣ ከነሱም ጋር ልዩ ጣዖት አልነበረም፤

፲፫፤ ወአዕረጎሙ ዲበ ኃይለ ምድር ወሲሰዮሙ እክለ ገራውህ፣

ወደ ኬብሮን ባለጸግነት አወጣቸው፣ በከነዓን እርሻ የበቀለውን አዝመራም መገባቸው፤

ወሐፀኖሙ በመዓር እምኰኵሕ በቅብዕ እምዕብን ጽንዕት፣

ከማን ከደበቅ የተገኘውን መዓር ከደንጊያ ይልቅ የጸናውን ቅቤ እየመገበ አሳደጋቸው፣ የደጋ ላም ጠስኝ የሚባል ቅጠል ይበላል፣

ቅቤው ያመረቃልና እንዲህ አለ

፲፬፤ በቅብዓ ላሕም ወበሐሊበ በግዕ ምስለ መቍዓለ ጠሊ ወላሕም ዕጉለ አልሕምት ወአባግዕ ምስለ ቂቅሐ ሥርናይ ወደመ አስካል ሰትዩ ወይነ፣

ከላሙና ከፍየሉ ወረም እርጎ ጋር በበጉ ወተትና በላሙ ቅቤ አሳደጋቸው፣ ልጠ ጉርዶ ከወጣው ስንዴ ጋር የበጎችና የላሞችን ጊደር ወተት መገባቸው፣ የወይኑንም ዘለላ ጠምቀው ወይን አድርገው ጠጡ፤

፲፭፤ በልዓ ያዕቆብ ወጸግበ ክረዮ ጽጋብ ለምንዙኅ፣

ለፍቁር ሲል ነው፣ ያዕቆብ ይህን ሁሉ በልቶ ጠገበ፣ ድልድል ቅምጥል ያዕቆብም ጥጋብ አቀናጣው፤

ስብሐ ወገዝፈ ወርኅበ ኀደጎ ለእግዚአብሔር ፈጣሪሁ ወርኀቀ እምእግዚአብሔር ሕይወቱ፣

ሰብሐ ወፈረ፣ ገዝፈ ረዘመ፣ ወርኅበ ሰፋ፣ ቢጠግብ ፈጣሪው እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮት ተወው፣ ከሕይወቱ ከእግዚአብሔርም ተለየ፤ አንድም ኀደጎ እግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

ፈጣሪሁ፣ ፈጣሪው እግዚአብ ሔር በረድኤት ተለየው፣ ወርኀቀ ሕይወቱ እምእግዚአ ብሔር፣ እነዋወሩም ከእግ ዚአብሔር ተለየ፤

፲፮፤ ወወሀኩኒ በገዘ ነኪር ወአ ምረሩኒ በርኵሶሙ፣

በዚህ በጣዖቱ ቅሠፈን ቅሠ ፈን ብለው አነሣሱኝ፣ በኃ ጢአታቸውም አሳዘኑኝ፤ አን ድም በርኵሶሙ ይላል፣ በጣ ዖታቸው አሳዘኑኝ፤

፲፯፤ ሦዑ ለአጋንንት ወአኮ ለእግ ዚአብሔር ለአማልክት እለ ኢየ አምርዎሙ ለአማልክተ ግብት እለ ይትገበሩ ወኢይበቍዑ ወእለ ኢየ አምሩ አበዊሆሙ፣

ለእግዚአብሔር ያይደለ ለአጋ ንንት መሥዋዕት ሠዉ፣ ተሠርተው ለማይረቡ ለማይ ጠቅሙ አባቶቻቸው ለማያ ውቋቸው፤ አንድም አባቶቻቸ ውን ለማያውቁ ድንገት ለተገኙ ለጣዖታት ሠዉ፣ (ሐታተ) ለእግዚአብሔር የሆነ እንደሆነ አነ ውእቱ አምላከ አብርሃም አምላከ ይስሐቅ አምላከ ያዕቆብ እያለ አባቶ ቻቸውን ይጠራላቸዋልና ጣዖ ታቱን ግን እለ ኢየአምሩ አበ ዊሆሙ አለ፤

፲፰፤ ኀደጎ ለእግዚአብሔር ዘወ ለደከ ወረሣዕከ ለእግዚአብሔር ዘሐፀነከ፣

በፍቅር በሃይማኖት የወለደህ እግዚአብሔርን በአምልኮት ተውከው፣ በመና በደመና ያሳ ደገህ እግዚአብሔርን ዘነጋኸው፤

፲፱፤ ወርእየ እግዚአብሔር ወቀንዓ ወተምዓ መዓተ ላዕለ ደቂቆሙ ወአዋልዲሆሙ፣

እግዚአብሔርም ይህን አይቶ ለአምልኮቱ ቀና፣ በወንዶ ችና በሴቶች ልጆቻቸውም ፈጽሞ ፈረደባቸው፤

፳፤ ወይቤ እመይጥ ገጽየ እም ኔሆሙ ወእሬእዮሙ ምንተ ዘይከ ውኑ በደኃሪቶሙ እስመ ውሉድ ዓላውያን እሙንቱ ውሉድ እለ አልቦሙ ሃይማኖት፣

ገጸ ረድኤቴን ከነሱ እመ ልሳለሁ፣ ሃይማኖት የሌላ ቸው ወንጀለኞች ልጆች ናቸ ውና፣ በፍጻሜ ዘመናቸው የሚሆኑት ምንም እንደሆነ አያቸዋለሁ፤ አንድም ወእሬ እዮሙ ዘይከውኑ በደኃሪ



ቶሙ ይላል፣ በፍጻሜ ዘመ ናቸው የሚሆኑትን አያቸ ዋለሁ፤

፳፩፤ እሙንቱሰ አቅንዑኒ በዘኢኮነ አምላክ ወአምዕዑኒ በአማልክቲ ሆሙ፣

እነሱስ በማይረባ በማይጠ ቅም ጣዖት አስቀኑኝ፣ በጣ ዖቶቻቸውም አሳዘኑኝ፤ አን ድም በዘኢኮነ አምላክ ይላል፣ አምላክን ባይደለ በጣዖቱ አስ ቀኑኝ፤

ወአነ አቀንዖሙ በዘኢኮነ ሕዝብ ወአምዕዖሙ በሕዝብ በዘኢይ ሌብዉ፣

እኔም ባልሆነ ወገን አስቀናቸ ዋለሁ፣ ሕገ እግዚአብሔርን በማያውቁ በአሕዛብ አሳዝናቸ ዋለሁ፤ አንድም ለሕዝብ በዘኢይሌብው ይላል፣ አእ ምሮ ለብዎ የሌላቸው እስራ ኤልን በአሕዛብ አሳዝናቸዋ ለሁ፤ አንድም ለሕዝብ በዘኢ ይሌብዉ፣ በሕዝብ ለዘኢይሌ ብዉ ይላል፣ እስራኤል ሲበ ድሉ በአሕዛብ፣ አሕዛብ ሲበ ድሉ በእስራኤል አድሮ ያጠፋ ቸዋልና እንዲህ አለ፤ አን ድም እሙንቱሰ አቅንዑኒ በዘኢኮነ ግብሮሙ ይላል፣ አይሁድ በማይረባ በማይጠ ቅም ሥራቸው አስቀኑኝ አሳ ዘኑኝ፣ ወአነ አቀንዖሙ በዘኢ ኮነ ሕዝበ፣ እኔም የእግዚአብ ሔር ወገን ባልነበሩ፣ ሕገ እግዚአብሔርን ልብ ያደርጉ ባልነበሩ በአሕዛብ አስቀናቸ ዋለሁ አለ፣ (ሐተታ) ወል ድየ ዘበኵርየ የተባሉ እስ ራኤል ባያምኑ፣ ኢይባእ ሞዓ ባዊ ወአሞናዊ የተባሉ አሕ ዛብ ሲቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ፣ ኤጲስ ቆጳስ እየሆኑ ተሹመውባቸዋ ልና፤

፳፪፤ እስመ እሳት ትነድድ እመዓትየ ወታውዒ እስከ ሲኦል ታሕተ፣

ከቍጣዬ የተነሣ ድርቅ ትመ ጣለች (ትሆናለች) ፣ ሥር መሠረት ትነቅላለች፤

ወትበልዓ ለምድር ወለኵሉ ፍሬሃ ወታነድድ መሠረታተ አድባር፣

ከፍሬዋ ሁሉ ጋር ምድርን ታጠፋታለች፣ የተራሮችንም መሠረት ታደርቃለች ፤ አን ድም እስመ እሳት ትነድድ እም ዓትየ ከቍጣዬ የተነሣ ጦር ነት መቅሠፍት ትታዘዛለች፤

www.ethiopianorthodox.org

ወታውዒ እስከ ሲኦል ታሕተ ወትበልዓ ለምድር ወለኩሉ ፍሬሃ፤

ፍሬ ልጅን፣ ምድር አባትን አያትን ቅድመ አያትን ታጠፋለች፤

ወያድለቀልቅ ኩሉ መሠረታተ አድባር፤

አድባር የነገሥታቱ፣ መሠረታት ልዑላኑ ትሑታኑ በሞት ይናወጣሉ፤

፳፫፤ ወአስተጋብአሙ ለእኪት ወአኀልቅ አሕፃየ በላዕሌሆሙ፤

ለመከራ እሰበስባቸዋለሁ፣ በጦርም አጠፋቸዋለሁ፤

፳፬፤ ወየኃልቁ በረኃብ ወይከውኑ መብልዓ ለአዕዋፈ ሰማይ ወይደክም ጽንዖሙ፤

በቀጠና አልቀው ቀን ለአዕዋፍ፣ ሌሊት ለአራዊት ምግብ ይሆናሉ፣ ጽንዖሙ ባለው ኃይሎሙ ይላል፣ የሚመኩበት ኃይላቸው ይደክማል፤ ሰርቀው ቀምተው ያጠራቀሙት ብዕላቸው ይጠፋል፤

ወእሬኑ ላዕሌሆሙ ስነነ አራዊተ ምድር ምስለ ሕምዝ ከመ ይጕየዩ እምድር፤

ከሚኖሩበት አገራቸው ሸሽተው ይሄዱ ዘንድ መርዝ ያላቸው አራዊትን እሰድባቸዋለሁ፣ በዘመነ ረኃብ አራዊት ይሠለጥናሉና፤ አንድም ከዚህ ዓለም በሞት ይርቁ ዘንድ ነገሥታቱን ከሠራዊቱ ጋር እሰድባቸዋለሁና ዘነኪር ሕምዙ እንዲል፤

፳፭፤ በአፍኣ ያጸምቶሙ መጥባሕት ለውሉዶሙ ወውስተ አብያቲሆሙ ድንጋፄ፤

ልጆቻቸውን በዘመቻ ጦር ያጠፋቸዋል፣ በቤታቸውም ድንጋጤ፣ ልቅሶ ይሰማል፤

ለወራዙቶሙ ምስለ ደናግሊሆሙ ለሕፃናቲሆሙ ምስለ አዕሩጊሆሙ፤

ጎልማሶችን ከቆነጃጅቱ ጋር በዘመቻ ጦር ያጠፋቸዋል፣ ሕፃናቱንም ከሽማግሌዎች ጋር በቤት ልቅሶ ያገኛቸዋል፤ አንድም ጎልማሶችን ከቆነጃጅቱ ጋር በቤት ልቅሶ ያገኛቸዋል፣ (ሐተታ) የማይዘምት ጎበዝ፣ የማትዘምት ቆንጆ አለችና፣ ሕፃናቱንም ከሽማግሌዎች ጋር በዘመቻ ጦር ያጠፋቸዋል፣ የሚዘምት ሕፃን የሚዘምት ሽማግሌ አለና፤



፳፮፤ ወይቤ ከመ እዝርዎሙ ወእሥዓር እምድር ዝክሮሙ ወእምዕጓለ እመሕያው፤

እነሱን አጠፋቸው ዘንድ ላጥፋቸው አልሁ፣ ከሰው ለይቼ ከዚህ ዓለም ስም አጠራራቸውን አጠፋ ዘንድ ላጥፋቸው አልሁ፤

፳፯፤ በመዓት ፀረ ኮኑኒ ከመ ኢይትዓበዩ ፀር ወኢይበሉ እዴነ ጸንዓት አኮኑ እግዚአብሔር ዘገብሮ ለዝ ኩሉ፤

ጣዖት በማምለክ ጠላት ሁነውኛልና ፀር እስራኤል እንዳይታበዩ፣ ሥልጣናችንም በአሕዛብ በረታች እንዳይሉ ይህን ሁሉ ያደረገ እግዚአብሔር አይደለምን ሰምን ይታበያሉ፤

፳፰፤ እስመ ሕዝብ ሕጉላን ምክር እሙንቱ አልቦሙ ምልሕ ወኢሃ ይማኖት፤

እስራኤል ምክር ያጡ ወገኖች ናቸውና፣ የበጎ ምግባር ሃይማኖትም የላቸውምና በከንቱ ይታበያሉ እንጂ፣ ይህን ሁሉ ያደረገ እግዚአብሔር አይደለምን፤

፳፱፤ ወኢሐለይዎ ከመ ያእምርዎ ለዝንቱ ወኢየአምርዎ በመዋዕል ዘይመጽእ፤

አኮኑ እግዚአብሔር ዘገብሮ ለዝ ኩሉ ብሎ ነበርና ይህን ያውቁት ዘንድ አላሰቡትም፣ በሚመጣው ዘመን የሚሆነውንም አያውቁትም፤

፴፤ እፎ ያነትዎሙ አሐዱ ለዓሠርቱ ምእት፤

ከአሕዛብ አንዱ ከእስራኤል ሺውን ድል እንዲነሣቸው፤

ወክልኤቱ ይሰድድዎሙ ለእልፍ፤

ከአሕዛብ ሁለቱ ከእስራኤል እልፉን ድል እንዲነሷቸው አያውቁም፤

እስመ እግዚአብሔር ፈደዮሙ ወአምላክነሂ አግብዖሙ፤

እግዚአብሔር ፍዳውን አምጥቶባቸዋልና፣ ፈጣሪያችን እርሱ በጠላቶቻቸው በአሕዛብ እጅ ጥሏቸዋልና፤

፴፩፤ እስመ ኢኮነ አምላክነ ከመ አማልክቲሆሙ ፀርነሰ አብዳን፤

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እነሱ እንደሚያመልኳቸው እንደ ጣዖታቱ አይደለምና

www.ethiopianorthodox.org

ጠላቶቻችን እስራኤልስ ሰነ ፎች ናቸው ይላሉ፣ ነቢያት ካህናት በዚያ ወራት እስራ ኤል ስንኳን የሰው ድምፅ ሰምተው የቀጠል ድምፅ ሲሰሙ ይሸበሩ ነበርና፣ ወይሚምዑ እምድምፀ ቈጽል እንዲል፤ አንድም ከመ ኢይትአበዩ ፀር ወኢይበሉ እዴነ ጸንዓት፣ ፀር አሕዛብ በእስራኤል እንዳይ ታበዩ፣ ሥልጣናችንም በእስ ራኤል ላይ ጸናች እንዳይሉ አኮኑ እግዚአብሔር ዘገብር ለዝ ኵሉ፣ ይህን ሁሉ ያደረገ እግዚአብሔር አይደለምን ፤ እስመ ሕዝብ ኅጕላነ ምክር እሙንቱ፣ እሊህ አሕዛብ ምክር ያጡ ወገኖች ናቸውና፣ የበጀ ምግባር ሃይማኖትም የላቸውምና ፤ ወኢሐለይዎ ከመ ያእምርዎ ለዝንቱ አኮኑ እግዚአብሔር ዘገብር ለዝ ኵሉ ብሎ ነበርና ይህን ሁሉ ያውቁት ዘንድ አላሰቡትም፣ ወኢየአምርዎ በመዋዕል ዘይ መጽእ በሚመጣው ዘመን

የሚደረገውንም አያውቁትም፣ እፎ ያነትዖሙ አሐዱ ለዓሠርቱ ምዕት፣ ከእስራኤል አንዱ ከአሕዛብ ሺውን ድል እንዲነሳቸው አላወቁም፣ ከእስ ራኤል ሁለቱም ከአሕዛብ እልፉን ድል እንዲነሷቸው አላወቁም፣ የሰምሶንንና የዮና ታንን ያስተርኳል፤

ኦሪ. ዘመሳፍ. ምዕ. ፲፭. ቍ. ፩-፳ መጽ. ሳሙ. ቀዳ. ምዕ. ፲፬ ቍ. ፮-፳፯

እስመ እግዚአብሔር ፈደዮሙ ወአምላክነ አግብኦሙ፣

እግዚአብሔር አሕዛብን የኃ ጢአታቸውን ፍዳ በራሳቸው አምጥቶባቸዋልና፣ ፈጣሪያች ንም በእጃችን ጥሏቸዋልና፣ እስመ ኢኮነ አምላክነ ከመ አማልክቲሆሙ፣ ፈጣሪያችን እንደነሱ ጣዖታት አይደለምና ማለት የነሱ ጣዖት እን ዳያድን እንዳይራዳ የኛ አም ላክ የማያድን የማይራዳ አይ ደለምና፣ የሚያድን የሚራዳ ነው እንጂ፣ ፀርነሰ አብዳን ነቢያት ካህናት ጠላቶቻችን እስራኤል ከሃይማኖት ከም ግባር ሰነፎች ናቸው ይላሉ፤



፴፪፤ እስመ ከመ ዐፀደ ወይነ ሰዶም ዐፀደ ወይኖሙ ወሐረጎ ሙኒ እምነ ገሞራ፣

የሕግ ማደሪያ ልቦናቸው እንደ ሰዶም ሕግ ማደሪያ ነውና ትውልዳቸውም ከገ ሞራ ወገን ነው፤ አንድም ግብራቸው ከገሞራ ነው ማለት የገሞራ ግብር ነው፣ ወሐረገ ሰዶምኒ ትእኀዝ በሊዓ እንዲል፤

ወአስካሎሙኒ አስካለ ሐሞት ወቀምሖሙኒ መሪር፣

ፍሬያቸው መራራ ነው አለ፣ ልጃቸው የተረገመ ነው፣ የር ጉም ልጅ ርጉም ይባላልና ግብራቸውም መራራ ነው ማለት ክፉ ነው፤

፴፫፤ ሐምዘ አርዌ ምድር ወይ ኖሙ ሐምዘ አፍዖት ዘይቀትል፣

ሐጋቸው የእባብ መርዝ ነው አለ ፤ ያ እንዲጎዳ የሚጎዳ ነው፣ ከዚያውም ዘንድ ፈጥኖ የሚገድል የእፍኝት እባብ መርዝ ነው አለ፣ ፈጥኖ የሚ ያጠፋ ነው፤ አንድም ፀርነሰ አብዳን ጠላቶቻችን አሕዛብ ከምግባር ከሃይማኖት ሰነፎች ናቸው ይላሉ እስራኤል ፤

(ነቢያት ካህናት) እስመ ከመ ዓፀደ ወይነ ሰዶም ዓፀደ ወይኖም ወሐረጎሙኒ እምነ ገሞራ ፣ ትውልዳቸውም ግብ ራቸውም ከሰዶም ከገሞራ ነው አለ፣ ለአሕዛብ የተ መቸ፣ ወአስካሎሙኒ አስካለ ሐሞት ወቀምሖሙኒ መሪር፣ እንዳለፈው ነው፤

፴፬፤ አኮኑ ዝንቱ ትእዛዝ ዘእም ኀቤየ ውእቱ ወተኀትመ ውስተ መዛግብትየ

ይህ ትእዛዝ ከኔ ዘንድ የተገኘ ነውና አሕዛብ ለጥፋት፣ እስ ራኤል ለድኅነት በሣጥን ልቡ ናዬ ተቈጠሩ፤

፴፭፤ ወበዕለተ ኵነኔ እትቤቀ ሎሙ ወበጊዜ ይድኀፅ እግሮሙ እስመ ቀርበ ዕለተ ኀርትም ናሆሙ፣

ፍርድ በሚደረግበት ቀን ተበ ቅዬ አጠፋቸዋለሁ፣ እግረ ልቡ ናቸው በገቢረ ኃጢአት በአ ምልኮ ጣዖት በተሰነካከለ ጊዜም አጠፋቸዋለሁ፣ የሚጠ ፉበት ቀን ደርሷልና ፤ አን ድም ዕለተ ኀልቆሙ ቢል ለጥፋት የተቈጠሩበት ቀን

www.ethiopianorthodox.org

ደርሷልና በጊዜው ጊዜ እግራቸው በመከራው ይሰነካከላል፤

እስመ በጽሐት ወድልውት ይእቲ ለከሙ፤

የሚጠፉባት ቀን ደርሳለችና፣ ይችውም ለነሱ የተዘጋጀች ናትና፤

፴፮፤ እስመ ይፈትሕ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ወይትናበብ በእንተ አግብርቲሁ፣

እግዚአብሔር ለወገኖቹ ለእስራኤል ይፈርዳልና ስለባሮቹ ስለ ነቢያት ካህናትም ብሎ በእስራኤል ይፈርዳልና፤ አንድም ስለወገኖቹ ስለ እስራኤል በነቢያት አድሮ ሚጠትን ይናገራልና፤

እስመ ርእዮሙ ከመ ተመስጡ ወኃልቁ ወተዘንጉጉ በነበ ሀለዉ፣

እንደ ሰም ቀልጠው በመከራው እንደተፈጸሙ ባሉበትም አገር መሸማጠጫ እንደ ሆኑ አይቷቸዋልና፤

፴፯፤ ወሶበ ሠርሑ ይቤ እግዚአብሔር አይቴ እሙንቱ አማልክቲክሙ እለ ትትዌከሉ ቦሙ፤

በመከራው ተይዘው በደከሙ ጊዜ እግዚአብሔር የምትታመኑባቸው ጣዖታት ወዴት አሉ? አለ፤

፴፰፤ ወእለ ትበልዑ መሳብሕተ መሥዋዕቶሙ ወትሰትዩ ወይነ ሞግሕቶሙ፣

ተረፈ መሥዋዕታቸውን የምትበሉላቸው፣ ከወይኑም ፍልቅ አድርጋችሁ አፍስሳችሁ የምትጠጡላቸው ጣዖታት ወዴት ናቸው?

ይትነሥኡኬ ወይርድኡክሙ ወይኩኑክሙ መድኃኔክሙ፤

ካሉማ ይነሱዋ ይርዷችሁ (ተነሥተው ይርዷችሁ)፣ ከመከራም ያድኗችሁ፤

፴፱፤ አእምሩ አእምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ወአልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ፣

እነዚህንስ ትታችሁ ፈጣሪያችሁ እኔ እንደ ሆንሁ ያለኔም ሌላ ፈጣሪ እንደሌለ ፈጽማችሁ እወቁ፤

አነ እቀትል ወአሐዩ እቀሥፍሂ ወእሠሃል ወአልቦ ዘያመሥጥ እምእዴየ፣



የምገድል የማድን እኔ ነኝ፤ አንድም እቀትል በሥጋ፣ ወአሐዩ በነፍስ በመከራ የምገርፍ መልሼ ይቅር የምል እኔ ነኝ፣ እንደ ኢዮብ፣ እንደ ንዕማን፣ ከሥልጣኔ የሚያመልጥ እንደሌለ ዕወቁ፤

፵፤ እስመ አሌዕል ውስተ ሰማይ እዴየ እምሕል በየማንየ ወእብል ሕያው አነ ለዓለም፣

እጄን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጌ ለዘለዓለሙ ሕያው ነኝ ብዬ በሥልጣኔ እምላለሁ፤

፵፩፤ ወአበልሐ ከመ መብረቅ ለመጥባሕትየ፣

ሥልጣኔን እንደ መብረቅ አፋጥናታለሁና፤

ወትቀውም እዴየ በኵነኔየ ወእትፌድዮሙ በቀለ ለፀርየ ወእትቤቀሎሙ ለጸላእትየ፣

ሥልጣኔ በፍርዴ ትጸናለች፤ አንድም ከፍርዴ ጋር ትጸናለች፣ ጠላቶቼንም ተበቅዬ አጠፋቸዋለሁ፤

፵፪፤ ወእሰክሮን በደሞሙ ለአሕፃየ ወትበልዕ ሥጋሆሙ መጥባሕትየ፣

ፍላፃዎቼን በደማቸው እሰክራቸዋለሁ፣ ሥልጣኔም ሰውነታቸውን፤ አንድም ወገናቸውን ታጠፋለች፤ አንድም የስልምናሶር የናቡከደነፆር ጦር እስራኤልን ታጠፋለች ፣ በተፈጥሮ ገንዘቡ ናትና እግዚአብሔር በአሥሩ ነገድ ቢቆጣ ስልምናሶር ፣ በሁለቱ ነገድ ቢቆጣ ናቡከደነፆር ዘምቷልና እንዲህ አለ፤

እምደመ ቅቱላን ወፂውዋን አር እስተ መላእክተ ፀር፣

ከተማረኩትና ከሞቱት ሰዎች የተነሣ፣ አሰክሮን በደሞሙ ለአሕፃየ ላለው፣ የጠላቶቻቸውን ራስ፤ አንድም የአለቆቻቸውን አለቆች፣ ትበልዕ መጥባሕትየ ላለው፣ ሐተታ ከሞቱትስ ይሁን ከተማረኩት ያለው እንደምን ነው ቢሉ ከማረኩ ኋላ ለግዳይ ለፈለማ እያሉ ይወጓቸዋልና፣

፵፫፤ ይትፌሣሕ ኵሎን ሰማያት ኅቡረ ፤

በሚጠት ሰማያት ደስ ይላቸዋል ማለት ዝናም ለዘር፣ ጠል ለመከር ይሰጣሉ፣ ጠፈርን ሰማያት ብሎ አበዛው፣ በአራት መዓዝን ያለ ነውና፤ አንድም ልዑ

www.ethiopianorthodox.org

ላኑ ሁሉ ባንድነት ደስ ይላቸዋል ፤

ወይሰግዱ ሎቱ ኵሎሙ መላእክተ እግዚአብሔር፡፡

እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ አለቆችም ሁሉ ይሰግዱለታል፤ ለአሥራ ሁለቱ ነገድ አሥራ ሁለት አለቆች አሉዋቸውና፤

ወይትፌሥሑ ሕዝብ ምስለ ሕዘቢሆሙ ወይብሉ ኵሎሙ ውሉደ እግዚአብሔር ጽኑዕ ውእቱ፤

ሁለቱ ነገድ ከአሥሩ ነገድ ጋር ደስ ይላቸዋል ፤

ወልድየ ዘበኵርየ ያላቸው እስራኤል ሁሉ እግዚአብሔር እኛን በመራዳት ጽኑዕ ከሐሊ ነው ይላሉ፤

እስመ ይትቤቀል ደመ ደቂቁ ወይትፈደዮሙ በቀለ ለፀሩ፤

የልጆቹን በግፍ የፈሰሰ ደማቸውን ተበቅሎ «እምፀሩ» ሲል ነው፤ ከጠላቶቹ ከአሕዛብ በቀልን ይከፈላልና፤

ወይትቤቀሎሙ ለጸላእቱ ወያነጽሕ እግዚአብሔር ምድረ ለሕዝቡ ፤

ጥንተ ጠላቶቹ አሕዛብን ተበቅሎ ምድረ ርስትን ለወገኖቹ ለእስራኤል የምትገባ አድርጎ ይሰጣቸዋል፤ ጥንቱን የሴም ዕፃ ናትና፤ አንድም ይትፌሥሐ ኵሎን ሰማያት ኅቡረ ወይሰግዱ ሎቱ ኵሎሙ መላእክተ እግዚአብሔር፤ በዕለተ ልደት መላእክት ደቂቀ አዳም፤ አንድም ልዑላኑ ትሑታኑ ደስ ብሏቸው ይሰግዱለታል፤ ወይትፌሥሑ ሕዝብ ምስለ ሕዝቢሆሙ፤

ኖሎት ከኖሎት ጋር፤ አንድም መላእክት ከኖሎት ጋር ደስ ይላቸዋል፤ ወይብሉ ኵሎሙ፤ ወልደ እግዚአብሔር ነው የአብ የባሕርይ ልጅ ክርስቶስ እኛን ከሲኦል በማዳን ጽኑዕ ከሃሊ ነው ይላሉ፤ እስመ ይትቤቀል ደመ ደቂቁ የወገኖቹ የምእመናንን ደም ተበቅሎ ከጠላቶቹ ከአጋንንት በቀልን ይከፈላልና፤ ወይትቤቀሎሙ ለጸላእቱ ወያነጽሕ እግዚአብሔር ምድረ ለሕዝቡ፤ ጥንተ ጠላቶቹ አጋንንትን



ተበቅሎ ገነት መንግሥተ ሰማያትን ለወገኖቹ ለምእመናን የምትገባ አድርጎ ያወርሳቸዋል፤ (ሐተታ) ፀር የሚላቸው በየጊዜው የሚቈራኟቸው ናቸው፤ ጸላዕት የሚላቸው ጥንቱን አዳምንና ሔዋንን ያሳቷቸው አጋንንት ናቸው፤

፵፬፤ ወጸሐፈ ሙሴ ለዛቲ ማኅሌት በይእቲ ዕለት ወመሀሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወቦአ ሙሴ ወነገሮሙ ለሕዝብ ወአስምዖሙ ውእቱ ወኢያሱ ወልደ ነዌ፤

ሙሴም በዚያች ቀን ይችን ዳግም ሕግን ጽፎ ለእስራኤል ልጆች ሁሉ አስተማራቸው፤ ሲያስተምራቸውም ወደ ከተማው ገብቶ ለሕዝቡ ይህን አስረድቶ ነገራቸው፤ ከሱ በኋላም የነዌ ልጅ ኢያሱ ነገራቸው ፤ አንድም ሙሴ ከነዌ ልጅ ከኢያሱ ጋር ሁኖ ይህን ነገራቸው አዳኘባቸው፤

፵፭፤ ወሶበ አኅለቀ ሙሴ ነጊሮቶሙ ለኵሉ እስራኤል፡፡

ሙሴም ለእስራኤል ሁሉ ይህን ነገር ነግሮ ከጨረሰ በኋላ ፤

፵፮፤ ይቤሎሙ ዕቀብዎ በልብክሙ ለዝንቱ ኵሉ ነገር ዘአስማዕኩ አነ ላዕሌክሙ የዮም ዘትኤዝዙ ለደቂቅክሙ ከመ ይዕቀቡ ወይገበሩ ኵሎ ነገራ ለዛቲ ሕግ፤

እኔ ዛሬ በናንተ ያዳኘሁባችሁ ያስተማርኳችሁ እናንተም የዚችን ሕግ ነገር ጠብቀው ይሠሩት ዘንድ ለልጆቻችሁ የምታገዙትን ይህን ሁሉ ነገር በልቡናችሁ አስተውሉት አላቸው ፤

፵፯፤እስመ ኢኮነ ዝንቱ ነገር ለክሙ እስመ ውእቱ ሕይወትክሙ፤

እሱ ሕይወታችሁ ስለሆነ ይህ ነገር ለናንተ ከንቱ አይደለምና ፤

ወበበይነዝ ነገር ይነውኅ መዋዕሊክሙ ውስተ ምድር እንተ ላቲ ተዓድዉ ዮርዳኖስ ከመ ትትዋረስዋ በህየ፤

ስለዚህም ነገር ትወርሷት ዘንድ ዮርዳኖስን በምትሻገሩላት አገር ዘመናችሁ በዚያ ይበዛል አላቸው ፤

## ጉባኤ

፵፰፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ በይእቲ ዕለት ወይቤሎ፤

www.ethiopianorthodox.org

በዚያች ቀን እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፵፱፤ ዕርግ ውስተ ደብረ አባሪም ዘውስተ ደብረ ናቦር ዘምድረ ሞአብ ዘመንገለ ገጸ ኢያሪኮ ወረ አያ ለምድረ ከነዓን ዘእሁቦሙ ለደቂቀ እስራኤል ያምልክዋ፤

በኢያሪኮ አንፃር በሞአብ አውራጃ ባለ በናቦር ተራራ አጠገብ ወደአለ ወደ አባሪም ተራራ ወጥተህ ይገዟት ዘንድ ለእስራኤል ልጆች የምሰጣቸው ከነዓንን እያት፤

፶፤ ወሙት በውስተ ደብር ዘውስቴታ ተዓርግ ህየ ወተወሰክ ኀበ ሕዝብከ ከመ ሞተ አሮን እኁከ በውስተ ደብረ ሆር ወአተወ ኀበ ሕዝቡ፤

በወጣህበት ተራራ ሳለህ ወንድምህ አሮን ሆር በሚባል ተራራ እንደ ሞተ ሙት ፤ እሱ አባቶቹ ወደ ወረዱበት መቃብር እንደ ወረደ አንተም አባቶችህ ወደ ወረዱበት መቃብር ተጨመር፤

፶፩፤ እስመ ክሕድክሙ ቃልየ በቅድመ ደቂቀ እስራኤል በኀበ ማየ ቅስት ዘቃዴስ በገዳም ዘፂን እስመ ኢቀደስክሙኒ በቅድመ ደቂቀ እስራኤል፤

ዘፂን ዘሲን ይላል፤ በደብረ ሲና አጠገብ ባለ ምድረ በዳ በቃዴስ ጠብ ክርክር በተደ ረገበት ውሀ ቃሌን ስለካዳ ችሁ በእስራኤል ልጆች ፊት አላመሰገናችሁኝምና፤

፶፪፤ ወረአያ ለይእቲ ምድር ቅድሜከ ወህየሰ ኢትበውእ፤

በፊትህ ያለች ከነዓንን አሻ ግረህ እያት፤ ወደሷ ግን አት ገባም አለው፡፡

## ምዕራፍ ፴፫

፩፤ ወከመዝ ይእቲ በረከት ዘባረ ኮሙ ለደቂቀ እስራኤል ሙሴ ብእሴ እግዚአብሔር ዘእንበለ ይሙት፤

የእግዚአብሔር ባለሟል ሙሴ ሳይሞት የእስራኤ ልን ልጆች የመረቃቸው ምርቃት እንዲህ ናት፤

፪፤ወይቤ እግዚአብሔር እምነ ሲና ወፅአ ወመጽአ ወአስተርአየኒ በሴይር ወአዕረፈ በደብረ ፋራን



ምስለ አዕላፈ ቃዴስ እለ እምየማኑ መላእክቲሁ ወእለ ምስሌሁ፡

እግዚአብሔር ከደብረ ሲና መጥቶ በሴይር ተገልጾልኝ አእላፈ እስራኤል፤ አን ድም አእላፍ መላእክት ከሱ ጋር ያሉ ሊቃነ መላእክት በቀኝ በግራ ሁነው በፋራን ተራራ በረድኤት አደረ፤

፫፤ ወምሕከሙ ለሕዝቡ ወለኵሎሙ እለ ተቀደሱ በእዴሁ ወእሉሂ እሊአከ እሙንቱ፤

በቃሉ ከሕዝቡ ለተለዩ ሌዋውያን ሁሉና ለወገኖቹ እስራኤልም ራራላቸው፤ አንድም ወመሀሮሙ ለሕዝቡ ይላል ፤ ለወገኖቹ ለእስራ ኤልና ከሕዝቡ ለተለዩ ለሌዋውያን ሕጉን አስተ ማራቸው፤ እሊህ ሌዋውያን ወገኖችህ ናቸው፤

፬፡ ወረከቡ ሕገ በቃለ ዚአሁ ዘአዘዘነ ወርስተ ለሕዝበ ያዕቆብ፡

እሱ በአዘዘን በቃሉም ሕጉን ጠበቁ ፤ ለያዕቆብም ወገኖች ሕጉ ርስት ሁኖ ተሰጠ፤

፭፡ ወይከውን መልአክ እምፍቁር ተጋቢኦሙ መላእክተ አሕዛብ ምስለ ነገደ እስራኤል፤

ከእስራኤል መስፍን ይሾማል፤ ኢያሱ ነው፤ የአሕዛብ አለቆች ከእስራኤል ጋራ ይገዙለ ታል፤ አንድም ከያዕቆብ ዳዊት ይወለዳል፤ የአሕዛብ አለቆችም ከእስራኤል ወገኖች ጋራ አንድ ሁነው ይገዙለታል፤

፮፤ አሕሥሥ ለሮቤል ኢይሙትኒ ወይኩን ኍላቌሁ ብዙኃ፡

በነፍስ እንዳይሞትብኝ ሮቤ ልን በጸሎት እፈልገዋለሁ፤ የዘሩ ቁጥርም ብዙ ይሁን፤ (ሐተታ) ሮቤልን ስለምን ከሁሉ አስቀድሞ አነሣው ቢሉ በኵሩ ሮቤል ነውና፤ አንድም ከአባቱ ዕቅብት ከባላ ደርሶ ነበርና ዕዳ አታድርግበት ሲል ነው፡

፯፡ ወለዝንቱኒ ይሁዳ ስምዖ እግዚኦ ቃሎ ለይሁዳ ወይግባእ ውስተ ሕዝቡ ወእደዊሁ ይኩን ናሁ ወኩኖ ረዳኤ እምፀሩ፡

በቁሙ ይሁዳን ፤ አንድም ከነገደ ይሁዳ የተወለደ ዳዊትን ልመናውን ስማው፤ ከኢሎፍላውያን አገር ወደ

www.ethiopianorthodox.org

ወገኖቹ ወደ እስራኤል ይመለስ፤ ሥልጣኖቹም እስራኤልን ፤ አንድም አሕዛብን ይግዙ ፤ ከጠላቶቹም ረዳት ሁነው፤

፰፡ ወለሌዊኒ ይቤሎ አግብእ ለሌዊ ቃሎ ወጽድቆ ለብእሲ ጻድቅ ዘአመከርዎ በመከራ ወፀዓልዎ በኀበ ማየ ቅስት፡

ሌዊን ነገር አድርጎ ተናገረው፤ በመከራ ለፈተኑት፤ ጠብ ክርክር በተደረገበት ውሀም ለሰደቡት እውነተኛ ለሆነ ሰው ለሙሴ የትሩፋቱን ዋጋ ስጠው፤ ልመናውን ስማው አለ፤ ሙሴ ራሱን አርቆ ይናገራል፤

፱፡ዘይቤሎሙ ለአቡሁ ወለእሙ ኢርኢክሙ ወበአኃዊሁኒ ኢያእመረ ወበደቂቁኒ ኢለበወ ወዐቀበ ቃለከ ወተማኅፀነ ኪዳነከ፤

እናቱንና አባቱን አላውቃችሁም ላላቸው በወንድሞቹ በእስራኤልና በልጆቹ የሚደረገውን ፍቅር ላላወቀ፤ ሕግህን ለጠበቀ፤ በመሐላውም ለጸና ለሙሴ የምግባሩን ዋጋ ስጠው፤

፲፡ከመ ይንግሩ ኰነኔከ ለያዕቆብ ወሕገከ ለእስራኤል ከመ ይደዩ ዕጣነ በማዕጠንትከ ወበኵሉ ጊዜ ውስተ ምሥዋዒከ፡

ለአሥሩ ነገድና ለሁለቱ ነገድ አምልኮትህንና ዘጠኙን ሕግጋት ያስተምሩ ዘንድ፤ በጽናሕም ዕጣንን ይጨምሩ ዘንድ፤ በመሠዊያህም በየጊዜው መሥዋዕት ይሠዉ ዘንድ ዓቀበ ቃለከ ላለው፤

፲፩፡ ወባርክ እግዚኦ ኃይሎ ወተወከፍ ግብረ እደዊሁ ወአውርድ ክበዶ ላዕለ እለ ይትቃወምዎ ፀሩ ወኢታንሥኦሙ ለእለ ይፃረርዎ፤

አቤቱ ሠራዊቱን አብዛ፤ አንድም ባለጸግነቱን አብዛ፤ የእጁን ሥራ፤ የቃሉን ልመና ስማ ፤ በሚቃወሙት ጠላቶቹ መከራን አምጣባቸው፤ የሚጣሉትንም ጠላቶቹን አትራዳቸው (ሐተታ) ፤ ለጊዜው ዳታን አቤሮንን ደቂቀ ቆሬን ነው ፤ ፍጻሜው ግን እስከ ዕለተ ምጽአት የሚነሡ የአገልጋዮቹ የካህናትን ጠላቶች ነው፡

፲፪፡ ወለብንያምኒ ይቤሎ ፍቁረ እግዚአብሔር የኃድር ተአሚኖ



ወእግዚአብሔር ይጼልሎ በኵሉ መዋዕሊሁ ወየዓርፍ ማዕከለ መታክፍቲሁ፡

ብንያምንም ነገር አድርጎ ተናገረው ፤ የእግዚአብሔር ወዳጅ ብንያምም ከመከራው ተዘልሎ ይኖራል፤ እግዚአብሔርም በዘመኑ ሁሉ ከመከራ ይሠውረዋል፤ በረድኤትም በብንያም አድሮ ይኖራል፤ አንድም ብንያም በወንድሞቹ መካከል ይኖራል፤ ዕፃው በይሁዳና በኤፍሬም መካከል ነውና፡

፲፫፡ ወለዮሴፍኒ ይቤሎ እምበረከተ እግዚአብሔር ምድሩ ወእም ዝናመ ሰማይ ወጠል ወእምነቅዐ ቀላይ ዘእምታሕቱ፡

ዮሴፍንም ነገር አድርጎ ተናገረው፤ የዮሴፍ ምድሩ ከእግዚአብሔር በተገኘ በረከት ከሰማይ የተገኘ ጠልና ዝናምን ከምድር የወጣ መስኖ ጠጥታ እህልን ታበቅላለች፡

፲፬፡ ወለለሰዓቱ እክሉ ወእም ሥርቀተ ፀሐይ ወእምነ ኍላቈ ሆሙ ለአውራኅ፡

በየዓመቱ እየመሸ እየነጋ በየጊዜው መከሩ ይከተታል፡

፲፭፡ ወይቀድም እምአርእስተ አድባር ወእምውስተ አርእስተ አውግር ዘአሕናዎን፡

ለዘለዓለም ጸንተው ከሚኖሩ ከረብቶችና ተራሮች ቀርቦ ይታያል ፡

፲፮፡ ምድር እንተ ዘልፈ ጽግብት ወሠናይት ለዘአስተርአየ በውስተ ዕፀ ጳጦስ ለይምጻእ ዲበ ርእሱ ለዮሴፍ ወበርእሱ ይክበር በውስተ አኃዊሁ ከመ በኵረ ላሕም ሥኑ፤

አገሪቱ ሁልጊዜ ዝናሙን ጠሉን የጠገበች ያማረች የተወደደች ናት፤ ጳጦስ በሚባል እንጨት የታየ የእግዚአብሔር ረድኤት በዮሴፍ ይደር፤ በወንድሞቹ መካከል በሥልጣኑ ይክበር፤ መወደዱም ከላም መጀመሪያ እንደ ተወለደ ወይፈን ነው፤

፲፯፡ወእምአቅርንተ ዘአሐዱ ቀርኑ አቅርንቲሁ፡

ቀንዱ አንድ የሆነ ርኤም በቀንዱ እንዲከብር በሥልጣኑ ይከብራል፤ በሀገራቸው ርኤም ድኤም ይለዋል፤ በሀገራችን ከረከንድ ነው፤ ይህ ቀንዱ ሐምሳ ስሳ ክንድ ይሆናል ሲገለት በሄዱበት ጊዜ ከቀንዱ ውስጥ ገብቶ

www.ethiopianorthodox.org

አይገኙቸውም፡ እንደምን አድ ርገው ይገድሉታል ቢሉ ባሕ ርዩ ዘማዊ ነው፡ ሹቱ አጣፍ ጠው አምጥተው ነፋስ ባለ በት ቦታ ያደርጉለታል፡ ያን አሸታለሁ ብሎ ሲወጣ ይገ ድሉታል፤ እንድም ብዙ ክፍለ ብርሃን ካላቸው ከከዋክብት ከጨረቃ ይልቅ በአንድ ክፍለ ብርሃኑ ተከብሮ እንደሚኖር እንደ ፀሐይ ገናና ነው፡

ወይወግዮሙ ለአሕዛብ በሙ ኅቡረ እስከ አጽናፈ ምድር ዝንቱ አእላፍ ዘኤፍሬም ውእቱ ወዝንቱ አእላፍ ዘምናሴ፡

በምድር ዳርቻ ያሉ አሕ ዛብን በሥልጣኑ ያጠፋቸ ዋል፡ ይህ የኤፍሬም ወገን ነው፤ ይህም የምናሴ ወገን ነው ይባላል፡

፲፰፡ ወለዛብሎንሂ ይቤሎ ተፈ ሣሕ በፀዓትከ ወይሳኮር በማኅደርከ፡

ዛብሎንን ነገር አድርጎ ተናገረው፤ ዛብሎን ወደ ዘመቻ በመውጣትህ ደስ ይበልህ፤ ይሳኮርም ከዘመቻ በመግባትህ ደስ ይበልህ፡

፲፱፡ እለ ያጠፍእዎሙ ለአሕዛብ ወጸውዑ በህየ ወሦዑ መሥዋዕተ ጽድቅ እስመ ብዕለ ባሕር የሐፅነከ ወየሐንፀከ ወንዋዮሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ጸራልያ፡

እነዚህ አሕዛብን የሚያጠፏ ቸው ናቸው፤ እውነተኛ መሥዋዕት ሠውተው በደ ብረ ታቦር አመሰገኑ፤ የአሕ ዛብን ገንዘብ ትመገባለህና፣ ቤትህን ያንጽልሃልና በደ ሴት የሚኖሩ የአሕዛብ ገንዘብ የአንተ ገንዘብ ነው፤

፳፡ ወለጋድሂ ይቤሎ ርኂብ በረከቱ ለጋድ ከመ አንበሳ የኃድር ቀጥቂጦ መዝራዕተ መላ እክት፡

ጋድንም ነገር አድርጎ ተናገረው፤ የጋድ ገንዘቡ ብዙ ነው፤ የጠላቶቹን ሥልጣን አጥፍቶ እንደ አንበሳ ተዘልሎ በማስፈራት ይኖራል፣

፳፩፡ ወርእየ ቅድሜሁ ከመ በህየ ተካፈልዋ ለምድር መላእክት እንዘ ጉቡአን መሳፍንት ኅቡረ ምስለ መልአከ አሕዛብ ወምስለ ሕዝበ እስራኤል፡

ከእስራኤል ወገኖችና ከእስ ራኤል አለቃ ከኢያሱ ጋራ ሸማምቱ ባንድነት ተሰብ ስበው የከነዓንን ምድር



የእስራኤል አለቆች በዚያ እንደተካፈሏት ጋድ ፊት ለፊት ቁሞ አየ፤

እግዚአብሔር ገብረ ጽድቆ ወኮነኔሁ ምስለ እስራኤል፡

እግዚአብሔር ቸርነቱንና ፍር ዱን ከእስራኤል ጋር፤ አን ድም ለእስራኤል ቸርነቱን አደረገ፡

፳፪፡ወለዳንሂ ይቤሎ ዳን ዕጓለ አንበሳ ወይሠርር እምባሳን ፡

ዳንንም ነገር አድርጎ ተናገረው፣ አንድም ለዳን ትንቢት ተናገረለት ፣ ዳን የአንበሳ ግልገል ነው፣ ወደ ባሳን ይዘምታል፤ አንድም የአንበሳ ግልገል ከጕድጓዱ ተወርውሮ ወጥቶ ላሞችን እንዲሰብር፤ እሱም ከባሳን ፈጥኖ ወጥቶ ጠላቱን ያጠፋል፡

፳፫፤ወለንፍታሌምኒ ይቤሎ ንፍ ታሌም ጽጉብ እምሥናያት ወይጸ ግብ እምበረከተ እግዚአብሔር ወይትዋረስ ባሕረ ወሊባ፡

ንፍታሌምንም ነገር አድርጎ ተናገረው፤ አንድም ትን ቢት ተናገረለት፡ አርሶ ቆፍሮ ወጥቶ ወርዶ ካገኘው ባለጸግነቱ የተነሣ የጠገበ ነው፡ ከእግዚአብሔርም በረከት የጠገበ ነው፤ ማለት ዝናም ለዘር ፤ ጠል ለመከር አያ ጣም፡ ከባሕር እስከ ሊባ ያለውን ዕፃውን ይወርሳል፡

፳፬፡ወለአሴርሂ ይቤሎ ቡሩክ ውእቱ እምውሉደ አሴር ወይ ከውን ኅሩየ ለአኃዊሁ ወየሐፅብ በቅብዕ እገሪሁ፡

አሴርንም ነገር አድርጎ ተና ገረው፤ አንድም ለአሴር ትን ቢት ተናገረለት፡ አሴር ከእስራኤል ይልቅ የተመረቀ ነው፣ ለወንድሞቹም የተመ ረጠ ይሆናል፣ እግሮቹንም በዘይት ያጥባል አለ፣ ባለ ጸግነቱን መናገር ነው፡

፳፭፤ ዘሐፂን ወዘብርት አማዕ ኒሁ ወይከውን በከመ መዋዕሊከ ኃይልከ፡

መጫማውም የብረትና የብርት ነው፣ ማለት ቢሮጥ ቢገሠግሥ አይደክምም፤ አንድም ሥል ጣኑ ጽኑ ነው ፤ ኃይልህም በዘመንህ ልክ ነው ማለት ባለ በዘመንህ ድካም አያገኝህም፡

፳፮፡ አልቦ ከመ አምላኩ ለፍቁር ዘይነብር ውስተ ሰማይ ውእቱ ረዳኢከ ወዕበየ ሥኑ ለሰማይ፡

www.ethiopianorthodox.org

‹‹ከመ አምላክኒ ፍቁር›› ሲል ነው፣ በሰማይ እንደሚኖር የተወደደ እንደሆነ እንደፈጣሪያችን ያለ የለም፡ ረዳትህ እሱ ነው፣ የሰማይም ጌጥ እርሱ ነው ማለት ሰማይ በየጊዜው ዝናም ለዘር፤ ጠል ለመከር እንዲሰጥ የሚያደርግ እሱ ነው፡

፳፯፡ ወይከድነከ እግዚአብሔር ፍጽመ በኃይለ መዝራዕቱ ለኢናዎን ወይወፅእ እምቅድመ ገጽከ ፀር በከመ ይቤ ከመ ያጥፍአሙ፡

እግዚአብሔርም ፈታውራሪ ሆኖ በኃያላኑ ሥልጣን ኃይል ከመከራው ይሠውርሃል፡ እግዚአብሔር ጠላቶችህን አጠፋልሃለሁ፣ ብሎ እንደተናገረ ጠላትህ ከፊትህ ይጠፋል፣

፳፰፡ ወያንብር ለእስራኤል ተአሚኖ ባሕቲቶ ውስተ ምድረ ያዕቆብ ውስተ ምድረ ሥርናይ ወወይን ወሰማይኒ ለከ ምስለ ደመና ወጠል፡

‹‹ወልድየ ዘበኩርየ›› ያለው እስራኤልን ወይንና ስንዴ ባለበት በያዕቆብ ርስት፣ በከነዓን ጠላት ጠፍቶለት ተዘልሎ እንዲኖር ያደርገዋል፤ ሰማይም ከጠልና ከደመና ጋር ላንተ ነው ማለት ዝናም ለዘር፤ ጠል ለመከር ሲሰጥህ ይኖራል፤

፳፱፡ ወብፁዕ አንተ እስራኤል መኑ ከማከ ሕዝብ ዘእግዚአብሔር ያድኅኖ ወያጸንዓከ ወይረድአከ ወበመጥባሕትከ ዕልገትከ፡

እስራኤል አንተ ንዑድ ክቡር ነህ፡ እግዚአብሔር ከመከራው ያዳነው እንዳንተ ያለ ወገን ማነው? በረድኤት አጽንቶ ይረዳሃልም የምትኖርም በሾተልህ ገድለህ ሰልበህ ነው፤

ሐሰው ፀርከ ወአንተሰ ትጼዓን ላዕለ ክሣዳቲሆሙ፡

ጠላትህ አንተን ያጠፋሃል ማለት ሐሰት ነው፤ አንተ ግን በጠላቶችህ ሰውነት ላይ ትሠለጥናለህ፤ አንድም ጠላቶችህን አንገታቸውን ረግጠህ ትገዛቸዋለህ፡፡

## ምዕራፍ ፴፬

፩፡ ወዓርገ ሙሴ እምአባሪም ዘሞዓብ ውስተ ደብረ ናቦር (ናባው) ውስተ ርእሰ ፋስጋ ዘሀለወ ቅድመ ኢያሪኮ፤

ዕርግ ውስተ ደብረ አበሪም ዘምድረ ሞዓብ ወረኢየ ለም



ድረ ከነዓን ብሎት ነበርና ከዚህ በኋላ ሙሴ የሞዓብ ክፍል ከምትሆን ከአባሪም በኢያሪኮ አንፃር ወዳለ ወደ ፋስጋ ራስ ናባው ወደሚባል ተራራ ወጣ፡

፪፡ ወአርአዮ እግዚአብሔር ኵሎ ምድረ ገለዓድ ወኵሎ ምድረ ንፍታሌም ወኵሎ ምድረ ምናሴ ወኵሎ ምድረ ይሁዳ እስከ ደኃሪት ባሕር፡

እግዚአብሔርም የገለዓድንና የንፍታሌምን ዕጣ፡ የምናሴንና የይሁዳንም ዕጣ ሁሉ እስከ ኤርትራ ባሕር መጨረሻ ድረስ አሳየው፡

፫፡ ወገዳመ ወአድያሚሃ ለኢያሪኮ ሀገረ ፊንቆን እስከ ሴይር፡

የፊንቆን አገር የምትሆን የኢያሪኮ አውራጃ ምድረ በዳውንም እስከ ሴይር ድረስ አሻግሮ አሳየው፤

፬፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዛቲ ይእቲ ምድር ዘመሐልኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ወእቤሎሙ ለዘርእክሙ እሁባ፡

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው ፡ በአሪት መቶ ሠላሳ ዘመን ለልጆቻችሁ አወርሳታለሁ ብዬ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ የማልኩላቸው አገር ይህች ናት፤

ወናሁ አርአይኩከ ለከ በአዕይንቲከ ወባሕቱ ህየ ኢትበውእ፡

እነሆ ላንተም ባይንህ አሳየሁህ፡ ነገር ግን ወደዚ አትገባም አለው፤

፭፡ ወሞተ ሙሴ ቊልዔሁ ለእግዚአብሔር በምድረ ሞዓብ በቃለ እግዚአብሔር፡

የእግዚአብሔር ባለሟል ሙሴ በእግዚአብሔር ቃል ታዝዞ በሞዓብ አውራጃ በደብረ ናባው ሞተ፤

፮፡ ወቀበርዎ ውስተ ምድረ ናባው ቅሩበ ቤተ ፌጎር ወአልቦ ዘየአምር መኑሂ መቃብሮ እስከ ዛቲ ዕለት፡

ለጣዖት ቤት አቅራቢያ በምትሆን በሞአብ ምድር፣ በናባው ቀበሩት፣ እስከዚች ቀንም ድረስ መቃብሩን ማንም ማን የሚያውቅ የለም፤ (ሐተታ) ሙሴን የቀበሩት ሰዎች አልታወቁም፤ አንድም መላእክት ናቸው ስለምን መቃብሩን ሠወረው ቢሉ እስራኤል ይወ

www.ethiopianorthodox.org

ዱት ነበርና እንዳያመልኩት ብሎ ነው ፤ አንድም የተቀበረበትን ቦታ ካወቁ ጧት ማታ እየሄዱ ከመቃብሩ እያለቀሱ ኀዘን እንዳይጸናባቸው ብሎ ነው፤

፯፤ ምእት ወእሥራ ዓመቲሁ ለሙሴ አመ ሞተ ወኢተሐምጋ አዕይንቲሁ ወኢማሰና፡

በሞተም ጊዜ ለሙሴ ዘመኑ መቶ ሐያ ዘመን ሁኖት ነበር ፤ ዓይኖቹም አልደፈ ረሱም አልፈዘዙም ነበር፤

፰፤ወበከይዎ ደቂቀ እስራኤል ለሙሴ በአራቦት ዘሞዓብ በኀበ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ ሠላሳ መዋዕለ ወተፈጸመ መዋዕለ ላሁ ለሙሴ ዘበከይዎ፤

የእስራኤል ልጆች የኢያሪኮ አንፃር በምትሆን በዮርዳኖስ ማዶ ባለች በሞአብ ክፍል በምትሆን በአራቦት ለሙሴ ሠላሳ ቀን አለቀሱለት፣ ለሙሴም ያለቀሱለት ወራት አለቀ፤

፱፤ ወኢያሱ ወልደ ነዌ ተመልዐ መንፈሰ ጥበብ እስመ ወደየ እዴሁ ሙሴ ላዕሌሁ፣

ሙሴ በአንብሮተ እድ ሾሞታልና የነዌ ልጅ ኢያሱም ጥበብን የሚገልጽ መንፈስ ረድኤትን ተመላ፤ ሥራ አሠራው፣ እውቀት ኃይል ሆነው፣ ሙሴ ኢያሱን በአንብሮተ እድ በሾመው ጊዜ በሱ አድሮ ሥራ ያሠራው የነበረ መንፈስ ረድኤት በኢያሱ አድሯል፤

ወተአዘዙ ሎቱ ኵሉ ደቂቀ እስራኤል ወገብሩ ኵሎ ዘከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

የእስራኤል ልጆችም ሁሉ ታዘዙለት፣ እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው ሁሉን አደረገ፤

፲፤ ወኢተንሥአ እንከ ነቢይ ውስተ እስራኤል ዘከመ ሙሴ ዘተናገሮ እግዚአብሔር ገጸ በገጽ፡

እግዚአብሔር ቃል ለቃል እንደ ተነጋገረው ፊት ለፊት እንደ ታየው እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ እንግዲህ በእስራኤል ዘንድ አይነሣም፤

፲፩፤ ወበኵሉ ተአምር ወመድምም ዘፈነዎ እግዚአብሔር ከመ ይግበሮ በምድረ ግብጽ ላዕለ ፈርዖን ወላዕለ መግብቱ ወላዕለ ምድሩ፡



በግብጽ ምድር በፈርዖንና በሹማምንቱ በአገሩም ያደርገው ዘንድ እግዚአብሔር በላከው ታምራት ሁሉ፤

፲፪፤ ዐበይተ መድምመ ወእደ ጽንዕተ ወመዝራዕተ ልዑለ ኵሎ ዘገብረ ሙሴ በቅድመ ኵሉ እስራኤል፤

በእስራኤል ፊት ታላላቅ ተአምራትን ፤ ዘጠኝ መቅሠፍትን፣ አሥረኛ ሞተ በኵርን፣ አሥራ አንደኛ ስጥመትን እንደ አደረገ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ አልተነሣም፤

ተፈጸመ ኦሪት ዘዳግም ወስብሐት ለእግዚአብሔር ጸጋዌ ጸጋ ፍጹም፣

ፍጹም ተስፋን ለሰጠ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና ሙሴ ዳግመኛ የተናገረው ሕግ ደረሰ ተፈጸመ ።

www.ethiopianorthodox.org